# የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደር
# እና
# እምነት

በ

ግርማ ቡኬ ጩዶ

አማካሪ

ፈቃደ አዘዘ ( ዶ/ር )

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ክፍል
የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት
ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ

ህዳር 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ክፍል

# የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደር

# እና

# እምነት

በ

ግርማ ቡኬ

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ፈቃደ፡ አዘዘ

አማካሪ ፊርማ

ገብሬ፡ ደንቴ

ፈታኝ ፊርማ

ፈታኝ ፊርማ

# ምስጋና

‹‹…የእኔ ሥራ በየጊዜው እንዲህ፣ እንዲህ እያልኩ የአንተን መስኮቶች ማንኳኳት ነው፡፡ እስከ ቴሲሱ ማጠናቀቂያ ድረስ ስንቶቹ እንደሚከፈቱ የምታውቀው አንተው ነህ›› (ፈቃደ አዘዘ፣ 2002)

ፈቃደ አዘዘ፣ የዚህ ስራ አማካሪዬና መምህሬ ነው፡፡ በአማካሪነቱ፣ በቃል መጠይቅ ለምሰበስበው መረጃ አጋዥ የሚሆኑ ጥያቄዎችን አዘጋጅቼ እንዳሳየው ጠይቆኝ ሰጥቼው ነበር፡፡ ፈቃደ ከፍ ሲል የተመለከተውን አስተያየት የሰነዘረውም አዘጋድቼ የሰጠሁትን ጥያቄዎች አይቶ፣ አርሞ፣ አቃንቶ…ሲመልስልኝ በጽሁፍ በማስፈር ነው፡፡ በወቅቱ ለአስተያየቱ ተኩረት አልሰጠሁትም ነበር፡፡ እንዲያውም (ይቅርታ ይደረግልኝና) በሆዴ ‹‹አሁን ይህን ማለት ለምን አስፈለገ›› ሣልል አልቀረሁም፡፡ የኋላ የኋላ፣ እየዋልኩ እያደርኩ፣ ቀስ በቀስ እያዘገምኩ ወደ ጥናቱ ሥራ ስገባ ግን፣ የአባባሉን እምቅነት፣ የአማካሪዬን አስተዋይነትና ብስለት እየተረዳሁ መጣሁ፡፡ በዚህም ሆነ በተለያየ መልክ፣ በአማካሪዬ የተሰነዘሩ አስተያየቶች፣ ለብዙ ዘመናት ተዘግተው የቆዩትን፣ የአእምሮዬን መስኮቶችንና በሮችን በእርግጥም አንኳኩተዋል፡፡ አንኳኩተው ከአሸለቡበት እንዲነቁ አድርጓቸዋል፡፡ ከነቁት መካከልም ገሚሶቹ ያህል መስኮታቸውንና በሮቻቸውን እንዲከፍቱ አስችሏቸዋል፡፡ እኔም በጣም ብዙ፣ ብዙ ነገሮችን ማየት፣ መመልከት፣ ማስተዋል፣ መገንዘብ፣ ወዘተ. የጀመርኩት፣ ለዘመናት አብረውኝ የነበሩትን፣ ግን ልብ ያላልኳቸውን በርካታ ድንቃ ድንቅ ትዕምርቶችንና ባህላዊ እሴቶችን ልብ ልል የቻልኩት፣ ፈቃዴ አንኳኩቶ ባስከፈታቸው በአዕምሮዬ በሮቼና መስኮቶቼ በኩል በገባው ብርሃን ተጠቅሜ፣ አንገቴን አሰግጌ፣ አይኖቼን አጮልቄ ማየት በመቻሌ ነው፡፡ ጊዜና አቅም ኖሮ፣ እንዲህ የፈቃዴ ተመካሪ ሆኜ ብቆይ ኖሮ፣ እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ ሁሉም የአዕምሮዬ መስኮቶችና በሮች በእርግጠኛነት ይከፈቱ፣ ይበረገዱ፣ በብርሃን ይሞሉ ነበር፡፡ በመሆኑም አማካሪዬንና መምህሬን ከልቤ እንዳመሰግን ይፈቀድልኝ፡፡ ምነው ምስጋናው አነሰብኝሣ! ትንሽ ላክልበትና አማካሪዬንና መምህሬን እንዲህ ብዬ ልሰናበተው፡፡ ‹‹የአንተ ደቀመዘሙር ሆኜ፣ አንተ በረገጥክበት እየረገጥኩ፣ አንተ የተናገርከውን እያስተጋባሁ እስከ ወዲያኛው ልከተልህ፣ የፎክሎር ‹‹ትንሹ ካድሬ›› ልሆን ቃል እገባለሁ፡፡

‹‹ጡ!›› እንዴት ብዬ እንደማመሰግንሽ ግራግቢት አለኝሳ! እስቲ አንቺው ንገሪኝ በሞ… እኔም፣ ሌሎች ምስጋና አቅራቢዎች እንደሚሉት ‹‹ውድ ባለቤቴ እንዲህ፣ እንዲህ ስላደረግሽልኝ…አመሰግንሻለሁ›› እንዳልል የሰደብኩሽ፣ ውለታሽን ያሳነስኩ ያህል ተሰማኝ፡፡

ገና ‹‹ጡን ምን ብዬ ላመስግናት›› ብዬ ሣስብ ይጨንቀኛል፡፡ እውነት እውነት እላችኊለሁ ይህን ምስጋና ለመፃፍ አንድ ወር ሙሉ ፈጅቶብኛል፡፡ ‹‹ጡ›› እንዲህ የመጨነቁ፣ የመጠበቤ ምንጩ፣ ምክንያቱ ላንች ያለኝ ታላቅ ክብርና ግምት እንጂ ሌላም አይደለም፡፡ አንቺ፣ የእኔ ምኞት እንዲሳካ፣ ሀሳቤ እንዲሞላ ብለሽ ራስሽን ጎዳሽ፡፡ ለእኔ ክብር ስትይ ከሰው ተራ ወጣሽ፡፡ ከመሰሎችሽ ዝቅ ብለሽ ራስሽን አዋረድሽ፡፡ ለሰላሳ ወራት ያህል ብክንክን አልሽ፡፡ በአጭሩ ‹‹የኢየሱስ ክርስቶስን የመሰለ›› ተግባር ፈፀምሽ፡፡ ልዩነት ቢኖር የአካልና የቁጥር ነው፡፡ እሱ ፈጣሪ አንቺ ተፈጣሪ፡፡ እሱ ለዓለም ሕዝቦች ሲል መከራ ተቀበለ፡፡ አንቺ ግን ለእኔ፣ ለአንድ ሰው ስትይ አበሣ አየሽ፡፡ ለውጤት አበቃሽኝ፡፡ እናም ‹‹ጥሩዬ›› እጅግ እጅግ፣ በጣም አድርጌ አመሰግንሻለሁ ከማለት ውጭ ሌላ ምን እላለሁ፡፡

የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ የጥናቱ ሥራ እንዲሳካ ለአደረገልኝ፣ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ምስጋና ይገባዋልና ይኸው ይድረሰው ብያለው፡፡

አንድ ጊዜ ቆዩኝማ! አንድ ታላቅ ቁም ነግር ልንገራችሁ! ወይም ሁለት ብሩክ ሰዎችን ላስተዋውቃችሁ፡፡ ምን መሰላችሁ፡፡ በዚህ የጥናት ሂደት ውስጥ የቸገረኝ፣ የተፈታተነኝ ምን ነገር እንደሆነ ታውቃላችሁ፣ ኮምፒዩተር ነው፡፡ ይህን ጥናት ላጠና ስነሳ ኮምፒዩተር አልነበረኝም፡፡ ዛሬም ቢሆን የለኝም፡፡ ኮምፒዩተር ያላቸው ወንድሞችና ‹‹የልብ›› ጓደኞች ስለነበሩኝ፣ ሊያውሱኝም ቃል ስለገቡልኝ፣ ኮምፒዩተር አጥቼ እቸገራለሁ ብዬ አስቤም አላውቅም ነበር፡፡ ነገር ግን ከአንዱ በስተቀር አንዳቸውም በቃላቸው አልፀኑም፡፡ የገዛ ወንድሞቼ፣ ሥጋዎቼ እንኳን ሣይቀሩ፣ በሙሉ ከለከሉኝ፡፡ ብዙ አምጦ፣ አምጦ ያዋሰኝ አንዱ ብቻ ነው፡፡ እሱም ቢሆን ሐሙስ ምሽት አውሶኝ ዓርብ ጧት የሚወስድብኝ ቢሆንም ጨርሰው ከከለከሉኝ ጋር ሲነፃፀር በልጦ ተገኝቷልና አቶ ታምራየሁ ስዩም ሊመሰገን ይገባል፡፡ ግን በወንድሞቼና በጓደኞቼ እጅግ አድርጌ አዘንኩባቸው፡፡ ተስፋም ቆረጥኩ፡፡

‹‹ግን ሣይደግስ አይጣላም›› ይባል የለም፡፡ ቢሮአቸውን ለቀውልኝ፣ የቢሮ ቁልፋቸውን ‹‹በእምነት›› ሰጥተውኝ ኮምፒዩተራቸውን እንዳሻኝ እንዲጠቀም በማድረግ፣ እምባዬን አብሰው፣ ተስፋዬን አለምልመው፣ የጥናቱ ሥራ ከዳር እንዲደርስ፣ ለፍሬ እንዲበቃ ያደረጉት ሰዎች እነማን እንደሆኑ ታውቃላችሁ፣ አንዷ ወ/ሮ የወግነሽ ለማ፣ ሌላዋ ወ/ት ዓለም በላይ ናቸው፡፡

የወግነሽ ለማ የሥራ ባልደረባዬ ነች፡፡ በደም በሥጋ አንገናኝም፡፡ ነገር ግን ከእናት ከአባቴ ልጆች፣ ከሥጋ ዘመዶቼ በልጣ ‹‹የልብ ጓደኞቼ›› ከሚላቸው ተሽላ ተገኘች፡፡ ‹‹መወለድ ከቋንቋ

ባለፈ ሌላ ምን ፋይዳ አለው›› አስባለች፡፡ እናም ለዚች ብሩክት እህት ምን ይገባታል? እንደሌላው ሰው ሁሉ ‹‹ከፍ ያለ ምስጋና›› ብቻ? ... በፍፁም፡፡ ግን ሌላ ምን? ....

ዓለም! አሳቢዬ! ከላይ ከተመለከተው ሌላ, ብዙ ብዙ ነገሮች፣ ከዚህ የማልዘረዝራቸው፣ ከመደበኛው የትምህርት ዘመኔ አንስተሽ ይህን ሥራ እስካጠንቀቅሁበት ጊዜ ድረስ የዋልሽልኝን ውለታ፣ ያደረግሽልኝን ድጋፍ መቼም፣ መቼም ቢሆን አልረሳውምና ዓለምዬ! ለጊዜው እጅግ አድርጌ አመሰግንሻለሁ ከማለት ውጭ ሌላ ምን እላለሁ፡፡

አብሮ አደጎቼ፣ የልብ ጓደኞቼ፣ የመስክ ረዳቶቼ፣ አቶ አበበ አርጋሞ እና አቶ አሊስ ቦቃ፣ ለዚህ ሥራ የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ቡርጂን ከረገጥኩበት ቀን ጀምራችሁ፣ አንድም ቀን ሣትለዩኝ ላደረጋችሁልኝ ድጋፍ ምሥጋና ይገባችኋልና እነሆ ይድረሳችሁ፡፡

ልጆቼ፣ ንፁህሰው ግርማ እና በትዕግስት ግርማ፣ እናንተም እንደ እናታችሁ፣ በእኔ ምክንያት፣ ለእኔ ስትሉ በልጅነታችሁ የሚገባችሁን በጣም ብዙ ነገሮችን እንዳጣችሁ፣ ያማራችሁን እንዳላገኛችሁ አሳምሬ አውቃለሁና...ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡ እደጉ ተመንደጉ እላለሁ፡፡

የቡርጂ ልዩ ወረዳ ባህል፣ ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚዩንኬሽን ጽህፈት ቤት፣ በእጁ የነበሩትንና ለሥራዬ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን እንድጠቀም በመፍቀዱ ሊመሰገን ይገባል፡፡

አቶ ደረጀ ብሩ እና ባለቤቱ ወ/ሮ በላይ መኩሪያ፣ ይህን ሥራ ጀምሬ እስከማጠናቅቅ ድረስ የሞራል ድጋፋችሁ አልተለየኝምና ልባዊ ምስጋናዬን እነሆ ጀባ ብያችኋለሁ፡፡

ሌላም ሰው አለ፡፡ አቤት ባለውለታዎቼ መብዛታቸው! ሰብሌ ኃይሌ ይህን ጥናት ሳዘጋጅ ብዙ ቀዳዳዎቼን ደፍነሽልኛልና ምሥጋናዬ ይድረስሽ፡፡

# ማውጫ

ርዕስ ገፅ

ምስጋና ---------------------------------------------------------------------------------------------------- i

ማውጫ ---------------------------------------------------------------------------------------------------- iv

መግለጫ ---------------------------------------------------------------------------------------------------- vi

አጠቃሎ ---------------------------------------------------------------------------------------------------- ix

1. መግቢያ ---------------------------------------------------------------------------------------------------- 1

1.1 የጥናቱ መነሻ ሀሳብ ---------------------------------------------------------------------------------- 3

1.2. የጥናቱ ዓላማዎች ---------------------------------------------------------------------------------- 5

1.3. የአጠናን ዘዴዎች ---------------------------------------------------------------------------------- 5

1.4 ጥናቱ የሚያስገኘው ጠቀሜታ ---------------------------------------------------------------------- 7

1.5 የጥናቱ ወሰን ---------------------------------------------------------------------------------------- 8

1.6 የጥናቱ የመረጃ ምንጮች ---------------------------------------------------------------------------- 8

1.7 ጥናቱ የተካሄደባቸው ቦታዎችና ቀኖች---------------------------------------------------------------- 9

1.8 በጥናቱ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች --------- 10

2. የተዛማጅ ጽሁፎች ክለሳና ግምገማ ------------------------------------------------------------------- 11

2.1 ስለ ባህላዊ አስተዳደር የምሁራን ሀሳቦችና ብያኔዎች------------------------------------------ 12

2.2. ስለ ሀገረሰባዊ ሃይማኖት ወይም እምነት የምሁራን
ሀሳቦችና ብያኔዎች----------------------------------------------------------------------------------- 16

2.3 በቡርጂ ላይ የተደረጉ የቀደምት ጥናቶች እና ጽሁፎች ክለሳና ግምገማ ------ 19

3. የቡርጂ ህዝብ አጫጭር መግለጫዎች ------------------------------------------------------------------ 27

3.1. መልክዓ ምድር----------------------------------------------------------------------------------------- 27

3.2 የሕዝቡ ስያሜ ---------------------------------------------------------------------------------------- 27

3.3 የቡርጂ ህዝብ ጥንተ አመጣጥ ታሪክ ------------------------------------------------------------ 31

3.4. ቋንቋ----------------------------------------------------------------------------------------------------- 36

4. የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደር---------------------------------------------------------------------------- 37

4.1 የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደር ታሪክ------------------------------------------------------------------ 37

4.1.1 የጎሳ አስተዳደር ተቋም ታሪክ---------------------------------------------------------------- 38

4.1.2 የህግ አስተዳደር ተቋም ታሪክ ---------------------------------------------------------------- 39

4.1.3. የክልል አስተዳደራዊ ተቋም ታሪክ ------------------------------------------ 41
4.1.3.1 የወማ አስተዳደር ታሪክ ------------------------------------------ 41
4.1.3.2 የዳይና አስተዳደር ታሪክ ------------------------------------------ 45
4.2 የባህላዊ አስተዳደር ተቋማት መዋቅርና ለመዋቅሩ መነሻ የሆኑ ምክንያቶችና አጋጣሚዎች ------------------------------------------ 49
4.2.1 የአስተዳደር ተቋማት መዋቅር ------------------------------------------ 50
4.2.2 ለአስተዳደራዊ መዋቅሩ መነሻ የሆኑ መሰረታዊ ምክንያቶችና አጋጣሚዎች ------------------------------------------ 52
4.3. የባህላዊ መሪዎች የአመዳደብ ሥርዓት ------------------------------------------ 61
4.3.1 በየባልባላው የሚመደቡ አባላት ብዛት ------------------------------------------ 61
4.3.2. ለሥልጣን የሚያበቁ መስፈርቶች ------------------------------------------ 65
4.3.3. የምርጫ ሥርዓት ------------------------------------------ 71
4.3.4. የባሻ ሥርዓት ------------------------------------------ 78
4.4. የባህላዊ መሪዎች ተግባር ------------------------------------------ 90
4.4.1 የኤላዎች ተግባር ------------------------------------------ 91
4.4.2 የሌሎች ባህላዊ መሪዎች ተግባር ------------------------------------------ 100
4.4.2.1 የኣንሽ ተግባር ------------------------------------------ 100
4.4.2.2. የሃዩ ተግባር ------------------------------------------ 102
4.4.2.3. የሉብ ተግባር ------------------------------------------ 104
4.4.2.4 የኦለይንካ ኣና ተግባር ------------------------------------------ 105
4.5 የስብሰባና የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት ------------------------------------------ 106
4.5.1. የስብሰባ ሥርዓት ------------------------------------------ 106
4.5.2. የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት ------------------------------------------ 108
5. የቡርጂ ባህላዊ ሃይማኖት ------------------------------------------ 110
5.1. የጋን እምነት ታሪክ ------------------------------------------ 110
5.2 የጋን እምነት መዋቅር ------------------------------------------ 114
5.3 በጋን የእምነት ተቋም ውስጥ የአባላት አመዳደብ፣ ተግባርና የአሠራር ሥርዓት ------------------------------------------ 114
5.3.1 የባለጋን አመዳደብና ተግባር ------------------------------------------ 115

5.3.2 የቢ.ታናች አመዳደብና ተግባር ---------------------------------------- 123
5.3.3 የኣላልች አመዳደብና ተግባር ---------------------------------------- 127
5.4 ከባህላዊ አስተዳደር ጋር ተያይዘው የሚፈፀሙ እምነታዊ ድርጊቶችና
የአፈፃፀም ሥርዓታቸው ---------------------------------------- 128
5.4.1. ሐ.ጣኖ ---------------------------------------- 129
5.4.2 ጎዴ ---------------------------------------- 133
5.4.3 ሞጨ ---------------------------------------- 138
5.4.4. ቦርቶማ ---------------------------------------- 140
5.5. የባህላዊ መሪዎች ገደቦችና የቁጥጥር ሥርዓቶች---------------------------------------- 142
6. ማጠቃለያና ይሁንታ ---------------------------------------- 146
ዋቢ. መጻሕፍት ---------------------------------------- 152
አባሪ 1 የቁልፍ መረጃ ሰጪዎች አጫጭር መግለጫዎች ---------------------------------------- i
አባሪ 2 ሙዳየ ቃላት ---------------------------------------- v
አባሪ 3 በዓለም አገሮች የቡርጂ ስርጭት---------------------------------------- xiv

## መ ግ ለ ጫ

1. ከዚህ በታች የተመለከቱትና በእኩል ይሆናል (=) ምልክት የተለዩት ቃላት፣ ሀረጋት ወይም ሀሳቦች፣ በዚህ ጥናት ውስጥ አቻ ትርጉምና ፍች ወይም ተመሳሳይ ፅንሰ ሀሳብ ይዘው የገቡ ናቸው።

- የቡርጂ ሕዝብ = የቡርጂ ማህበረሰብ = የቡርጂ ህብረተሰብ = የቡርጂ ብሔረሰብ = ቡርጂዎች
- ባህላዊ = ሀገረሰባዊ = ሀገር በቀል
- የአስተዳደር ሥርዓት = የፖለቲካ ሥርዓት
- ባህላዊ ቄስ = ባለጋን
- ባልባላ = ጽህፈት ቤት = ዋና በር = አደባባይ = የመሰብሰቢያ ሥፍራ
- የአስተዳደር መሪዎች = የፖለቲካ መሪዎች = ባህላዊ የፖለቲካ መሪዎች = ባህላዊ የአስተዳደር መሪዎች
- ቢያ= አካባቢ = የቢያ አስተዳደር = የአካባቢ አስተዳደር
- ህዝባዊ ሸንጎ = ምክር ቤት

2. ይህ ጥናት ያተኮረው በቡርጂ ብሔረሰብ ላይ ቢሆንም የተዘጋጀው ግን በአማርኛ ቋንቋ ነው። በመሆኑም በጥናቱ ውስጥ በርካታ የቡርጂኛ ቃላት በብሔረሰቡ በሚነገሩበት ሁኔታ ቀርበውበታል። አንባቢው ቡርጂኛውን ከአማርኛው መለየት እንዲችል በሚል በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተካተቱት አብዛኞቹ የቡርጂኛ ቃላትና ሐረጋት በተቻለ መጠን "Italic" የሚባለውን ቅርፅ ይዘው እንዲቀርቡ ተደርጓል።

3. እንዲሁም በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በምንጩ ቋንቋ (በቡርጂኛ) ለቀረቡት ቃላት በተቻለ መጠን ቃላቱ መጀመሪያ በቀረቡበት (በተጠቀሱበት) ቦታ የአማርኛ ፍቺያቸውን በቅንፍ ውስጥ ወይም በግርጌማው ላይ ለመስጠት ተሞክሯል። ከዚህ ውጭ የሆኑ ቃላትና ሐረጋት ካሉ ደግሞ ቅንፍና ግርጌማ ሣያስፈልጋቸው በጽሁፉ ውስጥ ተብራርተዋል ማለት ነው። ይሁን እንጂ የአንባቢን ጊዜ ለመቆጠብ ሲባል ለእነዚህ፣ ለሁሉም፣

የቡርጂኛ ቃላት በአባሪ 2 ላይ ከአማርኛ ፍቺያቸው ጋር ሙዳዬ ቃላት ተዘጋጅቶላቸዋል።

4. **ምህፃረ ቃላት**

- ራገአ - የራስ ገዝ አስተዳደር
- ሀና - ሀላሜ እና ናዳሌ
- ላዋጋ - ላድሼ፣ ዋለይ እና ጋራ
- ጉጉአ - የጉልጉባ አስተዳደር
- ቢአ - የቢያ አስተዳደር
- ቦአ - የቦሄ አስተደሰደር
- ጋቢአ - ጋሪንታ ቢያ አስተዳደር

## አጠቃሎ (Abstract)

ይህ ጥናት፣ የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደርንና ከአስተዳደር ሥርዐቱ ጋር ተያይዘው የሚፈጸሙ እምነታዊ ድርጊቶችን በገለፃ ለማሣየት ይሞክራል። በመሆኑም ጥናቱ ኳሊቴቲቭ (በፈቃደ አባባል ‹‹ኳልታዊ››) የአጠናን ዘዴን (Qualitative Research Methodology) ይከተላል። የቃል መጠይቅ (Interview) እና የቡድን ውይይት (Group Discussion) ዋነኞቹ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (data collecting methods) በመሆን አገልግለዋል። በባህላዊ የአስተዳደርና የእምነት ሥርዓቶች ውስጥ የተሣተፉ፣ በመሣተፍ ላይ ያሉና ባህላዊ ሥርዐቱን ጠንቅቀው የሚያውቁ አምስት ሰዎች የጥናቱ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች (Key Informants) ሆነው ተመርጠዋል።

በጥናቱም፣ ቡርጂዎች ያልተማከለ የአስተዳደር ሥርዓትን የሚከተሉና የጎሳ፣ የሀግ እና ክልላዊ የሚባሉ ሶስት ባህላዊ የፖለቲካ ተቋማት ያሏቸው መሆኑ ተመልክቷል። በቡርጂ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ጠንካራውና ወሳኙ የጎሣ አስተዳደር ተቋም መሆኑ በጥናቱ ተልጧል። የቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር መሪዎች ተቀዳሚ ተግባር ስለ ህዝቡና አካባቢው መፃኢ ሁኔታ በማስጠንቆልና በማስተንበይ ህዝቡን፣ የህዝቡን ንብረትንና ህዝቡ የሚኖርበትን አካባቢ፣ ወደፊት ይደርሳሉ ከሚባሉ ክፉ አጋጣሚዎች (ማለትም ከበሽታ፣ ከጦርነት፣ ከረሀብ፣ ወዘተ.) መከላከል መሆኑ፣ መሪዎቹ፣ በራሣቸው ልዕለ ተፈጥሮኣዊ ኃይል (Super Natural Power) የሌላቸው፣ ነገር ግን ተግባራቸውን የሚያከናውኑት በጠንቋዮች (magico-religion)፣ በተንባዮች (prophets) እና ‹‹ጋን (gann) የሚባል ልዕለ ተፈጥሮኣዊ ኃይል አላቸው›› ተብለው በሚታመኑ፣ በባህላዊ የእምነት መሪዎች በመታገዝ መሆኑ በጥናቱ የተገለፀ ሌላው ነጥብ ነው። የእምነት መሪዎችም ጋን የሚባል ልዕለ ተፈጥሮኣዊ ኃይል ያላቸው መሆኑ፣ በዚህ ኃይል በመታገዝም፣ በህዝብ ችግሮች ላይ ፈጥነው መድረስ፣ ደርሰው ከችግሮቹ ጋር ፊት ለፊት መጋፈጥ፣ ህዝቡንም ከችግሮቹ መታደግ፣ መመረቅ፣ መባረክ፣ መጸለይ የዘወትር ተግባራቸው እንደሆነ፣ ይህንን ለመፈጸም ሲሉ ወይም ያሉት እንዲሆንላቸው፣ የለመኑት እንዲሰምርላቸው ሲሉ ግን የሚፈጽሙት የተለየ ነገር የለም። የቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደርና የእምነት ተቋማት አንዱ በሌላው ውስጥ ያሉ፣ የሚደጋገፉ፣ እንዲሁም፣ የቡርጂ ህዝቦች በሙታን ሰዎች የሚያምኑ (ancestral worships) መሆናቸው በጥናቱ የተገለፀ ሌላው ነጥብ ነው። ሙታን ወገኖች ለቡርጂዎች ለፈጣሪ የቀረቡ፣ ፈጣሪን የሚያማልዱ፣ በህያዋን ወገኖቻቸው ላይ ያሻቸውን ማድረግ የሚያስችላቸው ልዩ ኃይል ያላቸው ናቸው። ለወገኖቻቸው ሞትና ህይወት፣ ለአካባቢው ልማትና ውድቀት ወዘተ ምክንያቶቹ የሙታን ወገኖች እርግማንና ምርቃት እንደሆነ ተደርጎ እንደሚታመን ጥናቱ ያሣያል። በቡርጂ ሀገረሰባዊ ሃይማኖት ውስጥ አንዱ የበላይ ሌላው የበታች፣ አንዱ አዛዥ ሌላው ታዛዥ የሆነበት የአሰራር ሥርዓት የለም።

የቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካና የእምነት ተቋማት መሪዎቹን የሚቆጣጠሩባቸው ጠንካራ የቁጥጥር ሥርዓቶች ያሏቸው መሆኑ፣ እንዲሁም በአሁኑ ዘመን ላይ በተለያዩ የዓለም ሀገሮች ውስጥ እየተተገበረ ያለው የዲሞክራሲ ሥርዐት በቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዐት ውስጥ ሙሉ ለሙሉ የለም ማለት ባይቻልም፣ ለዲሞክራሲያዊ የአሰራር ሥርዓት መሰረት ሊሆኑ የሚችሉ አንዳንድ እውነቶች ግን መኖራቸውን ጥናቱ ይጠቁማል። የቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካና የእምነት ሥርዓቶች ሙሉ ለሙሉ የወንድ የበላይነት የሚንፀባርቅባቸው መሆኑ በጥናቱ የተስተዋለ ሌላው ነጥብ ነው። በመጨረሻም እነዚህ ባህላዊ የፖለቲካና የእምነት ሥርዓቶች በአሁኑ ጊዜ በአብዛኞቹ (በተለይም በወጣቱ ዘንድ) በውል የማይታወቁ፣ በሚያውቁትም ዘንድ እየተረሱ፣ መልካቸው፣ ጠረናቸው እየተለወጠ ያለ ስለሆነ ከወዲሁ የማያውቁት እንዲያውቁ፣ በአግባቡ ተቀርፀው ቢቀመጡ ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም የሚለው በጥናቱ የተሰነዘረ አስተያየት ነው።

## 1. መግቢያ

ይህ ጥናት የቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓትንና ከአስተዳደር ሥርዓቱ ጋር ተያይዘው የሚፈፀሙ ባህላዊ እምነቶችን በማሣየት ላይ ያተከረ ነው። የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው የቡርጂ ብሔረሰብ በመላው ኢትዮጵያ ውስጥ ተሰራጭቶ የሚገኝ ሲሆን፣ በዋናነት ግን በደቡብ ብሔር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መስተዳደር፣ በቡርጂ ልዩ ወረዳ ሰፍሮ ይገኛል። እንደ (CSA, 2007) መረጃ መሰረት በመላው ኢትዮጵያ በጠቅላላ 71,871 ቡርጂዎች ይኖራሉ። ከእነዚህ ውስጥ፣ በደቡብ ክልል ወይም በቡርጂ ልዩ ወረዳ ውስጥ በጠቅላላ 56,523 የቡርጂ ህዝቦች የሚገኙ ሲሆን ከእነዚህም መካከል 27,643 ወንዶች፣ 28,880 ሴቶች ናቸው። ከኢትዮጵያ ውጭ ደግሞ በርካታ ቡርጂዎች በኬንያ ውስጥ ይኖራሉ (Encarta, 2007)።

የቡርጂ ሕዝብ በኢትዮጵያ ማዕከላዊ አስተዳደር ሥር ከመጠቃለሉ በፊት የሚመራበት ባህላዊ የፖለቲካና የእምነት ተቋማት ነበሩት። ባህላዊ የፖለቲካ ተቋማቱም የጎሣ፣ *የሆግ*[1] እና የክልል[2] በሚል በሶስት የተከፈሉና በራሣቸው ሥርዓትና ደንብ የሚመሩ፣ ነገር ግን እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉ ሲሆኑ፣ ባህላዊ የእምነት ተቋሙ ደግሞ *ጋን* ይባላል። እንዲሁም አንድ የቡርጂ *‹‹ቦሄ››* *ከጋን* በተጨማሪ ‹‹ጋዳ›› የሚባል የእምነት ተቋም እንደነበረው ይነገራል።

የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ዋና ዓላማም፣ እነዚህን ባህላዊ የፖለቲካ ሥርዓቶችን እና ከፖለቲካ ሥርዓቶቹ ጋር ተያይዘው የሚፈፀሙ እምነታዊ ሥርዓቶችን በገለፃና በትንታኔ ማሣየት ነው። በመሆኑም ከፍ ሲል ከተጠቀሰው፣ ከጋዳ ሥርዓት በስተቀር፣ የተቀሩት ባህላዊ የፖለቲካና የእምነት ሥርዓቶች በዚህ ጥናት ውስጥ ተካተው ቀርበዋል።

የጋዳ እምነታዊ ሥርዓት በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ያልተካተተው በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ነው። አንደኛው የ‹‹ጋዳ›› ሥርዓት በሁሉም የቡርጂ ሕዝቦች ዘንድ የሚታወቅ፣ ተግባራዊ የሆነ፣ ተቀባይነት ያገኘ ሥርዓት ባለመሆኑ ነው። ‹‹ጋዳ›› በአብዛኞቹ ቡርጂዎች ዘንድ፣ በወቅቱ ፖለቲካዊውንና እምነታዊውን ሥልጣን ደርበው በመያዝ ሲገዙ የነበሩ አምስቱ የቡርጂ ጎሳዎች፣ ሕዝቡ አልገዛ ሲላቸው፣ ሕዝቡን ለመጫን ሲሉ ከቦረናዎች ላይ ኮርጀው በማምጣት ቡርጂ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የሞከሩት ግን ያልተሣካ ሥርዓት እንጂ፣ እንደ ሌላው ባህላዊ ሥርዓት (ለምሳሌ እንደ *ወሚሶ፣ ዳይኖማ፣ ጋኖማ* ወዘተ.) ሁሉም የቡርጂ ሕዝብ አብሮ

---

[1] በተገረዙ ወጣት ወንዶች የተገነባ የመከላከያ ተቋም ነው።
[2] "Territorial Institution" የሚለውን የፈረንጂኛውን ቃል የሚተካ ቃል ነው።

መክሮ ያዋቀረው፣ ከአዕምሮው አፍልቆ ያበጀው ሥርዓት አይደለም (ቱኬ፣ አደን፣ አበበ፣ መኒአ፣ 2002)፡፡

የኦሮሞን የጋዳ ሥርዓት ገልብጦ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ቡርጂ በማምጣት፣ ከነባሩ የቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር (የፖለቲካ) ሥርዓት ጋር በማዋሄድ ተግባራዊ እንዲሆን ያደረገው፣ በወቅቱ የቡርጂ ወማ (ንጉሥ) የነበረው፣ ሺቴ የሚባል ሰው ነው (አበበ፣2002፣ 25-26)፡፡ ሺቴ ይህንን እንዲያደርግ ያነሣሣው ደግሞ የሕዝብ አመጽ ነው፡፡ የወሚሶ ሥርዓት ጨቋኝ ስለነበረ፣ ሕዝቡ አልገዛም ብሎ አመጸ፡፡ አመፁም በገዥዎችና በተገዢዎች መካከል ጦርነት ቀሰቀሰ፡፡ ይህን ጊዜ የወቅቱ ሹማምንት፣ የሕዝቡን አመጽ በመግታት ሕዝቡን ፀጥ ለጥ አድርገው ለመግዛት ሲሉ፣ የጋዳን ሥርዓት ከቦረናዎች ኮርጀው በማምጣት ከቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓት ጋር የቀየጡት እንጂ፣ ጋዳ በቡርጂዎች ዘንድ ቀደም ሲል የሚታወቅ፣ የቡርጂ ባህል አይደለም[3] (ማኒአ፣ አበበ፣ 2002)፡፡ ሥርዓቱ የተቋረጠው በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ (Amborn and Kellner, 1999) ሲሆን ለመቋረጡም ምክንያቱ ጋዳዎች በወቅቱ በሕዝቡ ላይ ይፈፅሙ የነበሩት የጭካኔ ተግባር ነው፡፡ ከእነዚህ መካከል ለአምልኮአዊ ሥርዓት ወይም ከእርኩሰታቸው ለመንፃት ሲሉ የወንድ ልጆችን ሆድ እየቀደዱ ልባቸውን በማውጣት በደማቸውና በልባቸው መታጠብ መጀመራቸው አንዱ እንደሆነ ሁሉም መረጃ አቀባዮች ይስማሙበታል፡፡

በአጭሩ፣ ጋዳ ከዚህ ያልተካተተበት የመጀመሪያው ምክንያት ከሌላ የተቀዳ፣ በቡርጂ ሕዝብ ላይ ተግባራዊ ለማድረግ ተሞክሮ ግን ያልተሳካ፣ ሁሉም ቡርጂዎች የማያውቁት፣ የሚያውቁትም ያልተቀበሉት ወዘተ ሥርዓት በመሆኑ ነው (ማኒአ፣ አበበ፣ ጫሜ፣ 2002)፡፡ ሁለተኛው ምክንያት፣ ጋዳን መመርመር፣ ይህንን ማድረግ የዚህ ጥናት ዓላማ ስላልሆነ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተው፣ ጋዳ ባብዛኛው እምነታዊ ተቋም ነው፡፡ አንድ የጋዳ ምድብ በሥልጣን ዘመኑ (በስምንቱ ዓመት ውስጥ) ተግባራዊ የሚሆኑ የመተዳደሪያ ደንቦችን ከማውጣት ውጭ ፖለቲካዊ ተግባራት አይመለከቱትም፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ደግሞ

[3] ከዚህ በተለየ፣ ቡርጂዎች ሲፈጠሩ ጀምሮ አብሮአቸው የተፈጠረ፣ እዚህ፣ ቡርጂ መጥተው ከመስፈራቸው በፊት ጀምረው ያራምዱት የነበረ፣ ከሌላ ያልተኮረጀ እምነታዊ ሥርዓት ነው ብሎ የሚሞግት መረጃ አቀባይ (ቱኬ፣ 2002፣ 67-74) አለ፡፡ እንደ መረጃ አቀባዩ አባባል፣ የቡርጂ ጋዳ አዖሌ፣ ሐርሙፋ፣ ሐሊቺሣ፣ ሮባሌ እና ሙዳና በሚሉ ስሞች የሚታወቁ አምስት ምድቦች (Five sets) አሉት፡፡ የእያንዳንዱ ምድብ የሥልጣን ዘመን ስምንት፣ ስምንት ዓመት ነው፡፡ በየስምንት ዓመቱ ይተካካሉ፡፡ ከጋዳ ተግባራት መካከል አንዱ በሥልጣን ዘመኑ ተግባራዊ የሚሆኑ (ለምሳሌ፣ ሴት ልጆች መቼ መዳር እንዳለባቸው፣ ወጣት ወንዶች በስንት ዓመታቸው፣ በምን ወቅት መገረዝ እንዳለባቸው፣ ወዘተ.) መተዳደሪያ ደንቦችን ያወጣል፡፡ ይህን የሚተካው ሌላው የጋዳ ምድብም እንዲሁ ሲሻው፣ የቀደመውን የመተዳደሪያ ደንብ ሙሉ በሙሉ ሰርዞ የራሱን አዲስ የመተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፡፡ አሊያም ከቀደመው የሚስማማውን ወስዶ፣ ሌላ አዲስ ጨምሮበት ወይም አሻሽሎ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ከዚህ ባለፈ፣ ጋዳ የሚያከናውነው ፖለቲካዊ ተግባር የለውም፡፡ አብዛኛው ተግባሩም ለሕዝብ፣ ለአካባቢው፣ ወዘተ መፀለይ ነው፡፡ ጋዳ በዚህ ዓይነት በቡርጂ ፖለቲካዊና እምነታዊ ተቋማት አናት ላይ የነበረ እምነታዊ ተቋም ቢሆንም ግን፣ ከፍ ብለው በተጠቀሱትና በሚፈፅማቸው አንዳንድ የጭካኔ ተግባራቱ የተነሣ በአብዛኛው የቡርጂ ሕዝቦች ዘንድ ተቀባይነት ስለአጣ ሊቋረጥ ችሏል፡፡

የቡርጂን ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓትንና ከአስተዳደር ሥርዓቱ ጋር ተያያዥ የሆኑ እምነታዊ ሥርዓቶችን ማሣየት እንጂ የቡርጂ ባህላዊ እምነቶችን በሙሉ የሚዳስስ አይደለም፡፡ በመሆኑም፣ ጋዳ የቡርጂ አዕምሮ ያፈለቀው እምነታዊ ሥርዓት ነው ቢባል እንኳን፣ ዓላማው ስላልሆነ ይህ ጥናት አያነሳውም፡፡

የተቀሩት የቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካና ከዚህ ጋር ተያያዥ የሆኑ እምነታዊ ሥርዓቶች ግን፣ ሙሉ በሙሉ ባይባልም፣ አብዛኞቹ በዚህ ጥናት ውስጥ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ እነዚህም በስድስት ዋና ዋና እና በንዑሳን ምዕራፎች ተከፍለው ቀርበዋል፡፡

ሥራውን የሚያስተዋውቀው፣ ይህ የመግቢያው ክፍል ቀዳሚ ምዕራፍ ሆኖ ቀርቧል፡፡ በውስጡም፣ የጥናቱን ዋናና ዝርዝር ዓላማዎችን፣ ጥናቱ ለምን እንዳስፈለገ፣ እንዴት እንደተካሄደ፣ ምን ችግር እንደገጠመው፣ ወዘተ. እና ሌሎች ነጥቦችን አካቷል፡፡ የተዛማጅ ጽሑፎች ክለሳና ግምገማ በምዕራፍ ሁለት ላይ ተካቷል፡፡ ምዕራፍ ሶስት ቡርጂን ባጠቃላይ የሚያስተዋውቅ ክፍል በመሆኑ የቡርጂ ህዝብ በኢትዮጵያ ውስጥ በዋናነት ሰፍረው ስለሚገኙበት፣ ስለ ቡርጂ ልዩ ወረዳ መልክዓ ምድር፣ ስለ ቡርጂ ሕዝብ ስያሜ፣ ጥንተ አመጣጥ ታሪክና ስለ ቋንቋ በጥቅሉ የሚያስተዋውቁ አጫጭር መግለጫዎችም ተካተውበታል፡፡ የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት የሆኑት የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደርና ተያያዥ እምነታዊ ሥርዓቶች በምዕራፍ አራትና አምስት ላይ በቅደም ተከተላቸው ይቀርባሉ፡፡ ይህ ሁሉ ተጠቃሎ፣ ከጥናቱ የመነጩ ይሁንታዎችን አካቶ በምዕራፍ ስድስት ላይ ቀርቧል፡፡ ዋቢ መጻሕፍትና ልዩ ልዩ አባሪዎች በጥናቱ መጨረሻ ላይ ተካተዋል፡፡

## 1.1 የጥናቱ መነሻ ሀሳብ

እንደ ዛሬው ዘመናዊ የአስተዳደር ሥርዓት ባልተዘረጋበት፣ ዘመናዊ ሃይማኖቶች ባልተስፋፉበት፣ ሥልጣኔ ባልነገሰበት በጥንቱ ዘመን አብዛኞቹ የዓለም ህዝቦች በተለይም አፍሪካዊያን ስለችግሮቻቸው የሚወያዩባቸው፣ ወግ ልማዳቸውን የሚያፀኑባቸው የራሣቸው የሆነ ሀገር በቀል የፓለቲካ ሥርዓትና እምነት ነበራቸው (Harris, 1957)፡፡ ይሁን እንጂ፣ እነዚህ ሀገር በቀል የአስተዳደር ሥርዓቶች አብዛኞቹ በቅኝ ገዥዎች ዘመናዊ አስተዳደር ሙሉ በሙሉ ሲተኩ፣ በአንዳንድ የአፍሪካ ሀገሮች ውስጥ ግን ከዘመናዊ አስተዳደር ጋር ተቀናጅተው ሲሠሩ ተስተውለዋል (Nsarkoh, 1964; Bahru, 2002)፡፡

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ ከዘመናዊው አስተዳደር ጋር ተቀናጅተው የመተግበር እድል ባያገኙም በማዕከላዊ መንግስት ተፅዕኖ ሥር ከመውደቃቸው በፊት በራሣቸው ህዝቦች ዘንድ ይተገበሩ የነበሩና የተጠናከሩ ባህላዊ የአስተዳደርና የእምነት ሥርዓቶች በእኛም ሀገር ስለመኖራቸው ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል፡፡ በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኙ የካምባታ፣ የሲዳማ እና የጉራጌ ህዝቦች ለዚህ ተጠቃሾች ናቸው (Bahru, 2002, 17; Yakob, 2002, 45; Aadland, 2002, 29)፡፡ የዚህ ዓይነቱ የቆየ ባህላዊ የአስተዳደርና የእምነት ሥርዓት ከነበራቸው፣ አሁንም በከፊል ካላቸው ህዝቦች መካከል አንዱ የቡርጂ ህዝብ ነው፡፡

የዚህ ጥናት ትኩረት የሆኑትና በኢትዮጵያ፣ በቡርጂ ልዩ ወረዳ ውስጥ የሚኖሩት የቡርጂ ህዝቦች፣ የማንነታቸው መገለጫ የሆኑ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ ከዚህ የደረሱ በርካታ ባህላዊ እሴቶች አሏቸው፡፡ ከእነዚህም መካከል ባህላዊ የአስተዳደርና የእምነት ስርዓቶች ተጠቃሾች ናቸው፡፡ የጎሳ አስተዳደር፣ ቡርጂዎች ጥንትም ሆነ ዛሬ ከሚመሩባቸው የአስተዳደር ተቋማት መካከል አንዱና ጠንካራው ሲሆን ጋን ደግሞ የቡርጂ ህዝቦች ሀገረሰባዊ እምነት ወይም ሃይማኖት (folk religion) ነው፡፡

ከፍ ተብለው እንደተጠቀሱት እንደ ካንባታ፣ ሲዳማና ጉራጌ ህዝቦች ሁሉ፣ የቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካና የእምነት ተቋማትም አንዱ በሌላ ውስጥ ሆነው፣ እየተደጋገፉ የህዝቡን የህይወት እንቅቅልሽ ሲፈቱ፣ ለችግሮቻቸው መፍትሔ ሲሰጡ፣ ወዘተ. እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ቆይተዋል (Mude, 1968, 26-27)፡፡ ምንም እንኳን፣ ወደ ደቡብ የተስፋፋው የምኒልክ አገዛዝ በተቆጣጠረባቸው አካባቢዎች የነበሩ ሀገር በቀል የአስተዳደርና የእምነት ተቋማትን በቀጥታ ለማፍረስ ባይቃጣም (Bahru, 2002; Hollpitike, 1972) የባህላዊ ሹማምንትን ክብርንና ሞገስን፣ ኃላፊነትንና ተግባርን በስልጣን ስም መገዝገዙ፣ ወይም *ወማውን* (ባህላዊ ‹‹ንጉሡን››) - ባላባት፣ *ዳይናውን* (ከንጉሡ ቀጥሎ ያለ ባህላዊ ሹሙን) - ቆሮ ማድረጉ ግን አልቀረም (Yakob, 2002, 45; Aaadland, 2002, 29)፡፡ የእነዚህ ሹማምንት ተግባርም ህዝቡን ከማዕከላዊ መንግስት ጋር ማገናኘትና የመንግስት ግብር ሰብሳቢ በመሆን ተገደበ (Mude, 1968, 28)፡፡

የቀዳማዊ ኃይሌ ሥላሴ መንግስት ወደ ስልጣን ከመጣ በኋላ በሀገር በቀል የአስተዳደር ተቋማት ምትክ ዘመናዊ የአስተዳደር መዋቅሩን እስከ ወረዳ ድረስ ዘረጋ፡፡ በመዋቅሮቹም ላይ የራሱን ሰዎች ገዢ አደርጎ ሾማቸው (Bahru, 2002, 12)፡፡ ባህላዊ የአስተዳደር ተቋማትንም አገለላቸው፡፡

ነገሮች የከፉት ግን፣ ደርግ ወደ ሥልጣን ከመጣ በኋላ ነው (Bahru, 2000)፡፡ በወቅቱ የቡርጂ ወማ ወይም ባላባት የነበረው ዳምጤ ዳዌ ‹‹አድሃሪ ነው›› ተብሎ ወህኒ በተወረወረበት ሞተ፡፡ በዚህም ምክንያት፣ አብዛኞቹ የቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደርና የእምነት ተቋማት ፈራረሱ፡፡ ይህም የቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር ተቋማት በጎሣና በመንደር ደረጃ ብቻ ተገድበው እንዲቀሩ ምክንያት ሆነ (አበበ፣ 2002)፡፡

ይሁን እንጂ፣ እነዚህ በጎሣና በመንደር ደረጃ ተገድበው ያሉት የቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር ተቋማትም ቢ ሆኑ አን ዳች አደጋ ሣያገኛቸው፣ ህልውናቸው ተ ጠብቆ፣ እስከ ወዲያኛ ው ይዘልቃሉ ማለት አይቻልም፡፡ ምንም እንኳን ሙሉ በሙሉ ይጠፋሉ ባይባልም፣ ቀስ በቀስ፣ ከጊዜ ወደጊዜ፣ ባህላዊ መልካቸው እየደበዘዘ፣ ሀገራዊ ጠረናቸው እየተለወጠ መሄዱ አይቀሬ ነው፡፡ ጊዜ ቢወስድ እንጂ፣ ጨርሰው ባይጠፉ እንኳን፣ በሌላ ባህል መዋጣቸው፣ በዘመናዊ ሥልጣኔ መተካታቸው ግን የማይቀር ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ከመሆኑ በፊት ግን፣ እነዚህ የማህበረሰቡ ባህላዊ ሀብቶች ዛሬ ባሉበት ሁኔታ ከነታሪካቸው በሣይንሣዊ መንገድ ሊቀረሱና ሊጠኑ የግድ ይላል፡፡ የዚህ ጥናት መነሻ ምክንያቱም ይኸው ስጋት ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ፣ የቡርጂ ብሔረሰብን ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓትን እና ከዚህ የአስተዳደር ሥርዓት ጋር ተያይዘው የሚፈጸሙ ሀገረሰባዊ እምነቶችንና እምነታዊ ድርጊቶችን ማሳየት ነው፡፡ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎችም ይኖሩታል፡፡

1. የቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓት አመሠራረትን፣ አወቃቀርንና አሠራርን በገለፃ ማሣየት፤
2. ከባህላዊ አስተዳደር ጋር ተያያዥ የሆኑ ባህላዊ እምነቶችን፣ በመሰብሰብና በመዘገብ ዓይነታቸውንና የአሠራር ሥርዓታቸውን በገለፃ ማሣየት፤
3. በአሁኑ ዘመን በዓለም ላይ ባሉ በዘመናዊ የአስተዳደር ሥርዓቶች ውስጥ እየተተገበረ ያለው የዲሞክራሲ ሥርዓት በቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓት ውስጥ መኖር አለመኖሩን መመርመርና መፈተሽ፤

## 1.3. የአጠናን ዘዴዎች

ከፍ ሲል እንደተመለከተው የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የቡርጂን ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓትንና ከአስተዳደር ሥርዓቱ ጋር ተያይዘው የሚፈፀሙ ባህላዊ እምነቶችን ማሣየት ነው፡፡ ስለሆነም

ይህ ጥናት ዓይነታዊ ወይም “ኂልታዊ” የአጠናን ዘዴን *(Qualitative Research Methodology)* የተከተለ ነው።

ይህ ጥናት ባብዛኛው በመስክ የተከናወነ ነው። በመሆኑም በጥናቱ ላይ ከጥናቱ ጅማሬ እስከ ፍፃሜ (በተለይም መረጃዎቹ ተሰብስበው እስከ ተጠናቀቁበት ጊዜ ድረስ) የተለያየ እውቀትና ተግባር ያላቸው በአማካይ 28 ሰዎች ተሳትፈውበታል። ለዚህ ሥራ በአማካይ 5 ቁልፍ እና 20 ሌሎች፣ በድምሩ 25 የመረጃ አቀባዮች ተመርጠዋል።

የመረጃ አቀባዮችን ለመምረጥ ከዋሉት መስፈርቶች መካከል አንዱ የመኖሪያ አካባቢ ነው። ቡርጂዎች በአራት የራስ ገዝ እና በስምንት የቢያ (የአካባቢ) አስተዳደሮች በተከፈሉ አካባቢዎች ውስጥ ይኖራሉ። ማህበረሰቡ እንደሚኖርበት አካባቢ፣ በተለይ በራስ ገዝ አስተዳደሮች መካከል፣ በባህላዊ የአስተዳደርና የእምነት ሥርዓቶች መካከል ሊኖሩ የሚችሉ መጠነኛ ልዩነቶችን ታሳቢ በማድረግ፣ በተቻለ መጠን ከእያንዳንዱ አካባቢ፣ በባህላዊ እውቀታቸውና በሥርዓቱ በነበራቸው ወይም ባላቸው ተሣትፎ የተመረጡ ሰዎች በመረጃ አቀባይነት እንዲሣተፉ ተደርገዋል።

ሁለተኛው መመዘኛ፣ በባህላዊ የፖለቲካና የእምነት ሥርዓት ውስጥ ያላቸው ተሣትፎ ነው። በዚህም በየትኛውም የቡርጂ አካባቢ የሚኖሩ፣ ነገር ግን ቀደም ሲሉ በባህላዊ የአስተዳደርና የእምነት ሥርዓት ውስጥ በኃላፊነት የሰሩና አሁንም በመሥራት ላይ ያሉት በመረጃ አቀባይነት ተመርጠዋል።

የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደርም ሆነ ተያያዥ እምነታዊ ሥርዓቶች ረዥም ሂደቶች በመሆናቸው የተነሣ፣ በየካቲት ወር መጀመሪያ አካባቢ የሚፈፀመውንና ከአዲሱ ሹም መኖሪያ ግቢ እስከ ክብረ በዓሉ መፈፀሚያ ሥፍራ (ሱቡሮ) ድረስ ያለውን የባሻን ሥርዓት ካልሆነ በስተቀር፣ ሁሉንም ሂደቶችን በሥፍራው ተገኝቶ በተፈጥሮአዊ መቼታቸው መመልከትም ሆነ መቅረፅ አልተቻለም። በዚህም በህብረተሰቡ የባሻ ሥርዓት ክዋኔ ላይ በአካል በመገኘት ክዋኔውን በመመልከትና በመቅረፅ መረጃ ተሰብስቧል።

የቡድን ውይይት፣ በጥናቱ ስለተጠቀሱት፣ ስለ ወማ እና ስለ ዳይና አስተዳደር ታሪክ፣ ቡርጂዎች በአራት የራስ ገዝ አስተዳደሮች ስለተከፈሉበት ሁኔታና አጋጣሚ፣ ስለ ቡርጂ ሕዝብ ጥንተ አመጣጥ ታሪክ፣ ስለ ጎዴ እና ስለ ሒጣኖ እምነታዊ ሥርዓቶች ጥልቅና ዝርዝር መረጃዎችን ለመሰብሰብ የዋለ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በመሆን አገልግሏል። እንዲሁም

በተሣትፎአዊ ምልከታና በቃል መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለማጠናከር ውሏል፡፡ ለዚህ ሲባልም ከ2-16 የሚሆኑ ሰዎች የተሣተፉበት ሦስት የቡድን ውይይቶች ተካሂደዋል፡፡

የቃል መጠይቅ፣ ለዚህ ጥናት የዋሉ አብዛኞቹን የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የዋለ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ በምልከታ ወቅት ግልጽ ያልሆኑና ሊብራሩ የሚገቡ ጉዳዮች፣ በቃል መጠይቅ አማካይነት እንዲብራሩ ተደርገዋል፡፡ እንዲሁም በተፈጥሮአዊም ሆነ በቅንብር ተፈጥሮአዊ መቼቶች ሊገኙ ያልቻሉ መረጃዎች በቃል መጠይቅ አማካይነት ተሰብስበዋል፡፡ በቃል መጠይቁ ላይም በዋናነት አምስት ቁልፍ እና ሌሎች ስምንት፣ በድምሩ 13 የመረጃ አቀባዮች ተሣትፈውበታል፡፡

ከፍ ሲሉ በተጠቀሱት ዘዴዎች አማካይነት ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በሙሉ፣ በመቅረፀ ድምፅ (በቴፕ)፣ በቪዲዮ፣ በፎቶግራፍ እና በጽሁፍ ተሰብስበዋል፡፡ ተቀርፀዋል፡፡ በዚህም መረጃዎቹ በጠቅላላው፣ በ23 የቴፕ ካሴቶች፣ ከአስር ሰዓት በላይ ቀረፃ በተካሄደባቸው፣ በ2 የቪዲዮ ካሴቶች ወይም በ3 የዲቪዲ ሲዲዎች አማካይነት ተሰብስበዋል፡፡ ተቀርፀዋል፡፡

### 1.4 ጥናቱ የሚያስገኘው ጠቀሜታ

የጥናቱ ዋና ዓላማ የቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓትንና ተያያዥ እምነታዊ ድርጊቶችን ማሣየት ነው፡፡ የእምነት ወይም የሃይማኖት ቀዳሚ ተግባር ደግሞ ማህበረሰቡ የደነገጋቸውን ባህላዊ ሥርዓቶችንና መተዳደሪያ ደንቦችን ማጠናከርና ቀጣይነት እንዲኖራቸው ማስቻል ነው፡፡ በመሆኑም፣ ይህ ጥናት ሲጠናቀቅ የተለያየ ዓላማና ተግባር ይዘው ወደ ቡርጂ ህዝብና ወደ አካባቢው የሚመጡ ግለሰቦችና ቡድኖች ወደ አካባቢው ህዝቦች ዘንድ ያለችግር የሚዘልቁበትን አቋራጭ መንገድ ያመላክታል ተብሎ ይታመናል፡፡ በተጨማሪም በቡርጂና በአንዳንድ አጎራባች ህዝቦች መካከል በተደጋጋሚ ለሚከሰቱ አለመግባባቶች ዘላቂ መፍትሔ ማምጣት የሚቻልበትን መንገድ በመጠቆም ጥናቱ የሚሰጠው ጠቀሜታ ቀላል አይሆንም፡፡

እንዲሁም፣ ጥናቱ ቡርጂን ለማወቅ ለሚፈልጉ ክፍሎች ህዝቡንና አካባቢውን በማስተዋወቅ ረገድ የራሱ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ በሌላ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ስለ ቡርጂ ማጥናት ለሚፈልጉ ተመራማሪዎችም ጥናቱ እንደ አንድ የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለግላል፡፡ በመሰል ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሌሎች ህዝቦችን ለሚያጠኑ ባለሙያዎችም እንዲሁ በማጣቀሻነት ሊያገለግል ይችላል፡፡ ጥናቱ፣ የመንግስትን ፕሮግራምና ፓሊሲ ለሚቀርፁ ባለሞያዎችም፣ ስለ ቡርጂ ህዝብ አንዳንድ መረጃዎችን ሊሰጥ ይችላል ተብሎ ይገመታል፡፡

ከሁሉም በላይ ግን ይህ ጥናት ሲጠናቀቅ፣ በኢትዮጵያ፣ በተለይም ‹‹በደቡብ በሚኖሩ በጉራጌ፣ በካምባታና በሲዳማ፣ ወዘተ. ህዝቦች ዘንድ ከመንደር የአስተዳደር *ሥርዓት (Village Administration System)* ከፍ ያሉና የተጠናከሩ፣ ብሎም ለዘመናዊ የአስተዳደር *ሥርዓቶች* መሠረት የሆኑ ቀደምት ባህላዊ የአስተዳደር ወይም የውሳኔ አሰጣጥ *ሥርዓቶች* ነበሩ›› ብለው የሚከራከሩ ተመራማሪዎችን ሀሳብ በማጠናከር በኩል ከፍ ያለ አስተዋፅኦ ያበረክታል የሚል ተስፋ አለኝ፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

የቡርጂ ህዝቦች በመላ ኢትዮጵያ ተሠራጭተው እንደሚኖሩ ከፍ ብለን ተናግረናል፡፡ ከኢትዮጵያ ውጭ በኬንያ፣ በናይጀሪያና በፑንጃብ (በፓክሲታን) ውስጥም "የቡርጂ ህዝቦች" እንደሚገኙ ጠቅሰናል፡፡ የኬንያ ቡርጂዎች ከኢትዮጵያ የተሰደዱ ከመሆናቸውም በላይ የሁለቱ ሕዝቦች ግንኙነት እስከዛሬም ድረስ አልተቋረጠም፡፡ በመሆኑም ጥናቱ በተለይ በኢትዮጵያና በኬንያ የሚገኙ የቡርጂ ህዝቦችን በጠቅላላው ሊያሳይ እንደሚችል ይገመታል፡፡ ይሁን እንጂ፣ የመስክ ሥራው በተለይም ለዚህ ጥናት የሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎች ሙሉ ለሙሉ የተሰበሰቡት በኢትዮጵያ ውስጥ፣ በተለይም በቡርጂ ልዩ ወረዳ፣ በስምንቱ ባህላዊ *የቢያ* አስተዳደር ውስጥ ሰፍሮ ከሚኖረው ህዝብና አካባቢ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት በቡርጂ ልዩ ወረዳ፣ በስምንቱ *ቢያ* ውስጥ ሰፍረው የሚገኙ የቡርጂ ህዝቦችን ብቻ የሚያሣይ ይሆናል፡፡

## 1.6 የጥናቱ የመረጃ ምንጮች

ይህ ጥናት የቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር እና የእምነት *ሥርዓትን* በማሳየት ላይ ያተኮረ መሆኑን ደጋግመን ገልፀናል፡፡ በመሆኑም በቡርጂ ልዩ ወረዳ ውስጥ የሚኖሩ፣ በእነዚህ ባህላዊ *ሥርዓቶች* ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ባህላዊ መሪዎችና አዛውንቶች ለዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ ምንጮች በመሆን አገልግለዋል፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ተቋርጦ የቆየውን የባህላዊ አስተዳደር *ሥርዓትን (ወሚሶንና ዳይኖማን)* እንደገና ለማስቀጠል ሲባል በ1995 ዓ.ም *የጉልጉባ ጎርሶማ* (የቡርጂ ህዝብ ከፍተኛው ምክር ቤት) ጉባኤ ተቀምጦ ነበር፡፡ በዚህ ጉባኤ ላይ የቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር *ሥርዓትንና* ደንቦችን በተመለከተ፣ ከተሳታፊዎች ከተሠነዘሩት ሀሳቦች መካከል ጥቂቶቹ፣ በልዩ ወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት ባለሙያዎች አማካይነት በመቅረፀ - ድምፅ (በቴፕ) ተቀርፀው ተቀምጠዋል፡፡ እነዚህና በጽህፈት ቤቱ በተለያዩ አጋጣሚዎች ተቀርፀው የተቀመጡ ሌሎች የድምፅና የምስል መረጃዎችም ለዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት

ውለዋል፡፡ በደቡብ ብሄረሰቦች ምክር ቤት አማካይነት ተቀርፀው የተቀመጡ ለዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ የመረጃ ምንጭ ከሆኑት መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች *(Primary and Secondary data sources)* ለዚህ ጥናት ዋነኞቹ የመረጃ ምንጮች በመሆን አገልግለዋል፡፡ ጥናቱ በመስክ የተካሄደ እንደመሆኑ፣ ተጠኚው ህብረተሰብ በዋናነት ሠፍሮ በሚገኝበት፣ በቡርጂ ልዩ ወረዳ ውስጥ ከሚገኙ ከማህበረሰቡ አባላት መካከል በባህላዊ እውቀታቸውና በተግባራቸው የተመረጡት፣ 25ቱ የመረጃ አቀባዮች፣ ለመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎች *(Primary data)* ዋንኞቹ ምንጮች በመሆን አገልግለዋል፡፡ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን ጨምሮ፣ ከተለያዩ የምርምር ተቋማት የተሰበሰቡ የተለያዩ የህትመት ውጤቶች፣ ያልታተሙ የምስል፣ የጽሁፍና የድምጽ መረጃዎች ደግሞ ከመስክ የተሰበሰቡ የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎችን ለማጠናከር የዋሉ የሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች *(Secondary data sources)* ናቸው፡፡

### 1.7 ጥናቱ የተካሄደባቸው ቦታዎችና ቀኖች

በደቡብ ብሄረሰቦች ባህል፣ ቋንቋና ታሪክ ጥናት ተቋም ውስጥ የስነ ቃልና የስነ ጽሁፍ "ባለሙያ" ሆኜ በምሰራበት ወቅት (ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ) በተለያዩ የደቡብ ህዝቦች ዘንድ ከባህላዊ ጋብቻ፣ ከለቅሶ፣ ከአስተዳደር፣ ወዘተ ጋር ተያይዘው የሚፈጸሙ እምነታዊ ድርጊቶችን ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች መሰብሰብ እንደ ጀመርኩ በ2001 ዓ.ም ትምህርት ቤት ስለገባሁ ተቋረጠ፡፡ ፋታ ሲገኝ ከትምህርቱ ጎን ለጎን በዩኒቨርስቲው ቤተመጽሐፍት ስለ ቡርጂ የተጻፉ ጽሁፎችን ማገላበጥ ጀመርኩ፡፡ የ2001 ዓ.ም የትምህርት ዘመን እንደተጠናቀቀ ወደፊት የመመረቂያ ጽሁፍ እሰራባቸዋለሁ በሚል በሀሳብ ደረጃ በመረጥኳቸው አርዕስት ዙሪያ መረጃ ማሰባሰቡ ተጀመረ፡፡ በታሳቢነት ከተመረጡት ሦስት አርዕስት መካከል ሁለቱ የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደርና እምነት ነበሩ፡፡

ጥናቱ በቡርጂ ባህላዊ አስተዳደርና እምነት ላይ የምር የጀመረው ግን ርዕሱ ከጸደቀበት ከ2002 አጋማሽ ጀምሮ ነው፡፡ በዚህም በመጋቢት 2002 አካባቢ ወደሚጠናው ህብረተሰብ ዘንድ ሄጄ፣ ቀደም ስል የማውቀውን፣ ተወልጄ የአደግሁበትን ህብረተሰብ ፣ በተመራማሪ ዓይን፣ በአዲስ መልክ ለማጥናት የመጀመሪያ ዙር መረጃ ሰበሰብኩ፡፡ በነሐሴ 2002 ውስጥ በድጋሜ ወደ ቡርጂ በመሄድ ተጨማሪ መረጃዎችን በመሰብሰብ በጥናቱ የነበሩ የመረጃ ክፍተቶችን አሟላሁ፡፡ ጥናቱን ለማጠናቀቅ በትንሹ ከአስር እስከ አስራ ሁለት ወር ፈጅቶብኛል ማለት ይቻላል፡፡

## 1.8 በጥናቱ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች

ለዚህ ጥናት የዋሉት የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎች በዋናነት የተሰበሰቡት ከ2002 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ ነው። ይህ ወቅት ለቡርጂ መንግስታዊም ሆኑ ባህላዊ ሹማምንት የውጥረት ወቅት ነበር። ውጥረቱ በሁለት ምክንያቶች የመጣ ነው። የመጀመሪያው በቡርጂና በአጎራባቹ በጉጂ ኦሮሞ ህዝቦች መካከል ለረጅም ዓመታት ያህል የዘለቀውን ግጭት ወይም አለመግባባት ለመፍታት እንቅስቃሴ መጀመሩ ነው። ለእኔ ሥራ በአውራ አቀባይነት የተመረጡት የባህላዊ አስተዳደርና እምነት መሪዎች ደግሞ በእርቁ ተግባር ላይ ዋነኞቹ ተሣታፊዎች ነበሩ። የመንግሥት ከፍተኛ ሹማምንት፣ በተለይም ሥራዬ በቀጥታ የሚመለከተው የልዩ ወረዳው የባህል፣ የቱሪዝምና የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጽህፈት ቤት ሹማምንት ግጭቱን በመፍታት ተግባር ላይ ከመነሻው ጀምሮ ግንባር ቀደም ተዋናይ ነበሩ። ይህም፣ ተገቢውን መረጃ በተገቢው ጊዜ እንዳልሰበስብ አድርጎኝ ነበር። ይሁን እንጂ፣ መፍትሔው የእርቅ ሥርዓቱ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በልዩ ወረዳው ባህል፣ ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጽህፈት ቤት አማካይነት ቀደም ሲል የተሰበሰቡ የድምፅና የምስል መረጃዎችን አንድ በአንድ መፈተሽና መረጃ መሰብሰብ እንደሆነ በማመን ይህን ስፈፅም ቆየሁ። በመጨረሻም የፈለኩትን አገኘሁ።

ሁለተኛው ምክንያት አራተኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ነው። ምርጫው የመንግሥት ሹማምንትን ድጋፍ በፈለኩት ጊዜ እንዳላገኝ ያድርግ እንጂ፣ አውራ አቀባዮቼን እንዳላገኝ ያሳደረው ተፅዕኖ ግን አልነበረም። ይህንንም ችግር ከፍ ሲል በተጠቀሰው መልክ በወረዳው የባህል፣ የቱሪዝምና የመንግስት ኮሙንኬሽን ጽህፈት ቤት ውስጥ ተቀርፀው የተቀመጡ መረጃዎችን በመመርመር ልወጣ ችያለሁ።

ሌላው የገንዘብ ችግር ነው። ለዚህ ጥናት ማስፈጸሚያ ሲባል ከትምህርት ተቋሙ የተመደበልኝ (የተሰጠኝ) ገንዘብ ፋይዳው ባይናቅም፣ መጠኑ ግን እጅግ አናሳ ነበር። ይህም በጥናቱ ላይ ያሳደረው አሉታዊ ተጽዕኖ ቀላል ባይሆንም ግን በቤተሰቤ ድጋፍ ችግሩን በከፍል መቅረፍ ችያለሁ።

## 2. የተዛማጅ ጽሁፎች ክለሳና ግምገማ

የሰው ልጅ አሁን ካለበት ለመድረስ ረዥም ዘመናትን አስቆጥሯል፡፡ በርካታ የህይወት ውጣ ውረዶችን አሳልፏል፡፡ በዚህ በህይወት ጉዞው ለሚያጋጥሙት ችግሮች በራሱ የእውቀት ደረጃ መፍትሄ እየሰጠ፣ ከአጋጣሚዎቹ እየተማረ አንድ የህይወት ስርዓት አበጅቷል፡፡ ከዚህ ከአኗኗር ስርዓቱ ጋር የሚሰምር ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ተቋማትን ገንብቷል፡፡ የአስተዳደር፣ የእምነት፣ የልማት ወዘተ. ስርዓቶችን መስርቷል፡፡ በአጭሩ፣ የሰው ልጅ ከዚህ በቴክኖሎጂ ከተራቀቀው ዓለም የደረሰው ከአኗኗር ስርዓቱና ከህይወት ገጠመኙ ባገኘው እውቀት ተጠቅሞ፣ ለራሱ በሚስማማው መልክ እየለወጠ፣ እያሻሻለ በመጓዝ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ ቁሳዊውና መንፈሳዊው ህይወቱ እየተደጋገፈ፣ የህይወት ሂደቱ ቀስ በቀስ እየተለወጠ ነው አሁን ታለበት የደረሰው (ፈቃደ፣ 1991፣ 47-48)፡፡

ይህ ሁሉ ሲጠቃለል ለሰው ልጅ ለአሁንነቱ ጥንታዊነቱ መሰረት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ወይም ለአሁኖቹ ዘመናዊ የፖለቲካና የእምነት ስርዓቶች ጥንታዊው ወይም ባህላዊው የአስተዳደርና የእምነት ስርዓቶች ጠንካራ መሰረት ነበሩ ማለት ነው፡፡ እዚህ ላይ የቡርጂን ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓትን መጥቀሱ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ቡርጂዎች፣ በአካባቢያቸው ዘመናዊ የፖለቲካ ሥርዓት ከመዘርጋቱ በፊት፣ ከህይወት ልምዳቸው ባገኙት እውቀት ላይ ተመስርተው ያበጁት ባህላዊ የፖለቲካ ሥርዓት ነበራቸው፡፡ የቡርጂን ባህላዊ የፖለቲካ ሥርዓትን ያነበበ የዚህ ዘመን ሰው "በአሁኑ ዘመን ላይ በአገራችንም ሆነ በሌሎች ጥቂት አገሮች ውስጥ የሚተገበረው ፌደራላዊ ሥርዓት ምንጩ ወይም መሰረቱ የቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓት ይሆን እንዴ?" ብሎ ሣይጠይቅ አይቀርም የሚል ግምት አለኝ፡፡ ለምን? ቢሉ አንዱ ከአንዱ የተቀዳ ስለሚመስል ነው፡፡ ግልጽ ባለ አነጋገር "ዘመናዊ"፣ "ባህላዊ" ከመባላቸው ውጭ ባብዛኛው ተመሳሳይ ናቸው፡፡

ይህ ምዕራፍ ሶስት ጉዳዮችን ያነሳል፡፡ በመጀመሪያ ስለ ባህላዊ አስተዳደር (ፈረንጆች *Local Government ወይም Traditional Government ወይም Native Government* ብለው ስለሚጠሩት ማለት ነው) ምሁራን የሰነዘሯቸውን ሀሳቦችንና የሰጧቸውን ብያኔዎችን ያቀርባል፡፡ በመቀጠልም ስለ ሀገረሰባዊ ሃይማኖት ወይም እምነት *(Folk religion /belief or primitive religion /belief)* በምሁራን የተሰነዘሩ ሃሳቦችንና የተሰጡ ብያኔዎችን ይዘረዝራል፡፡ በመጨረሻም በቡርጂ ባህላዊ አስተዳደርና እምነት ላይ የተሰሩ ቀደምት ሥራዎች ወይም የታተሙ ፅሁፎች ተከልሰውና ተገምግመው ይቀርባሉ፡፡

## 2.1 ስለ ባህላዊ አስተዳደር የምሁራን ሀሳቦችና ብያኔዎች

ባህላዊ አስተዳደርን በተመለከተ፣ በርካታ ምሁራን በርካታ ሀሳቦችን ሰንዝረዋል። ብያኔ ሰጥተዋል። ከእነዚህ ፀሐፊዎች መካከል Nsarkoh (1964) አንዱ ነው። *Nsarkoh* ባህላዊ አስተዳደር ከማዕከላዊ መንግስት (*Central Government*) አስቀድሞ የነበረ፣ በልማዳዊ ህግ እና በአካባቢያዊ ደንብ የሚመራ ሥርዓት ነው በማለት ጽፏል (13)።

*Harris (1957)* የተባለው ፀሀፊ ናይጄሪያን ዋቢ አድርጎ ናይጄሪያ እንደ አንድ ልዑላዊ ሀገር ወይም መንግስት ከመቆጠሯ አስቀድሞ ቢያንስ ቢያንስ በመንደር ደረጃ ወይም ከዚህም ሰፋ ያለ አስተዳደራዊ ስርዓት በናይጄሪያ ውስጥ ሲተገበር የነበረ መሆኑን በመጥቀስ የ‹Nsarkoh›ን ሀሳብ ይጋራል (5) ።

አሜሪካና ታላቋ ብሪታኒያም ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓትን በተመለከተ የራሳቸው አመለካከትና ግምት አላቸው። አሜሪካዊያን ለባህላዊ አስተዳደር ያላቸው አመለካከትና ግምት ላቅ ያለ ነው። ለዚህ በጎ አመለካከት መሰረታዊ ምንጩ ደግሞ "*The less government the better*" የሚለውና ረዥም ዘመናትን ያስቆጠረው የሀገሪቱ መሰረታዊ መርህ ነው። በታላቋ ብሪታኒያ (በስፋት በብሪታኒያ የጋራ ብልፅግና ሀገሮች ዘንድ) ደግሞ ባህላዊው የአስተዳደር ስርዓት እንደ አንድ ታላቅ የፖለቲካ ትምህርት ቤት፣ የአኗኗር (የህይወት) እና የባህርይ ማነጫ ተቋም ተደርጎ ነው የሚቆጠረው (Nsarkoh, 1964, 13) ።

እነዚህ ቀደምት አባታዊ የአስተዳደር ሥርዓቶች (*Paternal government*) ጊዜው ያለፈባቸው፣ የተረሱና ለመጪዎቹ ስርዓቶች የሚያበረክቱት (ያበረከቱት) አንዳች ፋይዳ የሌላቸው (ያልነበራቸው) ስርዓቶች እንደሆኑ አድርጎ ያቀረበ ጸሐፊም አለ። በጸሐፊው እምነት፣ በባህላዊ አስተዳደር ውስጥ በከፍተኛ የአመራር ቦታ ላይ ያሉ ሹማምንት፣ በሙስና የዘቀጡ፣ ለቦታው ብቃት የሌላቸውና ተገቢ ያልሆኑ ሰዎች ናቸው። በመሆኑም፣ ይህ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት እንደነዚህ ዓይነቶቹ አላስፈላጊ ሰዎች፣ በስልጣናቸው ላይ እስከ ወዲያኛው እንዲቆዩ ወይም ስልጣናቸው ቀጣይነትና ዘላቂነት እንዲኖረው የሚያደርግ፣ የክፉ ስርዓት ተምሳሌት ነው (Wraith, 1953, 33)[4]።

በሌላ ወገን ደግሞ Sklar (1999,117-118) እና Bahru (2006,18) ባህላዊ የፖለቲካ ስርዓቶች ጊዜ ያለፈባቸውና ረብ የለሾች ሳይሆኑ፣ ዛሬም ድረስ በበርካታ ወገኖች የሚፈለጉ፣ ቀደም ሲልም

---

[4] K.J. Nsakoh Local Government in Ghana Ghana University Press: Accra. (Ghana University Press: Accra 1964) በሚል ርዕስ በፃፈው መጽሐፍ ውስጥ ከተጠቀመው ሀሳብ ውስጥ ወስጄ የተጠቀምኩት ነው።

ለዘመናዊ የአስተዳደር ስርዓቶች መሰረት የሆኑ መሆናቸውን በመጥቀስ የ*Wraith*ን ሃሳብ ያጣጥሉታል፡፡ ለዚህ የመከራከሪያ ሀሳባቸውም፣ የተለያዩ የአፍሪካ ህዝቦችን ተሞክሮ በዋቢነት ይጠቅሳሉ፡፡ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በአፍሪካ ውስጥ የተካሄዱት የፀረ-ቅኝ አገዛዝ ትግሎችና ንቅናቄዎች፣ በእነርሱም የተገኙ ውጤቶች፣ በባህላዊው የፖለቲካ ስርዓት የታገዙ ነበሩ:: ከነፃነት በኋላም ቢሆን ከበፊቱ ባልተሻለ ወታደራዊ አገዛዝ ስር የወደቁና በሙስና የተዘፈቁ የአፍሪካ አገሮች፣ ከዚህ ከብልሹ ስርዓት ለመላቀቅ ብሎም አዲስ የዲሞክራሲ ስርዓት ለመገንባት ሲሉ ወደ ኋላቸው ተመልሰው፣ ከቅኝ የአገዛዝ ስርዓት በፊት የነበረውን ባህላዊ የፖለቲካ ስርዓታቸውን መልሰው ለማደስና በስራ ላይ ለማዋል ተገደው እንደነበር እነዚሁ ፀሐፍት ያትታሉ፡፡

የምዕራብ አፍሪካን ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት ያጠኑት *Fortes* እና *Earns* (1940) የምዕራብ አፍሪካ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓቶች ሶስት መልኮች ወይም ገፅታዎች እንዳሏቸው እንደሚከተለው ጽፈዋል፡፡

> *"The indigenous political systems of the parts of west Africa . . . would appear to fall into one or another of the three types . . . in which the political structure and kinship organization are completely fused; those in which the lineage structure is the framework of the political system, and finally, those to be found in larger groups in which an administrative organization is the frame work of the political structure "(6-7)*[5].

Cowan (1995) የተባለው ጸሐፊ ደግሞ የአፍሪካ ህዝቦች ሀገር በቀል የአስተዳደር ስርዓቶች የሚጋሯቸው ወይም ተለይተው የሚታወቁባቸው ባህሪያት እንዳሏቸው ያስረዳል፡፡ ከእነዚህ መለያ ባህሪያት መካከልም በ*Chief* (በባህላዊ ንጉስ ወይም በባላባት) የሚመሩ መሆናቸው አንዱ መሆኑን ይጠቅሳል (4-5)፡፡ የአፍሪካ ማህበረሰቦች በሚመሩባቸው ባህላዊ የፖለቲካ ስርዓቶች ውስጥ ቁንጮ ላይ የተቀመጡ ባህላዊ መሪዎች፣ ምንም እንኳን በአማካሪዎች እየታገዙ የሚሰሩ ቢሆንም፣ ጥቂቶቹ የለየላቸው አምባገነኖች *(complete autocrats*) መሆናቸውን ይሄው ፀሀፊ ያስረዳል፡፡ በአማካሪነት የሚመደቡላቸው ደግሞ ከ*Chief* ጋር ምንም ዓይነት የስጋ ዝምድና የሌላቸው፣ ታዋቂ አዛውንቶች አሊያም የጎሳ መሪዎች ናቸው፡፡ የአማካሪዎቻቸውን ምክር የማይቀበሉ መሪዎች ደግሞ በስልጣናቸው ላይ ብዙ እንደማይቆዩ ብዙ የአፍሪካ ህዝቦች የማህበረሰቡን ልማድ ወይም ደንብ የሚጥሱትን ባህላዊ መሪዎቻቸውን የሚቆጣጠሩበት ባህላዊ ስርዓት ያላቸው መሆኑን እንዲህ በማለት ፀሐፊው ያስረዳል፡፡

---

[5] L.Gray Cowan Local Government in West Africa (Colombia University Press: New York) በሚል መጽሐፍ ከተጠቀመው ሀሳብ ላይ የተወሰደ ነው፡፡

> *Few traditional chiefs in the political systems of Africa could be considered complete autocrat. In almost every case they were assisted by a council, sometimes made up of elders or of the heads of other lineages within the group. While the chief was not obliged to accept the advice of his council, no chief who expected to remain long in office would be unwise enough to ignore his council consistently. Many tribes had clearly defined traditional procedures for getting rid of a chief who had overstepped the bounds of tribal mores (Cowan, 1995, 5-6).*

በአንዳንድ የአፍሪካ ማህበረሰቦች ዘንድ ደግሞ ማህበረሰቡን የሚያስተዳድሩት ወይም የፖለቲካና የሃይማኖት ስርዓቱን በበላይነት የሚመሩት እድሜን (*Age group*) መሰረት አድርገው ከሚመሰረቱ ቡድኖች መካከል የሚወከሉ አባላት ይሆናሉ (Cowan, 1995)፡፡

እነዚህ ባህላዊ መሪዎች በተለያየ ህዝቦች ዘንድ ሁሉ እንደሚኖሩ፣ ተግባራቸውም በሚመሩት ህብረተሰብ የኑሮ ሁኔታ ላይ እንደሚመሰረት (Cowan, 1995,13) ያስረዳል፡፡ ጦረኛ በሆነ ህብረተሰብ ‹‹ንጉሥ›› ሆኖ የተመደበ ሰው ጦርነትን የሚመራ ብቻ ሣይሆን፣ በሥሩ ለሚተዳደር ሕዝብ ቀለብ የሚያቀርብ፣ የሚያስተዳድር፣ የሚዳኝና የማህበረሰቡን ንብረትና ደህንነት የሚያስጠብቅና የሚጠብቅ መሪ በመሆን ይሰራል፡፡ እንደ ፀሐፊው እምነት አርብቶ አደር በሆነ ህብረተሰብ ዘንድም ያለው ሁኔታ ተመሣሣይ ነው፡፡ እነዚህ ሕዝቦች በጎቻቸውንና ፍየሎቻቸውን ይዘው ግጦሽ ፍለጋ ከቦታ ወደ ቦታ በሚዘዋወሩባቸው ጊዜያት ሁሉ፣ ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓታቸውንም ከፍየሎቻቸውና ከበጎቻቸው ጋር ይዘው ይንቀሣቀሳሉ፡፡

ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት ከሁሉም በላይ የሚተገበረው፣ በአንድ በተወሰነ አካባቢ በሰፈረና በግብርና ሥራ በሚተዳደር ህብረተሰብ ዘንድ ነው፡፡ በእንደዚህ ዓይነቱ ህብረተሰብ ዘንድ የሚተገበረው ባህላዊ የፖለቲካ ስርዓት በአንፃራዊ መልኩ፣ በሚገባ የተጠናከረና የተደራጀ ነው፡፡ በእነዚህ ህዝቦች ዘንድ ባህላዊ መሪው ህዝቡን በችግርና በአደጋ ወቅት የሚመራ ብቻ ሳይሆን፣ ከሌሎቹ ረዳቶቹና አማካሪዎቹ ጋር በመሆን የሚያስተዳድር፣ የሚዳኝ፣ የህዝቡን ሀብትና ደህንነት የሚጠብቅ ‹‹ፖሊስ›› የሚያዘጋጅ፣ እያንዳንዱን ጎሳ በበላይነት የሚቆጣጠር መሪ በመሆን ያገለግላል፡፡ እንዲህ የሁሉ የበላይ የሆነ *Chief* በግብርና በሚተዳደር ህብረተሰብ ውስጥ ሁልጊዜ ይኖራል (Harris, 1957, 5; Cowan, 1995,14)፡፡

ሌላው የአፍሪካዊያን ባህላዊ የፖለቲካ ሥርዓት መለያ ባህርይ፣ በጥንቆላ (magic) መሰረት ላይ በተገነባ የፖለቲካ ሥርዓት የሚመራ መሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ባህላዊ የህዝብ መሪ ማናቸውንም ተግባራት የሚያከናውነው (በአማካሪ መታገዙ እንደተጠበቀ ሆኖ) ‹‹አለው›› በሚባለው በአስማታዊ፣ በጥንቆላዊና በልዕለ ተፈጥሮአዊ ሀይል በመታገዝ ይሆናል፡፡ መሪው መሬትን የማለምለም፣ ዝናብ የማዝነብ መለኮታዊ ሀይል አለው፡፡ ግልፅ በሆነ አነጋገር አንድ

Chief የሆነ ሰው በዚያ Chief በሆነበት ግዛት ውስጥ በሚኖሩ ማህበረሰቦች፣ ቡድኖችና ግለሰቦች ህይወት ወይም ሞት ላይ ሁሉ ስልጣን ይኖረዋል ማለት ነው:: እንደ ፀሀፊው አገላለፅ፣ በዚህ በጥንቆላዊ ወይም በአስማታዊ ሥራ ላይ ተመስርተው የሚወጡ ህጎችም የማህበረሰቡን የአይነኬን ልማድ ተገን ያደረጉና በሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ዘንድ ተቀባይነትን ያገኙ ናቸው (Cowan, 1959,5)::

የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው፣ የቡርጂ ህዝብ የሚመራበት ባህላዊ የፖለቲካ ሥርዓት ከፍ ሲል በCowan የተጠቀሱ ባህርያትን ባብዛኛው የሚጋራ ይመስለኛል:: የቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካ ሥርዓት ወማ በሚባል ባህላዊ መሪ ይመራል:: ወማውም ሆነ ሌሎች ባህላዊ መሪዎች አማካሪዎች አሉዋቸው:: አማካሪዎቻቸው ደግሞ የጎሳ መሪዎችና "በጡረታ" የተገለሉ የአመራር አባላት ናቸው:: ባህላዊ መሪዎቹ አንዳቸውም በራሳቸው አስማታዊም ሆነ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል ባይኖራቸውም ማንኛውንም ተግባር የሚያከናውኑት ግን አስማታዊና ጥንቆላዊ ወይም ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል ባላቸው ክፍሎች በመታገዝ ነው::

በCowan እንደተጠቀሰው ቡርጂ ውስጥም ዝናብ የማዝነብ፣ ጦርነት የማቆም፣ በሽታ የመከላከል፣ ወዘተ መንፈሳዊ ኃይል ያላቸው ባህላዊ መሪዎች አሉ ተብሎ ይታመናል:: በዚህም በማህበረሰቡ ዘንድ እንደ ‹‹ቅዱስ›› ይቆጠራሉ:: ይፈራሉ:: ይሁን እንጂ እንዳሻቸው እንዳይሆኑ ህዝቡ ይቆጣጠራቸዋል:: የቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካና የእምነት ሥርዓት አወቃቀርም አንዱ ሌላውን እንዲቆጣጠር ሆኖ የተዋቀረ በመሆኑ እንዳሻቸው እንዲሆኑ ዕድል የሚሰጥ አይደለም (ለዝርዝሩ የዚህን ጥናት ምዕራፍ 4 እና 5 ተመልከት)::

በአንዳንድ ማህበረ ሰቦች ዘንድ ባህላዊ መሪዎ ቹ የሚታገዙበት ልዕለ ተ ፈጥሮአዊ ወይም ጥንቆላዊ ሃይል ‹‹ማህበረሰቡን የመሰረቱ *(founders of the clan)* ናቸው›› ከሚባሉት ከአያት፣ ከቅድመ አያቶቻቸው ጋር የተሳሰረ ነው:: ይህ ሲሆንም፣ በማህበረሰቡ chief ሆኖ የሚሰየም ማንኛውም መሪ የአበው ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል እንዲሰፍርበት የሚፈፅማቸው በርካታ እምነታዊ ስርዓቶች ወይም ግዴታዎች ይኖራሉ:: የማህበረሰቡ የፖለቲካ ስርዓት ለአንዴ እንኳን ሳይሰናከል እንዲቀጥል፣ ዘላቂነቱና ቀጣይነቱ እንደተጠበቀ እንዲቆይ የሚደረገው በዚህ መልክ እንደሆነ (Cowan, 1959) ያስረዳል ::

ከፍ ተብለው የተጠቀሱትን ዓይነት ባህሪያት የነበራቸው ባህላዊ የፖለቲካ ስርዓቶች ከቅኝ የአገዛዝ ስርዓት አስቀድመው፣ በአፍሪካ ህዝቦች ዘንድ ተግባራዊ ይደረጉ የነበሩ ቢሆንም ግን

የኋላ የኋላ በቅኝ ገዢዎችና በነፃ የአፍሪካ መንግስታት አማካኝነት ተጨፍልቀዋል (Bahru,2002,17)፡፡ በዚህ ዓይነት በቅኝ ገዢዎች፣ ብሎም በአፖርታይድ ስርዓት አማካይነት ነባሩ ባህላዊ የፖለቲካ ስርዓታቸው ከተጨፈለቀባቸው የአፍሪካ ሀገራት መካከል ናሚቢያና ደቡብ አፍሪካ ይጠቀሳሉ (Sklar,1999,116)፡፡ በአንፃሩ የመጨፍለቅ ዕጣ ያላጋጠማቸው፣ ይልቁንም ከማዕከላዊ መንግስት ወይም ከዘመናዊ አስተዳደር ጋር ተቀናጅተው ህዝባቸውን ያገለገሉ ባህላዊ የፖለቲካ ተቋማትም አሉ፡፡ ለዚህ ደግሞ በታላቋ ብሪታኒያ የቅኝ አገዛዝ ስር ከነበሩት የምዕራብ አፍሪካ ሀገሮች መካከል ናይጄሪያንና ጋናን መጥቀስ ይቻላል (Cowan,1959; Amegashie, 1964)፡፡

ይሁን እንጂ፣ እነዚህ ከፍተኛ ዋጋ የነበራቸው ባህላዊ የአስተዳደር ተቋማት ጨርሶኑ አልጠፉም፡፡ እንደተጠሉም፣ እንደተናቁም አልቀሩም፡፡ ከነፃነት በኋላ በአፍሪካ ተዘርግቶ የነበረውን ፖርላሜንታዊ የዲሞክራሲ ስርዓት መውደቅን ተከትሎ አፍሪካውያን ወደ ጥንታዊውና ነባሩ የፖለቲካ ስርዓታቸው ለማተኮር ተገደዋል (Bahru, 2002, 17)፡፡

ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ፣ ከፍ ተብለው ከተጠቀሱት ጋር በብዙ መልካቸው የሚመሳሰሉ ባህላዊ የፖለቲካና የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓቶች በኢትዮጵያም ውስጥ በጉራጌ፣ በካምባታ፣ በሲዳማ... ወዘተ ህዝቦች ዘንድ በሚገባ ይተገበሩ ነበር (Bahru, 17; Yakob, 45; Aadland, 29; 2006)፡፡ ከሁሉም በላይ ግን እንዲህ ዓይነቶቹ ዲሞክራሲያዊ ይዘት ያላቸው የአስተዳደርና የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓቶች በደቡብ የኢትዮጵያ ህዝቦች አካባቢ ጎልተው ይታዩና ይዘወተሩ እንደነበር *"While northern Ethiopia, the seal of the classical Ethiopian civilization, offered few cases of democratic governance in the past, the southern part witness certain democratic and equalitarian forms of administration and decision making ..." (Bahru, 1999, 233)* በማለት ፀሐፊው ይገልጻል፡፡ ለዚህ አባባሉም የኦሮሞዎችን *የገዳ* ስርዓትንና *ሚታብ* የሚባለውን የሙርሲዎችን ባህላዊ የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓትን በዋቢነት ይጠቅሳቸዋል፡፡

## 2.2. ስለ ሀገረሰባዊ ሃይማኖት ወይም እምነት የመስኩ ምሁራን ሀሳቦችና ብያኔዎች

ሃይማኖት (እምነት) ምንድነው? አንድ ነገር ሃይማኖት (እምነት) ነው ወይም አይደለም የሚባለው ምን ሲሆን ነው? ወዘተ ለሚሉ ጥያቄዎች የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ምላሾችን ሰጥተዋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ሁሉንም ወገኖች የሚያስማማ፣ አንድ ወጥ የሆነ ብያኔ እስከ ዛሬ አልተሰጠም፡፡ እስከ ዛሬ ከተሰጡት ብያኔዎች መካከል ግን፣ በተወሰነ ደረጃ ተቀባይነትን ያገኘው

ሃይማኖታዊ እምነት (religious belief) ህያውና ረቂቅ በሆነ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል ማመን መሆኑን ፀሀፊው *"There seems to be no universally accepted definition of what constitutes religion. A fairly widely accepted aspect of most definitions is that religious belief implies a belief in the supernatural expressed in the form of both animate and abstract forces." (Posnansky, 1972, 29)* በማለት ይገልፃል፡፡

Spiro (1966, 97)[6] የተባለው ፀሐፊ ሃይማኖት የአንድ ህብረተሰብ መገለጫ የሆኑ ባህላዊ ቅርሶችን በሙሉ በአንድ ላይ አቅፎ የያዘ ተቋም መሆኑን ያትታል፡፡ *Wallaceም (1966, 46) "... religion is a conglomeration of rituals and beliefs whose components are integrated at the level of cult institution."* (ሃይማኖት በአምልኮ ሥፍራዎች ላይ የሚፈጸሙ የልማዳዊ ድርጊቶችና እምነቶች ውህደት ውጤት ነው) በማለት የSpiroን ሀሳብ በከፊል ይጋራል፡፡

Messenger (1972) በበኩሉ ሃይማኖትን *"Primitive religion"*፣ *"Folk religion"* እና *"Civilized religion"* በማለት በሶስት ይከፍላቸዋል፡፡ በዚህም ሀገረሰባዊ ሃይማኖት *(Folk religion)* አንድ ህብረተሰብ ጠቅላላ ካለው ባህል ውስጥ እንደ አንዱ ነጠላ የባህል ክፍል የሚቆጠር፣ የባላገር (የህዝብ) ሃይማኖት ነው በማለት ፅፏል (218)፡፡

አንድ ባህላዊ እሴት ወይም አንድ ነገር ‹‹ሃይማኖት ነው›› የሚባለው ምን ምን? ሁኔታዎችን ሲያሟላ እንደሆነ የፃፈም አለ፡፡ Wallace (1966) ማንኛውም ሃይማኖት ከሚከተሉት መካከል አብዛኛውን ወይም ሁሉንም ሊይዝ ወይም ሊኖሩት እንደሚገባ እንዲህ በማለት ጽፏል፡፡

> *Every religion recognizes several or all of the following entities: one or more deities, spirits and demons, personal and impersonal power, one or more souls, ghosts, fate, luck, magic, and witches. In addition each religion attaches religious significance to certain objects and plates, such as the insignia of a priest, or the mountain abode of a deity (pp, 52-101)[7].*

እንደ Wallace አባባል፣ እነዚህን ከፍ ብለው የተዘረዘሩትን ነገሮች ያሟላ ሁሉ ሃይማኖት ነው ማለት ነው፡፡ ወይንም ምንም ይሁን ምን፣ ብቻ አንድ ነገር ‹‹ሃይማኖት ነው›› ለመባል ከዝርዝሮቹ ቢያንስ አብላጫውን ነገር ሊያካትት ይገባል፡፡ ይሄው ፀሀፊ በዓለም ላይ አራት ዓይነት የአምልኮ ተቋማት ወይም ሃይማኖቶች እንዳሉም በሚከተለው መልኩ ያስረዳል፡፡

---

[6] M. Posnansky In Rangerst (eds.) The Historical Study of African Religion (1972) በሚል መጽሐፍ ውስጥ ከተጠቀመው የተወሰደ፡፡

[7] .John C. Messenger "Folk religion".In Dorson, M. Richard, (eds.) Folklore and Folk Life (1972, PP 217 -232) ውስጥ ከተጠቀመው ከWallace ሃሳብ ውስጥ ወስጄ የተጠቀምኩት ሃሳብ ነው፡፡ ዋናውን ጽሁፍ ላገኝ አልቻልኩም፡፡

*"According to the relative presence or absence of these cult institutions, four types of religions can be distinguished. <u>The Shamanic</u> possesses only individualistic and shamanic cult institution. <u>The Communal</u> possesses individualistic, shamanic and communal cult institutions. <u>The Olympian</u> possesses all four kinds of cult institution and is polytheistic. And <u>The Monotheistic</u> also possesses all four kinds but accepts one deity ...." (Wallace,1966, 52-101) 8* (አፅንኦቱ የራሴ ነው)::

Wallace በማያያዝም፣ *Shamanic* individualistic እና *Shamanic* የሆኑ የአምልኮ ተቋማትን ብቻ የያዘና በእስኪሞች እና በአንዳንድ የዓለም ህዝቦች አካባቢ ብቻ የሚገኝ ሃይማኖት መሆኑን ይገልጻል:: *Communal* የሚባለው ደግሞ በውስጡ የ*Shamanic*፣ የግልና የጋራ የሆኑ የአምልኮ ተቋማትን የያዘ ሃይማኖት ነው:: ሃይማኖቱንም የአሜሪካ ህንዶች፣ እንዲሁም የአውስትራሊያና የአፍሪካ (ማዕከላዊውና ሰሜናዊው ክፍል ሲቀር የተቀሩት) ህዝቦች እንደሚከተሉት ይጠቅሳል:: *Olympian* ሁሉም (አራቱም) ዓይነት የአምልኮ ተቋማት ያሉበትና የብዙ አምላክነትን መርህ የሚከተል ሃይማኖት ሲሆን፣ የመካከለኛ አሜሪካ፣ የማዕከላዊ አፍሪካና የምስራቅ እስያ ህዝቦች ይከተሉታል:: አራተኛው ዓይነት ሃይማኖት *Monotheistic* ይባላል:: ከፍ ተብለው የተጠቀሱትን፣ አራቱንም የአምልኮ ተቋማትን የያዘ ሲሆን፣ የአንድ አምላክነትን መርህ ይከተላል:: ይህ ዓይነቱ ሃይማኖት የህንዱን ቡድሂዚም፣ የአይሁድ፣ የእስልምና፣ የክርስትናና የቻይናዊያን ሃይማኖቶችን የሚያጠቃልል መሆኑን (Wallace,1966) ይጠቁማል::

እነዚህ፣ ከፍ ተብለው የተዘረዘሩት ሀሳቦችና ብያኔዎች ሃይማኖትን (religion) በሚመለከት በምሁራን የተሰነዘሩ ናቸው:: ቀጥለን ደግሞ ‹‹እምነትን›› (belief) በሚመለከት ምሁራን የሰነዘሩዋቸውን ሀሳቦችንና ብያኔዎችን እንመለከታለን::

Posnansky (1972) ሃይማኖትን ሲበይን፣ ሃይማኖት ከማህበረሰቡ በርካታ ባህላዊ የእምነት ስርዓቶች መካከል እንደ አንዱ ተደርጎ የሚቆጠር ነው (*Religion is seen as one of several culturally constituted belief systems (29)* በማለት ሃይማኖትና እምነት ተወራራሾች መሆናቸውን ያስረዳል:: ኪዳኔ ወልድ ክፍሌም (1948, 227) <u>መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ</u> በሚል መጽሐፉ ውስጥ "እምነት" ለሚለው ቃል "በቁሙ ሃይማኖት ማመን እሙንነት... ወዘተ የሚል ፍች በመስጠት እምነትና ሃይማኖት አንድ መሆናቸውን ያሳያል::

እምነት፣ በተለይም ሀገረሰባዊ እምነት የሰው ልጆችን ብቻ የሚመለከቱ ሀሳቦች (ideas) ናቸው ብሎ የበየነ ፀሐፊም አለ:: በፀሐፊው አባባል፣ እምነት በምትሃት ወይም በአስማት፣ በልዕለ

8 ከላይኛው ጋር ተመሳሳይ ነው::

ተፈጥሮአዊ ሀይል፣ በትንቢት፣ በጥንቆላ፣ በሙት መንፈስ ማለትም በጣዕረ ሞት፣ በቅዠትና በመሳሰሉት ሁሉ ማመንን ያጠቃልላል (Encyclopedia Encarta, 2005, 2)::

የHebding እና የGlick (1996) ብያኔም ከፍ ሲል ከተሰጠው ብያኔ ጋር ይስማማል። እንደ እነርሱ አባባል እምነት ወይም እምነቶች (beliefs) ሰዎች ስለ ሁለንተናዊ ዓለም ያላቸው ሀሳቦች (ideas) ናቸው። እንዲሁም እምነቶች ግለሰብን፣ ህብረተሰብ ን ወይም ሌሎች ማናቸውንም ማለትም ስነፍጥረታዊ፣ ማህበራዊና ልዕለ ተፈጥሮአዊ ዓለምን የሚመለከቱ የሰው ልጅ ሀሳቦች እንደሆኑ አድርገው ይበይናሉ (51-52)::

ፈቃደ (1991,14) ሀገረሰባዊ እምነት፣ በታወቁት የሃይማኖት መጻሕፍት ውስጥ ከታዘዘው ውጭ ሰዎች በየራሳቸው (በዋናነት የሚከተሉት ሃይማኖት ተከታይ መሆናቸው እንዳለ ሆኖ ማለት ነው) የሚከተሏቸውን እምነቶችና የሚፈጽሟቸውን ድርጊቶች፣ እንዲሁም በሰዎች በየዕለት ኑሮ የሚከሰቱ፣ በቤተ ፀሎት፣ በሃይማኖት መጻሕፍትና ተቋማት ሆነ ተብለው የማይመሩ እምነት ነክ ጉዳዮችን እንደሚያጠቃልል ይገልጻል።

በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ፣ በአፍሪካ ህዝቦች ዘንድ ተግባራዊ የሚደረጉት ባህላዊ የፖለቲካ እና የእምነት ተቋማት ሁልጊዜ አንዳቸው በአንዳቸው ውስጥ የሚኖሩ፣ የሚደጋገፉና የማይነጣጠሉ የህብረተሰብ ገፅታዎች ናቸው (Torrance, 1994, 4):: የዚህ ዓይነቶቹን የተደራጁና የተጠናከሩ ባህላዊ የፖለቲካና የእምነት ተቋማት ከነበራቸው፣ አሁንም በከፊል ካላቸው የኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል ቡርጂ አንዱ ነው።

## 2.3 በቡርጂ ላይ የተደረጉ የቀደምት ጥናቶች እና ጽሁፎች ክለሳና ግምገማ

ከፍ ሲል እንደተመለከተው *በአባ፣ በቦሄ፣ በቢያ፣ በጉልጉባ* ወይም በጎሣ ደረጃ እየተገናኙ የውስጥ ጉዳዮቻቸውን በጋራ የሚወያዩባቸው፣ ለችግሮቻቸው መፍትሄ የሚሰጡባቸው፣ ወዘተ ሀገር በቀል የእምነትና የፖለቲካ ሥርዓት ከነበራቸው ከደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል አንዱ የቡርጂ ህዝብ ነው (Amborn and Kellner, 1999):: ከእነዚህ ባህላዊ ተቋማት መካከል የየዘመኑን ተፅዕኖ መቋቋም ተስኗቸው የተቋረጡ የመኖራቸውን ያህል፣ አብዛኛውን ተፅዕኖ ተቋቁመው ከዚህ የደረሱና እስከዛሬም በመተግበር ላይ ያሉ አልታጡም። ተቋርጠው ከነበሩት መካከል ከ1996 ዓመተ ምህረት ጀምረው ተግባራዊ መሆን የጀመሩም እንዲሁ አሉ። ሣይቋረጡ ከዚህ የደረሱትም ሆኑ ከተቋረጡ በኋላ ያንሰራሩት የቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደርና የእምነት ሥርዓቶችም ቢሆኑ አንዳች አደጋ ሳያገኛቸው፣ ህልውናቸው እንደተጠበቀ እስከ ወዲያኛው

ይዘልቃሉ ማለት አይቻልም። በቀደመው ክፍል እንደተጠቀሰው ምንም እንኳን ሙሉ በሙሉ ይጠፋሉ ባይባልም ቀስ በቀስ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሀገራዊ መልካቸው እየደበዘዘ፣ ባህላዊ ጠረናቸው እየተለወጠ መሄዱ ግን አይቀሬ ነው። እስከ ዛሬ ድረስ ትኩረት ተነፍገው መቆየታቸው፣ በወጉ አለመጠናታቸው ታክሎበት ጊዜ ቢወስድ እንጂ፣ ጨርሰው ባይጠፉ እንኳን በሌላ ባህል መዋጣቸው፣ በዘመናዊ ስልጣኔ መተካታቸው የማይቀር ጉዳይ ነው። ይህ ከመሆኑ በፊት በሳይንሳዊ መንገድ ተሰብስበው ሊጠኑና ሊቀረሱ የግድ ይላል።

ይህ ሲባል ግን፣ በቡርጂ ባህላዊ አስተዳደርና እምነት ላይ የተደረጉ ቀደምት ጥናቶች፣ የተዘጋጁ ጽሁፎች ጨርሰው የሉም ማለት አይደለም። በተለያዩ ጊዜ፣ ለተለያዩ ዓላማዎች በውጭ ሀገር ዜጎችና በኢትዮጵያዊያን አማካይነት የተደረጉ ቀደምት ጥናቶችና ፅሁፎች አሉ። ይህ ክፍልም፣ ስለ ቡርጂ ባህላዊ አስተዳደርና እምነት እነማ? መቼ? ምን እንደፃፉ? ምን እንዳሉ? በጣም በጥቅሉ ለመከለስ ይሞክራል። በመቀጠልም በተጨባጭ በመረጃ ላይ በመመስረት ቀደምት ጥናቶቹን በተናጠልና በጥቅል ይገመግማል። በመጨረሻም ይህ ጥናት ከቀደምት ጥናቶች የሚለይበትን ነጥብ ለመጠቆም ይሞክራል። ክለሳውንና ግምገማውንም በውጭ ሀገር ዜጎች በተሰሩ ሥራዎች ጀምሮ የኢትዮጵያዊያንን ያስከትላል።

Mude (1968) ስለ ቡርጂ ከፃፉት ከውጭ ዜጎች መካከል አንዱ ነው። እሱም "*The History of Amaro-Burji of Southern Ethiopia*" በሚል ርዕስ አንድ ጥናታዊ ጽሁፍ አቅርቧል። ጥናቱን ያካሄደው ለአስራ አምስት ቀን እረፍት ከናይሮቢ ወደ ሞያሌ (ኬንያ) ሄዶ በቆየበት አጋጣሚ እንደሆነና ተጠኚው፣ የቡርጂ ህብረተሰብ በዋናነት ሰፍሮ ከሚገኝበት፣ ከቡርጂ (ኢትዮጵያ) ያልደረሰ መሆኑን በጽሁፉ መግቢያ ላይ ያስረዳል። ጥናቱንም ያዘጋጀው በኬንያ ውስጥ ከሚኖሩት ቡርጂዎች በሰበሰበው መረጃ ብቻ እንደሆነም ይገልፃል።

Mude በዚህ ስራው በርካታ ጉዳዮችን ለማሳየት ሞክሯል። ማህበረሰቡ በዋናነት ሰፍሮ ስለሚገኝበት፣ ስለ ቡርጂ መልክዓ ምድር፣ ስለ ህዝቡ ጥንተ አመጣጥ ታሪክ፣ ስለ ባህላዊ እምነት፣ ስለ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተቋማት፣ ስለ ግርዛትና ስለ ጋብቻ ስርዓት፣ ህዝቡ ወደ ኬንያ ስለተሰደደበት ሁኔታ፣ ወዘተ አንስቷል። ፀሐፊው በጽሁፉ ሰፊ ትኩረት የሰጠው የቡርጂ ሀገር በቀል እምነት (ሃይማኖት) ስለሆነው ስለ *ጋን* እምነት ነው። በዚህም በቡርጂ ውስጥ ከፍተኛው ባለስልጣን ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል *(ጋን)* እንዳሏቸው የሚታመኑት መንፈሳዊ መሪዎች *(ባለጋኖች)* እንደሆኑ ጽፏል (13)። ቡርጂ ውስጥ *ጋን* ያላቸው ጎሳዎች ሶስት ብቻ

ሲሆኑ እነዚህም *ቀዳዶ፣ ያቢ* እና *ኣናቡራ* የሚባሉ ጎሣዎች መሆናቸውን ፀሐፊው ያትታል። ከእነዚህ ከሶስቱ መካከል ደግሞ ቀዳሚው ወይም አንጋፋው *ቃዳዲንካ ጋን* መሆኑን

*"The senior Ganna is a member of the Qarado clan. Two other clans the Yabbi and the Annabura, also have Ganna who are junior to the Qarado one. <u>The other clans have no Ganna of their own</u> as the Qarado Ganna represents the whole tribe." (13)*

በማለት ፅፏል (አፅንኦቱ የራሴ ነው)። ከዚህም በላይ ስለ *ባለጋን የጋብቻ፣ የቀብርና* የስልጣን ሽግግር ስርዓት ያትታል።

Mude ስለ ማህበረሰቡ የጎሳ አስተዳደርና የእምነት ስርዓትም ጥቂት ነጥቦችን ያነሳል። በእሱ እምነት በቡርጂ ውስጥ *ቀዳዶ፣ ጋማዮ፣ ያቢ፣ ካራማ፣ ኣናቡራ፣ ኡማ፣ ጎዳ፣ ወቴይሽና ጣሜይ* የሚባሉ ዘጠኝ ጎሳዎች ብቻ አሉ። እያንዳንዱ ጎሳም *ጎሳንካ ኣና* በሚባል *መሪ* እንደሚመራ፣ የጎሣው አባላትም በቡርጂዎች አዲስ ዓመት *መጀመሪያ* አካባቢ በጎሳ *መሪያቸው* ቤት ተሰብስበው የሚያከብሩት የመስዋዕት በዓል *መኖሩን*፣ በበዓሉ ላይም *አያት*፣ ቅድማያቶቻቸውና አምላካቸው አዲሱን ዓመት የሰላምና የብልጽግና እንዲያደርጉላቸው እንደሚለማምኑ ይጠቅሳል (23-25)። ሌሎች ጉዳዮችንም ያነሳል።

Cerulli (1956) ስለ ቡርጂ ከጻፉት ከውጭ ሀገር ሰዎች መካከል አንዱ ነው። ይህ ፀሀፊ *"Peoples of South West Ethiopia and Its Borderland "* በሚል ርዕስ አንድ ጽሁፍ አቅርቧል። በጽሁፉም ቡርጂን ጨምሮ የደቡብ ኢትዮጵያ በርካታ ማህበረሰቦችን ባህል ቋንቋና ታሪክ ንፅፅራዊ በሆነ መልክ አቅርቧል።

Cerulli ቡርጂዎች የሁሉም ነገር አባትና ፈጣሪ የሆነ አንድ ልዕለ ኃይል መኖሩን እንደሚቀበሉ ይገልፃል። ይህ የቡርጂዎች ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል ወይም ፈጣሪ *ኢላሌይ* (Illalae) እንደሆነ ፀሀፊው ይጠቅሳል። እንዲሁም፣ ቡርጂዎችም ሆኑ ሌሎች የአካባቢ ህዝቦች እግዚአብሄርን (God)ን ኦሮሞዎች በሚጠሩበት ስም *ዋቅ* ብለው እንደሚጠሩ ይናገራል (Cerulli, 1956, 66)። በቡርጂዎች ዘንድ ዝናብ ማዘነብ የሚችሉ ወገኖች (*Rain-makers*) እንደሚገኙ፣ ስልጣናቸውም በዘር ሀረግ ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው የሚተላለፍ መሆኑን ጸሀፊው ይገልፃል (Cerulli, 1956, 67)። ቡርጂዎች ያቀዱትን ነገር (ሀሳብ) ተግባራዊ ከማድረጋቸው በፊት ወይም በህዝቡና በአካባቢው ላይ ወደፊት ሊደርሱ ስለሚችሉ ስላልተለመዱ ክስተቶች ለማወቅ ሲፈልጉ ተንባዮችን ወይም ጠንቋዮችን የማማከር ልማድ ያላቸው መሆኑን "Omens are consulted before

any important enterprise or to explain unexpected or unusual events..." (67) በማለት ጽፏል። እንዲሁም ስለ ቡርጂ ህብረተሰብ ጥንተ አመጣጥ፣ ስለ ባህላዊ ምግብ፣ ስለ አልባሳት፣ ስለ ባህላዊ የመኖሪያ ቤትና ስለመሳሰሉትም አጫጭር መግለጫዎችን አቅርቧል።

Amborn እና Kellner (1999) ስለ ቡርጂ ከፃፉት የውጭ ዜጎች መካከል ተጠቃሾች ናቸው። እነዚህ ፀሀፊት Helmut Straube በሚባል የስነ ሰብእ ምሁር (Anthropologist) አማካይነት እ.ኤ.አ. በ1955 እና በ1973/74 አካባቢ፣ በሁለት ዙር የመስክ ጉብኝት ተሰብስቦ የነበረውን የመጀመሪያ ደረጃ መረጃን መሰረት አድርገው *"Burji Vocabulary of Cultural Items"* በሚል ርዕስ ፅሁፍ ማሣተማቸውን በጽሁፉ መግቢያ ላይ አመልክተዋል:: ይህን ለማድረግ ያበቃቸው ደግሞ Straube ጅምር ሥራውን ሳያጠናቂቅ በመሞቱ ምክንያት እንደሆነ ይናገራሉ። ፅሁፉ ለቡርጂ በርካታ ባህል ተኮር ቃላትና ስያሜዎች ፍቺና አልፎ አልፎም ማብራሪያ በመስጠት ላይ ያተኩራል። ፍቺ ወይም ማብራሪያ ከተሰጠባቸው ቃላት ወይም ስያሜዎች መካከልም ከማህበረሰቡ ባህላዊ የአስተዳደር እና የእምነት ሥርዓቶች ጋር የተያያዙ ይገኙበታል።

Amborn እና Kellner (1999) በፅሁፋቸው መግቢያ ላይ ካነሷቸው ነጥቦች መካከል የቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር እና የእምነት ስርዓቶች ይጠቀሳሉ። በዚህም የቡርጂን የትውልድ አመዳደብ ስርዓትን (Generation grading system) ከአፍሪካ ቀንድ አገር ህዝቦች የትውልድ አመዳደብ ስርዓት ጋር ያነፃፅራሉ። ይህ የትውልድ አመዳደብ ሥርዓት፣ በቡርጂ የፖለቲካና የእምነት ህይወት ውስጥ እጅግ ጠቃሚ ከሆኑት ተቋማት መካከል አንዱ መሆኑን ያትታሉ። በአፍሪካ ቀንድ ህዝቦች ዘንድ ከተለመዱት ሁሉ የተለየ እንደሆነም ይገልፃሉ። የተለየ የሚያደርገውም የቡርጂዎች የትውልድ አመዳደብ ሥርዓት እንደ ኦሮሞዎቹ የትውልድ ምድብና የእድሜ እኩዮች ጥምረት የሌለው መሆኑን እንዲህ በማለት ይገልፃሉ።

> *One of the most important institutions in the ritual and political life of the Burji was a generation grading system which is a special case among comparable systems in the Horn of Africa. For example, it does not have the combination of generation sets and age grades which is typical for the Oromo (11-12).*

የቡርጂ ሀገረሰባዊ ሃይማኖት (እምነት) ስለሆነው ስለ ጋንም ጥቂት ነጥቦችን አንስተዋል። በቡርጂ ባህላዊ የእምነት ሥርዓት ባለጋኖች የጎሣ መሪዎች መሆናቸውን፣ ሁሉም ጎሣዎች ጋን እንደሌላቸው፣ ባለጋኖች ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል ያላቸው ቢሆኑም ህዝብ እንደሚቆጣጠራቸው፣ በአሁኑ ጊዜ ሁሉም ቡርጂዎች የአንድ አምላክነትን መርህ የሚከተሉ

ሃይማኖቶች ተከታይ ቢሆኑም *የጋን* ተፅዕኖና አስፈላጊነት ግን እስከዛሬም ድረስ ያልቀነሰ ስለመሆኑና ስለ ሌሎችንም ነጥቦች እንዲህ በማለት ጽፈዋል፡

> *The ganni are the most important religious dignitaries of the Burji and usually also clan leaders. But not every clan has a ganni. Their power is also subject to control by society. Thus they could be driven out if they failed. The ganni have special abilities which they inherit from their clan forebears. Their essential task is to ensure the success of crops and domestic animals. They are responsible for warding off danger and for the welfare of the community as a whole.*
>
> *Although today almost all Burji accept one of the main monotheistic religion, the influence and significance of the ganni remain unbroken. The people ensure that their functions are fulfilled in accordance with tradition. (Amborn and Kellner, 1999, 13)*

ግርማ ቡኬ (1982) ስለ ቡርጂ ከፃፉት ቀደምት ኢትዮጵያዊያን መካከል አንዱ ነው፡፡ እሱም ‹‹ግርዛት እና ዘፈኖቹ፣ በቡርጂ ህብረተሰብ›› በሚል ርዕስ አንድ የአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ (ድማፅ) ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አቅርቧል፡፡ ጽሁፉ ትኩረት ያደረገው ለቡርጂ ባህላዊ አስተዳደር መሰረት የሆነውን የግርዛት ስርዓትንና የግርዛት ዘፈን ግጥሞችን ከይዘታቸውና ከቅርፃቸው አንፃር ተንትኖ በማሳየት ላይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ፀሐፊው በማህበረሰቡ ባህላዊ የአስተዳደር *ሥርዓት* ውስጥ ቁልፍ ሚና ያላቸው *ሃዩ* እና *ጃልዓባ* ወደ *ሥልጣን* ስለሚመጡበት ሁኔታና ተግባር ማንሳቱ አልቀረም፡፡ በዚህም፣ ከግርዛት በኂላ ለተገረዙ የቡርጂ ወጣቶች ከሚሰጡ የማዕረግ ስሞች መካከል *ሃዩ* እና *ጃልዓባ* ተጠቃሾች እንደሆኑ ፀሀፊው ይገልፃል (24-26)፡፡ *ሃዩ* የመከላከያ *ኃይል (የሀግ)* መሪ ሲሆን አባላቱን በዘመቻ፣ በአደን፣ በዳኝነትና በመሳሰሉት *ሥራዎች* ላይ ማስተባበርና መምራት ዋነኛ ተግባሩ ነው፡፡ ጃልዓባ ደግሞ *የሃዩ ረዳትና* መልዕክተኛ ሆኖ የሚያገለግል ሹም መሆኑን ፅሁፉ ይጠቁማል (25)፡፡

አበበ አርጋሞ (1999፣18-21) ስለ ቡርጂ *የባሻ* (ባህላዊ *መሪዎች* ወደ *ሥ*ልጣን ስለሚመጡበት) ስርዓት (ለዝርዝሩ የዚህን ጥናት ምዕራፍ አራትን ተመልከት) የጻፈ ኢትዮጵያዊ ነው፡፡ እሱም *‹‹ባሻ፡-* የቡርጂ ብሄረሰብ ባህላዊ አስተዳደር›› በሚል ርዕስ፣ በቡርጂ ልዩ ወረዳ ባህልና ማስታወቂያ ጽህፈት ቤት አማካይነት በሚታተም ዓመታዊ መጽሔት ላይ ባቀረበው ጽሁፉ፣ የቡርጂ *የባሻ* ስርዓት የጀመረው *የጎዳ ወማ* ከስልጣን ከተወገደ በኂላ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ በየደረጃው ያሉት የህዝብ መሪዎች በስልጣን ላይ ስለሚመደቡበት የምርጫ ስርዓትም መጠነኛ ነጥቦችን ያነሳል፡፡ በዚህም *ዳይና* እና *ማሻ* በሚባሉ የ*ሥ*ልጣን እርከኖች ላይ ባህላዊ ሹሞችን መልምሎ የመመደብ ስልጣን *የቢታናች* መሆኑን፣ በእነዚህ ቦታዎች ላይ ለመወዳደር የሚፈልጉ ግለሰቦችም *ከቢታናቹ* ቤት *ጉሱማ* (በቦርዴ የተሞላ ቅል) ወስደው እንደሚሰቅሉ ይገልጻል(19)፡፡

ከፍ ሲል በተጠቀሰው *መፅሄት* ላይ *‹‹የኤሣ መገንቢያ ቁሶች ምንነትና ትርጉማቸው››* በሚል ርዕስ ጽሁፍ *ያቀረበው* ሌላው ኢትዮጵያዊ ጸሐፊ ጌታሁን አዶ (1999፣ 22-25) *ነው*። እሱም በቡርጂ ባህላዊ *መሪዎች* ደጃፍ እና *በባሻ* ስርዓት *መፈፀሚያ ቦታ (ሱቡሮ)* ላይ ስለሚተከለው፣ ስለ *ኤሳ* (ከተለያዩ የእንጨት ዓይነቶች ስለሚዘጋጀው ባህላዊ የአንድነት አርማ) አሰራርና ትርጉም *ያትታል*። በዚህም *ኤሳ* ከተለያዩ የእንጨት ዓይነቶች እንደሚዋቀር (እንደሚዘጋጅ) ትርጉሙም የቡርጂ ህዝብ የዓላማ ትስስርና የአንድነት መግለጫ መሆኑን ይጠቁማል።

በአጠቃላይ፣ በቡርጂ ላይ ከተሰሩትና ከፍ ተብለው ከተጠቀሱት ቀደምት ስራዎች *መካከል* አብዛኞቹ ከስምንት የቡርጂ *የቢያ* አስተዳደሮች *መካከል* ከአንዱ ቢያ ብቻ በተሰበሰቡ *መረጃዎች* ላይ ተመስርተው የቀረቡ ይመስሉኛል። በርግጥ የቡርጂዎች ቁሳዊና *መንፈሳዊ* ባህሎች አብዛኞቹ ተመሳሳይ ናቸው። ይሁን እንጂ፣ እንደ ማህበረሰቡ አሰፋፈርና አኗኗር አንዳንድ ልዩነቶች *መኖራቸው* አይቀሬ *ነው*። በመሆኑም፣ በቡርጂ ላይ የሚቀርቡ ስራዎች ቢቻል ሁሉንም የሚመለከቱ፣ ይህ ካልተቻለ ደግሞ አብዛኛውን ህዝብ የሚወክሉ ሊሆኑ ይገባል። የዚህ ዓይነት ችግር በጉልህ ከሚታይባቸው *ሥራዎች* መካከል የMudeንና (1968) የእነ Ambornን (1999) *ሥራዎች* መጥቀስ ይቻላል።

የMude ጽሁፍ *ሁሉን* የቡርጂ ህዝቦች እንዲወክል ተደርጎ የተዘጋጀ፣ በስምንቱም *የቢያ* አስተዳደር ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦችን የአኗኗር፣ የእምነት፣ የአስተዳደርና የፖለቲካ ስርዓቶችን እንዲያካትት ሆኖ የቀረበ ጥናት ነው ለማለት አልደፍርም። ለዚህ ደግሞ ቡርጂ ውስጥ *ጋን* ያላቸው አስራ አንድ ጎሳዎች እያሉ (ምዕራፍ አምስትን ተመልከት) ‹‹ቡርጂ ውስጥ *ጋን* ያላቸው *ቀዳዶ፣ ያቢ እና ኣናቡራ* የሚባሉ ሶስት ጎሳዎች ብቻ ናቸው›› (Mude, 1968, 13) ማለቱን መጥቀሱ ብቻ በቂ ይመስለኛል። ይህ የቡርጂዎች እምነት (*ጋን*) ዛሬ የጀመረ ሣይሆን ቡርጂዎች ከሊበን መጥተው አሁን ካሉበት *ሥፍራ* ሲሰፍሩ ጀምሮ ያለ፣ የነበረ መሆኑን ሁሉም መረጃ ሰጪዎች (ቱኬ፣ ቡኬ፣ ማኒኦ፣ ጫሜ፣ 2002) *ያስረዳሉ*። *ከባንባልንካ ጋን* በስተቀር የሁሉም *ጎሣ ጋኖች* ቡርጂ ከመስፈራቸው በፊት ጀምሮ የነበሩ ናቸው። በጸሐፊው የተጠቀሱት *የቀዳዶ፣ የያቢ* እና *የኣናቡራ ጎሣዎች*ም ከእነዚህ *ጋን* ከነበራቸው ወይም ካላቸው ከቡርጂ አስራ አንድ *ጎሣዎች* መካከል፣ በአንድ ቦሄ ወይም በአንድ ቢያ ውስጥ የሚገኙ ሶስት ጎሳዎች እንጂ ብቸኞች ናቸው የሚል እምነት የለኝም። ለፀሐፊው በመረጃ ሰጪነት ያገለገሉ ሰዎች በዚህ ቦሄ (በክሊቾ) ውስጥ ተወልደው ያደጉ፣ በኋላም ወደ ኬንያ (ሞያሌ) የተሰደዱ

ቡርጂዎች መሆናቸውን ጸሐፊው ራሱ በጽሁፉ አባሪ ላይ ባሰፈረው ማስታወሻው ላይ አመልክቷል።

Amborn እና Kellner ግን ይህን ሀቅ በከፊል ያምናሉ። በጥናቱ ለተጠቀሱት ለህግ ሥርዓት የዋሉ መረጃዎች የተሰበሰቡት ከተወሰነ የቡርጂ አካባቢዎች ስለሆነ ይህን የሚመለከቱ ሀሳቦችም በአብዛኛው በተወሰነ (እነርሱ Middle Burji ብለው በሚጠሩት) አካባቢ የሚኖሩ ቡርጂዎችን ብቻ የሚመለከቱ ሊሆኑ እንደሚችሉ በጽሑፋቸው የግርጌ ማስታወሻ (ቁ 9፣ ገጽ 12) ላይ ጠቅሰዋል። የሁለቱም ጸሐፊት ጥናት በተወሰነ የቡርጂ አካባቢ ከሚኖሩ ቡርጂዎች ብቻ በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀ፣ ሁሉንም የቡርጂ ህዝቦችን ባህላዊ የአስተዳደርና የእምነት ሥርዓትን ያካተተ ሥራ ነው ለማለት የማያስደፍር ነው ያስባለው ምክንያትም ይኸው ነው። ይሁን እንጂ፣ ፀሐፊዎቹ በእነዚህ አካባቢዎችና በሌሎች የቡርጂ አካባቢ ህዝቦች ባህላዊ የአስተዳደርና የእምነት ሥርዓቶች መካከል ያሉ ልዩነቶችንም አልፎ አልፎ ለማሳየት መሞከራቸው ሥራቸው ሙሉ ለሙሉ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ጥቂት ቡርጂዎችን ብቻ የሚመለከት ነው ብሎ መደምደም እንዳይቻል አድርጎታል።

የCerulli (1956) ጽሁፍም ቢሆን በመጀመሪያ ደረጃ መረጃ (Primary data) ላይ ተመስርቶ የቀረበ አይመስለኝም። በሌላ አገላለጽ ጽሁፉ በአብዛኛው የሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን (*Secondary data sources*) መሰረት በማድረግ የቀረበው ይመስላል። ሌሎች ሰዎች (Vannutelli, 1899; Moreno, 1938; Cipriani, 1940; Cavendish, 1898; Donaldson Smith, 1897…etc) ቀደም ሲሉ ስለ ቡርጂ የጻፉትን ሣያጣራ ነው ያቀረበው። አንዳች ማሻሻያ አላደረገባቸውም። ትክክል ይሁኑ አይሁኑ አላረጋገጠም። ይህንን አስተያቴን ለመደገፍ ከጽሁፉ ውስጥ አንዳንድ ምሳሌዎች እጠቅሳለሁ። ፀሐፊው *Guidi m.s.* የተባለውን ቀደምት ፀሐፊን ዋቢ በማድረግ *"The Burji, konso, Arbore, and Tsamai also call God by the Galla name of waq"* (Cerulli, 1956, 66) በማለት ቡርጂዎችና ሌሎች አጎራባች ማህበረሰቦች እግዚአብሄርን በኦሮሞዎች ቃል ዋቅ ብለው እንደሚጠሩ ጽፏል። በእኔ እምነት ቡርጂዎች ‹‹God›› የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ የሚገልጹበት፣ የሚጠሩበት የቡርጂኛ ቃል ሣይቸግራቸው ‹‹ዋቅ›› ብለው በኦሮምኛው ቃል የሚጠሩበት ሁኔታ ያለ አይመስለኝም። ቡርጂዎች ኦሮምኛ ተናጋሪ ከሆኑ ማህበረሰቦች ጋር ወይም እርስ በርሳቸው በኦሮምኛ ቋንቋ በሚነጋገሩበት ወቅት በእርግጥም ‹‹እግዚአብሄር›› ለማለት ዋቅ ይሉ ይሆናል። ይሁን እንጂ በራሱ በቋንቋው ባህርይም ይሁን በሌላ ምክንያት ቡርጂዎች እግዚአብሄርን ዋቅ እያሉ የሚጠሩበት ሁኔታ ፈጽሞ አይኖርም ወይም የለም ብዬ መከራከር

አልችልም። እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ስለ መኖራቸው ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። ለምሳሌ የተገረዙ ልጆችን ለመጠየቅ የሄደ አንድ የቡርጂ ወንድ ሰው ከውጭ ቆሞ ግርዘኞችን በቡርጂኛ *‹‹ሉብ ሃዶ ሆባኒቱ?››* (ግርዛቱን በሰላም ተገላገላችሁ) ይላቸዋል። ግርዘኞችም *‹‹ሆባስ ዋቅ!››* (እግዚአብሔር ገላገለን!) ብለው ሙሉ በሙሉ የኦሮምኛ በሆነ ቋንቋ ምላሽ እንደሚሰጡት አሳምሬ አውቃለሁ። ይህ ማለት ግን በማናቸውም ሁኔታና ጊዜ ቡርጂዎች እግዚአብሄርን *ዋቅ* ብለው ይጠራሉ ማለት አይመስለኝም። ወይም እግዚአብሄር በቡርጂኛ *ዋቅ* ይባላል ብሎ ድምዳሜ ለመስጠት የሚያስችልም አይደለም። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ቡርጂዎች ‹‹እግዚአብሄር›› ለሚለው *ቃል* *ወንቶ* የሚል አቻ *ቃል* ያላቸው ስለሆነ ነው። ቡርጂዎች ‹‹እግዚአብሄርን›› *ወንቶ* ብለው ነው የሚጠሩት። ቡርጂዎች ‹‹እግዚአብሄርን›› *ወንቶ* ብለው በመጥራት ብቻ አያበቁም። *ወንቶ* ብለው የሚጠሩት ጽንሰ ሀሳብ መልኩ ወይም ቀለሙ ምን ዓይነት እንደሆነ ጭምር፣ *ካለ ወንቶ* (ጥቁሩ እግዚአብሄር) በማለት ይገልጹታል። የቡርጂዎች እግዚአብሄር ስም ብቻ ሳይሆን መልክም ጭምር አለው። ስሙ *ወንቶ* መልኩ *ካለይ* (ጥቁር) ነው። ነጭ አይደለም። ይህን ሁሉ መግለጽ የሚችል ቋንቋ እያላቸው እግዚአብሄርን በኦሮሞ ቋንቋ *ዋቅ* ብለው የሚጠሩበት ሁኔታ አይታየኝም ያልኩትም ከዚህ በመነሳት ነው።

ግርማም፣ ከፍ ተብሎ እንደተመለከተው፣ በጽሁፉ ለማህበረሰቡ የአስተዳደር *ሥ*ርዓት መሰረት ስለሆነው፣ ስለ ግርዛት ስርዓት ትረኩት ሰጥቶ በሰፊው ይፃፍ እንጂ፣ ስለ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓቱ መዋቅርና አሰራር ያለው ነገር የለም። እንዲሁም ከዚህ ጋር ተያይዘው ስለሚፈፀሙ ባህላዊ እምነቶችም አንዳች ነገር አያነሳም።

በአጠቃላይ አነጋገር ከፍ ሲሉ የተመለከቱት አብዛኞቹ ጽሁፎች ህዝቡ ቀደም ሲል ይመራበት ስለነበረው፣ ስለ ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅርና አሰራርም ሆነ ከዚህ ጋር ተያይዘው ስለሚፈጸሙ እምነታዊ ስርዓቶች ያነሱት ነገር የለም። ያነሱትም ቢሆኑ ባህላዊ ስርዓቱን በዝርዝርና በጥልቀት አላዩትም። አልዳሰሱትም። ከሁሉም በላይ ደግሞ የቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደርና የእምነት ስርአቶች እጅግ ተደጋጋፊና አንዱ ካለሌላው ተግባራዊ ሊሆን የማይችል፣አንዳቸው በአንዳቸው ውስጥ ሁልጊዜም የሚኖሩ መሆናቸውን አላሳዩም። በአጭሩ አብዛኛዎቹ ስራዎች ክፍተቶች አሉባቸው። የእኔ ጥናት ዋና ዓላማ የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደርና ከአስተዳደሩ ጋር ተያይዘው የሚፈጸሙእምነታዊ ድርጊቶችን ማሳየት ስለሆነ እነዚህን ክፍተቶች ይሞላል የሚል እምነት አለኝ።

## 3. የቡርጂ ህዝብ አጫጭር መግለጫዎች

ይህ ምዕራፍ፣ ባህላዊ አስተዳደሩና እምነቱ የሚጠናውን የቡርጂን ህዝብና አካባቢ የሚያስተዋውቅ ነው፡፡ ህዝቡ በኢትዮጵያ ውስጥ በዋናነት ሠፍሮ ስለሚገኝበት አካባቢ ወይም መልክአ ምድር፣ የቡርጂ ህዝቦች ከየት መጥተው አሁን ካሉበት አካባቢ እንደሰፈሩና አሰፋፈራቸው ምን እንደሚመስል፣ አጫጭር ማብራሪያዎች ይሰጣሉ፡፡ የህዝቡ ስያሜና ቋንቋም በምዕራፉ የሚተኮርባቸው ነጥቦች ናቸው፡፡

### 3.1. መልክዓ ምድር

ቡርጂ፣ የቡርጂ ህዝብ በኢትዮጵያ ውስጥ ሠፍሮ ለሚገኝበት አካባቢ የተሰጠ መጠሪያ ነው ፡፡ የአካባቢው፣ የአሁኑ ሙሉ መጠሪያው የቡርጂ ልዩ ወረዳ ይባላል፡፡ የቡርጂ ልዩ ወረዳ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ውስጥ ይገኛል፡፡ ከአዲስ አበባ በስተደቡብ 545 ኪሎ ሜትር፣ የክልሉ ርዕሰ ከተማ ከሆነችው፣ ከአዋሳ ከተማ ደግሞ በስተደቡብ በ268 ኪሎ ሜትር ላይ ይገኛል ፡፡ በሎንግቲዩድ long $38^0$E' እና በላቲቲዩድ lat $5^0 30^0$N' (Mude,1968,4; Hallpilk,1972,3) ላይ ተቀምጧል፡፡

የቡርጂ ልዩ ወረዳ በሰሜን ከአማሮ፣ በምዕራብ ከኮንሶ ልዩ ወረዳ ጋር ይዋሰናል፡፡ በደቡብ እና በምሥራቅ ደግሞ ከኦሮሚያ ክልል ጋር ይዋሰናል፡፡ ቡርጂ ከመሬት ወለል በ6,000 ጫማ (Mude,1968,4) ወይም በ1800 ሜትር (Cerulli,1956,51) ከፍታ ላይ የሚገኝ ተራራማ አካባቢ ነው፡፡ ሁለት የዝናብ ወቅቶች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ከሚያዝያ - ሰኔ ባለው ጊዜ ውስጥ ሲሆን ሁለተኛው በህዳርና በጥር መካከል ነው (Mude,1968,4; Cerulli,1956,51)፡፡

### 3.2 የሕዝቡ ስያሜ

በአሁኑ ጊዜ ቡርጂ በሚል ስም የሚታወቀው ህዝብ በተለያዩ ስሞች ሲጠራ ኖሯል፡፡ ዛሬም ድረስ ይጠራል፡፡ ቡርጂዎችም ቢሆኑ እራሳቸውን የሚጠሩበት ስም አንድ አይነት አይደለም፡፡ የተለያየ ነው፡፡ Donaldson (1895) እስከ አሁን በተገኙ መረጃዎች መሠረት ስለ ቡርጂ ህዝብ ጽፎ ያሳተመ የመጀመሪያው አውሮጳዊ ነው (Mude,1968,18)፡፡ Donaldson (1895), *Through Unknown African Country* በሚል ርዕስ ባሳተመው መጽሐፉ ውስጥ የቡርጂን ህዝብ "Amara-

Burji"[9] በማለት ይጠራዋል። ይህንንም ስም ያገኘው ከእራሱ፣ ከህዝቡ ጠይቆ እንደሆነ ጸሐፊው ይገልጻል።

Mude (1968) በዚህ *አማራ-ቡርጂ* በሚለው በDonaldson (1895) ስያሜ የተስማማ ይመስላል። እሱም "*The History of Amaro-Burji of Southern Ethiopia*" በሚል ባቀረበው መጣጥፉ ላይ ከርዕሱ ጀምሮ፣ ይኸን የህዝቡን ስያሜ ሲጠቀም ይታያል። በጽሁፉ ውስጥም "*The word ‹Amara› by which Smith refers to the tribe was the original name of the Burji and the tribe still refers to itself occasionally as the Amara Burji" (4)* የሚል ሀሳብ በመሰንዘር የDonaldson ስያሜ ትክክል መሆኑን ያረጋግጣል። ማህበረሰቡ አሁን የሚጠራበት ቡርጂ የሚለው ስም የቡርጂ አጎራባች የሆነው የጉጂ ኦሮሞ ህዝቦች (እሱ ግን *Janjamtu* ብሎ የሚጠራቸው ህዝቦች) ድሮ የቡርጂ ህዝብ ይኖርበት የነበረውን ተራራ ወይም አካባቢ ይጠሩበት የነበረው ስም መሆኑን ጭምር ፀሐፊው ያብራራል።

Cerulli (1956) ይህንን ‹‹ቡርጂ የአካባቢ መጠሪያ ነበር›› የሚለውን የMudeን ሃሳብ ይጋራል። ቡርጂ፣ ቀደም ሲል ማህበረሰቡ ይኖርበት የነበረው አካባቢ ወይም መንደር ይጠራበት የነበረ ስም እንደነበረም *"Burji properly speaking is the name of a large village east of the Sagan River south east of Lake Camo at a height of about 1,800 meters but it has been extended to indicate the whole tribe."* (Cerulli, 1956, 51) በማለት ፅፏል። ፀሀፊው ይህን ይበል እንጂ ‹‹አማር›› የህዝቡ ነባር መጠሪያው (ስሙ) ነው በሚለው በMudeም ሆነ በDonaldson ሀሳብ ግን አይስማማም። ይልቁን ህዝቡ ራሱን *ባንባላ* ብሎ ይጠራል *"Burji call themselves Banbala"* (Cerulli, 1956, 52) በማለት ጽፏል። በመሠረቱ *ባንባላ* ከቡርጂ በርካታ ጎሳዎች መካከል አንዱ የሆነው ጎሳ የሚጠራበት ስም ነው። *ባንባላ* የአንድ ጎሳ እንጂ የአንድ ህብረተሰብ መጠሪያ አይደለም። Cerulli በዚህ ስም አጠቃላይ ህዝቡን ለምን? እና እንዴት? ሊጠራ እንደቻለ ያብራራው ነገር የለም። የቡርጂ ህዝብ ግን ጥንትም ቢሆን ራሱን *ባንባላ* ብሎ የጠራ አይመስለኝም። ዛሬም ቢሆን አይጠራም። ለዚህ ደግሞ ማረጋገጫ ማቅረብ ይቻላል። የመጀመሪያው ማረጋገጫ ቀደም ሲል የተጠቀሰው የDonaldson ጽሁፍ ነው። Donaldson ስለ ቡርጂ የጻፈ የመጀመሪያው አውሮጳዊ ብቻ ሳይሆን የቡርጂን መሬት የረገጠ፣ ቀርቦ ህዝቡን ያነጋገረ ጸሐፊም ነው። እሱ ቡርጂ ሄዶ ህዝቡን ያናገረው እ.ኤ.አ በ1894/95 ነው። ያን ጊዜ ህዝቡ እራሱን *አማራ-ቡርጂ (Amara-Burji)* ብሎ እንደሚጠራ ነግሮናል። ያን ጊዜ ‹‹ማን

[9] Kent Ali Mude (1968) "The History Of Amaro - Burji Of Southern Ethiopia" በሚል ርዕስ ባሳተመው መጣጥፉ ውስጥ ከተጠቀመው ከዶናልድሰን ሃሳብ ውስጥ ወስጄ የተገለገልኩት ነው። ዋናውን የዶናልድሰንን ጽሁፍ ማግኘት አልቻልኩም።

ትባላላችሁ?›› ሲባሉ ‹‹አማራ-ቡርጂ እንባላለን›› ያለው ህዝብ፣ ከስልሳ አንድ ዓመት በኋላ (እ.ኤ.አ. በ1956) ነባር ስሙን ለውጦ ‹‹ባንባላ እንባላለን›› የሚልበት ምክንያት ያለ አይመስለኝም፡፡ ቼሩሊ ለዚህ ጽሁፍ የሚሆነውን መረጃ በሰበሰበበት ወቅት በመረጃ ሰጪነት የተጠቀመው ሰው (ቡርጂ ድረስ ሄዶ በእርግጥም ቡርጂ የሆነን ሰው አናግሮ ከሆነ ማለት ነው) ከባንባላ ጎሳ ወገን የሆነ የቡርጂ ሰው ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት አለኝ፡፡ መረጃ ሰጪውም ምናልባት ጎሳውን የተጠየቀ መስሎት ‹‹ባንባላ›› ብሎ መልሶለት ሊሆን ይችላል፡፡ በዚያን ዘመን ደግሞ (ዛሬም ቢሆን) ቡርጂዎች ለጎሳቸው ታላቅ ቦታ ይሰጡ ስለነበር ይህ ግምት ትክክል አይደለም ብሎ መከራከር አይቻልም፡፡ ፀሀፊውም ይህን የመረጃ ሰጪውን የተሳሳተ መረጃ ይዞ፣ በሌላ የመረጃ ምንጭ ሳያጣራ ‹‹ቡርጂዎች እራሳቸውን *ባንባላ* ብለው ይጠራሉ›› ብሎ ጽፎ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ፡፡ ከዚህ ውጪ ምናልባት ፀሐፊው ይህን ያለበት የራሱ ምክንያት ሊኖረው ይችላል፡፡ እኔ ግን የለኝም፡፡ ቡርጂዎች እራሳቸውን ‹‹*ባንባላ*›› ብለው ሲጠሩ የሰማሁበትን ጊዜ ማስታወስ አልቻልኩም፡፡ መረጃ ሰጪዎቼም ይህንን አልነገሩኝም፡፡ ቡርጂዎችም ቢሆኑ ‹‹ባንባላ ነን›› አይበሉ እንጂ ራሳቸውን የሚጠሩበት ስም ተመሳሳይ አይደለም፤ የተለያየ ነው፡፡ የህዝቡ ጥቅል ስም ‹‹*ዳሹ*›› ነው የሚሉ ወገኖች የመኖራቸውን ያህል (ማኒኦ፣2002፣ 3፤ ጫሜ፣ 2002፣ 3) ህዝቡ ተጠቃሎ ሲጠራ ‹‹ቡርጂ›› ይባላል ብለው የሚሞግቱ መረጃ ሰጪዎች አሉ (ቱኬ፣ 2002፣ 6፤ አበበ፣ 2002፣ 4)፡፡

ህዝቡ ተጠቃሎ ሲጠራ ‹‹ዳሽ›› ይባላል የሚሉ ወገኖች፣ ለዚህ ሀሳባቸው ማጠናከሪያነት የቡርጂ ህዝብ *ዳሺቻ* እና *ጂራንካ ጆራ* (jiiranka joora) በሚባሉ በሁለት አብይ ጎሳዎች የሚከፈል መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡ *ዳሽ* የሚባሉት ከሊበን በቀጥታ መጥተው ቡርጂ ላይ የሠፈሩ ነባር ህዝቦች መሆናቸውን በመግለጽ *ዳሽ* የሚለው የህዝቡ መጠሪያ ከጥንት ጀምሮ ያለ ነው በማለት ይከራከራሉ፡፡ በነዚህ ወገኖች እምነት ‹‹ቡርጂ›› የሚለው ስም ቡርጂ ውስጥ ያለ የአንድ *ቦሄ* (ቀበሌ) መጠሪያ እንጂ አጠቃላይ የህዝቡ መጠሪያ አይደለም፡፡ ይህ ሀሳባቸው ደግሞ ከፍ ሲል ከተጠቀሰው ከMude እና ከCerulli ሃሳብ ጋር የሚስማማ ይመስለኛል፡፡

ህዝቡ በአንድ ላይ ‹‹ቡርጂ ይባላል›› የሚሉ ወገኖች ደግሞ ህዝቡ አሁን ካለበት ቦታ (ቡርጂ) ከመምጣቱ በፊት ጀምሮ ‹‹ቡርጂ›› ተብሎ ይጠራ እንደነበር በአጽንኦት ይናገራሉ፡፡ ይሁን እንጂ ‹‹ቡርጂ›› ከጥንት ጀምሮ የህዝቡ ስያሜ መሆኑን ከመግለጽ ባለፈ ለዚህ አባባላቸው ማጠናከሪያነት የሚያቀርቡት መረጃ የላቸውም፡፡ ቀዳሚዎቹ ወገኖች እንደጠቀሱት፣ አሁን ህዝቡ በሚኖርበት አካባቢ ‹‹ቡርጂ›› ተብሎ የሚጠራ አካባቢ መኖሩ እነዚህኞቹ ወገኖች፣

አንድም መረጃ ማቅረብ ካለመቻላቸው ጋር ተደምሮ ቡርጂ የሚለው ስያሜ በእርግጥም የአካባቢ እንጂ የህዝቡ መጠሪያ አይደለም ወደሚለው ድምዳሜ እንድንደርስ ይገፋፋናል። ይሁን እንጂ ‹‹ቡርጂ የአካባቢ መጠሪያ ነው›› ብለን እንዳንደመድም የሚያደርጉ ሁኔታዎች አልጠፉም። ከእነዚህ ውስጥ በጥንታዊቷ የግብጽ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ ከነበራቸው ነገዶች (daynasty) መካከል የቡርጂ ነገድ (Burji daynasty) አንደኛውና ዋነኛው መሆኑን የሚጠቁመው መረጃ አንዱ ነው። በዚያን ዘመን ማምሉክስ (mamluks) የሚባሉ፣ ከተለያዩ አካባቢዎች ተገዝተው በግድ እንዲሰልሙ የተደረጉ ባሪያ ወታደሮች መኖራቸውንና በኋላም እራሳቸውን ከፍተኛ ወታደራዊ ገዢ በማድረግ ግብጽን የገዙ ሁለት ነገዶች መኖራቸውን ይኸው መረጃ ያመለክታል። መረጃው፣ ከእነዚህ መካከልም አንዱ ግብጽን እ.ኤ.አ. ከ1382-1517 ድረስ የገዛው የቡርጂ ዳይናስቲ (Burji ruling dynasty) መሆኑ እንደሚከተለው ተጠቅሷል።

> *Mamluks also spelled Mamelukes, purchased slaves converted to Islam who advanced themselves to high military posts in Egypt. From this class sprang two ruling dynasties the Bahri (1250-1382) made up of Turks and Mongols and the Burji (1382-1517) made up of circassians both were named for places where the troops who seized power had been quartered (Encarta,2007,1)*

በዚህ መረጃ መሠረት ቡርጂ የሚባሉ ህዝቦች በአሁኑ ጊዜ በናይጀሪያ (Burji Nigeria)፣ በፑንጃብ (Burji Punjab) (በአብዛኛው በፓኪስታን፣ በጥቂቱ በህንድ ግዛት የሚገኝ አካባቢ ነው)፣ በኬንያ (Burji Kenya) እና በኢትዮጵያ (Burji Ethiopia) ውስጥ ይገኛሉ። ነገር ግን የኢትዮጵያ ቡርጂዎች ከፍ ሲል የተጠቀሱት ህዝቦች (የግብጽ ቡርጂዎች) አካል ይሁኑ አይሁኑ የተጠቀሰ ነገር ባይኖርም ቡርጂ የሚለው ስም ከዚህ መጠቀሱ የህዝቡን ስያሜ በተመለከተ ለተነሳው ክርክር ያለው ፋይዳ ቀላል አይደለም። ምክንያቱም አንዳንድ ወገኖች እንደሚሉት ቡርጂ በርግጥም ከጥንት ጀምሮ ህዝቡ የሚጠራበት ስም ሳይሆን አይቀርም እንድንል ያደርገናል።

የቡርጂ አጎራባች ህዝቦች ቡርጂዎችን የሚጠሩበት የየራሳቸው ስያሜ አላቸው። ቡርጂን በሰሜን የሚያዋስነው የኮሬ ህዝብ የቡርጂን ሰው *"አልጋ"*፣ ኮንሶዎች *"ካይሪታ"* ፣የጉጂ ኦሮሞዎች *"ቡርጂ"* ብለው ሲጠሩት ቦረናዎች ደግሞ *"አማር"* ይሉታል።

ይህ *"አማ"ር* የሚለው የቦረናዎች ስያሜ ከሌሎች ይልቅ ትኩረት የሚስብ ሆኖ ነው ያገኘሁት። ምክንያቱም ይህ *አማር* የሚለው የቦረናዎች ስያሜ፣ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ከDonaldson (1895) እና ከMude (1968) ስያሜዎች ጋር የሚገጥም መስሎ ስለታየኝ ነው። Donaldson ህዝቡ ራሱን *‹‹አማር- ቡርጂ››* ብሎ ይጠራል ሲል ሙዴም *‹‹አማር ቡርጂ››* የህዝቡ ነባር መጠሪያ እንደነበር ያትታል። የቦረናዎች ቡርጂን *‹‹አማር››* ብለው መጥራታቸው ትኩረት ሊስብ

የቻለበት ምክንያት ይህ ነው። ያም ሆኖ፣ ህዝቡም ሆነ ህዝቡ የሚኖርበት አካባቢ በአሁኑ ጊዜ የሚጠሩት ቡርጂ ተብለው ነው።

### 3.3 የቡርጂ ህዝብ ጥንተ አመጣጥ ታሪክ

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ[10]፣ በቡርጂ ልዩ ወረዳ ውስጥ የሚኖሩት የቡርጂ ህዝቦች ከሌላ አካባቢ መጥተው የሰፈሩ መሆናቸውን ሁሉም መረጃ ሰጪዎቹ (ጫሜ፣ 6፤ ቱኬ፣ 6፤ ማጊኦ፣ 8፤ ቡኬ፣ 3፣ 2002) ይስማሙበታል። የተገኙት አብዛኛዎቹ መረጃዎችም፣ ህዝቡ ከሌላ አካባቢ መጥቶ የሰፈረ እንጂ ከጥንት ከመሰረቱ እዚሁ የነበረ፣ ከዚሁ የተገኘ ነባር ህዝብ ያለመሆኑን ይናገራሉ፡ ፡ ነገር ግን ከየት መጣ? እንዴት ወደዚህ ሊመጣ ቻለ? ...ወዘተ የሚሉት ጥያቄዎች እስካሁን በቂ ምላሽ ያላገኙ፣ በራሳቸው ጠለቅ ያለ ጥናት የሚሹ ናቸው።

የቡርጂ ሕዝቦችን ከየት መጣነትን በሚመለከት የተጻፉት አብዛኞቹ ጽሁፎች መሰረት ያደረጉት የአፈ ታሪክ መረጃዎችን ነው። በዚህ ክፍል የሚቀርበው የቡርጂ ህዝብ ጥንተ አመጣጥ ታሪክም በአብዛኛው ከዚህ የተለየ አይሆንም። በአጭሩ በዚህ ክፍል ‹‹ቡርጂዎች አሁን ካሉበት ቦታ ከየት መጥተው ሰፈሩ?›› ለሚለው ጥያቄ በሁለት ዓይነት መረጃዎች ላይ በመመርኮዝ ምላሽ ለመስጠት ይሞከራል።

የመጀመሪያዎቹ የአፈ-ታሪክ መረጃዎች ናቸው። እነዚህም ቢሆኑ አንድ ወጥ አይደሉም፤ ሶስት መልክ አላቸው። የመጀመሪያው ህዝቡ ከሊበን[11] ተነስቶ ቡርጂ መግባቱን የሚተርክ ነው (ቡኬ፣ 2002፣ 3-5) ። ሁለተኛው ደግሞ ህዝቡ ከሰሜን ምስራቅ ኢትዮጵያ፣ ቡልጋ ከሚባል አካባቢ ተነስቶ በሲዳማ አድርጎ ሊበን፣ ከሊበን ቡርጂ መጥቶ መስፈሩን ያትታል (ማጊኦ፣ 2002፣ 8-9)። ሶስተኛው አፈ-ታሪክ የቡርጂዎችን መንገድ የሚያራዝም፣ መነሻቸውን ከባህር ማዶ የሚያደርግ ነው (ቱኬ፣ 2002፣ 6-9)። ይህ ሶስተኛው አፈ-ታሪክ መነሻቸውን ከዓረብ ሕዝቦች ያድርግ እንጂ፣ ባህሩን አሻግሮ ኢትዮጵያ ካደረሳቸው በኋላ ግን፣ ከሁለተኛውና ከአንደኛው አፈታሪክ ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ይተረካል። እያንዳንዳቸው፣ በቅደምተከተላቸው እንዲህ ይተረካሉ።

---

[10] የእኔ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው፣ በኢትዮጵያ፣ በተለይም በቡርጂ ልዩ ወረዳ ውስጥ በሚኖሩ የቡርጂ ህዝቦች ላይ ብቻ መሆኑን፣ እንዲህ በተደጋጋሚ የምለፈልፈው ወድጄ አይደለም ። ቡርጂዎች ከኢትዮጵያ ውጪ በኬንያ፣ በናይጄሪያና፣ በፑንጃብ (Burji Punjab) ውስጥም የሚኖሩ መሆናቸው (Encarta, 2007) መጠቀሱ አንዱ ምክንያት ነው። ሌላው ምክንያት ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥም ቢሆን ከቡርጂ ልዩ ወረዳ ውጭ(በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች ውስጥ የሚኖሩ በመሆናቸው ነው (ESSP,2007)።

[11] በአሁኑ ኦሮሚያ ክልል በጉጂ ዞን ውስጥ የሚገኝ አካባቢ ሲሆን በአለፉት መንግስታት ነገሌ ቦረና እየተባለ ይጠራ የነበረ አካባቢ ነው።

የመጀመሪያው አፈ-ታሪክ፣ ጥንት የቡርጂ ህዝቦች ከቦረናና ከኮንሶ ህዝቦች ጋር በመሆን ሊበን ላይ ይኖሩ እንደነበር በመተረክ ይጀምራል፡፡ ሶስቱም ህዝቦች በራሳቸው መሪዎች እየተመሩ በሊበን ላይ ሲቀመጡ የቡርጂና የቦረና ህዝቦች ባህላዊ የእምነት ሥርዓት በጋራ የመፈፀም ልማድ ነበራቸው፡፡ ከዕለታት በአንዱ ቀንም እንደተለመደው አንዲት በግ *(ሆላ ፉጋ)* አርደው በመቅበር እምነታዊ ሥርዓቱን ይፈጽማሉ፡፡ ሌሊት ላይ ግን ኮንሶዎች መጥተው በጓን ከተቀበረችበት አውጥተው በሏት፡፡ ፈርሷንም አምጥተው የቡርጂዎች መሪ ከሆነ ሰው ግቢ ውስጥ ጥለው ሄዱ፡፡ የበጓን መበላት ያወቁ ቦረናዎችም የድርጊቱን ፈፃሚ ፍለጋ ወጡ፡፡ ፈርሱን የቡርጂዎች መሪ ግቢ ውስጥ ሲያገኙም የቡርጂዎችን መሪ ጠርተው ‹‹እንዲህ ያለ ከእርስዎ የማይጠበቅ ክፉ ሥራ ከግቢዎ ተፈፅሞ አገኘን፡፡ ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?›› በማለት ጠየቁት፡፡ ባልሰራው ስራ ስሙ በመነሳቱ የተናደደው የቡርጂ መሪ ጦር አንስቶ የቦረናዎችን መሪ ወጋው፡፡ በዚህም በሁለቱ ህዝቦች መካከል ጦርነት ተቀሰቀሰ፡፡ በጦርነቱ ቦረናዎች አየሉ፡፡ ቡርጂዎች ተጠቁ፡፡ ቡርጂዎች መቋቋም ባለመቻላቸው ሽሽት ጀመሩ፡፡ *ከሊበን* ሸሽተው *አቡኖ* ከሚባል ቦታ ሰፈሩ፡፡ ቦረናዎች እዚያም ተከታትለው በመምጣት ስለወጉዋቸው *አቡኖን* ለቀው *ባርጉዳ* ከሚባል ቦታ ላይ መጥተው ተቀመጡ፡፡ ከባርጉዳ ተነስተው በሁለት አቅጣጫ ተጓዙ፡፡ አንደኛው ወገን ግራውን ይዞ *ሙሬ* ከሚባል ተራራ ላይ ሲሰፍር ሁለተኛው ወገን ደግሞ ቀኙን ይዞ በመጓዝ *ኡሬ* ተራራ ላይ ተቀመጠ፡፡ በመጨረሻም አሁን ካሉበት ቡርጂ አካባቢ መጥተው መስፈራቸው ይነገራል (ቡኬ፣ 2002፣ 3-7)፡፡

ሁለተኛው አፈ-ታሪክ የቡርጂዎችን መነሻ ሰሜን ምስራቅ ኢትዮጵያ የሚያደርግ ነው፡፡ እንደ አፈታሪኩ ከሆነ የቡርጂ ህዝቦች፣ ጥንት ከሚኖሩበት፣ ቡልጋ ከሚባል ከሰሜን ምስራቅ ኢትዮጵያ ተነስተው ወደ ደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ ጉዞ ጀመሩ፡፡ ካምባታን፣ አላባን አቋርጠው ሲዳማ ደረሱ፡፡ በሲዳማ ጥቂት ከተቀመጡ በኂላ *ጊዳቦ* ወንዝን ተሻግረው ወደ ደቡብ በመጓዝ ሊበን መጥተው ሰፈሩ፡፡ ከሊበን ላይም ከኮንሶና ከቦረና ህዝቦች ጋር ለረዥም ጊዜ ከተቀመጡ በኂላ፣ ቀደም ሲል በተተረከው ምክንያትና ሁኔታ ከሊበን-ቡርጂ መጥተው መቀመጣቸው ይተረካል (ማንኦ፣ 2002፣ 9)፡፡

ሶስተኛው አፈታሪክ፣ የቡርጂ ህዝቦች ጥንት ከሚኖሩበት፣ ከዓረቦች ምድር ፈልሰው ወዲህ መምጣታቸውን የሚያመለክት ነው፡፡ እንደ አፈ ታሪኩ የቡርጂ ህዝቦች፣ ከአማራና ከሲዳማ ህዝቦች ጋር በመሆን ባህር አቋርጠው ይመጣሉ፡፡ ባህሩን ከተሻገሩ በኂላ የአማራ ህዝቦች ከዚያው ሲቀሩ ቡርጂዎችና ሲዳማዎች ተያይዘው ወደ ደቡብ ጉዞ ጀመሩ፡፡ *ጊዳቦ* ወንዝ አካባቢ

ሲደርሱም ከዚያው ተቀመጡ። ይሁን እንጂ፣ ያንን አካባቢ የሲዳማ ሕዝቦች ጠቅልለው ስለያዙባቸው፣ ቡርጂዎች ወደ ደቡባዊ ምስራቅ አቅጣጫ ለመጓዝ ተገደዱ። በዚህም የጊዳሞ ወንዝ ተሻግረው በመጓዝ ሊበን ላይ መጥተው እንደተቀመጡ ይተረካል (ቱኬ፣2002፣ 6-9)። ከዚህ በኋላ ያለው ትረካ ከሌሎቹ ጋር ተመሳሳይ ነው። የቡርጂ ህዝብ አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ሰፍሮ በሚገኝበት፣ በቡርጂ አካባቢ መጥቶ የሰፈረው በዚህ መልክ መሆኑ በአፈታሪክ ይነገራል።

በዚህ ዓይነት ከሊበን የመጣው ህዝብ ሁሉ ከቡርጂ ላይ እንዳልተቀመጠ፣ ከቡርጂም አልፈው የሄዱ የቡርጂ ህዝቦች መኖራቸው ይተረካል። እንደ አፈታሪኩ፣ እነዚህ የቡርጂ ሕዝቦች ከቡርጂ አልፈው ወደ ምዕራብ አቅጣጫ፣ ወደ ቤንች ማጂ ከሄዱ በኋላ *ጃባ ቡርጂ* በሚል ስም የሚጠሩ መሆኑ ይነገራል። እንደ መረጃ ሰጪዎቹ አባባል እነዚህ *ጃባ-ቡርጂ* በሚል ስም የሚታወቁት ቀደምት የቡርጂ ህዝቦች፣ እዚህ ቡርጂ ውስጥ ካለው ወገናቸው የሚለዩት በቋንቋቸው ብቻ ነው። የሚያራምዱት ባህላዊ ስርዓት ሁሉ ከዚህ ካለው ከቡርጂ ህዝብ ጋር ተመሳሳይ ነው። ልክ እዚህ እንዳሉት ቡርጂዎች *ሐጣኖ* የሚባለውን እምነታዊ *ሥ*ርዓት ይፈጽማሉ (ስለ ዝርዝር መረጃው ምዕራፍ አምስትን ተመልከት)። *ሔሳን* ከደጃቸው ይተክላሉ። ይህንንም አይተው የመጡ የቡርጂ ሰዎች አሉ። ነገሩ እንዲህ ነው ።

> በጣሊያን ወረራ ወቅት ነው አሉ። ጨኖ ሎሎ እና ወጌ ግሬ የሚባሉ የቡርጂ ወጣቶች ባንዳ ሆነው፣ ለጣሊያን ጦር አድረው፣ ከእነሱ ጋር ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሄዱ። እዚያ በሄዱበት አካባቢም ከቋንቋቸው በስተቀር በስምም፣ በባህልም ከቡርጂ ህዝብ ጋር የሚመሳሰሉ፣ ጃባ ቡርጂ የሚባሉ ህዝቦችን ያገኛሉ። ሲጠያየቁም ጥንት ከቡርጂ አልፈው የሄዱ የራሳቸው የቡርጂ ወገኖች መሆናቸውን አወቁ። እነዚያ ህዝቦችም ልጆቹ ቡርጂ መሆናቸውን ሲያውቁ ‹‹የእኛን ወገኖች አገኘን›› በማለት በሬ አርደው ጋበዙአቸው። እስከተመለሱበት ጊዜ ድረስም ማብላት፣ ማጠጣቱ እንዳልተቋረጠባቸው እነዚያ ልጆች ወዲህ ከተመለሱ በኋላ መናገራቸው ይተረካል[12] ።

Amborn እና Kellner (1999) የተባሉ ፀሀፊዎች፣ ከፍ ሲል የተጠቀሰውን ሀሳብ ይጋራሉ። እነዚህ ጸሀፍት *"Burji Vocabulary of Cultural Items"* በሚል ርዕስ ባሳተሙት መጣጥፋቸው ውስጥ፣ በወቅቱ በቡርጂ አካባቢ ይተረክ የነበረውን፣ ይሄንኑ አፈ ታሪክ መነሻ በማድረግ፣ *ጃባ ቡርጂ (Jaba-Burji)* ለሚለው ቃል ፍቺ ሲሰጡ እንዲህ በማለት ጽፈዋል።

[12] አንሸ ቱኬ ህርቦ ፣ 2002፣ 9-10።

> *Burji group which, according to Burji Tradition emigrated from Liban to Dawaya*[13] *and from there moved on westward into the area beyond Bako …. During colonial times some Burji came with Italian "banda" in which many of them served into the maji highlands. There they came to know Jaba-Burji who, as they noticed, not only has a similar name but also cultural traits which reminded them of their own culture … (45). (አፅንኦቱ የራሴ ነው)።*

እንዲሁም፣ በወቅቱ እነዚህ ሕዝቦች (ጃባ ቡርጂዎች) በመሪያቸው አማካይነት፣ እዚህ ቡርጂ ከነበረው ወገናቸው ጋር በደብዳቤ ግንኙነት ለመፍጠር ሞክረው እንደነበረ፣ ነገር ግን ይህ ሙከራቸው ከነጻነት በኋላ በነበረው የአስተዳደር ሁኔታ ሳይሳካ መቅረቱን እኒሁ ጸሓፍት ይጠቁማሉ። ‹‹ከቡርጂ ተነጥሎ የሔደ፣ *ጃባ-ቡርጂ* የሚባል ህዝብ አለ›› የሚለውን፣ይህን አፈ-ታሪክ የሚያጠናክር ሌላም መረጃ ማቅረብ ይቻላል። በተለይ ደግሞ ከፍ ሲል በተጠቀሰው ሃሳብ ውስጥ ከኢጣሊያ ጦር ጋር ከሄዱት ከቡርጂ ወጣቶች መካከል፣ አብዛኞቹ ያገለገሉት በማጂ ደጋማ አካባቢዎች መሆኑ ነገሩን ከአፈ ታሪክነት ወደ ‹‹እውነተኝነት›› ሳያስጠጋ አይቀርም የሚል ግምት አለኝ። ለዚህ መነሻዬ በደቡብ ብሔረሰቦች ባህል፣ ቋንቋና ታሪክ ጥናት ተቋም አማካይነት፣ *የደቡብ ብሄር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ፕሮፋይል* (2001) በሚል ርዕስ የታተመው መጽሐፍ ነው።

መጽሐፉ በቤንች ማጂ ዞን ውስጥ ቤንች፣ ዲዚ፣ መኢኒት፣ ሸኮ፣ ሱርማና ዝልማሙ (ባሌ) የሚባሉ ስድስት ብሔረሰቦች እንደሚገኙ ይናገራል (64)። ከስድስቱ ብሔረሰቦች፣ በተለይ ስለ ሸኮና ስለ ዲዚ ብሔረሰቦች ጥንተ አመጣጥ ታሪክን በተመለከተ በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሰውን እንመልከት። ጽሁፉ በማህበረሰቡ የሚነገረውን አፈ ታሪክ መሰረት ያደረገ ነው። በአፈ ታሪኩ መሰረት ለሸኮ ብሔረሰብ መፈጠር ዋነኛው ምክንያት *ከጃባ ቡርጂ* ወገን የሆነና በማጂ አካባቢ ይኖር የነበረ አንድ ባህላዊ መሪ (ንጉስ) እንደሆነ ይነገራል። ይህም ባህላዊ ንጉሥ በማጂ ተራራማ አካባቢ ሲኖር አምስት ወንድ ልጆችን ይወልዳል። ከአምስቱ ወንድ ልጆች መካከል አንደኛው *ኮኛብ* ይባላል። ከዕለታት አንድ ቀንም *ሚያንግ* በሚል ስም የሚታወቀው የጎሳው ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል *በኮኛብ* ላይ ይሰፍርበታል። በዚህ የተነሳም *ኮኛብ* ሦስት ወንድሞቹን ከዚያው ከማጂ ትቶአቸው አንድ ወንድሙን ብቻ አስከትሎ ወደ ዛሬዋ ሸኮ መጥቶ በመስፈር የዛሬውን የሸኮን ብሔረሰብ እንዳስገኘ ይነገራል። ከማጂ የቀሩት ሦስት ወንድሞቹ ደግሞ ለዲዚ

---

13 በቡርጂ ልዩ ወረዳ በሰገን ሸለቆ ጠርዝ ላይ የሚገኝ ሰንሰለታማ ኮረብታ (ተራራ) ነው። ይህ ቦታ ጥንት የቡርጂ ወገን የነበሩ ማሌዳ እና ጃባ-ቡርጂ የሚባሉ ቡድኖች ከሊበን መጥተው ያረፉበት ስፍራ እንደሆነ የቡርጂ አፈ ታሪክ ይተርካል። ከዚህ ተነስተውም ጃባ ቡርጂዎች ወደ ምዕራብ አቅጣጫ፣ ባኮ አካባቢ ሲጓዙ ማሌዳዎች ደግሞ ወደ ኮንሶ መሻገራቸው ይነገራል (Amborn & kellner,1999,31)።

ብሔረሰብ መመስረት ምክንያት እንደሆኑ በመጽሐፉ ተጠቅሷል (76)። ይህም ‹‹ጥንት ከቡርጂ አልፈው ሄዱ የተባሉ ህዝቦች፣ አሁን ቤንች ማጂ ዞን ውስጥ የሚኖሩትና የሸኮን እና የዲዚን ብሔረሰቦች ያስገኙት ጃባ ቡርጂዎች ይሆኑ ይሆን?›› የሚል ጥያቄ እንድናነሳ ያደርገናል። ለሸኮዎችና ለዲዚዎች መገኘት መሰረት የሆኑት ጃባ ቡርጂዎች፣ በትክክል በቡርጂ አፈ-ታሪክ የተነገሩት ጃባ ቡርጂዎች ይሁኑ አይሁኑ፣ ለጊዜው በጥናት ባልተረጋገጠበት፣ ተጨባጭ መረጃ በሌለበት ሁኔታ ‹‹ናቸው›› ወይም ‹‹አይደሉም›› ብዬ ለመናገር አልደፍርም። ነገር ግን ጉዳዩ ጥናት የሚፈልግ መሆኑን ለመጠቆም እወዳለሁ። ያም ሆነ ይህ፣ እነዚህ ሁሉ ስለ ቡርጂ ህዝብ ጥንተ አመጣጥ የሚናገሩ አፈታሪኮች ናቸው።

ቁልጭ ባለ መልክ የተቀመጡ ባይሆኑም ‹‹ቡርጂ›› በሚል ስም ስለሚጠራ ህዝብ ወይም አካባቢ የሚያትቱ የፅሁፍ መረጃዎችም አሉ። በእነዚህ መረጃዎች ውስጥ ‹‹ቡርጂ›› ተብለው የተጠቀሱት ህዝቦች እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ቡርጂዎች ጋር በደምና በሥጋ አንድ ሕዝቦች ይሁኑ፣ በአጋጣሚ የተገናኙ የስም ሞክሼዎች፣ እርግጠኛ ሆኜ መናገር አልችልም። ጽሁፉም አያስረዳም። ይሁን እንጂ በጥንታዊቷ ግብጽ ታሪክ ግብጽን ከ1382-1517 ድረስ የገዙት የቡርጂ ዳይናስቲ እንደሆነ ከኢንተርኔት የተገኙ የጽሁፍ መረጃዎች (Encarta, 2007 p1 )ይጠቁማሉ። ከዚህም በተጨማሪ፣ እንዴት አድርገው እንደሄዱ ወይንም በየት በኩል አድርገው እንደገቡ? ባይገለጽም፣ በአሁኑ ጊዜ ‹‹ቡርጂ›› በሚል ስም የሚታወቁ ህዝቦች በናይጄሪያ፣ በኬንያ፣ በጙንጃብና (በፓክሲታንና) በኢትዮጵያ እንደሚኖሩ ይሄው መረጃ ይገልጻል (አባሪ ቁጥር 3 ተመልከት)።

ይህ የጽሁፍ መረጃ ሲታይ፣ ቀደም ሲል ‹‹ቡርጂዎች ባህር ተሻግረው መጡ›› በሚል የተጠቀሰው አፈታሪክ ‹‹እውነት ይሆን እንዴ?›› ብለን እድንጠይቅ ማድረጉ አይቀርም። ይህም በራሱ ጥናት የሚሻ ጉዳይ ይመስለኛል። በተለይ፣ ይህ በኢንተርኔት ግብፅን ከ1382-1517 ድረስ ገዝተው፣ በኦቶማን መንግስት በመሸነፋቸው ከአገር ወጥተው ሄዱ የተባሉት ቡርጂዎች (Burji dynasty) እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ጋር አንድ ይሁኑ አይሁኑ አፍ ሞልቶ መናገር የሚቻለው በጥናት ሲረጋገጥ ብቻ ነው። ከዚህ ባለፈ ግን፣ አፍ ሞልቶ መናገር የሚቻለው አብዛኛው የሚስማማበትን ‹‹ቡርጂዎች ከሊበን መጥተው ቡርጂ ላይ ሰፈሩ። የቡርጂዎች እትብት የተቀበረው ከሊበን ላይ ነው።›› የሚለውን አፈ-ታሪክ ብቻ ይሆናል። ‹‹ከሰሜን ምስራቅ ኢትዮጵያ ከቡልጋ መጡ›› የሚለው አፈታሪክም፣ Amborn እና Kellner (1999) እንደሚሉት ከአማራው መንግስት መስፋፋት ጋር ተያይዞ የተፈበረከ አፈ-ታሪክ ይመስለኛል። ህዝቡ አገዛዙን

እንዳይቃወም ‹‹የእኛው ወገኖች ናቸው›› ብሎ እንዲቀበላቸው የአፄው የጦር መሪዎችና አንዳንድ እንደ ባላምበራስ ዶንጬ ጮታ (ጉዮ) የመሳሰሉት የቡርጂ ወገኖች፣ ሆን ብለው ፈጥረው ያስወሩት አፈታሪክ እንደሆነ እኒሁ ጸሐፍት ላይ ጠቁመዋል (በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 49፣ ገጽ 45)።

## 3.4. ቋንቋ

አብዛኞቹ ቡርጂዎች ቋንቋቸውን *ዳሻ* ይሉታል። ጥቂቶቹ ደግሞ *ቡርጃ* በማለት ይጠሩታል። ቋንቋቸውን *ዳሻ* የሚሉት እራሳቸውን *ዳሽ* ብለው የሚጠሩ ወገኖች ሲሆኑ፣ *ቡርጃ* የሚሉት ደግሞ ህዝቡ ተጠቃሎ ሲጠራ ‹‹ቡርጂ›› ይባላል የሚሉ ወገኖች ናቸው።

ቋንቋውን *Banbala Language* (Cerruli,1965; Bender,1972) ብለው የሚጠሩም አልጠፉም። ያም ሆነ ይህ ቋንቋው በአሁኑ ጊዜ በአማርኛ ‹‹ቡርጂኛ›› በእንግሊዝኛው ደግሞ *‹‹Burji Language››* በመባል ይታወቃል። ከ*Highland East Cushitic* የቋንቋ ቤተሰብ ይመደባል። ከሌሎች የኩሽ ቋንቋዎች ጋር 20% (ሃያ በመቶ)፣ በተለይ ከሲዳምኛ ቋንቋ ጋር አርባ በመቶ (40%) የቃላት ተመሳስሎ አለው (Bender,1972; ELRC,2005)። ቋንቋው በወጉ አልተጠናም። በመጀመሪያ ዲግሪ ተመራቂ ተማሪዎች ከተደረጉት ጥቂት ሙከራዎች (Roba,1981; Buzayehu,1994) በስተቀር፣ በቋንቋው ላይ ጠለቅ ያለ ጥናት አልተካሄደበትም። በዚህ የተነሳም ቋንቋው እስከዛሬ ድረስ ከንግግር ቋንቋነት ባለፈ ለሌላ አገልግሎት መዋል አልቻለም። የጽሑፍ ቋንቋ አልሆነም። ቋንቋው በአሁኑ ጊዜ በአጎራባች ቋንቋዎች የመዋጥ አደጋ እንደተጋረጠበት፣ በዚህም ለመጥፋት መንገድ ከጀመሩት *(Endangered Languages)* ቋንቋዎች መካከል አንዱ እንደሆነ (Amborn and Kellner,1999, 8-9) ይናገራሉ።

# 4. የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደር

የቡርጂ ህዝቦች፣ እንደ አብዛኞቹ የአፍሪካ ህዝቦች ሁሉ፣ በሀገሪቱ ማዕከላዊ መንግስት ከመመስረቱ፣ ዘመናዊ የአስተዳደር ሥርዓት ከመዘርጋቱ በፊት ይተዳደሩባቸው የነበረ የጎሜ፣ የሀግ እና የክልል ባህላዊ የአስተዳደር ተቋማት እንደነበሯቸው፣ ዛሬም በከፊል እንዳሏቸው ቀደም ሲል ገልጸናል። የዚህ ምዕራፍ ዋነኛው ትኩረትም፣ እነዚህን ባህላዊ የአስተዳደር ተቋማትን አወቃቀርና የአሰራር ሥርዓት አንድ በአንድ ማሳየት ይሆናል። ለአቀራረብ እንዲመች ሲባል ምዕራፉ በአራት ንኡሳን ክፍሎች ተከፍሎ ይቀርባል።

የቡርጂ ህዝብ በራሱ የአስተዳደር ስርዓት መተዳደር የጀመረው ከመቼ ጀምሮ እንደሆነ፣ ከዚያ በኋላ እንዴት እንደቀጠለና እንደተቋረጠ ለማስረዳት የሚሞክሩ ታሪኮችን የሚያትተው ክፍል ቀዳሚ ይሆናል። ቀጥሎ ይህ ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓት አወቃቀሩ ምን እንደሚመስልና ምንን መሰረት እንዳደረገ ተብራርቶ ይቀርባል። ባህላዊ መሪዎች በሥልጣን ላይ ስለሚመደቡበት መንገድና ስለ ተግባራቸው በቅደም ተከተላቸው በምዕራፉ ሥር የሚቀርቡ ነጥቦች ናቸው።

## 4.1 የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደር ታሪክ

ከፍ ሲል ቡርጂዎች የጎሜ፣ የሀግ እና ክልላዊ በሚባሉ በሶስት አስተዳደራዊ ተቋማት እንደሚተዳደሩ ተናግረናል። ለእያንዳንዱ ተቋም መመስረትም መነሻ የሆኑ ምክንያቶችና ታሪካዊ አጋጣሚዎች አሉ። የዚህ ንዑስ ክፍል ዋነኛ ትኩረትም፣ ለእያንዳንዱ ተቋም መመስረት ምክንያትና አጋጣሚ የሆኑት ታሪካዊ ክስተቶች ምን ምን እንደሆኑ ማሣየት ይሆናል። ይህ ሲባል ግን ሶስቱም ተቋማት በዚህ መልክ ይቀርባሉ ማለት አይደለም። የጎሜና የሀግ ተቋማት በውስጣቸው ንዑሳን ተቋማትን ያልያዙ ስለሆኑ ለመመስረታቸው መነሻ ምክንያትና አጋጣሚ የሆኑ ነጥቦች አንድ በአንድ ይቀርባሉ። ክልላዊ ተቋም ግን የተዋቀረው በውስጡ በርካታ ንዑስ ተቋማትን ይዞ ስለሆነ፣ ከቦታና ከፋይዳው አንፃር፣ ስለ እያንዳንዱ ታሪክ እዚህ ቦታ ከማቅረብ ይልቅ የተወሰኑትን ብቻ መርጦ መተረኩ ተገቢ ይመስለናል። ስለሆነም ከክልላዊ ተቋማት መካከል *የወማ* እና *የዳይና* አስተዳደሮች መቼና እንዴት እንደጀመሩ፣ እንዴት እንደቀጠሉና እንደተቋረጡ በህብረተሰቡ ዘንድ የሚነገሩ አፈ-ታሪኮችን እና ሌሎች መረጃዎችን መሰረት አድርገን ለማቅረብ እንሞክራለን።

### 4.1.1 የጎሳ አስተዳደር ተቋም ታሪክ

በቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር ታሪክ ውስጥ ቀዳሚው የጎሳ አስተዳደር ነው። ቡርጂዎች በጎሳ በጎሳቸው ሆነው መተዳደር የጀመሩት ከመቼ ጀምሮ እንደሆነ ለጊዜው የሚታወቅ ነገር የለም። ይሁን እንጂ፣ ወዲህ ወደ ቡርጂ ሲመጡ ጀምረው በጎሳ ይተዳደሩ እንደነበር የሚጠቁሙ የአፈ-ታሪክ መረጃዎች አሉ። ከእነዚህም መካከል አንዱ፣ ከሁሉ ቀድሞ ከሊበን ቡርጂ ስለገባው ጎሳ ማንነት የሚተርከው አፈታሪክ ነው። ነገሩ እንዲህ ነው።

> ቡርጂዎች፣ አሁን ካሉበት (ቡርጂ) መጥተው ሲሰፍሩ፣ አካባቢው ማንም ያልነበረበት፣ ጫካ ነበር። አገሩ እንዲህ ጫካ በነበረበት ዘመን፣ *ካራማ* የሚባል የቡርጂ ጎሳ ወደ አካባቢው መጣ። እንደመጣም ከመሬት ጉድጓድ ቆፍሮ አንዲት ሴት በግ ቀበረበት። ከዚህ በኋላ ደግሞ *ጊነ* የሚባል ሌላ የቡርጂ ጎሳ ወደ አካባቢው መጣ። መጥቶም በቅርብ ጊዜ ተቆፍሮ የተደፈነ ጉድጓድ ተመለከተ። ‹‹*ከዚህ ውስጥ ምን አለበት?*›› ብሎ ጉድጓዱን ሲቆፍር፣ በውስጡ በግ ተቀብሮበት አገኘ። ይህን ጊዜ የጊነ ጎሳ የራሱን በግ አምጥቶ በጉድጓዱ ከስር በኩል ቀበረበት። ቀድሞ ከጉድጓድ ውስጥ የነበረውን በግ ደግሞ ከላይ በኩል አድርጎ ከቀበረው በኋላ ጉድጓዱን መልሶ ደፈነው። ይህ ከሆነ ከጥቂት ቀናት በኋላ ሁሉም የቡርጂ ጎሳዎች ተጠቃለው ገቡ። ገብተው ጉባኤ አደረጉ። በጉባኤውም ‹‹*ከሁሉም ቀድሞ እዚህ ሀገር የገባው ጎሳ ማነው?*›› ተባለና ተጠየቀ። የካራማ ጎሳ ተነስቶ ‹‹*ከሁሉም መጀመሪያ ከዚህ ሃገር የመጣሁት እኔ ነኝ። ለዚህም ማስረጃ አለኝ*›› ብሎ ተቀመጠ። ቀጥሎ የጊነ ጎሳ ተነሳ። ተነስቶም ‹‹*ሐሰት*። አንተ አይደለህም። ከሁሉም ቀድሜ ከዚህ የገባሁት፣ እኔ ነኝ። ለዚህም ማስረጃ አለኝ።›› በማለት ተሟገተ። ሁለቱም ጎሳዎች እንዲህ ሙግት በመግጠማቸው ማስረጃ እንዲያቀርቡ ተጠየቁ። ከዚህ እንደደረሱ ከመሬት ውስጥ ጉድጓድ ቆፍረው በግ መቅበራቸውን አሳወቁ። የተቀበረበትንም ጉድጓድ አሳዩ። ጉድጓዱ ሲቆፈር የጊነ ጎሳ በግ ከስር፣ *የካራማ* በግ ደግሞ ከላይ በኩል ተቀብሮ ተገኘ። በመሆኑም ‹‹ከዚህ አገር ከሁሉም ቀድሞ የገባው፣ በጉ ከስረኛው በኩል ያለው የጊነ ጎሳ ነው›› ስለተባለ የጊነ ጎሳ አገሩን ወሰደ። አገሩን ወስዶ፣ መሪ ሆኖ፣ አገሩንና ህዝቡን ማስተዳደር ጀመረ ይባላል።[14]

ከዚህ አፈታሪክ የቡርጂ ህዝብ ከሊበን-ቡርጂ ያደረገው ጉዞ በቡድን የተከፈለ፣ ቡድኑ ደግሞ በጎሳ ላይ የተመሰረተ እንደነበረ መረዳት ይቻላል። እንዲሁም በቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር ታሪክ፣ የጎሳ አስተዳደር ቀዳሚ መሆኑን ከአፈታሪኩ እንገነዘባለን። የቡርጂ ህዝቦች በጎሳ በጎሳቸው ሆነው መተዳደራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሁሉም በአንድ ጎሳ የመተዳደር፣ የመመራት ስርዓት የነበራቸው መሆኑን መገመት አያዳግትም። ለዚህ ደግሞ የጊነ ጎሣ ህዝቡንና አገሩን እንዲመራ መደረጉን መጥቀሱ በቂ ይመስለኛል።

የቡርጂ ህዝብ፣ በአንድ ጎሳ የመተዳደር ልማድ ቀደም ሲልም የነበረው ስለመሆኑ ሌላ መረጃ መጥቀስ ይቻላል። ለዚህ ደግሞ ስለ ህዝቡ ጥንተ አመጣጥ የሚተርከው አፈ-ታሪክ (ክፍል 3.3 ተመልከት) ጥሩ ማስረጃ ይመስላል። ከአፈታሪኩም ቡርጂዎች ሊበን ላይ ከቦረናና ከኮንሶ

---

14 የኣናቡራ ጎሳ መሪ ለሆኑት፣ ለኣንሽ ቱኬ ሀርቦ፣‹‹ ከቡርጂ ጎሳዎች መካከል ከሁሉ ቀድሞ ቡርጂ የደረሰው ጎሳ የትኛው ነው?›› በማለት፣ በ23/07/2002 ዓ.ም፣ ከመኖሪያ ቤታቸው ለአቀረብኩላቸው ጥያቄ ከሰጡኝ ምላሽ የተወሰደ (ገጽ 14 )።

ህዝቦች ጋር ሲኖሩ የራሳቸው መንደርና ሊሶ[15] ያለው መሪ እንደነበራቸው፣ በሊሶውም የቡርጂና የበረና ህዝቦች በጋራ እምነታዊ ስርዓት ይፈፅሙበት እንደነበር እንገነዘባለን። ከዚህ ‹‹ሊሶ ያለው መሪ›› ከሚለው ሀሳብ ተነስተን ‹‹የቡርጂ ህዝቦች በአለፉት ዘመናት ይመሩበት የነበረው የአስተዳደር ሥርዓት፣ ፖለቲካዊ ሳይሆን መንፈሳዊ ይዘት የነበረው ሣይሆን አይቀርም›› ብለን መላምት እንድንሰነዝር ያስገድደናል። የቡርጂ ህዝቦች ፖለቲካዊ ይዘት ያለውን የአስተዳደርና የቁጥጥር ሥርዓት ዘርግተው መተዳደር የጀመሩት ግን ቡርጂ መጥተው ከሰፈሩ በኋላ ነው። ይህ የቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካ ሥርዓት የሚጀምረው ደግሞ *በወማ* (በባህላዊ ንጉስ) አስተዳደር ታሪክ ነው (ክፍል 4.1.3.1 ተመልከት)።

### 4.1.2 የሀግ አስተዳደር ተቋም ታሪክ

*ሀግ*፣ ለቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካ ሥርዓት መሰረት የሆነ ተቋም ነው። ከሁሉም በላይ ግን ይህ *የሀግ ሥርዓት*፣ በባህላዊ የግርዛት ሥርዓት አማካይነት፣ የማህበረሰቡ ወንድ ልጆች ለአቅመ አዳም መድረሳቸው፣ ቀዳሚውን ትውልድ ለመተካት፣ ኃላፊነትን ለመሸከም ብቁ መሆናቸው የሚረጋገጥበት መሣሪያ ነው። በአጭሩ *ሀግ* ቡርጂዎች ትውልድን ለመመደብ የሚገለገሉበት ባህላዊ ተቋም (Generation grading system) ነው። ተቋሙ የሚመሰረተው በግርዛት ሥርዓት ውስጥ ሲሆን፣ ይህም የራሱ የሆነ የአፈፃፀም ሥርዓት አለው (ለዝርዝር አፈፃፀሙ ግርማ፣ 1982 ተመልከት)።

በቡርጂዎች ዘንድ የሴት ልጅ ግርዛት አልተለመደም። አይታወቅምም። በአንፃሩ ግን የወንድ ልጅ ግርዛት ቡርጂዎች ዘንድ ታላቅ ባህላዊና ፖለቲካዊ ፋይዳ ያለው ተግባር ነው። በመሆኑም ቡርጂዎች እድሜያቸው ከ9-12 የሆናቸውን ወንድ ልጆቻቸውን በየሶስት ወይም በየሰባት ዓመት[16] አንዴ፣ በአንድ ላይ፣ በአንድ ወቅት ያስገርዟቸዋል። እነዚህ የተገረዙ ልጆችም *ሉባ* በሚል የማዕረግ ስም ይጠራሉ። በዚህ ዓይነት በየሶስት ዓመት ልዩነት የተገረዙት የስድስት ዙር ሉባዎች፣ ወይም በየሰባት ዓመቱ አንዴ በሚያስገርዙ አካባቢዎች ደግሞ፣ የሁለት ዙር

---

[15] የቡርጂ ባህላዊ መሪዎች የሚይዙት፣ መለያ ምልክታቸው የሆነ፣ ባህላዊ የክብር አለንጋ (ዕቃ) ነው። የሚሰራው ከጉማሬ ቆዳ ሆኖ እጀታው በነሀስ የተለበጠ ነው። የሚይዙት ደግሞ ባህላዊ የፖለቲካና የእምነት መሪዎች ናቸው። ብዙውን ጊዜ የሚያዘው በምርቃትና በቡራኬ የእምነት ስርዓቶች ወቅት ነው። ማህበረሰቡ በሚኖርበት አካባቢ የተከሰቱ ክፉ ነገሮች (በሽታ፣ ጦርነት ወዘተ.) ሲኖሩ ደግሞ ክፋውን ለማውገዝም ይገለገሉበታል። Amborn እና Kellner (1999, 51) ሊሶ የሰላም ባንዲራ ተደርጎ በቡርጂዎች ዘንድ እንደሚቆጠር ዕፈዋል። ለምሳሌ አንድ የቡርጂ ወማ፣ ዳይናው በእሱ ላይ ጦርነት ሊከፍትበት ማቀዱን በሰማ ጊዜ የራሱን ጃልዐባ (ረዳቱን) ሊሶ አስይዞ ወደ ዳይናው ይልካል። ዳይናውም እንዲሁ፣ ወማው ጦር ልኮበት ሊወጋው ማሰቡን ሲሰማ፣ እሱም በተመሳሳይ ሁኔታ ጃልዐባውን ሊሶ አስይዞ ወደ ወማው ይልከዋል። ሁለቱም ባለሥልጣናት ረዳቶቻቸውን (ጃልዐባቸውን) ሊሶ አስይዘው መላካቸው፣ አንዳቸው ለአንዳቸው ‹‹ከአንተ ጋር ሠላምን እንጂ ጦርነትን አልሻም›› ማለታቸው እንደሆነ እኒሁ ፀሐፍት ያስረዳሉ።

[16] ግርዛቱ በሶስት ዓመት አንዴ ወይም በሰባት ዓመት አንዴ የሚፈፀመው ለምንና መቼ እንደሆነ በዝርዝር ለማወቅ፣ ግርማ፣ 1982፣ ‹‹ግርዛትና ዘፈኖቹ በቡርጂ ህብረተሰብ›› የሚለውን ዲማፅ እንዲሁም፣ ግርማ፣ 2001፣ ‹‹ባህላዊ የግርዛት ሥርዓት በቡርጂ›› የደቡብ ንጋት ጋዜጣ፣ ቅፅ ቁ....ን ተመልከት።

*ሉባዎች* በሙሉ በአንድ የሀግ ስም ወይም ምድብ *ሥር* ይመደባሉ (ይጠራሉ)፡፡ የሀግ ስሞች ወይም የምድቦች ቁጥርም እንዲሁ *ከቢያ ቢያ* (ከአካባቢ አካባቢ) ወይም *ከቦሄ ቦሄ* (ከቀበሌ ቀበሌ) የሚለያዩ ቢሆንም ግን ዝቅ ሲል ከስድስት፣ ከፍ ሲል ደግሞ ከአስራ አንድ አይበልጥም፡፡ ለምሳሌ *ጋሻራ*፣ የበን እና ኦቶማል በሚባሉት፣ በቡርጂ አካባቢዎች የሚታወቀው የሀግ ስሞች ብዛት ስድስት ሲሆኑ፣ እነሱም በቅደም ተከተላቸው *ወላሳ፣ ፍላታ፣ ጂቦታ፣ ጉቼ፣ ሞተ* እና *ቃላላ* በሚል ስም ይታወቃሉ፡፡ በዚህም በእነዚህ የቡርጂ አካባቢዎች ትውልድ የመመደቡ *ሥ*ርዓት ከመጀመሪያው ከወላስ ጀምሮ፣ ከመጨረሻው ምድብ፣ *ከቃላላ* ላይ ሲደርስ እንደገና ከመጀመሪያው ምድብ፣ *ከወላሳ* ላይ ‹‹ሀ›› ተብሎ ይጀመራል (ግርማ፣ 1982፣ 29)፡፡ እያንዳንዱ *ሀግም ሃዩ* በሚባል መሪ ይመራል፡፡

በአጠቃላይ *ሀግ* በወጣት ወንዶች የተገነባ የመከላከያ ተቋም ነው፡፡ ዋና ተግባሩም የሕዝቡንና የአካባቢውን ደህንነት መጠበቅ ነው (ዝርዝር ተግባሩን በክፍል 4.4 ላይ ተመልከት)፡፡ ለዚህ፣ *ለሀግ* ተቋም *መመሥረት* መነሻ የሆነ አንድ አጋጣሚ እንደነበረ በቡርጂዎች አፈታሪክ ይነገራል፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፤

> በድሮ ጊዜ ቡርጂዎች *ማቴ* የሚባል ጦረኛ የሆነ ጠላት ነበራቸው፡፡ *ማቴዎች* ጦርና ጋሻ ይዘው፣ በፈረስ የሚዋጉ አደገኛ ህዝቦች ነበሩ፡፡ በአንድ ወቅት ቡርጂዎች በዚህ ጦር ተከበቡ፡፡ *መግቢያ*፣ *መሸሸጊያ* አልነበራቸውም፡፡ በዚህም ህዝቡ ተጨነቀ፡፡ *የመኖር*፣ በህይወት የመሰንበት ተስፋቸው *መነመነ*፡፡ ተስፋ ቆርጠው ሞታቸውን ይጠባበቁ ጀመር፡፡ ይህ፣ የህዝባቸው ጭንቀት፣ ተስፋ መቁረጥ ያሳሰባቸው የተገረዙ ወጣቶችም (*ሉባዎች*) ተሰባሰቡ፡፡ ህዝባቸውን፣ ከዚህ ከከበባቸው የሞት መልዕክተኛ በሚታደጉበት መንገድ ላይ ተወያዩ፡፡ የወጣቶቹ ቁጥር ከጠላት ጦር ጋር ሲነፃፀር እጅግ አናሳ ቢሆንም ወጣቶቹ አልፈሩም፡፡ ይልቁን ጠላትን ለመፋለም ወሰኑ፡፡ ከመካከላቸው አንድ የጎበዝ አለቃ መረጡ፡፡ ጦርና ጋሻቸውን ይዘው ለጠላት በግልፅ በሚታዩበት ስፍራ ላይ ተሰባሰቡ፡፡ ውጊያ ለመግጠም እየጨፈሩ ወደ ጠላት አቅጣጫ ነጎዱ፡፡ ጠላት ከመሸገበት ሆኖ ለውጊያ ሲዘጋጅ ወጣቶቹ ግን ከጫካ ገብተው ተሰወሩባቸው፡፡ በአሳቻ መንገድ ወደ ኋላቸው ተመልሰው፣ ከመጀመሪያው ስፍራ ላይ ተሰባሰቡ፡፡ ገላቸውን ነጭ ኖራ ቀብተው፣ ሌላ የቡርጂ ጦር መስለው፣ አሁንም ወደ ጠላት ገሰገሱ፡፡ ጠላት ለውጊያ ተዘጋጅቶ ሲጠባበቅ፣ እነርሱ ግን፣ አሁንም ከጫካ ገብተው ተሰወሩባቸው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በጠላት ሳይታዩ፣ ገላቸውን ጥላሸት ቀብተው በመደበኛው ስፍራቸው ላይ ተሰባሰቡ፡፡ አሁንም እንዳለፈው አደረጉ፡፡ ይህን፣ ጠላትን የማታለል ተግባራቸውን ደጋግመው ተወኑት፡፡
>
> ይህ ሲሆን፣ ጠላት ሁኔታውን በእርጋታ ይከታተል ነበር፡፡ ያን፣ እራሱን እየለዋወጠ የሚዘምትባቸውን፣ ዘምቶ፣ ከጫካ ገብቶ የሚሰወርባቸውንም ጦር፣ እነርሱን ሊወጋ፣ ከተለያዩ አካባቢዎች የተሰባሰበ የቡርጂ ጦር እንደሆነ አድርገው ቆጠሩት፡፡ ቁጥሩን ቢያሰሉትም ከእነርሱ ቁጥር በእጥፍ የሚበልጥ መሆኑን ተረዱ፡፡ ጫካ እየገቡ በመሰወራቸውም ‹‹ሳናውቅ በቡርጂ ጦር ተከበናል›› የሚል ስጋት ፈጠረባቸው፡፡ ቀስ በቀስም፣ ስጋቱ ወደ ‹‹እውነት›› ተለወጠና ጠላት ምሽጉን እየለቀቀ ሸሽት ጀመረ፡፡ አብዛኛው እርስ በርሱ ተላለቀ፡፡ ጥቂት የቀሩትንም፣ የቡርጂ ወጣቶች ተከታትለው ፈጁዋቸው፡፡ ወጣቶቹም፣ በዚህ ዓይነት ህዝባቸውንና ሃገራቸውን ከአንዣበበባቸው አደጋ መታደግ ቻሉ፡፡ ከዚያ በኋላ *ማቴዎች* ወደ ቡርጂ አልመጡም፡፡
>
> ይህን የተመለከተው ህዝብም፣ በልጆቻቸው ጀግንነትና ብልሃት እጅግ አድርጎ ተደነቀ፡፡ በመጨረሻም፣ የህዝቡ ከፍተኛ ሹማምንትና የጎሳ መሪዎች ስብሰባ ተቀመጡ፡፡ ያንን ታሪክ

> የሰሩትን ግርዘኞችንም ሀግ ብለው አዋቀሩዋቸው፡፡ በዕለቱ አዝማቻቸው የነበረውን ወጣት ደግሞ፣ *ሃዩ ብለው፣ መሪያቸው አድርገው ሰየሙት*፡፡ የስራ ድርሻቸውም፣ የመከላከያ ኃይል በመሆን፣ የህዝቡንና የአገሪቱን ደህንነት መጠበቅ እንዲሆን ተስማሙ፡፡[17]

በዚያን ጊዜ እንዲህ የጀመረው የመከላከያ ተቋም *(ሀግ)* ሳይቋረጥ ቀጥሎ፣ አሁን ካለንበት ዘመን ደረሰ፡፡ መዋቅሩ እስከዛሬ ድረስም  በሁሉም አካባቢዎች አለ፡፡

### 4.1.3. የክልል አስተዳደራዊ ተቋም ታሪክ

ክልላዊ አስተዳደር በራሱ *ጉልጉባ* (መላው ቡርጂ)፣ *ራስ ገዝ*፣ *ቢያ*[18]፣ *ቦሄ* (ቀበሌ) እና *ኦላ* (ጉርብትና) *ወይም ገሬኤ* በሚባሉ በሌሎች የአስተዳደር ክፍሎች ይከፈላል፡፡ *ጉልጉባ* ከፍተኛው ክልላዊ አስተዳደር ሲሆን ዝቅተኛው ደግሞ *የኦላ* አስተዳደር ነው፡፡ *የጉልጉባ* አስተዳደር *በወማ*፣ የራስ ገዝ አስተዳደር ደግሞ *በዳይና* ይመራል፡፡ በዚህ የተነሳም *የወማ* አስተዳደር፣ *የዳይና* አስተዳደር እየተባሉ የሚጠሩበት አጋጣሚ አለ፡፡ ከፍ ተብሎ በተገለፀው መሰረት ከክልላዊ ተቋማት መካከል *የወማን* እና *የዳይናን* አስተዳደር ታሪኮችን ብቻ ቀጥለን እናቀርባለን፡፡

#### 4.1.3.1 የወማ አስተዳደር ታሪክ

በቡርጂ ባህላዊ *ሥርዓት* ውስጥ፣ በ*ወማ ማዕረግ* የሚጠሩ ሁለት ባህላዊ *መሪዎች* አሉ፡፡ አንደኛው መንፈሳዊ *ሥልጣን ያለው ወማ (ባለጋን)* ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ *ፖለቲካዊ ሥልጣን ያለው ወማ* ነው፡፡ *መንፈሳዊ ወማ መንፈሳዊ ተግባራትን ብቻ የሚያራምድ፣ ጋን* የሚባል ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል አድሮበታል ተብሎ የሚታመነው ሰው የሚጠራበት ማዕረግ ነው፡፡ በአጭሩ የእምነት ተቋሙን በበላይነት የሚመራ ሰው ነው *ወማ* የሚባለው፡፡ ይህ ሲባል ግን ሁሉም ባለጋኖች በዚህ ማዕረግ ይጠራሉ ማለት አይደለም፡፡ ቡርጂ ውስጥ ካሉት ባለጋኖች መካከል ወማ የሚባሉት *ሣጋናንካ ጋን* እና *ባንባልንካ ጋን* ብቻ ናቸው (ለተጨማሪ መረጃ ምዕራፍ አምስትን ተመልከት)፡፡ የፖለቲካ ወማ የሚባለው ደግሞ የህዝቡን ባህላዊ የፖለቲካ *ሥርዓት* በበላይነት የሚመራ፣ በመዋቅሩ ቁንጮ ላይ የተቀመጠ፣ በመንፈሳዊ ጉዳዮች ውስጥ የማይገባ ባህላዊ *መሪ* ነው፡፡ መጠሪያ ማዕረጋቸው ይመሳሰል እንጂ፣ ተግባራቸው ግን ለየቅል ነው፡፡ ስለ መንፈሣዊው *ወማ* በቦታው (በምዕራፍ 5 ላይ) ይነሣል፡፡ ከዚህ ቀጥሎም ሆነ በዚህ ምዕራፍ *ሥር ሙሉ ለሙሉ* የሚቀርበው ግን፣ *የፖለቲካውን ወማ* የሚመለከቱ ነጥቦች ብቻ ይሆናሉ፡፡

---

[17] ሙጎ ባቴ፣ ከብሔረሰቦች ምክር ቤት ባለሞያዎች በሚያዝያ 14 ቀን 1997 ዓ.ም ለቀረበላቸው የቃል መጠይቅ ከሰጡት ምላሽና በድምጽ ተቀርጾ በምክር ቤቱ  ከተቀመጠው መረጃ  የተወሰደ፡፡

[18] በቁሙ ‹‹ሀገር›› ማለት ሲሆን፣ በዚህ አገባቡ ግን፣  በሁለትና ከሁለት በላይ በሆኑ በቦሄ (በቀበሌ) አስተዳደሮች ጥምረት የሚመሰረት፣ የራሱ መሪና ወሰን ያለው የመኖሪያ አካባቢ የሚጠራበት ስም ነው፡፡

*ወማ* በቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካ ሥልጣን ቁንጮ ላይ የተቀመጠ፣ እንደ ንጉስ የሚቆጠር ባህላዊ መሪ ነው፡፡ የቡርጂ ህዝብ በ*ወማ* መተዳደር የጀመረው ከመቼ ጀምሮ እንደሆነ በእርግጠኛነት ለመናገር የሚያስችል ተጨባጭ መረጃ የለም፡፡ ይሁን እንጂ፣ ቡርጂዎች አሁን ካሉበት መጥተው ከሰፈሩ በኂላ ወይም እንደ መረጃ ሰጪዎቹ አባባል የምኒልክ ጦር አካባቢውን ከመቆጣጠሩ በፊት ጀምሮ መሆኑን ሁሉም ይስማሙበታል (አበበ፣ 28፤ ቱኬ፣ 35፣ 2002፤ ጮጎ፣ 1995)፡፡

የቡርጂ የመጀመሪያው *ወማ*፣ ከጎዳ ጎሳ የሚወለድ፣ *የጎዳ ወማ* ነው፡፡ የ*ወማ* አስተዳደር ታሪክም የሚጀምረው *ከጎዳ ወማ* እንደሆነ ብዙዎቹ ይስማማሉ[19]፡፡ ስለ *ጎዳ ወማ* አነሳስና አወዳደቅ የሚተርክ፣ በህዝቡ ዘንድ ተዘውትሮ የሚነገር አንድ አፈ-ታሪክ አለ፡፡ እንዲህ ይተረካል፡፡

> ከሲበን የመጣው አብዛኛው የቡርጂ ህዝብ እዚህ ቡርጂ ላይ ተቀመጠ፡፡ *ጎዳ* የሚባል ጎሳ ግን አልፎ ሄደ፡፡ ከቡርጂ አልፎ ጨንቻ ወደሚባለው አካባቢ ተሻገረ፡፡ ከዚያ ላይም ለብዙ ጊዜ ተቀመጠ፡፡ የጎሳው መሪም፣ የጎሳውን አባላት እየመራ ወደ ኂላው ተመልሶ፣ ቡርጂ ገብቶ ተቀመጠ፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኂላም፣ *የጎዳ ወማ*፣ የቡርጂን አገር ጠቅልሎ ወሰደ፡፡ ህዝቡንም ‹‹ከዛሬ ጀምሮ መሪያችሁ እኔ ነኝ›› አለ ፡፡ በዚህም የቡርጂ *ወማ* ሆኖ ቡርጂን በጠቅላላው መግዛት ጀመረ፡፡ አገዛዙ ግን በጭቆናና በጭካኔ የተሞላ፣ ሰብዕናን የሚነካ ነበር፡፡ የጎዳ ጎሳ አባል ያልሆነን ሰው *‹‹ምንድነህ?›› ቢሉት ‹‹አውሬ ነኝ››* ማለት አለበት፡፡ መልሰው *‹‹ምን ትመገባለህ?›› ያሉት* እንደሆነ መላሹም ‹‹አፈር›› ይላል፡፡ ‹‹ምንድነህ?›› ሲሉት ‹‹ሰው ነኝ››፣ ‹‹ምን ትበላለህ?›› ተብሎ ሲጠየቅ ‹‹እህል›› ያለ እንደሆነ አሳር ያገኘዋል፡፡ ጎዳዎች ቅጥቅጥ አድርገው ይደበድቡታል፡፡ የታዘዘውን ያልፈጸመ ይገረፋል፡፡
>
> በአንድ ወቅት *ወማው* ህዝቡን ሰበሰበ፡፡ ‹ብሁለቱም በኩል ፀጉር ካለው ቆዳ ለእግሬ ጫማ ሠርታችሁ አምጡልኝ›› ሲል አዘዘ፡፡ ህዝቡ በሁለቱም በኩል ፀጉር ያለውን ቆዳ ማፈላለግ ጀመረ፡፡ በአንድ በኩል እንጂ በሁለቱም በኩል ፀጉር ያበቀለ ቆዳ አጡ፡፡ ‹‹*አዋቂ*›› ዘንድ ሄዱ፡፡ ‹‹ወማው በሁለቱም በኩል ፀጉር ካለው ቆዳ ጫማ እንድንሰራለት አዘዘን፡፡ ግን ያን የመሰለ ቆዳ አጣን፡፡ ምን ይሻለናል?›› በማለት ምክር ጠየቁት፡፡ ‹‹አዋቂው›› ሰውም አሉቸው ‹‹የአህያ ጆሮ ቆርጣችሁ ጫማ ሥሩለት፡፡ የአህያ ጆሮ በሁለቱም በኩል ፀጉር አለው፡፡›› ህዝቡም እንደተባለው አደረገ፡፡ በዚህም ከቅጣት አመለጠ፡፡
>
> *ወማው* በሌላ ጊዜም እንዲሁ ህዝቡን ጠራ፡፡ ‹‹ለመኖሪያ የሚሆን አዲስ ቤት ያስፈልገኛል›› አለ፡፡ ‹‹ለዚህ ቤት የሚሆን ምሰሶ *ቃርቃዶ* ከሚባል እንጨት ቆርጣችሁ አምጡልኝ›› አለና አዘዘ፡፡ *ቃርቃዶ* ለምሰሶ ሊሆን የማይችል ሰነፍ እንጨት በመሆኑ ህዝቡ ተቸገረ፡፡ መላ ፍለጋም ከአዋቂ ዘንድ ሄዱ፡፡ *በወማው የታዘዙትን ነገሩት፡፡* እሱም የሚያደርጉትን በነገራቸው ጊዜ ተመልሰው *ከወማው* ዘንድ ቀረቡ፡፡ ‹‹ወማ ሆይ! ከነሀስ የተሰራ ምሳር ከአንተ ዘንድ ይኖራልን?›› በማለት ጠየቁት፡፡ ‹‹ሌላው ብረት ሁሉ *የቃርቃዶን* እንጨት መቁረጥ አልቻለም፡፡ ስለሆነም የነሃስ ምሳር ካለህ ስጠንና ምስሶውን ቆርጠንበት እናምጣው›› *አለና ህዝቡ ጠየቀው፡፡* ‹‹በምንም ቁረጡት፡፡ ብቻ

[19]በዚህ የማይስማማ አለ (አበበ፣ 2002፣ 18-21)፡፡ በአበበ እምነት፣ የቡርጂ *የወማ* አስተዳደር *ታሪክ* የሚጀምረው *ኣኮ ማኖዬ* በምትባል ሴት ነው፡ ፡ ከጎዳ *ወማ* በፊት *ኣኮ ማኖዬ* የምትባል ሴት ቡርጂን ታስተዳድር ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ አመራሩዋ በጭካኔና በጭቆና የተሞላ ነበር፡፡ አገዛዙዋም ሆነ ትዕዛዞቹዋ ገዝቅ ሲል ከሚተረከው ከጎዳ ወማ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ የሞተችውም ሆነ ከስልጣን የተወገደችው በህዝብ አመፅ ነው፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡፡ በአንድ ወቅት *ኣኮ ማኖዬ*፣ *ቃርቃዶ* ከሚባል እንጨት ምስሶ ቆርጠው ቤት እንዲሰሩላት ህዝቡን አዘዘች፡፡ *ቃርቃዶ* ለምስሶ ሊሆን የማይችል ደካማ እንጨት ነው፡፡ በመሆኑም ህዝቡ ተጨነቀ፡፡ ከአዋቂ ዘንድ ሄዶው ምክር ጠየቁ፡፡ አዋቂውም የሚያደርጉትን ነገራቸው፡፡ ተመልሰው *ኣኮ ማኖዬ* ዘንድ ቀረቡ፡፡ ‹‹ንግስት ሆይ! ምስሶውን አዘጋጅተናል፡፡ ነገር ግን የቱ ላይ እንደሚተከል አናውቅም፡፡ ስለሆነም መጥተው ያሳዩን›› አሉዋት፡፡ ለቤት መስሪያ ከተመረጠው ቦታ ምስሶው መቆም ያለበትን ቦታ ልታሳይ ከአደባባይ ወጣች፡፡ ህዝቡ በክብር ተቀበላት፡፡ ከአደባባዩ ላይ፣ ለክብሯ ሲባል በተዘጋጀላት ጊዜያዊ ማረፊያ ቦታ ላይ እንድትቀመጥ መሩዋት፡፡ ኣኮ ማኖዬ ከተዘጋጀላት መቀመጫ ላይ ቁጭ ከማለቷ፣ ከተማሰላት ጥልቅ ጉድጓድ ገባች፡፡ ህዝቡም አፈር መለሰባት፡፡ ከዚያው ቀበሩዋት፡፡ የኣኮ ማኖዬ ስልጣንም በዚህ መልክ ማብቃቱን ይተርካል፡፡ የጎዳ ወማ የመጣው ከዚህ በኂላ ነው በማለትም ይከራከራል ፡፡

ምስሶውን በአስቸኳይ አምጡት›› በማለት ንጉሱ አሰናበታቸው፡፡ ህዝቡ ተመልሶ መጣ፡፡ በአዋቂው በተነገራቸው መሰረት እንጨት ቆርጠው አመጡለት፡፡ ያዘጋጁትን እንጨት ይዘው ከንጉሱ ፊት ከቀረቡ በኋላ ‹‹ወማ ሆይ! ምስሶ ያልከው ይኸውልህ፡፡ ከሁሉም እንጨት ከሚበልጥ እንጨት ቆርጠን አመጣንልህ›› ብለው የጥጥ ግንድ (እንጨት) አሳዩት፡፡ ይህን ጊዜ ንጉሱ አላቸው፡፡ ‹‹*ያመጣችሁት እንጨት አላረካኝም፡፡ ስለሆነም ትቀጣላችሁ፡፡*›› ህዝቡም መልሶ ‹‹ወማ ሆይ! ቅጣቱስ እሺ ይሁን፤ እንቀጣለን፡፡ *ነገር ግን እንዴት አድርገህ እንደምትቀጣን ንገረን*›› አሉት፡፡ ‹‹እገርፋችኋለሁ፡፡ ለዚህ የሚሆን ዱላ ቆርጣችሁ አምጡልኝ›› አላቸው፡፡
ህዝቦቹ ወደ ቆላ ወረዱ፡፡ *ሹሙሌይ* ከሚባል ከሰነፍ እንጨት ለወማው ዱላ አዘጋጁ፡፡ *ዳዌ* ከሚባለው፣ ከጠንካራ እንጨት ደግሞ፣ ለራሳቸው ዱላ አዘጋጅተው ያዙ፡፡ ወደ ሰፈር ከተመለሱ በኋላ ለራሳቸው ያዘጋጁትን ዱላ ደበቁት፡፡ ለመገረፊያቸው ያዘጋጁትን ደግሞ ለወማው እና ለጎሳው አባላት አስረከቡ፡፡ በውሳኔው መሰረት *ጎዳዎች* ህዝቡን *መግረፍ* ያዙ፡፡ ይህን ጊዜ ህዝቡ ዱላውን ከደበቁበት እየመዘዙ ጎዳዎችን ያነክቱ ጀመር፡፡ ጎዳዎች አንድ ጎሳ ቢሆኑም ግን፣ በቁጥር እጅግ ብዙ ነበሩ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ህዝቡን መቋቋም ስላልቻሉ ሸሽት ጀመሩ፡፡ ህዝቡም እየተከተለ አሳደዳቸው፡፡ እያሳደዱዋቸው ከአገር አስወጡዋቸው፡፡ *ኮትሌን* [በአሁኑ፣ በቡርጂና በአማሮ ልዩ ወረዳዎች ወሰን ላይ የሚገኝ አካባቢ ነው] ከአሻገሯቸው በኋላ፣ *ዳግም ተመልሰው እንዳይመጡ*፣ ከ*ኮትሌ* ላይ ድንበር ተክለው ተመለሱ[20] ፡፡

የመጀመሪያው የቡርጂ *ወማ* ወደ ስልጣን የመጣው፣ መጥቶ ህዝቡን የገዛው፣ በኋላም ከሥልጣን የተወገደው በዚህ መልክ እንደሆነ ይተረካል[21]፡፡ የመጀመሪያው የቡርጂ *ወማም* የጎዳ *ወማ* ሆነ፡፡ ከጎዳ *ወማ* መባረር በኋላ ደግሞ ስልጣኑ *ጋሚዮ* በሚባል *ቦሄ* በሚኖሩ ቡርጂዎች እጅ ገባ፡፡ *የጋሚዮ* ቀበሌ ነዋሪዎችም ከመካከላቸው *ወማ* እያነገሡ፣ የቡርጂን ህዝብና አገር ማስተዳደር ጀመሩ[22] ፡፡

---

[20] ወርቁ (ማሻ)፣ (ከራለያ አካባቢ የመጡ) እና ስማቸው ያልተጠቀሰው አንድ ሌላ የምክር ቤት አባል፣ ለረዥም ጊዜ ተቋርጦ የቆየውን፣ የቡርጂን ባህላዊ አስተዳደር፣እንደገና ለማስጀመር በተጠራው ጉባኤ (ጉል ጉበይንካ ጎርሶማ) ላይ ከተናገሩት የተወሰደ፡፡

[21] የአንድ *መረጃ* አቀባይ (ቱኬ፣ 2002፣ 35-38) ትረካ ከዚህ ትንሽ ለየት ይላል፡፡ የሚለየው በአመፁ ምክንያትና በአመፀው ህዝብ ማንነት ላይ ነው፡፡ በእሱ አባባል፣ በጎዳ ወማ ላይ አምፆ ከሥልጣን ያባረረው ሁሉም የቡርጂ ህዝቦች አይደሉም፡፡ *ኣናቡራ፣ ያቢ፣ ካራማ፣ ቀዳደና ጋማዮ* የሚባሉ፣ የአምስት ጎሳ ህዝቦች ብቻ ናቸው፡፡ የአመጹ መነሻም ሌላ ነው፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡፡ ከላይ በተተረከው መልኩ በጎዳ *ወማ* ጭቆና ህዝቡ ተማረረ፡፡ ይህን የተመለከቱት የአምስቱ ጎሳ *መሪዎች*፣ ማለትም፣ ከአናቡራ - *ሀቡራ*፣ ከያቢ- *ጎና*፣ ከካራማ- *ያዮ*፣ ከቀዳዶ - *አንዱለ* እና ከጋማዮ ጎሳ ደግሞ *ሎሎ* በመሆን ተገናኝተው በጉዳዩ ላይ ተነጋገሩበት፡፡ ‹‹*እኛ ቀድመን ከዚህ የገባን እያለን፣ ጎዳዎች ከእኛ በኋላ መጥተው አገራችንን ወሰዱብን፡፡ አፈር እንድንበላ አደረጉን፡፡ ከሰው ተራ አወጡን፡፡ ምን ይሻለናል?*›› ብለው ተጠያየቁ፤ ተመካከሩ፡፡ በምክክሩም በወማውና በጎሳው ላይ ሊያሚፁባቸው፣ አምፀው ሊወግሯቸው፣ ወግረው ከሃገር ሊያስወጡዋቸው ተስማሙ፡፡ በዚያን ዘመን የጎዳ ጎሳ ያልሆነ ሰው ቀጥ ያለ ዱላ ይዞ እንዲንቀሳቀስ አይፈቀድለትም ነበር፡፡ ይዞ የተገኘ ዱላው ይነጠቅበትና ይገረፍበታል፡፡ በመሆኑም የአምስቱ ጎሳ መሪዎች ህዝባቸውን ሰብስበው እንዲህ አሉዋቸው፤ ‹‹ሂዱ! ሰገን (ቆላ) ውረዱ፡፡ ሹሙሌይ የሚባለውን (ሰነፍ) እንጨት ቆርጣችሁ ቀጥ ያለ ዱላ አዘጋጁ፡፡ *ዳዌ* ከሚባለው (እጅግ ጠንካራ የሆነ፣ ነገር ግን ጠማማ እንጂ ቀጥ ያለ ከማይገኝበት) እንጨት ደግሞ ለራሳችሁ ዱላ አዘጋጁና ደብቁት፡፡ ቀጥ ያለውን፣ ግን አቅመ-ቢሱን ዱላ ይዛችሁ ከመንደር ግቡ፡፡ ›› ህዝቡ እንደተባለው አደረገ፡፡ የአናቡራ ጎሳ *መሪ* የሆነው፣ *ሀቡራም* ህዝቡን ‹‹ከመንደር ስትደርሱ *ዎያ* የሚባለውን ባህላዊ ዘፈን ዝፈኑ፡፡ ያን ጊዜ ደግሞ እኔ የወማውን ሚስት ‹*አነግሳታለሁ*› ብዬ አዝላታለሁ፡፡ በሰበቡም ፀብ ይቀስቀስ›› አላቸው፡፡ ህዝቡ ከመንደር እንደደረሰ *መዝፈን* ጀመረ፡፡ *ሀቡራም* ‹‹*አነግሣታለሁ*›› በሚል የወማውን ሚስት አፈፍ አደረጋት፡፡ ይህን ጊዜ ‹‹*እንዴት ተደፈርን?*›› በሚል የጎዳ ጎሳ አባላት ከህዝቡ እጅ ዱላ እየቀሙ መልሰው ህዝቡን ይደበድቡት ጀመር፡፡ የአምስቱ ጎሳ ህዝብም ዱላቸውን ከደበቁበት እየመዘዙ፣ ከጎዳ ወማውና ከጎሣዎቹ ላይ መዓቱን አወረዱባቸው፡፡ እያሳደዷቸው ኮትሌ አሻገሯቸው፡፡ *ዳግም እንዳይመለሱም* ከኮትሌ ላይ ድንበር ተክለው ተመለሱ›› በማለት ይተርካል፡፡

[22] ይህን ‹‹*ሐሰት*›› በማለት የሚሞግት *መረጃ* አቀባይ (ቱኬ፣ 2002፣ 46) አለ፡፡ በመረጃ አቀባዩ እምነት ከጎዳ *ወማ* መባረር በኋላ *ወሚሶ* የገባው በአምስቱ ጎሳዎች እጅ *ነው*፡፡ *የመጀመሪያው* የወማነቱ ስልጣን የተሰጠውም፣ የኣናቡራ ጎሳ *መሪ* ለነበረው፣ ለሀቡራ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ስልጣኑ በአምስቱ ጎሳዎች እጅ ሲፈራረቅ ቆይቶ ተቋረጠ እንጂ፣ ከመነሻውም ከጋሚዎች እጅ አልገባም፡፡ በቡርጂ የወማ *ታሪክ ጋሚዮ* ለአንድ ጊዜ እንኳን ነግሶ አያውቅም

*ከጋሚዮ* ቀጥሎ *ወማ* በመሆን አገር የማስተዳደርን ስልጣን የወሰዱት፣ *የኪልቾ ቦሄ (ቀበሌ)* ነዋሪዎች ናቸው፡፡ የስልጣን ሽግግሩ የተደረገው ስርዓታዊ በሆነ መንገድ አይደለም፡፡ በሃይል ነው፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡፡

የጎዳ ወማ ከሥልጣን እንደተባረረ ህዝቡ የአስተዳደር *ሥርዓት* አበጀ፡፡ *ሥልጣኑንም ጋሚዮዎች* ተረከቡ፡፡ *ወማ* ሆነው ህዝቡን *መግዛት* ጀመሩ፡፡ ይህ የንግስና *(የወሚሶ)* ስርዓት ይካሄድ የነበረውም በዚያ አካባቢ በነበረ፣ *ወሚንታ ኡራ* (የንጉስ ተራራ) በሚባል ተራራ ላይ ነበር፡፡ በአንድ ወቅት ከዚያ ተራራ ላይ በዓል ተደረገ፡፡ በዓሉም፣ *ዳኦ የሚባለውን፣ የጋሚዮን* ሰው *ወማ* አድርጎ ለማንገስ ሲባል የተደረገ ነበረ፡፡ *ዳኦ* ሊነግስ፣ *ወማ* ሊሆን፣ አስፈላጊውን ስርዓት በሚፈፅምበት ሰዓት *የክሊቾ ቦሄ* ነዋሪ የሆኑ የተደራጁ ቡድኖች፣ ከስፍራው መጥተው ረብሻ አነሱ፡፡ ሽብር ፈጠሩ፡፡ *ሥርዓቱንና ታዳሚዎችን* በታተኗቸው፡፡ ንግስናውንም *(ወሚሶውንም) ከዳኦ* ነጥቀው ወሰዱበት (አደን፣ 2002፣ 42)፡፡ ወስደው የራሳቸው አደረጉት፡፡ በዚህም ስልጣኑ *ከኪልቾ* ነዋሪዎች እጅ ገባ፡፡ *ከኪልቾ* ነዋሪዎች መካከል በተለይ *ኣናቡራ፣ ያቢ፣ ቀዳደ፣ ካራማ* እና *ጋማዮ* የሚባሉ (አምስቱ) ጎሳዎች ስልጣኑን የራሳቸው አደረጉት፡፡ *ሥልጣኑንም* ተራ በተራ እየተቀባበሉ እስከ ጣሊያን ወረራ ድረስ ህዝቡንና አገሩን ገዙ፡፡ ይሁን እንጂ፣ እነርሱም በተራቸው በሌላ ሃይለኛ ተነጠቁ፡፡ ዳምጤ ዳዌ የሚባለው *የዋለያ ቦሄ* ሰው፣ *የወማነቱን* ስልጣን በሃይል ነጥቆ ወሰደባቸው፡፡

ይህ የሆነው ግን፣ በኢትዮጵያ የፊውዶ ቡርዧው ስርዓት ባቆጠቆጠበት፣ ጠንካራ መሰረት የነበራቸው ባህላዊ የፖለቲካና የእምነት ተቋማት፣ በማዕከላዊ *መንግስት* በተጨፈለቁበት ዘመን ውስጥ ነበረ፡፡ በመሆኑም፣ *ወሚሶ* በዳምጤ እጅ ከመግባቱ በፊት አሽልቦ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ፣ ዶንጬ ጮታ የተባለው የቡርጂ ሰው ከማዕከላዊ *መንግስት* የባላንበራስነትን ማዕረግ ደርቦ በመውሰድ በህዝቡና በአገሩ ላይ *ወማ* (ባላባት) ሆኖ ተሹሞ ስለነበረ ነው፡፡ ዳምጤ ዳዌ ከሁሉም አስቀድሞ የነጠቀው፣ የዶንጬን ባላንባራስነትን ነበር፡፡ ከዚያም በባላባትነቱ ላይ ባህላዊውን ስልጣን *(ወማነቱን)* ጨምሮ ‹‹*የቡርጂ ወማ እኔ ነኝ*›› አለ፡፡ በዚህም፣ ግራዝማች ዳምጤ ዳዌ የቡርጂ ባላባትና *የቡርጂ* ወማ[23] በመሆን ደርግ ስልጣን ላይ እስከወጣበት፣ እስከ 1967 ዓ.ም ድረስ አገለገለ፡፡ በመጨረሻም ‹‹*አድሃሪ ነው*›› ተብሎ ወህኒ

---

[23] በዚህ ሃሳብ የማይስማሙ አሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች ‹‹ዳምጤ የመንግስት ሹም (ባላባት) እንጂ የቡርጂ *ወማ* አይደለም፣ ወይም አልነበረም›› ይላሉ፡፡ በዚህም ስለ ቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት፣ በተለይ ስለ *ወማ* ስርዓት ሲነሳ፣ እነዚህ ወገኖች የዳምጤን ስም አይጠሩም፡፡ በወማዎች ዝርዝር ውስጥም አያስገቡትም፡፡ የቡርጂ የወማ ስርዓት የተቋረጠው ከጣሊያን ወረራ ጀምሮ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ በእነዚህ ወገኖች እምነት የቡርጂ የመጨረሻው *ወማ* የነበረው ኡራጎ ጩዶ የሚባል የጋማዮ ጎሳ ሰው ነው፡፡ በቡርጂ የወማ ታሪክ ወሚሶ የተቋረጠው በእሱ ነው፡፡

ተወረወረ፡፡ ወህኒ በተወረወረበትም ለዘለአለሙ አሸለበ፡፡ ሞተ፡፡ የእሱ ሞትም ለቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር ተቋማት በተለይም፣ *ለወሚሶ* እና *ለዳይኖማ ሥ*ርዓት ማክተሚያ ሆነ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስርዓቱ ለሃያ ሰባት ዓመታት አልቀጠለም፡፡ ተቋርጦ ቆየ፡፡ ዛሬም ቢሆን *ወሚሶ* የለም፡፡ *ዳይኖማ* ግን አንሰራርቷል፡፡

#### 4.1.3.2 የዳይና አስተዳደር ታሪክ

*የዳይና* አስተዳደር *ኦወማ* ቀጥሎ የተዋቀረና በሁለተኛው የሥልጣን እርከን ላይ ያለ ከፍተኛ አስተዳደራዊ ተቋም ነው፡፡ በቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት ውስጥ ተጠሪነታቸው ለአካባቢው ጎርሶማ (ህዝባዊ ሸንጎ) የሆኑ ሶስት ዓይነት *ዳይናዎች* (*የዳይና* አስተዳደሮች) አሉ፡፡ አንደኛው በቡርጂ ሰሜናዊ ጫፍ፣ በአማሮና በቡርጂ ድንበር አካባቢ፣ *በሐላሜና በናዳሌ ቦሄዎች* ውስጥ በሚኖሩ፣ *በኮይሬቴ* ቋንቋ ተናጋሪ ቡርጂዎች ዘንድ የሚተገበረውና በተለምዶ *ሸይሼንታ ዳይና የሚባለው ነው፡፡* ሁለተኛው ከስምንቱ የቡርጂ *የቢያ* አስተዳደሮች መካከል በአምስቱ *ቢያዎች* (በግምት ከመቶ 80 እጅ በሚሆኑ ህዝቦች) ዘንድ የሚተገበረው *ዳይና* ሲሆን፣ በቡርጂኛ *ጋሪንታ ዳይና* ይባላል፡፡ ‹‹የብዙሃኑ *ዳይና*›› እንደማለት ነው፡፡ ሶስተኛው *ላድሼ፣ ዋለይ* እና *ጋራ* (garra) በሚባሉ በሶስት *የቦሄ* (ወይም በአንድ *የቢያ)* ህዝቦች ዘንድ ተግባራዊ የሚደረገው *ዳይና* ሲሆን በተለምዶ *ላድሼንታ*[24] *ዳይና* ወይም *ዋለይንታ ዳይና* በመባል ይጠራል፡፡ እነዚህ ሶስቱ *የዳይና* አስተዳደሮች እንዴትና በምን ምክንያት ሊመሰረቱ እንደቻሉ የሚያስረዳ የየራሳቸው *ታሪክ*ና ምክንያት አላቸው፡፡ *ታሪካ*ቸውና ምክንያታቸውም በማህበረሰቡ ዘንድ በስፋት በሚነገረው *አፈ -ታሪክ* ላይ የተ መሰረተ ሲሆን ፣ እን ደሚከተለው ተ ራ በተ ራ ይቀርባል ፡፡ *ለሸይሼንታ ዳይና* አስተዳደር መመስረት ምክንያት ስለሆነው አጋጣሚ ከሚያወሳው *አፈታሪክ* እንጀምር፡፡ *ነገሩ* እንዲህ *ነው*፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው *የጎዳ ወማ* ጭቆናው በዛና ህዝቡ አመፀበት፡፡ አምጸው ከስልጣን አባረሩት፡፡ ከአገር አስወጡት፡፡ ወደ አጎራባቹ፣ ወደ አማሮ ልዩ ወረዳ አሻገሩዋቸው፡፡ *ኮትሌ*

---

24 እኔ ግን፣ ለአጠራር ወይም ለአፃፃፍ እንዲመች በሚል *ላዋጋንታ* ዳይና በሚል ስም (ምህፃረ ቃል) መጥራቱን መርጫለሁ፡፡ ስሙ የተመሰረተውም ላድሼ፣ ዋለይ፣ ጋራ የሚለውን፣ የሶስቱን ቦሄዎች መነሻ ፊደሎችን ወስጄ በማገጣጠም ወይም ስሞችን በማሳጠር ነው፡፡ በዚህም ላ , ላድሼ፣ ዋ , ዋለይ፣ ጋ , ጋራ ማለት ሲሆን -ንታ ደግሞ ‹‹የ›› የሚለውን የአማርኛውን ዘርፍ አያያዥ ቅጥያን ይወክላል፡፡ ላዋጋንታ ዳይና ማለት በአጭሩ የላድሼ፣ የዋለይና የጋራ ዳይና ማለት ነው፡፡ በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ውስጥ ላዋጋንታ ዳይና ሲል የላድሼ፣ የዋለይና የጋራ ዳይና ማለት እንደሆነ ልብ ይሏል፡፡

ከሚባል ቦታ በደረሱ ጊዜም ‹‹*ወማ ሆይ!* ከዛሬ ጀምሮ የአንተና የእኛ ወሰን ይህ ይሁን›› ብለው ከስፍራው ላይ ሶስት ድንጋይ በመትከል ድንበር አበጁ[25]፡፡

ቡርጂዎች የጎዳ ወማ ዳግም እንዳይመለስ በሚል *ኮትሌ* ላይ ድንበር *ያብጁ* እንጂ ተመልሶ ስላለመምጣቱ ግን እርግጠኞች አልነበሩም፡፡ ‹‹ጊዜንና አጋጣሚን ጠብቆ አንድ ቀን ተመልሶ ይመጣ ይሆናል›› የሚል ጥርጣሬ አደረባቸው፡፡ ስጋት ገባቸው፡፡ ለዚህም መላ ዘየዱ፡፡ ከዚያ ከድንበሩ አካባቢ ከሚኖሩ *የኮይሬ* ጎሳዎች መካከል ‹‹ሌሎችን ጎሳዎች ያስገኙ ናቸው›› ተብለው የሚታመኑ ቀደምት ቤተሰቦችን (ጎሳዎችን) ማፈላለግ ጀመሩ፡፡ በዚህም *ጉሌይሽ* የሚባለውን ጎሳ፣ *ከጉሌይሽ* ጎሳ መካከል ደግሞ ጫሞ በሚባል ሰው የሚመራውን ቤተሰብ አገኙ፡፡ የቡርጂ ህዝብም ከዚያ ቤተሰብ (ጎሳ) *መሪ* (ከጫሞ) ጋር ‹‹አንተ በትውልድህ (በዘርህ) ኮይሬ ነህ፡፡ የእኛ (የቡርጂ) ወሰን እስከ የት ድረስ እንደሆነ ታውቃለህ፡፡ ወሰናችን ይኸውልህ፡፡ ከዚህ አንስቶ ወደ ላይ ያለውን ክልላችንንና ህዝባችንን እንድታስተዳድር መርጠንሃል፡፡ ከዛሬ ጀምረን *ዳይና* አድርገን ሾመንሃል፡፡ *ማዕረግህም ሸይሼንታ ዳይና* ይሆናል፡፡ አካባቢው *በዳይኖማ ሥርዓት* ይተዳደር፡፡ እኛ በየዓመቱ በምናካህደው *በወሚሶ* (በንግስና) ስርዓት ላይ *የቢያ* አስተዳደሩን ወክለህ፣ *ለኤሳ* መትከያ የሚሆን ቀርከሃ ይዘህ ትገኛለህ፡፡ በዚህም ለአንድ *የቢያ* አስተዳደር የሚገቡ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞችን ታገኛለህ›› የሚል ውል ገባ፡፡ ስምምነት አደረገ፡፡ እንዲህ አድርጎ ህዝቡ ተመለሰ፡፡ *ያ የጉሌይሽ* ጎሳም፣ ከጎሳውም የዳይና ጫሞ ቤተሰብ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በአካባቢው ህዝቦች ላይ ታላቅ *መሪ* ሆኖ ማስተዳደር ጀመረ፡፡ *የሸይሼንታ ዳይና* ስልጣንም በዚህ አጋጣሚና መንገድ የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደር አካል ሆኖ ተዋቀረ [26]፡፡

‹‹*ሸይሼ*›› *ድንበር፣ ወሰን፣ ይዞታ ማለት ነው፡፡ ሸይሼንታ ዳይና ማለት የድንበር፣ የወሰን፣ የይዞታ ዳይና* ማለት ነው፡፡ ወይም *የድንበር ጠባቂ፣ የይዞታ አስከባሪ ባለስልጣን* ማለትም ይቻላል፡፡ ለስልጣኑ መነሻ ምክንያቱ ደግሞ ስጋት፣ ጥርጣሬ ነው፡፡ ‹‹የጎዳ *ወማ* ዳግም ይመለሳል:: ተመልሶ እንደተለመደው አሰቃይቶ ይገዛናል›› የሚል ነው ስጋቱ፡፡ ለዚህም ቡርጂዎች *ማሰሪያ* አበጁ፡፡ ጠንካራውን፣ በአካባቢው ህዝቦች ዘንድ የሚከበረውንና የማይደፈረውን ቤተሰብ (ጎሳ) *ዳይና* አድርገው ሾሙ፡፡ ሹመትና ግዛት ጀባ ብለው ከድንበሩ ላይ ተከሉት፡፡ ዘብ አቆሙት፡፡ *የሸይሼንታ ዳይና* አስተዳደርም በዚህ መልክ ጀመረ፡፡ እኒያ ቤተሰቦች

---

25 ያን ጊዜ የተተከሉ ድንጋዮች ዛሬም ድረስ እንዳሉ ይነገራል፡፡ ድንጋዮቹ በቁጥር ሶስት ናቸው፡፡ ከዛ የተወሰዱትም ቃሌንካ ላግ ከሚባለው ሥፍራ እንደሆነ ይነገራል፡፡ በድሮ ጊዜ በየዓመቱ በዚህ ሥፍራ ላይ፣ የወማ ረዳት የሆነው፣ ጋና እና ሼይሼንታ ዳይናው ወይም ተወካዩ በተገኙበት፣ በዓል ተደርጎ እንስሳት ይታረዱበት ነበር፡፡ በድንጋዮቹ ላይም የእንስሳው ደም ይረጭባቸዋል፡፡ አጥንቶች ይጣልባቸዋል፡፡ ደም መርጨቱ ሒጣኖ የሚባለውን እምነታዊ ሥርዐት ለመፈፀም ሲባል ነው፡፡ አጥንቶቹ ለምን እንደሚጣሉባቸው ግን ለማወቅ አለቻልኩም፡፡

26 ቱኬ (2002፣ 35-38) ለአቀረብኩላቸው የቃል መጠይቅ ከሰጡኝ ምላሽ ውስጥ የተወሰደና ተቀናብሮ የቀረበ፡፡

ዛሬም ድረስ ከዚያው አሉ፡፡ ስልጣናቸውም አብሮአቸው አለ፡፡ *ሥልጣኑ* በዘር *ሀረግ* ከአባት ወደ ልጅ *የሚተላለፍ* ስለሆነ *ማንም* አይወስድባቸውም፡፡

*ሁለተኛው ዓይነት የዳይና* አስተዳደር *ጋሪንታ ዳይና* ይባላል፡፡ *የብዙሃን ሥልጣን* እንደ *ማለት* ነው፡፡ *የብዙሃን ሥልጣን መ*ባሉም ቡርጂ ውስጥ ካሉት ስምንት *የቢያ* አስተዳደሮች መካከል አምስቱን ይዞ የተዋቀረ አስተዳደራዊ ተቋም፣ አምስቱ *የቢያ* አስተዳደሮች ተራ በተራ የሚቀባበሉት ስልጣን በመሆኑ ነው፡፡ እንደ *ሺይሼንታ ዳይና* በአንድ ቤተሰብ የተያዘ ስልጣን አይደለም፡፡ ከቡርጂ ጠቅላላ ህዝብ በግምት ሲሶውን የሚያስተዳድር *ታላቅ መሪ* ነው *-ጋሪንታ ዳይና፡፡ ጋሪንታ ዳይና* በድሮ ጊዜ *ከወማ* ጋር የሚስተካከል፣ እኩል እንደሆነ ተደርጎ የሚታይ ስልጣን እንደነበረ ይነገራል (*Amborn and kellner,1999*)፡፡ *ለጋሪንታ ዳይና መመስረት ምክንያቱ* በዚያን ወቅት የነበረው ብልሹ *የወማ* አስተዳደር *መሆኑን* ከአፊ *ታሪኩ መረዳት* ይቻላል፡፡ እንዲህ ይተረካል፡፡

> ቡርጂዎች በወሚሶ *ሥርዓት መተዳደር* እንደጀመሩ፣ በተለይ ሀቡራ[27] ወማ ሆኖ እንደተሰየመ ወሚሶ *መልኩን* ለውጦ ዘርፎ የመብላት፣ የመጠጣት *ሥርዓት* ሆነና አረፈው፡፡ የሚዘረፈው ደግሞ የቡርጂ ህዝብ ሀብት ነው፡፡ የወማው ‹‹ወታደሮች›› ከአንዱ መንደር ገብተው ያገኙትን ቀምተው፣ በሬ ከሆነ አርደው ይበላሉ፡፡ ጎተራ ከፍተው ያገኙትን ገልብጠው ይወስዳሉ፡፡ ያሻቸውን ያደርጋሉ፡፡ ከልካይ አልነበራቸውም፡፡ ከህዝቡ ዘርፈው ለወማው ይወስዱለታል፡፡
> *ወማው* እንዲህ እየዘረፈ በሚገዛበት ወቅት አንድ ሰው ጋሻራ በሚባል አካባቢ ተወለደ፡፡ ስሙም *ዲርቦ* ይባላል፡፡ *ዲርቦ ሱቡሮ ከሚባል ሰፍራ፣* ቤት ሰርቶ ይኖር ነበረ፡፡ ወማው በሚሰራው ክፉ ስራም ይናደድ ነበር፡፡ ተናዶ ብቻ አልተወም፡፡ የወማው ‹‹ወታደሮች›› ለዘረፋ ማለፋቸውን በሰማ በአንዱ ቀን እሱም ጭፍሮቹን አስከትሎ ወጣ፡፡ የወማው ‹‹ወታደሮች›› ለወትሮአቸው ከህዝቡ የዘረፉትን ጭነው ከሚመለሱበት መንገድ ላይ አድፍጦ ጠበቃቸው፡፡ ሲያገኛቸውም የጫኑትን አንድ ሳያስቀር ወሰደባቸው፡፡ ሠራዊቱንም ‹‹ጌታችሁ ይህን ሲሰማ ‹ይህን ያደረገው ማነው?› ብሎ በጠየቃችሁ ጊዜ ‹የጋሻራው ዲርቦ ነው› ብላችሁ ንገሩት›› በማለት ዘርፎአቸውና ገርፎአቸው ባዶ እጃቸውን ሰደዳቸው፡፡ ከመንደር በደረሱ ጊዜም ወማው ‹‹የት አለ ያመጣችሁት ነገር? ባዶ እጃችሁን የተመለሳችሁትስ ለምንድነው?›› በማለት ጠየቃቸው፡፡ ‹‹*ሱቡሮ* ላይ ቤት ሰርቶ የሚኖር፣ አንድ ጉልበተኛ ቀማብን›› አሉት፡፡ ወማውም ‹‹እንዲህ ዓይነት የድፍረት ስራ የሰራው ሰው ማነው?›› ባላቸው ጊዜ ‹‹*ዲርቦ* ነው፤ የጋሻራ ሰው›› በማለት ነገሩት፡፡
> በሌላ ጊዜም ወማው ዘርፈው እንዲያመጡለት የሰራዊቱን ቁጥር በእጥፍ ጨምሮ ቢልክም፣ ዲርቦ መልሶ መዝረፉን አልተው አለ፡፡ ይህን የተመለከተው ወማም ረዳቶቹን፡፡ ‹‹አብረን የምንማከረው ነገር ስላለ፣ ለአንድ አፍታ እኔ ዘንድ ደረስ በል፡፡ እኔ ዘንድ እንድትመጣ ይሁን›› የሚል መልዕክት አስይዞ ከዲርቦ ዘንድ ላካቸው፡፡ መልዕክቱ የደረሰው ዲርቦም ‹‹ይህ ሰው የሚጠራኝ ሊገድለኝ እንጂ ለበጎ አይደለም፡፡›› በማለት ሳይሄድ ቀረ፡፡ ወማው ግን ‹‹*አንድ አፍታ እኔ ዘንድ ብቅ በል*›› ማለቱን አልተወም፡፡ በመጨረሻም ዲርቦ፣ ጭፍሮቹን ሰብስቦ ‹‹*ወደ ጠራኝ ሰውዬ ዘንድ ለመሄድ* ወስኛለሁ፡፡ ለክፉም ለደጉም፣ በቅርብ ርቀት ሆናችሁ ጀርባዬን ጠብቁ›› ብሎ፣ ጥቂት ሰዎችን ብቻ አስከትሎ፣ ከወማው ዘንድ ወረደ፡፡ ከቤቱ እንደደረሰም፣ ወማው

[27] ቡርጂዎች ባህላዊ *መሪዎቻቸው* ወደ *ሥልጣን የሚመጡበትን ሥርዓት* (የባሻ *ሥርዓት*) በአዲስ *መልክ* አዋቅረው፣ *ሥርዓት* አበጅተው፣ *መተዳደሪያ* ደንብ ቀርፀው *መተዳደር* እንደጀመሩ *ለመጀመሪያ* ጊዜ የሰየሙት ወማ *መጠሪያ* ስም ነው፡፡ (ቀደም ስል በስም *ያልተጠቀሰው*፣ የጎዳ ወማ ግን፣ ይህ የባሻ *ሥርዓት* ከመዋቀሩ በፊት፣ ማለትም ቡርጂዎች ‹‹ወማ›› በሚል *ማዕረግ* በሚጠራ *መሪና ሥርዓት መተዳደር* እንደጀመሩ የቡርጂ *የመጀመሪያ* ወማ የሆነው ሰው የሚጠራበት ስም መሆኑን፣ እንዲሁም ‹‹ጊኑ›› ደግሞ በቡርጂ የጎሣ አስተዳደር *ታሪክ* ውስጥ (የወማ አስተዳደር ሣይመሰረት በፊት ማለት ነው) በሁሉም የቡርጂ ጎሣዎች ላይ *መንፈሳዊ መሪ* ሆኖ ለገዛ ለአንድ ጎሣ የተሰጠ *መጠሪያ መሆኑን* ልብ ይሏል)

> ከቤቱ ቦርዴ አስጠምቆ፣ ከደጁ ኮርማ በሬ አስሮና ደግሶ ሲጠባበቀው አገኘ፡፡ በክብር ተቀብሎት ከቤቱ አስገባው፡፡ ቁርበት አስነጥፎለት ከጎኑ አስቀመጠው፡፡ ቁርበት ላይ ወጥቶ እንደተቀመጠ ቦርዴ በቅል ቀረበለት፡፡ ዲርቦ ግን ይህን ሽር ጉድ ለመልካም እንዳልሆነ ገምቷል፡፡ ‹‹እንዲህ አድርጎ፣ አብልቶኝ፣ አጠጥቶኝ ሊገድለኝ ነው›› ብሎ ደምድሞ ቦርዴውን መጠጣት ጀመረ፡፡ በመሀሉ፣ ወማውና ዲርቦ ተያይዘው ወደ ውጪ ወጡ፡፡ ከኮርማው በሬ ዘንድ እንደደረሱ ወማው ‹‹*በል በሬውን ባርከው*›› ብሎ ካራውን ለዲርቦ አቀበለው፡፡ ዲርቦ አላመነም፡፡ ‹‹ይህ እንዴት ይሆናል? አንተ፣ ወማው እያለህ እኔ በሬውን ልባርከው አይገባኝም›› በማለት ዲርቦ ተከራከረ፡፡ ወማውም እንዲህ አለው ‹‹ከዛሬ ጀምሮ አንተ *ዳይና* ነህ፡፡ እኔ ደግሞ *ወማ* ነኝ፡፡ እኔ *ወማ* ሆኜ ከዚህ ያለውን ህዝብ አስተዳድራለሁ፡፡ አንተ ደግሞ *ጋሪንታ ዳይና* ሆነህ ከላይ፣ ከደጋው አካባቢ ያለውን ህዝብና አገር እንድትገዛ፣ እንድታስተዳድር ሾሜሃለሁ፡፡ ለሚፈልጉትም ያሻህን ስልጣን ስጥ፡፡ ሙሉ *ሥ*ልጣን ሰጥቼሃለሁ፡፡ ከአሁን በኋላ ሁለታችንም የቡርጂን ሀገርና ህዝብ በጋራ እናስተዳድራለን፡፡›› በዚህም ዲርቦ በአምስት ክልሎች ላይ ገዢ ሆኖ ማስተዳደር ጀመረ፡፡ እሱም በተራው በእያንዳንዱ *ቢያ እና ቦሄ* ላይ አስተዳዳሪዎችን መሾም ጀመረ፡፡ የ*ማሻ*ትን ስልጣን እየሰጠ፣ በ*ማሻ* እንዲተዳደሩ አደረገ፡፡ ይህም ለጋሪንታ ዳይና (*ለዳይኖማ)* እና *ለማሾማ ሥ*ርዓት መጀመር ምክንያት ሆነ፡፡[28]

ሶስተኛው ዓይነት *የዳይና* አስተዳደር *ላዋጋንካ ዳይና* ይባላል፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተው *ላዋጋንካ ዳይና ላድሼ፣ ዋለይና ጋራ* (garra) በሚባሉ፣ በሶስት *የቦሄ* አስተዳደሮች ወይም በእነርሱ ጥምረት በሚመሰረተው *ላዋጋንታ ቢያ* ውስጥ ተግባራዊ የሚደረግ ባህላዊ የአስተዳደር *ሥ*ርዓት ወይም *ሥ*ልጣን ነው፡፡ እንደሌሎቹ የቡርጂ ህዝቦች ሁሉ፣ *የላዋጋ ቦሄ ነዋሪዎች*ም ቀደም ብለው በአንድ *ወማና በጋሪንታ ዳይና* አስተዳደር *ሥ*ር ይተዳደሩ፣ *በባሻ ሥ*ርዓት (ስለ ባሻ *ሥ*ርዓት ምንነት ክፍል 4.3.4 ተመልከት) ይካፈሉ ነበር፡፡ ኋላም የራሳቸውን የራስ ገዝ አስተዳደር መስርተው፣ የራሳቸውን የፖለቲካ *ሥ*ርዓት ዘርግተው፣ በራሳቸው መሪዎች፣ በራሳቸው የአስተዳደር *ሥ*ርዓት መተዳደር ጀመሩ፡፡ ለዚህ እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው ደግሞ አንድ የታሪክ አጋጣሚ እንደሆነ በቡርጂ አፈታሪክ እንዲህ ይተረካል፡፡

> እኛ ላድሼዎች እስከ ዛሬ ልማድ አድርገን የቆየነው ነገር አለ፡፡ ወይም ዳይናነትን ከቤታችን ለመውሰድ የተገደድንበት ምክንያት አለ፡፡ አንድ፣ ስሙ አይላ ማንቃ የሚባል ሰው በእኛ ሀገር ነበር፡፡ ዳይናነት ድሮ የሚወሰደው እታች ቡርጂ ተክዶ ነበር፡፡ በድሮ ጊዜ *ባሻ* ከአንዱ ወደ ሌላው ሰው እንዲህ እንደዛሬው በቶሎ አይዛወርም፡፡ *ሥ*ልጣኑ ወደ ሌላው ሰው እስካልተዛወረ ወይም ተላልፎ እስካልተሰጠ ድረስ በየዓመቱ ለወማው ጊደር ይሰጣል - ዳይናው ማለት ነው፡፡ በዚያ ሰውዬ ላይ የዳይናነት *ሥ*ልጣን ለሰባት ዓመት ቆዬ፡፡ በዚህ ዘመን ሁሉ ከወማው አጠገብ ለአንድ ቀን እንኳን አይታጣም፡፡ ከቡርጂ ወማ አጠገብ ንቅንቅ አይልም፡፡ ለእርሱ የሚያርስ፣ የሚያርም ሰው የለም፡፡ ነገር ግን በዓመት በዓመቱ ለወማው ጊደር ይሰጣል፡፡ በሰባት ዓመት ሰባት ጊደር አውጥቶ ለወማው ሰጠ፡፡ በዚያን ዘመን እንዲህ በየዓመቱ ጊደር ለወማው መስጠት ባለመቻሉ ምክንያት ተሸጦ ባሪያ የሆነ ቤተሰብ ሁሉ በእኛ ሀገር ውስጥ አለ፡፡...በዚህ የተነሳ አይላ ማንቃ ምሎ ወደ ቤቱ መጣ፡፡ ምሎ እንደመጣ በመጀመሪያ የላድሼን የባሻ ቤተሰቦችን ወስዶ እዚያ፣ በስተግራ በኩል፣ ከገደሉ ላይ አዛወራቸው፡፡ ከገደሉ ውስጥ ከአዛወራቸው በኋላ *‹‹ካዮ ቡርጄንኮ ማራ ላም ኮሌይ ወቾ ቃሎ››* (ከዛሬ ጀምሮ ከቡርጄ ወማ ዘንድ የሚሄድ ሰው ጥቁር ውሻ ይውለድ) ብሎ ማለ፡፡ የቡርጄ ወማ የራሱን ወታደሮች (ናና) ይዞ ወጣ፡፡ እሱ ድሮ ድሮ ወደ ገደሉ ተዛውሯል፡፡...ዋጩ (ውቃቢው) ደመና አምጥቶ ጋረደበት፡፡ ማየት ተሣነው፡፡ ማግኘት

---

[28] ጫሜ (2002፣ 16 -19)፡፡

> አልቻለም፡፡ ትቶ ተመለሰ፡፡...ልክ እንዲህ ጎርሶማ ወጣ፡፡ ለብዙ ጊዜ ተቀመጠ፡፡ ከስምንቱ ቢያ ሰባቱ ተቀምጦ ‹‹ስምንተኛውን ቢያ፣ ላድሼን ከእኛ ጋር እንዳይቀመጥ ምን ከለከለው?›› አሉ፡፡ ቦታው እዚሁ *ሻቻ* ነው አሉ፡፡ እናም ዳይናው ተጠራ፡፡ ሲጠራ የራሱን *ሉብ* (ወታደር)፣ የራሱን ጃልዓባና የራሱን ማሻ አስከትሎ ወዲህ ወደ (ጎርሶማው) ጉባኤው መጣ፡፡ ደርሶ ፈንጠር ብሎ ተቀመጠ፡፡ ለምን ብሉ፣ በዚያን ዘመን ሰውን አንቆ መግደል ነበረና ነው፡፡ ‹‹እኔን የጠሩኝ አንቀው ልገድሉኝ ነው፡፡ እነዚህ ሰባቱ *ቢያዎች* የጠሩኝ ለቡርጂ ወማ ሰጥተው ልያሳንቁኝ ነው›› በማለት ነው ከነረዳቶቹ ፈንጠር ብሎ ለብቻው የተቀመጠው፡፡ ‹‹ዳይና ከእኛ ተለይተህ ለብቻህ የምትቀመጠው ለምንድነው?›› ብለው ጠየቁት፡፡ ‹‹ፈርቼ ነው››፤ ‹‹እንዳትመጣ የከለከለህስ ነገር ምንድርነው?›› ‹‹የቡርጂ ወማ እንዲህ፣ እንዲህ አድርጎ ተጫወተብኝ፡፡ እንዲህ በመሆኑ የተነሳ ‹‹እኔ ከዛሬ ወዲያ ወደ ጎርሶማም አልሄድም፡፡ ከወማው ዘንድም አልሄድም ብዬ ስለማልኩ ነው ያልመጣሁት›› አላቸው፡፡ የዚያን ቀን ነው እንግዲህ እንዲህ ያሉት- ሰባቱ ቢያዎች ማለት ነው፡፡ ‹‹እንግዲህ በመሃላህ ጽና፡፡ ወደ ታች (ወደ ወማው) አትሂድ፡፡ *ሥልጣኑንም* ከቤታችሁ ውሰዱ፡፡ ላድሼ የዳይናነትን *ሥልጣን* ከቤቱ ይውሰድ፡፡›› ያን ጊዜ እንዲህ በተባለው መሰረት ነው እኛ ከእራሳችን ኡቱባ [ከቤታችን] *ሥልጣኑን* የምንወስደው፡፡[29]

በዚህ *መልክ የጀመሩት ሶስቱ የዳይና* አስተዳደር *ሥርዓቶች* ሳይቋረጡ ለበርካታ ዓመታት ዘለቁ፡፡ *ሽይሼንታ ዳይናነት* በዘር ሐረግ የሚሰጥ ስልጣን ስለሆነ ከአባት ወደ ልጅ ሲተላለፍ ቆየ፡፡ እስከ ዛሬም ሳይቋረጥ ቀጠለ፡፡ *ላዋጋንታ ዳይናነትም* እንዲሁ አንዴም ሣይሰናከል ቀጠለ፡፡ ዛሬም ድረስ እንደነበረ አለ፡፡ *የጋሪንታ ዳይና* አስተዳደርና *ሥ*ልጣን ግን በአምስት *የቢያ* ህዝቦች ዘንድ ለበርካታ ዓመታት ተግባራዊ ሲሆን ከቆየ በኋላ የዳምጤ ዳዌን ሞት ተከትሎ ተቋረጠ፡፡ ለምን? ቢባል *ዳይናነትን* የሚሰጥ አካል ስለጠፋ ነው፡፡ በቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር ደንብ መሰረት፣ ለአንድ ሰው *የጋሪንታ ዳይናነትን* ስልጣን በዋናነት የሚሰጠው (መስጠት የሚችለው) *ወማው* ነው፡፡ አሁን ግን *ወማ* የለም፡፡ የመጨረሻው የቡርጂ ‹‹*ወማ*›› ወይም ባላባት የነበረው ግራዝማች ዳምጤ፣ በ1967 ዓ.ም ሞተ፡፡ ከእሱ በኋላ ቡርጂ ውስጥ *ወማ* ሆኖ የተሰየመ ሰው አልነበረም፡፡ *ወማ* ከሌለ ደግሞ *ጋሪንታ ዳይና* አይኖርም፡፡ በዚህ የተነሳ *ጋሪንታ ዳይኖማ ከወሚሶ ጋር* እኩል ተቋርጦ እስከ 1995 ዓ.ም ድረስ ቆየ፡፡ ከሀያ ሰባት ዓመት በኋላ ግን ስርዓቱ እንዲቀጥል ተደርጓል (ዝርዝሩን በክፍል 4.3 ላይ ተመልከት)፡፡ *የማሻም* ሆነ *የጃልዓባ ሥ*ልጣንና ተግባር ግን አንዴም አልተቋረጠም፡፡ ዛሬም ድረስ አለ፡፡

## 4.2 የባህላዊ አስተዳደር ተቋማት መዋቅርና ለመዋቅሩ መነሻ የሆኑ ምክንያቶችና አጋጣሚዎች

በዚህ ክፍል ሁለት አንኳር ነጥቦች ይነሳሉ፡፡ የቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር ተቋማት ስንት እንደሆኑ፣ እንዴት እንደሚዋቀሩ በስዕልና በገለፃ ማሣየት ቅድሚያውን ይይዛል፡፡ በመቀጠልም፣

---

[29] ለበርካታ ዓመታት ተቋርጦ የቆየውን የቡርጂን የዳይኖማን ሥርዓት በአዲስ መልክ ለማስጀመር ሲባል በተካሄደው *በ‹‹ጉልጉቤይንካ ጎርሶማ››* ላይ የወቅቱ *የላዋጋ ዳይና* የሆኑትና በስም ያልተጠቀሱት፣ አንድ ሹም በጎርሶማው ላይ ከተናገሩት ሀሳብ የተውሰደ ነው፡፡

እነዚህ አስተ ዳደራዊ ተ ቋማት እንዲህ ሆነ ው ለመዋቀራቸው መነሻ የሆኑ ም ክንያቶችና አጋጣሚዎች ምን ምን እንደሆኑ የሚያስረዳ ክፍል ይቀርባል፡፡

### 4.2.1 የአስተዳደር ተቋማት መዋቅር

ቡርጂ ውስጥ ሦስት ታላላቅ ባህላዊ የአስተዳደር ተቋማት እንደሚገኙ፣ እነዚህም የክልል (Territorial)፣ የጎሳ እና የህግ አስተዳደራዊ ተቋማት እንደሆኑ ቀደም ብለን ጠቅሰናል፡፡ ክልላዊ የአስተዳደር ተቋም (Territorial Institution) በራሱ የተለያየ ሥልጣንና ተግባር ባላቸው በአምስት ንዑሳን አስተዳደራዊ ክፍሎች ይዋቀራል፡፡ እነዚህም፣ ከዝቅተኛው ወደ ከፍተኛው ሲጠሩ፣ የ*ኦላ* (የ*ገሪኤ* ) አስተዳደር፣ የ*ቦሄ* አስተዳደር፣ የ*ቢያ* አስተዳደር፣ የራስ ገዝ አስተዳደር እና የ*ጉልጉባ* አስተዳደር በመባል ይታወቃሉ፡፡

*ኦላ* ዝቅተኛውና ትንሹ የቡርጂ ክልላዊ የአስተዳደር ክፍል ነው፡፡ የ*ኦላ* አስተዳደር በአንድ *ቦሄ* ውስጥ በጉርብትና የሚኖሩ (የሚጎራበቱ) ቤተሰቦችን ይዞ የሚዋቀር ሲሆን በነዋሪዎቹ በሚመረጥ *ኦለይንካ ኣና* (የጎረቤት መሪ) ይተዳደራል፡፡ ከ*ኦላ* በአንድ ደረጃ ከፍ ብሎ የሚዋቀረው አስተዳደራዊ ተቋም ደግሞ የ*ቦሄ* አስተዳደር ነው፡፡ የ*ቦሄ* አስተዳደር በውስጡ በርካታ የ*ኦላ* አስተዳደሮችን ይዞ ይዋቀራል[30]፡፡ ይህ የ*ቦሄ* አስተዳደር *በባሻ* እና በምርጫ ስርዓት በሚሰየም በአንድ *ማሻ* ይተዳደራል፡፡ ቡርጂ ውስጥ በዚህ ደረጃ የተዋቀሩ ከሃያ የሚበልጡ የ*ቦሄ* አስተዳደሮች እንደሚገኙ ይገመታል፡፡

በውስጡ ሁለትና ከሁለት በላይ የሚሆኑ የ*ቦሄ* አስተዳደሮችን በመያዝ ከ*ቦሄ* አስተዳደር በአንድ ደረጃ ከፍ ብሎ የሚዋቀረው ሶስተኛው ክልላዊ ተቋም *ቢያ* ይባላል፡፡ *ቢያ* በቀጥተኛ ትርጉሙ *አገር* እንደ ማለት ነው፡፡ ቡርጂ ውስጥ በዚህ ደረጃ የተዋቀሩ ስምንት የ*ቢያ* አስተዳደሮች አሉ፡፡ እነዚህን የ*ቢያ* አስተዳደሮችን በውስጣቸው ከያዟቸው ከ*ቦሄ* አስተዳደሮች ጋር እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ማሳየት ይቻላል፡፡

---

[30] ይህ ተቋም፣ በተወሰኑ የቡርጂ አካባቢዎች የሚዋቀረው ከዚህ በተለየ መልክ ነው፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች ከ*ኦላ* አስተዳደር በአንድ ደረጃ ከፍ ብሎ የ*ገሪኤ* አስተዳደር ይገኛል፡፡ *ገሪኤ*፣ በውስጡ በርካታ *ኦላዎችን* ይዞ ይመሰረታል፡፡ የሚተዳደረውም ልክ እንደ *ኦላ*፣ በነዋሪዎቹ በሚመረጥ በአንድ *ገሪኤንካ ኣና* (በ*ገርኤ መሪ*) ነው፡፡ የ*ቦሄ* አስተዳደር (በእነዚህ አካባቢዎች ማለት ነው) የሚመጣው ከዚህ ከገሪኤ አስተዳደር አንድ እርከን ከፍ ብሎ ነው፡፡ አብዛኞቹ የቡርጂ ህዝቦች የሚኖሩባቸው አካባቢዎች ግን የተዋቀሩት በመጀመሪያ ላይ በተመለከተው መልኩ ነው፡፡

| ተራ ቁጥር | የቢያአስተዳደር ስም | በቢያ አስተዳደር ውስጥ የሚገኙ የቦሄ አስተዳደር ስሞች | የቦሄዎች ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | ቡርጂ | ክሊቾ፣ጋሚዮ፣ሌሞ | 3 |
| 2 | ላዋጋ | ላድሼ፣ ዋለይ፣ ጋራ | 3 |
| 3 | ሀና [31] | ሀላሜ፣ ናዳሌ | 2 |
| 4 | ኦቶማል | | |
| 5 | ወርዴይ | ጉዴ፣ ዲንቤቾ | 2 |
| 6 | ራለይ | ቢላ፣ ጎቼ | 2 |
| 7 | የበን | ሐሮ፣ ማርካሌ፣ ኢላሎ፣ የበን፣ ዛቡሩ ጋልዳፌ | 5 |
| 8 | ጋሻራ | ጋሻራ፣ ጋላባ፣ ሀርቴይሼ፣ ሐራወንጂ፣ ዳሊኦ | 5 |

ሠ. ቁ. 1- የቢያ እና የቦሄ አስተዳደሮች ብዛትና ጥምረት

እነዚህ ስምንቱ የቢያ መስተዳደሮች እንደገና ቡርጂ፣ ላዋጋ፣ ሀና እና ጋሪንታ ቢያ በሚባሉ በአራት የራስ ገዝ ወይም የፌደራል አስተዳደሮች ይዋቀራሉ። ከፊት፣ ከተራ ቁጥር 1-3 ድረስ ያሉት ሶስቱ አካባቢዎች የራስ ገዝ አስተዳደር የሚሆኑት ቀደም ሲሉ የቢያ አስተዳደር ሆነው በተዋቀሩበት ሁኔታ ነው። ጋሪንታ ቢያ የራስ ገዝ ግን፣ ከቀደሙት፣ ከሶስቱ በተለየና ሰፋ ባለ ሁኔታ አምስት የቢያ አስተዳደሮችን ይዞ የተመሰረተ ነው። ጋሪንታ ቢያ የሚባለውን የራስ ገዝ አስተዳደርን በጋራ የሚመሠርቱትም ጋሻራ፣ የበን፣ ኦቶማል፣ ወርዴይ እና ራለይ የሚባሉ አምስት የቢያ አስተዳደሮች ናቸው። የቡርጂ ራስ ገዝ አስተዳደር የሚተዳደረው በወማ ሲሆን የተቀሩት ሶስቱ ግን በዳይና ይተዳደራሉ።

ከቢያ አስተደሰደር ከፍ ብሎ የሚመሰረተው ክልላዊ አስተዳደር ጉልጉባ ይባላል። ጉልጉባ ቡርጂን በሙሉ የሚያጠቃልል፣ ከቁንጮ ላይ ያለ አስተዳደራዊ አካል ነው። Amborn እና Kellner (1999) “Middle Burji“and "Highland Burji” የሚሏቸውን የቡርጂ አካባቢዎችን የሚያጠቃልል ማለት ነው። ጉልጉባ በምርጫና በባሻ ሥርዓት በሚመደብ ወማ ይተዳደራል።

ሁለተኛው ባህላዊ የአስተዳደር ተቋም፣ የጎሳ አስተዳደር ነው። የጎሳ አሰተዳደራዊ ተቋም ከጎሳው አባላት መካከል በሚመረጡ በአንድ ኣንሽ እና በአንድ ጎሳንካ ኣና (የጎሳ መሪ) የሚመራ ተቋም ነው። ከቡርጂ አስተዳደራዊ ተቋማት መካከል በምንም ኃይል ሣይሰበር እስከ ዛሬ የዘለቀ ጠንካራ ተቋም ቢኖር የጎሳ አስተዳደር ነው። በቡርጂ ፖለቲካዊና እምነታዊ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ሚና የሚጫወተው ይሄው የጎሳ አስተዳደር ነው። የጎሳ አስተዳደር ከፍ ሲሉ ከተመለከቱት

[31] ማህበረሰቡ በዚህ ስም አይጠራውም። እኔ ለአፃፃፍ እንዲመች በሚል የቢያ አስተዳደሩን የሚመሰርቱ ቦሄዎችን መነሻ ሆሄያቸውን በመውሰድ የሰጠሁት ስያሜ እንጂ የተለመደ አያደለም። በዚህ ጥናት ውስጥ ሀና ማለት ሀላሜ እና ናዳሌ ማለት እንደሆነ ልብ በል። እንደ (ጌታሁን፣ 1995) አባባል፣ ይህ የቢያ አስተዳደር ድሮ በአስራ አንድ የቦሄ አስተዳደሮች የተዋቀረ ነበር። በህዝበ ውሳኔ ዘጠኙ ወደ አማሮ ልዩ ወረዳ ሲካለሉ እነዚህ ሁለቱ ብቻ ቀሩ።

ከሀግ እና ከክልላዊ የአስተዳደር ተቋማት ጋር ቀጥተኛ ብቻ ሣይሆን ጠንካራ ግንኙነት አለው። የተቀሩት ሁለቱ ግን እርስ በርሳቸው ያላቸው አስተዳደራዊ ግንኙነት ቀጥተኛ ያልሆነ ነው።

*የሀግ* አስተዳደር በወጣት ወንዶች የተገነባ፣ የመከላከያ ኃይል ተቋም ነው። አባላቱም የተገረዙ ወይም በትውልድ የአመዳደብ *ሥርዓት* ውስጥ የተካተቱ ወጣቶች ሲሆኑ *ሉብ* በሚል የማዕረግ ስም ይጠራሉ። የሀግ አስተዳደራዊ ተቋም *ሃዩ* በሚባል በአንድ መሪና ረዳቱ በሆነው በአንድ *ኣርጉማንቾ* ይመራል። ዋነኛው ተግባሩም የህዝቡንና የአካባቢውን ደህንነትና ፀጥታ ማስጠበቅና መጠበቅ ሲሆን ፣ ማንም በቀጥታ የማያዘው፣ ራሱን ችሎ የሚንቀሳቀስ ተቋም ነው። *የሀግ* መዋቅር በአብዛኛቹ የቡርጂ አካባቢዎች፣ *ከጉልጉባ* እስከ ቦሄ ደረጃ የተዋቀረ ሲሆን፣ በተወሰኑ የቡርጂ አካባቢዎች ግን ከቦሄም ዝቅ ብሎ፣ እስከ ገሬኤ (ቀጠና አስተዳደር) ድረስ ይዋቀራል። ከፍ ሲሉ የተመለከቱትን የአስተዳደር ተቋማትን መዋቅር በ*ሥዕል* ቁጥር 3 ላይ ተመልከት)።

### 4.2.2 ለአስተዳደራዊ መዋቅሩ መነሻ የሆኑ መሰረታዊ ምክንያቶችና አጋጣሚዎች

የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደር በሶስት ታላላቅ አስተዳደራዊ ተቋማት የተዋቀረና ከእነዚህ አንዱ የሆነው ክልላዊ አስተዳደር እንደገና በአምስት የአስተዳደር እርከኖች የሚከፈል መሆኑ ከፍ ሲል ተመልክቷል። ስለ ጎሳና ስለ *ሀግ* ተቋማት በቀደሙት ክፍሎች ተወስቷል። እዚህ የምናነሳው የክልል አስተዳደሮችን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ብቻ ይሆናል። በክልል አስተዳደር ውስጥ በሁለቱም ጫፎች ላይ ያሉትን (*የጉልጉባን* እና *የኦላን* አስተዳደሮች) ትተን የተቀሩትን ማለትም *የቦሄ*፣ *የቢያ* እና የራስ ገዝ አስተዳደሮችን ስንመረምራቸው እንዲህ ሆነው ለመዋቀራቸው መነሻ የሆኑ መሰረታዊ ምክንያቶችና አጋጣሚዎች መኖራቸውን እንገነዘባለን። ዋና ዋና ምክንያቶቹና አጋጣሚዎቹ ሶስት ናቸው። ለቦሄ መመስረት መነሻ ከሆነው ምክንያትና አጋጣሚ እንጀምር።

አንደኛው ምክንያት፣ ዋና በር (Main gates) በጋራ ያላቸው መሆኑ ነው። በቡርጂ ልማድ፣ በአንድ ቦሄ የሚኖሩ ህዝቦች፣ ከራሳቸው ቦሄ ሲወጡም ሆነ ወደ *ቦሄ* ሲመለሱ በጋራ የሚጠቀሙበት (የሚጋሩት) አንድ ዋና በር ይኖራቸዋል። ይህ ዋና በርም በቡርጂኛ *ባልባላ* *(balbbala)* ይባላል።

*ባልባላ* እንደ የጋራ መግቢያና መውጫ በር ተደርጎ ይተርጎም እንጂ፣ ዋነኛው አገልግሎቱ ግን ሌላ ነው። የመጀመሪያው፣ የአንድ አካባቢ (የቦሄ ወይም የክልል ሊሆኑ ይችላሉ) ህዝቦች የጋራ በሆኑ ጉዳዮቻቸው ላይ ለመወያየት ሲፈልጉ የሚሰበሰቡበት ወይም የሚቀመጡበት፣ የሚገናኙበት ስፍራ ነው - *ባልባላ* የሚባለው። በቡርጂ ልማድ (በጥንቱ ልማድ ማለት ነው)

በአመት አንድ ጊዜ የሚፈፀመው *የሐጣኖ* እምነታዊ ስርዓት (ምዕራፍ አምስትን ተመልከት) የሚከናወነው በዚሁ *በባልባላ* ውስጥ ነው፡፡ እንዲሁም፣ *ባልባላ* የህዝብ ሹማምንት አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ለማከናወን (*ሥራቸውን ለመስራት*) የሚገለገሉበት ስፍራም ነው፡፡ በአጭሩ *ባልባላ* ማለት *ዋና በር*፣ *አደባባይ* ወይም *ጽህፈት ቤት* እንደ ማለት ነው፡፡

ሁሉም የቡርጂ *ቦሄዎች* እያንዳንዳቸው አንድ፣ አንድ *ባልባላ* አላቸው፡፡ ይህ፣ በቦሄ ደረጃ የተዋቀረው ባልባላ፣ የቦሄም ሆኑ በቦሄ ውስጥ የሚኖሩ የኦላ ነዋሪዎች በጋራ የሚገለገሉበት አደባባይ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት፣ አንድ *ባልባላ* የሚጋሩ፣ ሁለትና በላይ የኦላ አስተዳደሮች በአንድ ላይ አንድ *የቦሄ* አስተዳደር ሆነው ይዋቀራሉ፡፡ በዚህም *ባልባላ*፣ *የቦሄ* አስተዳደርን ለማዋቀር አንዱ መነሻ ምክንያት ይሆናል ማለት ነው፡፡

*ባልባላ*፣ *የቢያ* አስተዳደርን ለማዋቀር ጭምር፣ እንደ አንድ መነሻ ምክንያት ወይም መስፈርት በመሆን ያገለግላል፡፡ በግላቸው አንድ፣ አንድ *ባልባላ* ያላቸው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ *የቦሄ* አስተዳደሮች፣ በጋራ የሚገለገሉት አንድ ሌላ *ባልባላ* ሲኖራቸው፣ በአንድ ላይ አንድ *የቢያ* አስተዳደር ሆነው ይዋቀራሉ፡፡ ይህን ሀሳብ በምሳሌ ማስረዳት ይቻላል፡፡ ቡርጂ ውስጥ ስምንት የቢያ መስተዳድሮች አሉ ብለናል፡፡ ከእነዚህ መካከል አንዱ *ጋሻራ* ነው፡፡ *ጋሻራ* አንድ የቢያ አስተዳደር ሆኖ የተዋቀረው በውስጡ *ጋላባ*፣ *ሐርተይሼ*፣ *ሐራወንጄ*፣ *ጋሻራ* እና *ዳሊያ* የሚባሉ፣ አምስት የቦሄ አስተዳደሮችን ይዞ ነው፡፡ አምስቱም ቦሄዎች እያንዳንዳቸው በግላቸው አንድ፣ አንድ *ባልባላ* አላቸው፡፡ በዚህም በጋሻራ ውስጥ አምስት *የቦሄ ባልባላዎች* አሉ፡፡ ወደ *ቢያ* ጉዳይ ሲመጣ ደግሞ፣ እነዚህ አንድ *ቢያ* (ጋሻራን) የመሰረቱት፣ አምስቱም የቦሄ አስተዳደሮች፣ ጋሻራን የሚመለከቱ ወይም የጋራ ጉዳዮች ሲኖራቸው የሚቀመጡበት፣ የሚገናኙበትና በጋራ ጉዳያቸው ዙሪያ የሚወያዩበትና *‹‹ጋሻሪንካ ባልባላ››* የሚባል አንድ ሌላ *ባልባላ* በጋራ ይኖራቸዋል ማለት ነው፡፡ በዚህ መሰረት በጋሻራ የቢያ አስተዳደር ውስጥ በጠቅላላው ስድስት ባልባላዎች ይኖራሉ ማለት ነው፡፡ ስምንቱ የቡርጂ የቢያ አስተዳደሮች በዚህ መልክ ለመዋቀራቸው አንዱ መስፈርቱ፣ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የቦሄ አስተዳደሮች የሚጋሩት፣ የአንድ *ባልባላ* መኖር ነው፡፡

*የቢያ* መስተዳድሮችን ለማዋቀር የሚያገለግለው ሁለተኛው መስፈርት ወይም ምክንያት ኩታ ገጠምነት ነው፡፡ በቡርጂ የአስተዳደር መዋቅር ውስጥ፣ አንድ የቢያ አስተዳደርን የሚመሰርቱት ሁለትና ከዚያ በላይ *የቦሄ* አስተዳደሮች አብዛኞቹ ኩታገጠም ናቸው፡፡ ለምሳሌ *ቡርጂ* የሚባለውን ቢያ (ሠ.ቁ. 1 ተመልከት) እንውሰድ፡፡ *ክልቾ*፣ *ጋሚዮ* እና *ሌም* በተባሉ በሶስት

*የቦሄ* አስተዳደሮች ጥምረት የተዋቀረ ነው፡፡ እነዚህ ሶስቱ *ቦሄዎች* በአቀማመጣቸው ኩታ ገጠም ናቸው፡፡ ሶስቱም የሚጋሩት አንድ *ባልባላ* አላቸው፡፡ በግላቸውም እንዲሁ አንድ፣ አንድ *ባልባላ* አላቸው፡፡ ቦሄዎቹ፣ በጋራ አንድ *ባልባላ* ያላቸው ከመሆኑም በላይ ኩታገጠም በመሆናቸው የተነሳ፣ ሶስቱም አንድ ላይ ተጣምረው *ቡርጂ* የሚባለውን አንድ የቢያ አስተዳደር እንዲመሰርቱ ሆኑ፡፡ በዚህም *የቦሄንና የቢያ* አስተዳደሮችን ለማዋቀር ኩታገጠምነትና *ባልባላ* ዋነኞቹ መስፈርቶች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ሶስተኛው መስፈርት፣ (ይህን እንኳን መስፈርት ከማለት፣ መነሻ ምክንያት ወይም አጋጣሚ ማለቱ የሚሻል ይመስለኛል) የራስ ገዝ አስተዳደሮችን አወቃቀር የሚመለከት ይሆናል፡፡ ይህም አጋጣሚ፣ የቡርጂ ህዝቦች በምን መነሻ፣ በአራት የራስ ገዝ ወይም የፌደራል አስተዳደሮች ተከፍለው ሊተዳደሩ እንደቻሉ የሚያስረዳ ነው፡፡

ከፍ ሲል፣ *ቡርጂ፣ ጋሪንታ ቢያ፣ ላዎጋ* እና *ሀና* የሚባሉ አራት የቡርጂ ራስ ገዝ አስተዳደሮች (ራገአ) ተመልክተዋል፡፡ እነዚህ የራስ ገዝ አስተዳደሮች በዚህ መልክ ስለመዋቀራቸው የየራሳቸው መነሻ ምክንያትና አጋጣሚ አላቸው፡፡ *ጋሪንታ* ቢያ የሚባለውን ራስ ገዝ የመሰረቱት አምስቱ የቢያ አስተዳደሮች፣ ራሳቸውን ችለው በምርጫ እና *በባሻ ሥርዓት* በሚመደብ *ዳይና* እንዲተዳደሩ ምክንያት የሆነው፣ የህዝብ አመፅ ወይም ተቃውሞ እንደሆነ፣ ይህ የህዝብ አመፅም ዲርቦ በሚባል በጋሻራ ሰው መመራቱን ከፍ ባለው ክፍል (4.1.3.2) ጠቅሰናል፡፡

ራሱን ችሎ *በሻይሼንታ ዳይና* ለሚተዳደረው *ለሀና* የራስ ገዝ አስተዳደር መመስረትም እንዲሁ መነሻ ምክንያቱ፣ *የጎዳ ወማ* ከስልጣንና ከቡርጂ መባረር እንደሆነ ከፍ ሲል ተብራርቶ ቀርቧል፡፡ ስለሆነም እነዚህ ሁለቱ የራስ ገዝ አስተዳደሮች በዚህ ደረጃ ለመዋቀራቸው መነሻ የሆነውን ምክንያት በድጋሚ ከዚህ አናነሳም፡፡ ቡርጂ የሚባለው ራስ ገዝም ቢሆን፣ በዚህ ደረጃ ለመዋቀሩ ዋነኛው ምክንያት የራስ ገዙ ለረዥም ዓመታት *በወማ* (በወሚሶ *ሥርዓት*) ይተዳደር የነበረ መሆኑ ነው፡፡ *የወማነት* ስልጣን በዳምጤ እስከተነጠቁበት ወይም የወሚሶ *ሥርዓት* በኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግስት እስከተደፈጠጠበት ጊዜ ድረስ፣ ወማ ሆነው ሙሉ ቡርጂን ሲገዙ የነበሩት የቡርጂ ራስ ገዝ ነዋሪዎች ብቻ ነበሩ፡፡ ይህም፣ ቡርጂ ራሱን ችሎ፣ አንድ የራስ ገዝ አስተዳደር ሆኖ እንዲዋቀር ምክንያት ሆነ፡፡ ይህም ቢሆን ከፍ ባሉት ክፍሎች ውስጥ በቀጥታም ባይሆን በተለያየ መልኩ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል፡፡ ስለሆነም በድጋሚ ከዚህ አናነሳውም፡፡ ከዚህ የምናነሳው፣ እንዲህ ሆኖ ለመዋቀሩም ሆነ ለመመስረቱ መነሻ የሆነው ምክንያትና አጋጣሚ በየትኛውም ቦታ እስካሁን ስላልተገለፀው ስለ *ላዎጋ* የራስ ገዝ አስተዳደር ብቻ ይሆናል፡፡ የላዎጋን

*ራስ ገዝ የሚመሰርቱት ላድሼ፣ ዋለይ* እና *ጋራ የሚባሉ ቦሄዎች* በምን *አጋጣሚ* ወይም *ምክንያት ራሳቸውን* ችለው *የሚተዳደሩ፣* በራሳቸው *መሪ የሚመሩ የራስ ገዝ* አስተዳደር *ሆነው ሊዋቀሩ* እንደቻሉ እስካሁን *የተጠቀሰ ነገር የለም*። ስለሆነም ከዚህ ቀጥለን ስለ *ላዋጋ ራገአ* ቅድሚያውን ሰጥተን እንናገራለን።

በድሮ ጊዜ *ሁሉም* (8ቱም) የቡርጂ *የቢያ* አስተዳደሮችና ህዝቦች በአንድ *ወማ* እና *ዳይና* ስር ይተዳደሩ ነበር። በዚያን ዘመን *ዳይና የሚኮነው፣ የዳይናነት* ስልጣን የሚገኘው፣ *ከወማው* ዘንድ ተሄዶ፣ *የወማው* ደጅ ተጠንቶ፣ *ለወማው* ተገብሮ፣ በአጭሩ ብዙ ተሁኖ፣ ብዙ ነገር ተሰጥቶ ነው። *ላዋጋዎችም* እንደ አንድ *የቢያ* አስተዳደር እንዲሁ ያደርጉ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ግን ራሳቸውን ችለው የራስ ገዝ አስተዳደር ሆነው እንዲተዳደሩ ለቡርጂ *ወማ* የእጅ መንሻ ከመስጠት፣ ደጅ ከመጥናት፣ ከመገበር ያስመለጣቸው፣ ዳይናነቱን ከራሳቸው *ወማ (ከሣጋናንካ ወማ)* እንዲወስዱ፣ በራሳቸው ዳይና እንዲተዳደሩ ምክንያት የሆናቸው አንድ አጋጣሚ ተፈጠረ፡ ፡ ይህም አጋጣሚ በቡርጂ አፈታሪክ እንደሚከተለው ይተረካል።

> በድሮ ጊዜ ላድሼና ዋለይም *የባሻ* ስርዓት ተካፋይ ነበሩ። እነርሱም የዳይናነትን *ሥልጣን ለመውሰድ፣ ታች* ቡርጄ፣ ከወማው ዘንድ ይወርዱ ነበር። በዚያን ዘመን ደግሞ ከዳይናነት ስልጣን *ጋር ተያይዞ* በሁሉም ቢያ ውስጥ በየዓመቱ ፍየል *ይታረዳል*። የፍየሉ ደምም *በቢታና* አማካይነት ለወማው ይወሰድለታል። በአንድ ወቅት እንደተለመደው ሁሉም ፍየል አርደው ደሙን ለወማው ወሰዱለት። ዋለይና ላድሼ ግን ለወማው ደም ሳይወስዱለት ቀሩ። ወማውም የመጣለትን ደም ተራ በተራ እየተቀበለ ከግንባሩ ላይ ሲይዝ (ሲቀባ) ቆይቶ ‹‹አንድ ይቀራል። ደሙን *ያላመጣው* የትኛው ቢያ ነው?›› በማለት ጠየቀ። ‹‹ዋለይ ነው *ያላመጣው*›› ተብሎ ተነገረው። ዋለይና ላድሼ ያው አንድ ቢያ ስለሆኑ ሁለቱም ተጠርተው ከወማው ዘንድ ቀረቡ። በቀረቡ ጊዜም ‹‹*ለምንድነው ደሙን ያላመጣችሁልኝ?*›› ተብለው በወማው ተጠየቁ። ያን ጊዜ ዋለይዎች ኦዳ የሚባል ወማ [32] (*ሣጋናንካ ወማ*) ነበራቸው። እሱም ከዋለይዎች *ጋር* ተጠርቶ ከቡርጄ ወማ ፊት ቀርቧል። የቡርጄ ወማ ‹‹*ደሙ የት አለ?*›› ባለ ጊዜ ወማ ኦዳም መልሶ *‹‹ናኑ ጨና ማሌ ጨጅ ቃፊነይ››* (እኛ ዝናብ እንጂ ደም የለንም) በማለት ተናገረ። የቡርጄ *ወማም መልሶ* ‹‹እንግዲህ ዝናብ *ያለህ* ከሆነ ዝናቡ የት አለ? እስቲ አሳየና! እንየው!›› አለው። ያን ጊዜ ወቅቱ ከረር ያለ ሐሩር የበዛበት *በጋ* ነበር። *ወማ* ኦዳ ይህን ጊዜ ተከናንቦ ከመሬት ላይ ተኛ ። ልክ ወማ ኦዳ ተከናንቦ እንደተኛ፣ ከየት *መጣ?* ሳይባል ዝናብ *ዶፉን ያወርደው* ጀመር። ከሰማዩ ላይ ጠብታ ዝናብ የቀረ *በማይመስል መልኩ ለቀቀው*። ከዝናቡ *ጋርም* የድንጋይ በረዶ ከሰማይ ወደ *መሬት* መናድ ጀመረ። ትላልቅ አለቶችና ቋጥኞች በጎርፍ *እየተፈነቃቀሉ* ወደ መንደር ተምዘገዘጉ። ህዝቡም ይህን ሲመለከት ሽሽት ጀመረ። እሱ፣ ወማ ኦዳ ብቻ፣ ጋቢውን ተከናንቦ እንደተኛ ከዚያው ቀረ። ህዝቡም ‹‹ንጉስ ሆይ! ንጉስ ሆይ! ኧረ አለቅን፣ ኧረ አለቅን!›› እያለ ጮኸ። ይኸነ ዝናቡ ለጥቂት ጊዜ *መዝነቡን* አቆመ። ህዝቡም ፋታ አገኘ። ዝናቡ ከአባራ በኋላ የቡርጄ *ወማ መጥቶ* ‹‹እንግዲህ ምን ይሻላል?›› በማለት *ለወማ* ኦዳ ጥያቄ አቀረበ። ‹‹እንግዲህ የሚሻለውማ አንድ ነገር ብቻ ነው። ለእኔ አገር (ግዛት) መስጠቱ ነው የሚሻለው። እኔም በራሴ *ወማ* ስለሆንኩ ግዛት ይገባኛል። ለኔም ግዛት (ሀገር)

[32] *መንፈሳዊ* ወማ ነው። በቡርጂ ባህላዊ የእምነት *ሥርዐት* መሰረት በአካባቢው ዝናብ እንዲዘንብ ወይም እንዳይዘንብ ማድረግ ይችላል ተብሎ የሚታመን ሰው ወይም ጎሳ አለ። ጎሳው *ሣጋና* ይባላል። ይህ ጎሳ ይህን ማድረግ የሚያስችለው *ጋን* የሚባል ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል እንዳለው ይታመናል። *ጋን* ያደረበት የጎሳው አባልም ወማ ወይም *ሣጋናንካ ወማ* ይባላል። አማርኛው *የዝናብ ንጉስ* ቢል በትክክል አልገለፀውም አይባልም። ተግባሩ *መንፈሳዊ* ብቻ ነው። *ፖለቲካ* ነክ ጉዳዮች አይመለከቱትም። በቡርጂ ባህላዊ *ሥርዐት* ውስጥ በዚህ *ማዕረግ* (ወማ ተብለው) የሚጠሩ ሁለት ከፍተኛ ሹማምንት መኖራቸው ቀደም ሲል መጠቀሱን ልብ ይሏል (ለተጨማሪ መረጃ ምዕራፍ 5 ተመልከት)።

> ስጠኝ!›› በማለት የዝናቡ ንጉስ መለሰለት፡፡ በዚህን ጊዜ የቡርጂ ወማ እንዲህ አለው አሉ፡፡ ‹‹ሳድሼና ዋለይ ከቤትህ ይዋሉ (በአንተ ስር ይተዳደሩ)፡፡ *ዳይና* መሆን የሚፈልግ የሳድሼና የዋለያ ሰውም አንተ ዘንድ *መጥቶ*፣ ለአንተ *ገብሮ ሥልጣኑን* ይውሰድ›› አለ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሳድሼና ዋለይ ለዳይናነት ከቡርጂ ወማ ዘንድ *መሄዱን* አቆሙ፡፡ ከዋናው የቡርጂ የባሻ *ሥርዓት* ወጥተው ዳይኖማነቱንም ከቤታቸው *መውሰድ* ጀመሩ፡፡ *ራሳቸውን* ችለው የሚተዳደሩ፣ አንድ የራስ ገዝ አስተዳደር ሆነው *መተዳደር* ጀመሩ፡፡[33]

ከፍ ተብለው የተመለከቱት፣ ስምንቱ የቢያም ሆኑ አራቱ የራስ ገዝ አስተዳደሮች እርስ በርሳቸው ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት የላቸውም፡፡ ግንኙነታቸው ቀጥተኛ ያልሆነ ነው፡፡ እያንዳንዳቸው የሚተዳደሩትም ሆነ የሚንቀሳቀሱት ራሳቸውን ችለው ነው፡፡ የራሳቸው ወሰን፣ የራሳቸው መሪ አላቸው፡፡ እያንዳንዱ የቢያ አስተዳደር የየራሱ የህግ አውጭና የህግ አስፈፃሚ አካላት አለው፡፡ የህግ አውጭ አካሉ *ጓንሽ-ጎርስ*፣ የህግ አስፈፃሚው ደግሞ *‹‹ሌላ››* ይባላል፡፡

*ጓንሽ-ጎርስ*፣ ከላይኛው *ከጉልጉባ* እስከ *ታችኛው* የቦሄ አስተዳደር ድረስ በደረጃ ባሉት ክልላዊ የአስተዳደር ተቋማት ውስጥ የሚዋቀር ከፍተኛ አካል ነው፡፡ *ጓንሽ-ጎርስ* በአንድ ጉዳይ ላይ ለመነጋገር ሲሰበሰብ ወይም ጉባኤ ሲቀመጥ *ጎርሶማ* ይባላል፡፡ በአማርኛ ‹‹ምክር ቤት›› የሚል ፍቺ አለው፡፡ በዚህ መልክ ከላይ፣ ከመዋቅሩ አናት ላይ የተዋቀረ አንድ *ጎርሶማ* ይኖራል፡፡ ይህም *ጉልጉብይንካ ጎርሶማ* ይባላል፡፡ በአንድ ሰብሳቢና *(በወማ)* በአንድ አፈ ጉባኤ *(በቆማች)* ይመራል፡፡ የራሱ *ባልባላ* (ጽህፈት ቤት) አለው፡፡


ከእሱ ዝቅ ብሎ፣ በአምስቱ የቢያ አስተዳደር ደረጃም እንዲሁ የተዋቀረ አንድ *ጎርሶማ* አለ፡፡ ይህ ደግሞ *ጋሪንካ ጎርሶማ* ይባላል፡፡ *ጋሪንካ ጎርሶማ በጋሪንታ ዳይና* ሰብሳቢነት ይመራል፡፡ *ቃሌንካ ቆግ* የሚባል የራሱ *ባልባላ* አለው፡፡ ከዚህ ዝቅ ብለው፣ በቢያና እና *በቦሄ* ደረጃ የተዋቀሩት ጎርሶማዎች በቅደም ተከተላቸው፣ *ቢያንካ ጎርሶማ* እና *ቦሄንካ ጎርሶማ* በመባል ይጠራሉ፡፡ እነዚህ *ጎርሶማዎች* በተዋቀሩበት ደረጃ ላለው አካል የመጨረሻ ደረጃ የህግ አውጭ አካላት ናቸው፡፡ እነርሱ የሚያወጡት ሕግ፣ የሚያስተላልፉት ውሳኔ በሁሉም ወገኖች ዘንድ ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ የአንዱ ቢያ ወይም የራስ ገዝ *ጎርሶማ* ከሌላው ቢያ ወይም ራስ ገዝ *ጎርሶማ* ጋር የሚኖረው ግንኙነት ቀጥተኛ ያልሆነ ነው፡፡

---

[33] ዋዮ፣ (1995)፡፡ ተቋርጦ የነበረውን የባሻ *ሥርዐትን* (የወሚሶንና የዳይኖማን ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓትን) እንደገና ለማስጀመር ሲባል፣ በተጠራው በበጉልጉቤይንካ ጎርሶማ (ጉባኤ) ላይ ከተናገረው የተወሰደ ነው፡፡ ዋዮ፣ ይህንን አፈ *ታሪክ* የተረተው ያለ ምክንያት አይመስለኝም፡፡ ጎርሶማው ‹‹በወማ *መተዳደሩ* ለጊዜው ይቆይ፡፡ ከአሁን ጀምሮ ህዝብ በዳይና ይተዳደር፡፡ የዳይኖማ ስርአት ይቀጥል›› በማለት የሰጠውን ውሳኔ ተከትሎ ‹‹የዳይናነት ስልጣን በመጀመሪያ ለየትኛው ቢያ ይሰጥ? ከየት ይጀምር?›› የሚል ጥያቄ የመወያያ ርዕስ ሆኖ ቀረበ፡፡ የእያንዳንዱ ቢያ ተወካዮችም ‹‹ ለእኔ፤ ለእኔ ›› በሚል *ሙግት* ገጠሙ፡፡ *ሙግቱም* ከሮ የሚያለያይ ፤ አንድነታቸውን የሚበታትን አቋም ከአባላቱ *መሰንዘር* ተጀመረ፡፡ በዚህም፣ ቀደም ሲሉ አንድ ሆነው፣ በአንድ የባሻ *ሥርዐት* (ዳይና) ይተዳደሩ የነበሩት አምስቱ የቢያ አስተዳደሮች ‹‹ስልጣኑ ለእኔ ይገባኛል፣ ለእኔ ይገባኛል›› በሚል ምክንያት አንድነታቸው ሊፈርስ ማለቱን ተገንዝበው፣ ህዝቡ ከዚህ፣ በታች ከሆነ ድርጊቱ እንዲቆጠብ ለማሳሰብ ሲሉ ይመስለኛል፡፡


ጎርሶማዎች ወይም የአስተዳደር ተቋማት የሚገናኙት የጋራ ጉዳዮች ሲኖሩ ብቻ ነው። ለምሳሌ፣ ቀደም ሲሉ የተጠቀሱት አምስቱ የጋሻራ *የቦሄ* አስተዳደሮችም ሆኑ *የቦሄ ጎርሶማዎች* የሚገናኙት በጋሻራ ደረጃ በተዋቀረው በጋሻራ *ጎርሶማ* ላይ ብቻ ነው። እያንዳንዱ *ቦሄ* በጋሻራ *ጎርሶማ* ውስጥ የሚኖረው እኩል፣ አንድ አንድ መቀመጫ ብቻ ይሆናል። በጋሻራ ደረጃ የሚገናኙትም የጋራ የሆኑ፣ አጠቃላይ ጋሻራን የሚመለከቱ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ፣ በጉዳዩ ላይ ለመወያየት ሲሉ ነው። የጋራ ጉዳዮች የሚባሉት ለምሳሌ፣ ወደፊት በአካባቢው የሚደርሱ እንደ በሽታ፣ ጦርነት፣ ረሀብ፣ ወዘተ. የመሳሰሉ ክፉ አጋጣሚዎች አሉ ተብለው ሲታመኑ፣ ችግሩን በጋራ በሚከላከሉበት መንገድ ላይ ለመወያየት ሲሉ ይገናኛሉ። እያንዳንዱ የአስተዳደር አካባቢ ከሌላው ጋር ሣይገናኝ ሊፈፅማቸው የሚችሉ በርካታ የአካባቢ ጉዳዮች ቢኖሩም፣ ችግሩ ቡርጂ አቀፍ (ለምሳሌ እንደ ጦርነት ያለ) ሲሆን ግን መካላከል የሚቻለው በጋራ ይሆናል። የመከላከሉ ተግባር መፈፀም ያለበት በጋራ ይሁን በግል ወሳኞቹ ግን የአካባቢ መሪዎች ወይም *ጎርሶማዎች* ሣይሆኑ ጠንቋዮችና ተንባዮች ናቸው (ለዝርዝር መረጃው ምዕራፍ 5 ተመልከት)።

ከፍ ብለው በተዋረድ በተዋቀሩት *በጋሪንካ ጎርሶማና በጉልጉብይንካ ጎርሶማ* ውስጥ ያለው የመቀመጫ ድልድልም እንዲሁ እኩል ይሆናል። በዚህም *በጋሪንካ ጎርሶማ* ውስጥ እያንዳንዱ ቢያ አንድ አንድ መ ቀመጫ ብቻ ይኖረ ዋል። *በጉልጉብይንካ ጎርሶማ* ደረጃም እንዲሁ ፣ እያንዳንዱ የቢያ አስተዳደር አንድ አንድ መቀመጫ ይኖረዋል። አንድ ቢያ (ለምሳሌ ጋሻራ) በጉል ጉቤይንካ ጎርሶማ ውስጥ የሚወከለው በአንድ *ኣንሽ* (የጎሳ መሪ) እና በአንድ *ማሻ* (*ፊዚ*) ብቻ ይሆናል። እነዚህ ሁለቱ ባለስልጣናት በጎርሶማው ላይ የሚሳተፉት ረዳቶቻቸውንና አማካሪዎቻቸውን በመያዝ ሲሆን፣ በሚወክሉት ቢያ ስም የሚኖራቸው ድምፅ ግን፣ አንድ ብቻ ይሆናል። በቡርጂ ባህላዊ አስተዳደር ውስጥ በደረጃ የሚገኙ የህግ አውጪ ተቋማት መዋቅርም ከዚህ በታች በሥዕል ቁ.2 ላይ የተመለከተውን ይመስላል።




<u>ሥዕል ቁጥር 2፡-</u> በቡርጂ ባህላዊ አስተዳደር ውስጥ በደረጃ ያሉ የሕግ አውጪ አካላት (ጎርሶማዎች) መዋቅር፡፡ (<u>ምንጭ</u>፡ በጥናቱ ፀሐፊ የተዘጋጀ)

ከነዚህ የህግ አውጪ ተቋማት በደረጃ ዝቅ ብለው ደግሞ አስፈጻሚ ተቋማት (ጽህፈት ቤቶች) ተዋቅረዋል፡፡ እነዚህ አስፈፃሚ ተቋማትም ከከፍተኛው *ከጉልጉባው ጀምረው* ወደ ዝቅተኛው ሲጠሩ 1.*ወሚንካ ባልባላ (የወማ ጽህፈት ቤት)*፣ 2. *ጋሪንታ ቢያንካ ባልባላ* (*የዳይና* ጽህፈት ቤት)፣ 3. *ቢያንካ ባልባላ* (*የፊዜ* ጽህፈት ቤት)፣ 4. *ቦሄንካ ባልባላ* (*የማሻ* ጽህፈት ቤት)፣ 5. *ሀግንካ ባልባላ* (*የሃዩ* ጽህፈት ቤት)፣ 6. *ኦለይንካ (ገሪኤንካ) ባልባላ* (*የኦለይንካ /የገሬንካ ኣና* ጽህፈት ቤት) ናቸው፡፡ *ወሚንካ ባልባላ በጉልጉባ አስተዳደር* ደረጃ የሚዋቀር ሲሆን፣ *ጋሪንታ ቢያንካ ባልባላ* ደግሞ በራስ ገዝ ደረጃ ይዋቀራል፡፡ በሶስተኛው እርከን ላይ ያለው *ቢያንካ ባልባላ* ደግሞ በቢያ ደረጃ የሚዋቀር አስፈጻሚ ጽህፈት ቤት ይሆናል፡፡ *ቦሄንካ ባልባላ* ደግሞ *በቦሄ* ደረጃ ይዋቀራል፡፡ *ሀግንካ ባልባላም* እንዲሁ ራሱን ችሎ *በቦሄ* ደረጃ የሚዋቀር ተቋም ነው፡፡ የመጨረሻው፣ *ኦለይንካ (ገሪኤንካ) ባልባላም*፣ ጉርብትናን መሰረት አድርጎ የሚዋቀር ይሆናል፡፡ ከእነዚህ መካከል *ሀግ* ሲቀር፣ ከአምስቱ አስፈጻሚ ተቋማት ጋር ቀጥተኛና ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖረው ተደርጎ፣ በሁሉም ደረጃ የሚዋቀር፣ ሌላ አንድ *ባልባላ* ይኖራል፡፡ ይህም *ጎሣንካ ባልባላ* (*የኣንሸ* ጽህፈት ቤት) ይባላል፡፡ *ከሀግንካ ባልባላ* በስተቀር የተቀሩት አስፈጻሚ ተቋማት *(ባልባላዎች)* እርስ በርሳቸው ያላቸው ግንኙነት ቀጥተኛ ነው፡፡ *ሀግንካ ባልባላ* ግን ከሁሉም ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት የለውም፡፡




ሥዕል ቁ.3 ሦስቱ የቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር ተቋማት መዋቅር (ምንጭ፡ በጥናቱ ፀሐፊ የተዘጋጀ)

### 4.3. የባህላዊ *መሪዎች* የአመዳደብ *ሥርዓት*

የቡርጂ ባህላዊ *ፖለቲካ መሪዎች* ወደ *ሥልጣን* የሚመጡት በሁለት *መንገዶች* ነው፡፡ አንደኛው በምርጫ ሲሆን፣ ሁለተኛው ባሻ[34] በሚባለው ባህላዊ *ሥርዓት* ነው፡፡ ከጉልጉባ እስከ ኡላ ድረስ በተዘረጉ በክልላዊና በተቀሩት በሀግ እና በጎሳ አስተዳደራዊ ተቋማት ውስጥ የሚመደቡት *ኣንሸ፣ ጎርስ፣ ወማ፣ ዳይና፣ ፊዜ፣ ማሻ፣ ጋና፣ ጃልዓባ፣ ሃዩ፣ ኣርጉማንቾ፣ ሉብ፣ ገሪኤንካ ኣና ወይም ኦለይንካ ኣና* የሚባሉ ባህላዊ *መሪዎች* ናቸው፡፡ ከእነዚህ መካከል *ኣንሸ፣ ሃዩና ገሪኤንካ ወይም ኦለይንካ ኣና* የሚመደቡት በምርጫ ብቻ ሲሆን፣ የተቀሩት *መሪዎች* ግን በሁለቱም *መንገዶች ማለትም* በምርጫና *በባሻ ሥርዓት* ይመደባሉ፡፡ በመጀመሪያ በምርጫው ይወዳደራሉ፡፡ በምርጫው ሲያሸንፉ ደግሞ *ያሸነፉበትን ሥልጣን ለመረከብ* በባሻ *ሥርዓት* ውስጥ ማለፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ ለመድረስ ግን ሁሉም ተወዳዳሪዎች ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶች አሉ፡፡ ይህ ክፍል አራት ነጥቦችን ያነሣል፡፡ በእያንዳንዱ አስተዳደራዊ ተቋም ወይም *ባልባላ* ውስጥ ስንት? ስንት? አባላት እንደሚመደቡ ማስተዋወቅ ቅድሚያውን ይይዛል፡፡ በመቀጠልም አንድን ሰው *ለሥልጣን* የሚያበቁ መስፈርቶች ምን? ምን? እንደሆኑ ይዘረዘራሉ፡፡ የምርጫ ደንቦችና *ሥርዓቶች* ምን እንደሚመስሉ በዚህ ክፍል *ሥር* የሚቀርብ ሶስተኛው ነጥብ ይሆናል፡፡ በመጨረሻም *ባሻ* ስለሚባለው ባህላዊ *ሥርዓት* ምንነትና የአፈጻጸም *ሥርዓት* የሚያትተው ክፍል ይቀርባል፡፡

#### 4.3.1 በየባልባላው የሚመደቡ አባላት ብዛት

ቡርጂዎች የሀግ፣ የጎሣ እና ክልላዊ የሚባሉ ሦስት አስተዳደራዊ ተቋማት እንዳሏቸው ከፍ ሲል ተጠቅሷል፡፡ በየተቋማቱም አስተዳደራዊ ተግባራትን የሚያከናውኑ አስፈፃሚ ጽህፈት ቤቶች *(ባልባላዎች)* አሉ፡፡ እነዚህም *ወሚንካ ባልባላ፣ ጋሪንታ ቢያንካ ባልባላ ወይም ዳይናንካ ባልባላ፣ ቢያንካ ባልባላ፣ ቦሄንካ ባልባላ፣ ጎሣንካ ባልባላ፣ ሀግንካ ባልባላና ኦለይንካ ባልባላ* በመባል ይጠራሉ፡፡ *በየባልባላዎቹም* የተለያየ ተግባር፣ ማዕረግና ቁጥር ያላቸው ባህላዊ *መሪዎች* ይመደባሉ፡፡

*ወሚንካ ባልባላ* ከሁሉም ከፍ ብሎ *በጉልጉባ* ደረጃ የሚገኝ አስፈጻሚ ጽህፈት ቤት ነው፡፡ *በባልባላውም ወማ፣ ጋና (ወሚንካ ጋና) እና ጃልዓባ (ወሚንካ ጃልዓባ)* የሚባሉ ሶስት አባላት ይገኛሉ፡፡ የአባላትን ቁጥር አራት የሚያደርሱ (Amborn and Kellner, 1999, 62) አሉ፡፡ በእነዚህ

---

[34] በቁሙ ‹‹ሣር›› ማለት ሲሆን፣ ቡርጂዎች በባህላዊ *መሪዎቻቸው* እራስ ላይ እርጥብ ሣር በመነስነስ የመሪዎቻቸውን ሹመት የሚያፀድቁበትን፣ *መሪዎቻቸውን* የሚመርቁበትን ባህላዊ *ሥርዓት* የሚጠሩበት ስያሜ ነው (ለዝርዝር ማብራሪያው ክፍል 4.3.4 ተመልከት)፡፡

ጸሐፍት አገላለጽ *ወማ፣ ጋና (ወሚንካ ጋና)፣ ማሻ (ወሚንካ ማሻ)* እና *ጃልዓባ (ወሚንካ ጃልዓባ) የወሚንካ ባልባላ* አባላት ናቸው።

*ዳይናንካ* ባልባላ ከ*ወሚንካ ባልባላ* ቀጥሎ ያለ ከፍተኛ የአስተዳደር አካል ነው። ቡርጂ ውስጥ ሶስት ዓይነት ዳይናንካ ባልባላዎች እንደሚገኙ ቀደም ሲል ገልጸናል። የአባላቱ ቁጥርም እንደ ባልባላዎቹ ዓይነት ይለያያል። አንደኛው *ሺይሽንታ ዳይናንካ ባልባላ* ነው። ሁለተኛው *ላዋጋንታ ዳይናንካ ባልባላ* ይባላል። *በላዋጋንታ ዳይናንካ ባልባላ* ውስጥ የተለያየ ማዕረግና ተግባር ያላቸው ሶስት አባላት ይመደባሉ። እነዚህም *ዳይና፣ ማሻ (ዳይናንካ ማሻ)* እና *ጃልዓባ (ዳይናንካ ጃልዓባ)* በሚል የማዕረግ ስም የሚታወቁ ናቸው። ሶስተኛው *ጋሪንታ ዳይናንካ ባልባላ* የሚባለው ነው። *በባልባላውም ዳይና እና ጃልዓባ (ዳይናንካ ጃልዓባ) የሚባሉ ሁለት*[35] ከፍተኛ የአመራር አባላት ይመደባሉ።

*ቢያንካ ባልባላ*፣ በቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካ መዋቅር ውስጥ *ከጋሪንታ ቢያንካ ባልባላ* ዝቅ ብሎ (ቀጥሎ) የሚገኝ፣ *በፊዜ (በማሻ)* እና ረዳቱ በሆነው፣ በ*ጃልዓባ* የሚመራ የአስተዳደር አካል ነው። *ፊዜ ከዳይና* ባይበልጥም የሚስተካከል ባለሥልጣን ነው። ሥልጣኑ የሚሰጠው አንድን *ቢያ* በበላይነት ለሚያስተዳድር ሰው ይሆናል።

በርግጥ *ፊዜ* ማለት፣ ራሱ ማሻ ሆኖ ለሌሎች ማሻዎች አለቃ የሆነ ሰው ማለት ነው። አንድ ሰው *ፊዜ* (የአንድ ቢያ መሪ) ሆኖ ለመመደብ ሲፈልግ ውድድሩን የሚጀምረው አንድ ደረጃ ወደታች ዝቅ ብሎ ነው። በመጀመሪያ *ለቦሄ* አስተዳዳሪነት ይወዳደራል። ያንን ሲያሸንፍ ደግሞ እንደገና ቀጥሎ ለሚገኘው *ለቢያ* አስተዳዳሪነት ሥልጣን ይወዳደራል። ይህንንም ሲያሸንፍ *በማሻ ማዕረግ*፣ *ፊዜ* (የቢያ አስተዳዳሪ) ሆኖ ይሰየማል። በማዕረጉ *ማሻ*፣ በሥልጣኑ ግን *ፊዜ* ይሆናል። በሌላ አገላለፅ፣ ይህ ሹም በሌሎች ሰዎች ሲጠራ ‹‹ማሻ እገሌ›› ይባላል እንጂ፣ ‹‹ፊዜ እገሌ›› እየተባለ አይጠራም።

---

[35] የባልባላውን አባላት ቁጥር አራት የሚያደርሱ ወገኖች አሉ። በእነዚህ ወገኖች *ማሻ* እና *ጋና በዳይና ባልባላ* ውስጥ የሚመደቡ ተጨማሪ አባላት ናቸው (Amborn and kellner ,1999, 62):: እንደ አንዳንድ መረጃ ሰጪዎቼ (ቱኬ፣ 47፤ አደን፣ 12፣ 2002) አባባል *የጋሪንታ ዳይና* ባልባላ አባላት *ጋናን* ጨምሮ ሶስት ናቸው። ዳይና፣ ጋና እና ጃልዐባ በዳይና ባልባላ ውስጥ አባላት ናቸው ማለት ነው። የእነዚህ ወገኖች አባባል በእርግጥም ትክክል ነው። ትክክል የሚሆነው ግን በጥንቱ ስርዓት ነው። በድሮ ጊዜ የወማውና የዳይናው ስልጣን እኩል በነበረበት ዘመን፣ ባልባላቸውም ተዋቅሮ የነበረው በተመሳሳይ ደረጃ ነበር። አሁን ግን ይህ ሁኔታ ያለ የለም። አብዛኞቹ መረጃ ሰጪዎቼ (ማኒኦ፣ 50፤ ጫሜ፣ 34፤ ቡኬ፣ 18፣ 2002) የሚናገሩት የጋሪንታ ዳይና ባልባላ አባላት ዳይና እና ጃልዐባ፣ ሁለት ብቻ መሆናቸውን ነው። ይህ መረጃ ከመሰብሰቡ ከሶስት፣ ከአራት ዓመት ቀደም ብሎ ዳይና ሆኖ ያገለገለው መረጃ ሰጪዬም (ማኒኦ፣ 2002፣ 50) በእርሱ ባልባላ ውስጥ እርሱና ረዳቱ የሆነው ጃልዐባ በድምሩ ሁለት አባላት ብቻ የነበሩ መሆናቸውን ነው የነገረኝ። ስለሆነም እኔም በጋሪንታ ዳይናንካ ባልባላ ውስጥ ሁለት አባላት ይገኛሉ በሚለው ልወሰን ተገድጃለሁ።

*የፊዜነት* *ሥ*ልጣን የሚሰጠው *በቢያ* ደረጃ ነው ብለናል፡፡ ይህ ሲባል ግን በሁሉም *ቢያ* ውስጥ *ፊዜ* ይኖራል ማለት አይደለም፡፡ *በቢያ* ደረጃ *የፊዜን* ጽህፈት ቤት ለመክፈት ሁለት እና ከዚያ በላይ *የቦሄ* አስተዳደሮች *(village administration)* ሊኖሩ የግድ ይላል፡፡ ከሁለት ቢያንስ ግን፣ የሚኖረው *ማሻ* ወይም *የማሻ* ፅህፈት ቤት እንጂ *ፊዜ* ወይም *የፊዜ* ፅህፈት ቤት አይደለም፡፡ በቡርጂ የአስተዳደር *ሥ*ርዓት *መሠረት*፣ አንድ *ቦሄ* የሚተዳደረው *በማሻ* ነው፡፡ በዚህ *መሠረት*፣ አራት ቦሄዎች ባሉበት በአንድ *ቢያ* ውስጥ አራት ማሻዎች ይኖራሉ ማለት ነው፡፡ ከእነዚህ ከአራቱ ማሻዎች መካከል ደግሞ አንዱ፣ የሁሉም አለቃ ሆኖ ይመረጣል፡፡ ይህም አለቃ ፊዜ ይባላል፡፡ በዚህም ከቦሄ አስተዳዳሪነቱ በተጨማሪ የቢያ አስተዳዳሪነቱንም *ሥ*ልጣን ደርቦ ይይዛል፡፡ የተቀሩት ሶስቱ ማሻዎች ደግሞ *ሮጋ* በሚል ጥቅል ስም ይጠራሉ፡፡ ከእሱ ከፍ ብለው ያሉት፣ *ወማውም* ሆነ *ዳይናው*፣ አንድን *ቢያ* በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የሚነጋገሩት፣ የሚወያዩት ከፊዜው ጋር ብቻ ይሆናል ማለት ነው፡፡

*በጋሪንታ ቢያ* የራስ ገዝ አስተዳደር ውስጥ ፊዜ የሚሰየመው፣ ዳይናው የዚያ ቢያ ሰው ካልሆነ ብቻ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ፣ ለምሳሌ በ2002 ዓመተ ምህረት *ጋሪንታ ዳይና* የተሰየመው *ከጋሻራ ቢያ* ከሆነ፣ በዚያ አመት በጋሻራ ውስጥ ፊዜ አይሰየምም፡፡ ይህ የሚሆነው በአንድ ቢያ ውስጥ በአንድ ጊዜ ሁለት መሪ (ዳይናና ፊዜ) እንዲኖር የቡርጂ ባህላዊ ደንብ ስለማይፈቅድ ነው፡፡ ምንም እንኳን ዳይናው በአምስቱ የቢያ አስተዳደሮች ላይ መሪ ሆኖ ቢመደብም በጋሻራነቱ የጋሻራ መሪነቱንም *ሥ*ልጣን ደርቦ ይይዛል፡፡

ይህ የሚሆንበት ሌላም ምክንያት አለ፡፡ ቀጥሎ ባለው ክፍል ላይ በዝርዝር እንደሚገለፀው፣ ዳይናው *ሱቡሮ* (ባህላዊ የባሻ *ሥ*ርዓት በሚፈፀምበት ቦታ) የሚወጣው በራሱ ቢያ ውስጥ ባሉ (በቀደመው ምሳሌ በጋሻራ) *ማሻዎች ታጅቦ* ነው፡፡ *በጋሻሪንካ ባልባላ* ላይ *ኤሣ* (የአንድነት አርማ) የሚያቆመው በጋሻራ *ማሻዎችና ጃልዓባዎች ታጅቦ* ነው፡፡ ለዚህ ባህላዊ *ሥ*ርዓት ሲሉ *ማሻዎቹ ከዳይናው* ዘንድ ይመጣሉ፡፡ *ዳይናው ከቢያንካ ባልባላውና* ከራሱ ደጅ ላይ *ኤሣ* ሲተክል ያጅቡታል፡፡ በመጨረሻም *ዳይናውን* አጅበው ወደ *ሱቡሮ* ይወጣሉ (ለዝርዝር ማብራሪያው <u>የባሻ *ሥ*ርዓት</u> የሚለውን ክፍል ተመልከት)፡፡ *ዳይናውን* በሰየመው *የቢያ* አስተዳደር ውስጥ ፊዜ የተሰየመ ከሆነ ልክ ለዳይናው እንደተደረገው ሁሉ ለፊዜም ይደረጋል፡፡ ማሻዎች ከፊዜ ዘንድ መጥተው ፊዜው ከራሱ ደጅና ከቢያንካ ባልባላ ላይ ኤሣ ሲተክል ያጅቡታል፡፡ በመጨረሻም ፊዜውን በማጀብ ሱቡሮ ይወጣሉ፡፡ *ዳይናውም ፊዜውም* በአንድ *የቢያ* አስተዳደር ውስጥ በአንድ ጊዜ የሚመደቡ ከሆነ ግን፣ ማሻዎቹ ከየትኛው አለቃቸው ዘንድ ይሂዱ? ከየትኛው ዘንድ

ሣይሄዱ ይቅሩ? ከአንዱም መቅረት ግን አይችሉም፡፡ በአንድ ጊዜ ደግሞ ከሁለቱም መሆንም አይችሉም፡፡ ስለሆነም ከፍ ሲል የተጠቀሰው ባህላዊ *ሥርዓት* ይፋለሳል ማለት ነው፡፡ ሌሎችንም ምክንያቶች መጥቀስ ይቻላል፡፡ የነገሩን አስቸጋሪነት፣ የመዋቅሩንና የህገ ደንቡን ተገቢነት ለማስረዳት ግን እነዚህ ሁለቱ የሚበቁ ይመስለኛል፡፡

*ቦሄንካ ባልባላ ከቢያንካ ባልባላ* ዝቅ ብሎ በቦሄ ደረጃ የሚዋቀር ነው፡፡ በ*ባልባላው*ም *ማሻ* እና *ጃልዓባ (ማሽንካ ጃልዓባ)* በሚል ማዕረግ የሚጠሩ ሁለት አባላት ይመደባሉ፡፡ ሌላው በጎሳ አስተዳደራዊ ተቋም ደረጃ የሚዋቀር ባልባላ ነው፡፡ ይህም *ጎሣንካ ባልባላ* ይባላል፡፡ አብዛኞቹ *ጎሳንካ ባልባላዎች ኣንሽ* እና *ጎሣንካ ኣና* በሚባሉ በሁለት ከፍተኛ ሹማምንት ይመራሉ፡፡ *ማሻን (ጎሣንካ ማሻን)* ጨምረው የአባላቱን ቁጥር *(ጎሳንታ ጪማዬ - የጎሣ ሽማግሌዎች-ሣይታሰቡ ማለት ነው)* ሶስት የሚያደርሱ ጥቂት የቡርጂ ቦሄዎችም አሉ፡፡ *ሀግንካ ባልባላ* የሚባልም ጽህፈት ቤት አለ፡፡ *ሀግንካ ባልባላ* በቦሄ ደረጃ የሚዋቀር ሲሆን ባልባላውን በበላይነት የሚመሩ ሁለት[36] አባላት በጽህፈት ቤቱ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ እነሱም *ሃዩ* እና *ኣርጉማንቾ* በመባል ይጠራሉ፡፡

*ጎርሶማ ከጉልጉባ* እስከ *ቦሄ* ድረስ ባሉት የክልል አስተዳደሮች ውስጥ የሚዋቀርና የተለያዩ የማህበረሰቡ ክፍሎች የሚወከሉበት ከፍተኛው የህዝብ ሸንጎ መሆኑን ገልጸናል፡፡ በሁሉም ደረጃ ባሉት *ጎርሶማዎች* ውስጥ አባላት የሚወከሉበት መንገድ ተመሣሣይ ቢሆንም ግን ብዛታቸው ይለያያል፡፡ *በጉልጉባ ጎርሶማ* ውስጥ ከእያንዳንዱ ቢያ አንድ *ኣንሽ*፣ አንድ *ማሻ (ፊዜ)*፣ አንድ *ጎርስ*፣ አንድ *ሃዩ*፣ አንድ *ቢታናች*፣ እንዲሁም አንድ *ወማ*፣ ሦስት *ዳይናዎች (ጋሪንታ ዳይና፣ ሽይሼንታ ዳይና እና ላዋጋንታ ዳይና)* ከነረዳቶቻቸው *የጎርሶማው* አባል ይሆናሉ፡፡ በዚህም፣ በዚህ ደረጃ በሚዋቀረው ጎርሶማ ውስጥ በጠቅላላው በግምት ስልሳ ዘጠኝ እና በላይ አባላት ይኖራሉ ማሊት ይቻላል፡፡

---

[36] ቁጥሩን /ብዛቱን /ወደ ዘጠኝ የሚያደርሱ አሉ፡፡ Amborn እና Kellner (1999, 33) Straube (1955)ን በመጥቀስ ሀግንካ ባልባላ ዘጠኝ አባላት አሉት በማለት ጽፈዋል፡፡ በእነሱ እምነት በሀግንካ ባልባላ ውስጥ አራት ሃዩ እና አምስት ኣርጐማንቾች፣ በድምሩ ዘጠኝ አባላት ይመደባሉ፡፡ ጸሐፊዎቹ እንዲህ ይበሉ እንጂ እነዚህ አባላት እንዴት እንደሚሰሩ የገለፁት ነገር የለም፡፡ በእኔ እምነት ግን ጸሐፊዎቹ ከዚህ የጠቀሱት ወይም ለአንድ የሀግ ጽህፈት ቤት የሰጡት ቁጥር በአንድ ቢያ ደረጃ የሚመደቡትን ነው፡፡ መረጃውን የሰጧቸው ሰዎች በቢያ ደረጃ የሚመደቡ አባላትን ብዛት የነገሯቸውና እነርሱ ደግሞ ቁጥሩን ለአንድ ባልባላ አድርገው እንደጻፉት አስባለሁ፡፡ እንዴት ብትሉኝ እንዲህ ነው፡፡ ለምሳሌ ጋሻራ አንድ ቢያ ነው፡፡ በሥሩ አራት የቦሄ ባልባላዎች አሉት፡፡ በእያንዳንዱ ቦሄ ውስጥም አንድ ሃዩ እና አንድ ኣርጉማንቾ ማለትም ሁለት ሁለት አባላት ይመደባሉ፡፡ ይህ አንዱን ሀግንካ ባልባላ ብቻ ስንወስድ የምናገኘው ቁጥር ነው፡፡ በጋሻራ ውስጥ ያሉትን አራቱን ባልባላዎች የወሰድን እንደሆነ ግን /4×2 = 8/ ስምንት አባላት ማለትም አራት ሃዩዎችና አራት ኣርጉማንቾዎች ይኖራሉ ማለት ነው፡፡ ክሊቾ የሚባለውን የአንድ ቦሄን አደረጃጀት ብቻ የወሰድን እንደሆነ ግን ይህ የፀሀፊቱ አባባል በርግጥም ትክክል ሊሆን ይችላል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በዚህ አካባቢ ሀግንካ ባልባላ ይዋቀር የነበረው በቦሄ ደረጃ ሣይሆን በጌሪኤ ደረጃ ስለነበረ ነው፡፡ እያንዳንዱ ጌሪኤ የየራሱ ሀግንካ ባልባላ አለው፡፡ በአንድ ቦሄ አራት ጌሪኤዎች ካሉ በቦሄ ደረጃ ስምንት አባላት ይኖራሉ ማለት ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ አሰራር ግን በሌሎች የቡርጂ አካባቢዎች አልተለመደም፡፡ የእነ Amborn መረጃም ከዚህ አካባቢ የተገኘ ሳይሆን አይቀርም፡፡ በአብዛኞዎቹ የቡርጂ አካባቢዎች ግን ሀግንካ ባልባላ የሚባለው በቦሄ ደረጃ የተዋቀረው እንጂ በጌሪኤ ደረጃ የተዋቀረው አይመስለኝም፡፡ በሀግንካ ባልባላ ውስጥ የሚመደቡት አንድ ሃዩ እና አንድ ኣርጉማንቾ በድምሩ ሁለት አባላት ብቻ ናቸው፡፡

*ጎርሶማው ጋሪንካ ጎርሶማ* ሲሆን የአባላቱ ቁጥር ቀደም ሲል ከተመለከተው፣ ከጉልጉባው ጎርሶማ አባላት ቁጥር ይቀንሣል። በዚህ *ጎርሶማ ዳይና (ጋሪንታ ዳይና)፣* ከአምስቱም የቢያ አስተዳደሮች ከእያንዳንዳቸው አንድ *ኣንሽ፣* አንድ *ማሻ* ወይም *ፊዜ*፣ አንድ ጉርስ፣ አንድ ሃዩ፣ አንድ ቢታናች ከነረዳቶቻቸው የጎርሶማው አባላት ሲሆኑ ጠቅላላ ብዛታቸው አርባ ሁለት እና በላይ ይሆናል ተብሎ ይገመታል። *በቢያንካ ጎርሶማ* ውስጥ ደግሞ *ፊዜ* ወይም *ማሻ፣* ከየቦሄው አንድ *ማሻ፣* አንድ *ሃዩ፣ (ምናልባት አንድ ኣንሽ)፣* አንድ *ጉርስ፣* አንድ *ቢታናች* ከነረዳቶቻቸው አባል በመሆን ይሳተፋሉ። በእያንዳንዱ ቢያ ውስጥ ያለው የቦሄ ብዛት የተለያየ በመሆኑ በዚህ ደረጃ የሚዋቀረው ጎርሶማ በጠቅላላው ስንት አባላት እንዳሉት እርግጠኛ ሆኖ መናገር አይቻልም።

ከፍ ሲል የተመለከተው የጎርሶማ አባላት አወካከል በቅርብ ጊዜ የተለመደ ነው። በድሮ ጊዜ ግን፣ ከእያንዳንዱ *ቢያ በጉልጉባው ጎርሶማ* የሚወከሉት አንድ *ኣንሽ* እና አንድ *ማሻ* በድምሩ ሁለት ሁለት ባለሥልጣናት ብቻ ነበሩ። በዚህ *መሠረት* ወማውንና ዳይናውን ከነረዳቶቻቸው ጨምሮ *የጉልጉባው ጎርሶማ* አባላት ጠቅላላ ብዛት በግምት *ሠላሣ* ስድስት እና ከዚያ በላይ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል።

ዝቅተኛውና የመጨረሻው የአስፈፃሚ አካል *ኦለይንካ ባልባላ* ነው። *ባልባላውም ኦለይንካ ኣና* በሚባል በአንድ *መሪና* ያልተወሰነ ቁጥር ባላቸው (በግምት ሁለት ወይም ሶስት በሚሆኑ) ሽማግሌዎች *(ኦለይንታ ጨ.ማዬ)* በድምሩ በግምት ሶስትና በላይ በሆኑ አባላት ይመራል። በአንዳንድ የቡርጂ አካባቢዎች (በክሊቾና በጋሚዮ ቦሄዎች) ደግሞ ማሻን *(ኦሌንካ /ገሪሌንካ ማሻን)* ጨምሮ በእያንዳንዱ *ኦለይንካ ባልባላ* ውስጥ በግምት ከአራት በላይ የሚሆኑ አባላት ይመደባሉ። በእያንዳንዱ *ባልባላዎች* ውስጥ ለመመደብ የሚፈልጉ ግለሰቦች ግን እንዲያሟሉ የሚፈለጉ መስፈርቶች አሉ።

### 4.3.2. ለሥልጣን የሚያበቁ መስፈርቶች

በተለያየ ደረጃ ባሉ ባልባላዎች ውስጥ የተለያየ *ሥልጣንና* ተግባር ያላቸው ባህላዊ *መሪዎች በባሻ* እና በምርጫ *ሥርዓቶች* የሚመደቡ *መሆናቸውን* ከፍ ሲል ገልፀናል። ለዚህ ደግሞ ሊሟሉ የሚገቡ መስፈርቶች አሉ። መስፈርቶቹም እንደ *መሪዎቹ ሥልጣንና* ወደ *ሥልጣን* እንደሚመጡባቸው *መንገዶች* የተለያዩ ናቸው። አንድን ሰው *ለሥልጣን* የሚያበቁ ወይም የማያበቁ ነገሮች ምን ምን ናቸው? ቀጥለው አንድ በአንድ ይቀርባሉ። በቅድሚያ በምርጫና

በባሻ ሥርዓት የሚመደቡ ባህላዊ መሪዎች እንዲያሚሉ የሚፈለጉት መስፈርቶች ምን ምን እንደሆኑ እንመለከታለን። ቀጥለን በባሻ ሥርዓት ለማይካፈሉ፣ በምርጫ ብቻ ለሚመደቡ ባህላዊ መሪዎች የተቀመጡ መስፈርቶችን እናያለን። መስፈርቶቹ በሁለት መልክ ይቀርባሉ። ሁሉንም መሪዎች የሚመለከቱት በአንድ በኩል፣ አንዱን ወይም የተወሰኑትን ብቻ የሚመለከቱት መስፈርቶች ደግሞ እንዲሁ ተለይተው ይቀርባሉ።

የጎሣ ማንነት ወይም ተገቢነት በምርጫና በባሻ ሥርዓት ወደ ሥልጣን የሚመጡ ሁሉም መሪዎች እንዲያሚሉ ከሚፈለጉት መስፈርቶች መካከል ቅድሚያውን ይይዛል። በቡርጂ ባህላዊ ደንብ መሰረት ሁሉም የቡርጂ ጎሳዎች በባሻ ሥርዓት አይካፈሉም። በባሻ ሥርዓት እንዲካፈሉ ደንቡ ከማይፈቅድላቸው የቡርጂ ጎሳዎች መካከል ሸክላ ሰሪ (ቢጅር) የሆኑ ጎሳዎች ቅድሚያውን ይይዛሉ። ሌሎቹ ደግሞ ብረት በመቀጥቀጥ የሚተዳደሩ (ቱንቶ) እና ጋን የሚባል ልዕለ ተፈጥሮኣዊ ኃይል አላቸው የሚባሉ ጎሳዎችም በባሻ ሥርዓት ከማይካፈሉት ውስጥ ናቸው። የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ (ቢጅር እና ቱንቶ) ጎሳዎች በባሻ ሥርዓት እንዳይካፈሉ የተከለከሉት በማህበረሰቡ ዘንድ እንደ ዝቅተኛ ጎሳ ተደርገው ስለሚታዩና ስለሚናቁ ይመስላል።

ምንም እንኳን፣ በእነዚህና በሌሎች ምክንያቶች ሁለቱ ጎሳዎች በባሻ ሥርዓት እንዳይካፈሉ፣ ዳይና፣ ማሻ...ወዘተ ሆነው እንዳይመደቡ፣ የህዝብ መሪ እንዳይሆኑ ቢከለከሉም በማህበረሰቡ የፖለቲካና የእምነት ሥርዓት ውስጥ የሚጫወቱት ወይም የተጫወቱት ሚና ግን ቀላል አይደለም። በተለይም፣ የባሻ ሥርዓቱ ሥርዓታዊ በሆነ መልኩ እንዲጀምርም ሆነ እንዲቀጥል ያደረጉት፣ ለቡርጂ ህዝብ አንድነት መሰረት የጣሉት ብረት የሚቀጠቅጡ ጎሣዎች (ቱንቶዎች) እንደሆኑ ይታመናል። ይህንንም ፊኒና ፍርዳ፣ ፊዜ ወልዴይሣ [37] ከሚለው ምሳሌያዊ አባባልና ለአባባሉ መፈጠር ምክንያት ስለሆነው አጋጣሚ ከሚተረከው አፊ ታሪክ መረዳት ይቻላል። ነገሩ እንዲህ ነው።

> በድሮ ጊዜ ቡርጂዎች ከአምስት ጎሣዎች ተራ በተራ በሚመደብ ወማ ወይም በወሚሶ ሥርዓት ይተዳደሩ ነበር። የወሚሶ አገዛዝም ጭቆና የበዛበት ስለነበር ከወደ ደጋው አካባቢ ያለው ህዝብ በአገዛዙ ላይ አመፀ። በዚህም በደገኞችና በቆለኞች መካከል ጦርነት ተቀሰቀሰ። በመጨረሻም ጋሻራ፣ አቶማል፣ ወርዴይ፣ ራለይ እና የበን የተባሉት አምስቱ የቡርጂ ቢያዎች ራሳቸውን ችለው (ራስ ገዝ ሆነው) በባሻ ሥርዓት እንዲተዳደሩ፣ በአንድ ዳይና እንዲመሩ ተደረገና ግጭቱ ተፈታ። አምስቱ የቢያ አስተዳደሮችም የዳይናነትን ሥልጣን ተራ በተራ ሊወስዱ፣ ዳይናም የጋራ መሪያቸው እንዲሆን፣ እያንዳንዱ ቢያ ደግሞ በፊዜ እንዲመራ

[37] ፊኒና አንድ ላይ የተቀጠቀጠ ብረት (ዙፋን) ነው። ፊርዳ ሁሉም ብረቶች የተቀጠቀጡበት (አንድ ሆነው የተዘጋጁበት) ቦታ ወይም ብረቶቹን በአንድ ላይ መቀጥቀጥ፣ ቀጥቅጦ ማዘጋጀት ማለት ነው። ፊዜ የአንድ ቢያ መሪ የሆነ ሰው የሚጠራበት ማዕረግ ሲሆን ወልዴይሣ ማለት ደግሞ አንድ ላይ መሰብሰብ ማለት ነው። አባባሉ በአንድ ላይ ሲፈታ በራሰያ ውስጥ የተዘጋጀው አርማ (ብረት) አምስቱን የቢያ አስተዳደሮችን አንድ ላይ ሰበሰባቸው፣ አንድ አደረጋቸው...ወዘተ ማለት ይሆናል።

> ተስማሙ። ለስምምነታቸው ማሰሪያ፣ ለአንድነታቸው ማፅኛ፣ ለባህላዊ ሥርዓታቸው ዘላቅነት የሚበጅ ሥርዓት አወጡ። ደንብ ቀረጹ። ከደንቦቹ መካከል አንዱ ‹‹የእያንዳንዱ ቢያ መለያ (አርማ) የሆነው ፊኒና (የህዝብ መሪዎች ከግንባራቸው ላይ የሚያስሩትና ቡርጂዎች ካላች የሚሉት ብረት ወይም ዙፋን ነው) ተሰብስቦ፣ በአንድ ላይ ቀልጦና ተቀጥቅጦ ለሁሉም የጋራ የሆነ አንድ ዙፋን (ፊኒና ወይም ሺጊዳ) ይዘጋጅ። ፊኒናውም የስምምነታችን፣ የአንድነታችን ማረጋገጫ፣ ቃልኪዳናችን ሆኖ ይቀመጥ›› የሚል ነበር። እንደተባለው ከአምስቱም ቢያ ፊኒናዎቹ ተሰበሰቡ። ይሁን እንጂ ፊኒናዎቹን አቅልጦና ቀጥቅጦ መልሶ በአንድ ላይ የሚሰራቸው ባለሙያ (ቱንቶ) ጠፋና ችግር ተፈጠረ። በዚህም የህዝቡ አንድነት ሊፈርስ፣ የአስተዳደር ሥርዓቱ ሊቋረጥ እንደሚችል ይታወቅ ነበርና ህዝቡ ተጨነቀ። ከብዙ ፍለጋና ድካም በኋላ ግን ራለይ ውስጥ ቀጥቃጮች (ቱንቶዎች) ተገኙና የታለመው ተፈጸመ። የአምስቱ ቢያ አርማ በአንድ ላይ ተቀጥቅጦ የጋራ አርማ፣ የአንድነታቸው፣ የቃል ኪዳናቸው ማሰሪያ የሆነው ፊኒና (ዙፋን) ተሰራ። ተሰርቶ ከተጠናቀቀ በኋላ ‹‹ፊኒና ፍርዳ ፊዜ ወልዴይሣ›› ተብሎ ተወስዶ ለወማው ተሰጠ ይባላል (ወርቁ፣ 2002)።

*ፊኒና* ወይም *ሺጊዳ* በድሮ ጊዜ የወማ መለያ በመሆን ያገለግለል ነበር። ከቀድሞው ወማ ወደ አዲሱ ወማ የሥልጣን ሽግግር ሥርዓቱ የሚፈፀመው ከፍ ሲል በተመለከተው መሰረት የተዘጋጀውን *ፊኒናን* ወይም *ሺጊዳን* ለአዲሱ ወማ በመስጠት ይሆናል። በአሁኑ ወቅት *ፊኒናው* *ባንባልንካ ጋን* በሆነው *ወማ* እጅ እንደሚገኝ ይነገራል። እንግዲህ በችሎታቸው የተናቁት፣ ከባሻ ሥርዓት የተገለሉት እንዲህ ዓይነት ተግባር የፈጸሙ ጎሳዎች ናቸው።

*በባሻ* ሥርዓት የማይካፈሉት ሌሎች የማህበረሰቡ ክፍሎች ደግሞ *ጋን* ያላቸው ጎሳዎች ናቸው። *ጋን* ያላቸው ጎሳዎች በባሻ ሥርዓት እንዳይካፈሉ፣ *ወማ፣ ዳይና፣ ማሻ* ወዘተ. ሆነው እንዳይመደቡ የመደረጋቸው ምክንያት ፖለቲካዊ ፋይዳ ያለው ይመስለኛል። ዋነኛው ዓላማ ግን የህዝብ መሪዎች ሥልጣናቸውን አለአግባብ እንዳይጠቀሙ፣ በሥልጣን እንዳይባልጉ ሲባል፣ አምባገነንነትን ለመከላከል ታስቦ ይመስለኛል። በቡርጂ የአስተዳደር ሥርዓት መሰረት የእምነት መሪዎች በፖለቲካ ጉዳዮች፣ የፖለቲካ መሪዎች በእምነታዊ ጉዳዮች ውስጥ አይገቡም። እያንዳንዳቸው የየራሳቸውን ሥራ ነው የሚሰሩት። ሥራቸውን የሚሰሩት ግን እርስ በርሳቸው ተደጋግፈው ነው። አወቃቀራቸውም አንዱ ሌላውን መቆጣጠር እንዲችል ተደርጎ ነው። *ዳይናው* ወይም *ማሻው* በአንድ በኩል የራሱን ሥራ እየሰራ በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ *ባለጋኑን* ይቆጣጠራል። *ባለጋኑም* እንዲሁ እምነታዊ ሥራዎችን እየሰራ፣ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የፖለቲካ መሪዎችን ይቆጣጠራቸዋል። በአጭሩ ሁለቱም ተቋማት ህዝብን የሚመሩት እንዲህ በቀጥታ እየተደጋገፉ፣ ቀጥተኛ ባልሆነ መልኩ ደግሞ አንዱ ሌላውን እየተቆጣጠሩ ነው። ይህ ሣይሆን ቀርቶ አንድ ሰው የፖለቲካውንና የእምነት ሥልጣን ደርቦ እንዲይዝ ወይም *ጋን* ያላቸው ጎሳዎችም በባሻ ሥርዓት እንዲካፈሉ ቢደረግ ኖሮ የቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓት ውስጥ አሁን እንደሚናየው፣ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ጥሩ መሰረት

ሊሆኑ የሚችሉ አንዳንድ አሰራሮች ሊኖሩት ቀርቶ፣ ሥርዓቱ የለየለት አምባገነናዊ ይሆን እንደነበር መገመት አያዳግትም።

ሀብት በባሻ ሥርዓት ሥልጣን ለመያዝ የሚፈልጉ ሰዎች እንዲያሟሉ የሚጠበቅ ሌላው መስፈርት ነው። ባሻ ብዙ ጣጣ፣ ብዙ ወጪ ያለበት ባህላዊ ሥርዓት ነው። ባሻ ብዙ ድግስ አለው። ህዝብን፣ ሹማምንትን፣ ወዘተ ደግሶ ማብላት፣ ማጠጣት የሚጠይቅ ሥርዓት ነው። ከሁሉም በላይ ግን ወማ ወይም ዳይና ሆኖ ለመመረጥ ሀብት በእጅጉ ያስፈልጋል።

በአጠቃላይ ዳይናነት (ወማነት) በሀብት ብዛት የሚገኝ የቡርጂ ባህላዊ ስልጣን ነው። ብዙ ጣጣ፣ ብዙ ወጪ ያለበት ስልጣን ነው። ዳይናነት (ወማነት) አቅምን አውቀው የሚጠይቁት፣ አቅም ታይቶ የሚሰጥ ስልጣን ነው። ብዙ ወጪ ወጥቶ፣ ሀብት ተረጭቶ የሚገኝ ስለሆነ ስልጣን ፈላጊው ወይም ጠያቂው ሰው፣ ኪሱ ያበጠ፣ ጎተራው የሞላ፣ በረቱ የተጨናነቀ፣ በሀብቱ የናጠጠ፣ በራሱ የተማመነ ሰው ሊሆን ይገባል። ስልጣኑ ከእጁ ሳይገባ፣ ለሚመለከታቸው ሁሉ ሰጥቶ፣ አብልቶ ሳያበቃ ሀብት ንብረቱ ከተሟጠጠ፣ ኪሱ ከተራቆተና የሚከፍለውን ቢያጣ እንኳን ጎሳው አዋጥቶ ይሰጠዋል። ይከፍሉለታል። አሊያም መሬቱን ሽጦ ተገቢውን ያሟላል እንጂ፣ በምንም መንገድ "የለኝም" ብሎ አይተውም። ከሁሉም በላይ ግን ዳይና ለመሆን ሲባል የሚሰጠው እጅ መንሻ ልክ የሌለው መሆኑን፣ ተቋርጦ የነበረውን የባሻን ስርዓት እንደገና ለማስጀመር ሲባል ተጠርቶ በነበረው በጉልጉብይንካ ጎርሶማ ላይ በስም ያልተጠቀሰ አንድ ተሳታፊ ከተናገረው፣ ከሚከተለው ሀሳብ መገንዘብ ይቻላል።

> ዳይናነት ብዙ ወጭ ያለበት ስልጣን ነው። በድሮ ጊዜ ዳይና የሚሆን ሰው ለወማው የሚከፍለውን ቢያጣ እንኳን ቀደም ሲል ባሪያ ትሁነኝ ብሎ የገዛትን ልጃገረድ ወስዶ ለወማው ይሰጥ ነበር። ለራሱ እንዲሰራለት እንዲያርስለት ሲል ገዝቶ ያሳደገውንና ያስገረዘውን ወንድ ባሪያውን ወስዶ ለወማው ያስረክብ ነበር። የምትታለብ ላም ከነጥጃዋ ከጋጥ ፈትቶ መስጠት ሁሉ ነበር። የእኔ አያት ዳይና ሆኖ የተሰየመው ለወማው አምስት ከብት ሰጥቶ ነው።

የንግግር ችሎታና ጠለቅ ያለ ባህላዊ እውቀት፣ በሁሉም የሥልጣን ቦታዎች ላይ የሚወዳደሩ ግለሰቦች እንዲያሟሉ የሚፈለጉ መስፈርቶች ናቸው። የተሟላ ጤንነትም እንዲሁ ተፈላጊ መመዘኛ ነው። የቡርጂ ባህላዊ ደንብ፣ አካሉ የጎደለ ሰው በባሻ ሥርዓት እንዲካፈል፣ የህዝብ መሪ እንዲሆን አይፈቅድም። የሥራ ታታሪነት፣ በህዝብ ዘንድ ያለው ተደማጭነት አንድን ሰው ለባህላዊ ሥልጣን የሚያበቁ መመዘኛዎች በመሆን ያገለግላሉ።

ጉልበት ወይም ኃይል አንድን ሰው ለወማነት የሚያበቃ መመዘኛ ነው። ከፍ ብለን እንደጠቀስነው የቡርጂ የወሚሶ (የወማ አስተዳደር) ታሪክ በኃይልና በንጥቂያ ተግባር የታጀበ

ነው። የወማ ሥልጣን ከጎዳዎች ወደ ጋሚዮዎች፣ ከጋሚዮዎች ወደ ክሊቾዎች ከዚያ ወደ ዳምጤ ዳዌ የተሸጋገረው በኃይል ወይም በንጥቂያ ነው። በአጭሩ ወማነት ሀብትና ጉልበት ያለው ሰው የሚወጣበት ሥልጣን ነው። ወማነትም ሆነ ዳይናነት ታላቅ ታናሽ የሚል፣ ከቀዳሚ ቤተሰብ መወለድን የሚጠይቅ ሥልጣን አይደለም። በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ታናሽ የሆነ ሰው፣ ሀብት ካለው፣ የሁለት የሶስት ጊዜ ታላላቆቹ እያሉ ወማ ወይም ዳይና ሆኖ መሰየም ይችላል። *ለማሽነት (ለፊዜነት)* ግን ይህ ፈፅሞ አይሞከርም። ለምን ቢባል ምክንያቱ *ማሽነት (ፊዜነት)* ለታላቅ እንጂ ለታናሽ የማይሰጥ ሥልጣን በመሆኑ ነው።

በምርጫ ህገ ደንብ መሰረት፣ አንድ ሰው *ማሽ* ሆኖ ለመመደብ፣ ከፍ ሲሉ ከተጠቀሱት የወል መስፈርቶች በተጨማሪ የሚከተሉትን ሶስት መስፈርቶች ሊያሟላ ይገባል። አንደኛ፡- ለወላጆቹ የመጀመሪያ (ታላቅ) ወንድ ልጅ ሊሆን ይገባል። ሁለተኛ፡- ለጎሳው መገኘት ምክንያት ነው ወይም ጎሳውን አስገኝቷል ከሚባል ቤተሰብ (ቡርጂኛው እንዲህ ዓይነቱን ቤተሰብ *ጫሪንካ ጀራ* ሲል ለቤተሰቡ ታላቅ ለሆነ ወንድ ልጅ ደግሞ *ጫሪንታ ቃላ* ይላል) ሊወለድ ይገባል። ሶስተኛ፡- ወላጅ አባቱ በህይወት የሌለ ወይም አባቱ የሞተበት ሰው ሊሆን ይገባል። በቡርጂ ባህላዊ ደንብ መሰረት አንድ ሰው ወላጅ አባቱ በህይወት እያለ *ማሽ* ሆኖ ሊሰየም ፈጽሞ አይችልም (ጌታሁን፣ 1999፣ 25)። በአጭሩ *ማሽ* ለመሆን በተለይ እነዚህ ሶስቱ መስፈርቶች የግድ ሊሟሉ ይገባል። ከሶስቱ አንዱን ያጎደለ *ማሽ* ሆኖ ሊመደብ አይችልም።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት በምርጫና በባሻ ሥርዓት ወደ ሥልጣን የሚመጡ ባህላዊ መሪዎች እንዲያሟሉ የሚፈለጉ መስፈርቶች ናቸው። ከዚህ ቀጥለን በባሻ ሥርዓት የማይካፈሉ፣ በምርጫ ብቻ ወደ ሥልጣን የሚመጡ ባህላዊ መሪዎች ሥልጣኑ ላይ ለመመደብ ሲፈልጉ ሊያሟሉ የሚገቧቸውን ነጥቦች እናያለን።

*ኣንሽ፣ ጎርስ፣ ሃዩ፣ ኣርጉማንቾ እና ኦለይንካ (ገሪኤንካ)* ኣና በባሻ ሥርዓት የማይካፈሉ፣ በምርጫ ብቻ ሥልጣን የሚይዙ ባህላዊ መሪዎች ናቸው። *ኣንሽ* ለአንድ ጎሳ መሪ ለሆነ ሰው የሚሰጥ *ማዕረግ* ነው። *ኣንሽ* የሚመረጠው ከጎሳው አባላት መካከል ሲሆን፣ የፖለቲካ እውቀት፣ የንግግር ችሎታና የማስተዳደር ብቃት ለኣንሽነት የሚያበቁ መለኪያዎች ናቸው። የኣንሽ ዋና ተግባር የጎሳውን አጠቃላይ አስተዳደራዊ ተግባራትን በኃላፊነት መምራት (ክፍል 4.4.2.1 ተመልከት) በመሆኑ ሰውን የማግባባትና ተናግሮ የማሳመን ችሎታ፣ ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ብቃት ዋነኛ መለኪያዎች ይሆናሉ። ከጐሳው መካከል ‹‹በመጀመሪያ የተፈጠረ፣ ጎሳውን ያስገኘ ነው›› ተብሎ ከሚታመን ቤተሰብ መወለድም

ለኣንሽነት ከሚያበቁ መስፈርቶች መካከል ተጠቃሽ ነው፡፡ በአጭሩ፣ አብዛኛው የኣንሽ ሥልጣን በችሎታ የሚሰጥ እንጂ በውርስ የሚገኝ አይደለም፡፡

ሃዩና ኣርጉማንቻ ሆኖ ለመመረጥ ደግሞ የጎሳ ማንነት ቀዳሚ መለኪያ ነው፡፡ በቡርጂ ባህላዊ ህገ ደንብ ማንም ሰው ሃዩ ሆኖ ሊመደብ አይችልም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ሃዩን የማስመደብ ሥልጣን ለተወሰኑ ጎሳዎች ብቻ ተከልሎ የተሰጠ በመሆኑ ነው፡፡ በቡርጂ ልማድ የሃዩ ሥልጣን የራሱ ባለቤት፣ የራሱ ጎሳ አለው፡፡ የዚህ ጎሳ አባል ያልሆነ አንድ ሉብ የቱንም ያህል ጠንካራ ቢሆን እንኳን፣ ሃዩ ሆኖ ሊመደብ አይችልም፡፡ ሃዩ ለመሆን የዚህ ሥልጣን ባለቤት ከሆነው ጐሣ ሊወለድ ይገባል፡፡ ይህ ማለት ግን የዚያ ጐሣ አባል መሆን ብቻውን ለሃዩነት ያበቃል ማለት አይደለም፡፡ ሌሎች መስፈርቶችም አሉ፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ወይም በራሱ የሀግ አባላት ዘንድ ያለው ተደማጭነት፣ ግለሰቡ በሶስት ወሩ የግርዛት ቆይታው ወቅት ያሣየው ባህርይና ተሣትፎ፣ አባላቱን አስተባብሮ የመምራት ብቃትና ታታሪነት ለሃዩነት የሚያበቁ መመዘኛዎች ናቸው፡፡ እነዚህን ሙሉ በሙሉ ወይም በአብዛኛው ያሟላ ሰው ሃዩ ሆኖ ይሰየማል፡፡ የሃዩ ሥልጣን የእድሜ ልክ ነው፡፡ ግለሰቡ በእድሜ ወይም በበሽታ ምክንያት መስራት ባለመቻሉ ሥልጣኑ ለሌላ ሰው ተላልፎ እንዲሰጥ ራሱ ጥያቄ ሲያቀርብ ካልሆነ በስተቀር የቀድሞው ሃዩ በህይወት እያለ ሌላ ሃዩ አይመደብም፡፡ አዲስ ሃዩ የሚመደበው የመጀመሪያው ሃዩ የሞተ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ተተኪው ሃዩ የሚመደበው ግን የቀድሞው ሃዩ ከተመደበበት የሀግ አባላት ሣይሆን ተረኛ ከሆነው ከሌላ የሀግ አባላት መካከል ይሆናል፡፡ ከእነዚህም ቢሆን ሃዩ ሆኖ የሚመረጠው ለዚህ ሥልጣን ከተሰጣቸው ጐሣዎች መካከል ከአንዱ ጎሳ የተወለደ ብቻ ነው[38]፡፡ ቀደም ሲል ወማ፣ ዳይና ወይም ማሽ ሆኖ ማገልገልና የአገልግሎት ጊዜን ጨርሶ መቀመጥ አንድን ሰው ለጎርስነት (ለአማካሪነት) የሚያበቃ ብቸኛው መስፈርት ነው፡፡

[38] ዛሬም ቢሆን የሚሠራው እንዲሁ ነው፡፡ ሃዩ የሚመደበው ከተወሰኑ ጐሣዎች ነው፡፡ ይህ አሠራር በአሁኑ ጊዜ ችግር ገጥሞታል፡፡ በቡርጂ በአንዱ ቦሄ /ቀበሌ/ ውስጥ ነው፡፡ አሁን በዚህ ዓመት፣ በ2002 ዓ/ም መሆኑ ነው፡፡ አንዱን ሰው አንስተው ሃዩ አድርገው ይመድቡታል፡፡ ይህን ያየ ህዝብ ተቃውሞ ያሠማል፡፡ የአካባቢው አዛውንቶችና ሥርዓቱን ጠንቅቀው የሚያውቁ ግለሰቦች ‹‹ሃዩ የሰየማችሁት /የመደባችሁት/ ደንቡንና ሥርዓቱን ባልተከተለ መንገድ ነው፡፡ ስለሆነም በደንቡ መሠረት ሥሩ፡፡ አሰራሩን ወደ ደንቡ መልሱት›› ይላሉ፡፡ ይህ ሊባል የተቻለው አዲሱ ሃዩ የሌላ ጎሣ አባል በመሆኑ ነው፡፡ አዲሱ ሃዩ የተመደበው ሃዩን የመመደብ ሥልጣን ካላቸው፣ ከጥንት እስከዛሬ ድረስ ሃዩ ከሚመደቡባቸው ጎሣዎች ውጭ ከሆነ ጎሣ ነው፡፡ የህዝቡም ሆነ የሹማምንቱ /የአዛውንቶቹ/ ጥያቄ ይኸው ነው፡፡ ‹‹አዲሱ ሃዩ መመደብ ያለበት የዚህ ባለቤት ከሆኑት ጎሣዎች መካከል መሆን አለበት›› ነው ጥያቄያቸው፡፡ ሃዩን የመመደብ ሥልጣን ያላቸው፣ ጥያቄው የቀረበላቸው ወገኖች ምን ያድርጉት? ሃዩውን ከእነዚያ ከታወቁ ጎሣዎች መመደብ እንደነበረባቸው አላጡትም፡፡ ያውቁታል፡፡ ግን ምን ያድርጉት? እነዚያ ቀደም ሲል ሃዩ የሚመደብባቸው ጎሣዎች በሙሉ በአሁኑ ወቅት የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮች ሆነዋል ወይም ናቸው፡፡ ፕሮቴስታንቶች ደግሞ ማነኛውንም ባህላዊ ሥርዓት በጅ አይሉም፡፡ በሥርዓቱ ውስጥም እንዲሣተፉ አይፈቀድላቸውም፡፡ እነዚህ ጎሣዎችም /ቤተሰቦችም/ ቢሆኑ ‹‹ከመካከላችን ሃዩ አንሰይምም፡፡ ሃዩ አንሆንም፡፡ የምንከተለው እምነትም ይህንን እንድናደርግ አይፈቅድልንም›› አሉ፡፡ በዚህ የተነሣ ሥርዓቱ ችግር ገጠመው፡፡ የሚያደርጉትን ቢያጡ፣ ሃዩን የግድ መመደብ ስለነበረባቸው፣ከሌላ ጎሣ ሃዩ መደቡ፡፡ ይህም ከህዝቡ ተቃውሞ አስከተለ (ጫሜ፣ 2002፣ 45 - 46)፡፡

4.3.3. የምርጫ ሥርዓት

ምርጫ፣ ፖለቲካዊ (አስተዳደራዊ) ተግባራትን የሚያከናውኑ የህዝብ መሪዎች በሙሉ ወደ ሥልጣን የሚወጡበት ሌላው መንገድ እንደሆነ ጠቅሰናል፡፡ ምርጫ ሲባል ግን እንደ ዘመናዊ የምርጫ ሥርዓት ህዝብ በነቂስ ወጥቶ ድምፅ የሚሰጥበት፣ አብላጫ ድምፅ ያገኘ አሸናፊ የሚሆንበት፣ ወዘተ ሥርዓት ነው ማለት አይደለም፡፡ የቡርጂ ባህላዊ የምርጫ ሥርዓት ከዚህ፣ ከዘመናዊ የምርጫ ሥርዓት በእጅጉ የተለየ፣ የራሱ ሂደትና ደንብ ያለው ነው፡፡

በቡርጂ ባህላዊ የምርጫ ሥርዓተ ደንብ መሰረት እጩ ተወዳዳሪዎችን የመመልመልም ሆነ የመምረጥ ሥልጣን ለአንድ ወይም ለተወሰኑ ክፍሎች የተሰጠ እንጂ፣ የህዝብ ሥልጣን አይደለም፡፡ ህዝብ ወጥቶ መሪዎቹን አይመርጣቸውም፡፡ ወይም ድምፅ አይሰጥባቸውም፡፡ በአብዛኛው የህዝብ መሪዎችን የመመልመልና የመምረጥ ሥልጣን ያላቸው *ቢታና* (በብዙ ቁጥር ሲጠሩ) ወይም *ቢታናቾ* (በነጠላው ሲጠራ) በሚል ማዕረግ የሚታወቁ ሹሞች ናቸው፡፡ ከቢታናች ሌላ ቤተሰብ፣ ጎሳ፣ ጎርሶማ እና ወማ በተወሰነ ደረጃ የህዝብ መሪዎችን የመመልመልም ሆነ የመምረጥ ሥልጣን ያላቸው ክፍሎች ናቸው፡፡ የዚህ ክፍል ዋና ትኩረትም የቡርጂ ባህላዊ የምርጫ ሥርዓቶችን፣ ደንቦችንና የአፈጻጸም ሂደቶችን በቅደም ተከተላቸው ማሳየት ይሆናል፡፡ ለአቀራረብ እንዲመች ሲባልም በሁለቱም መንገዶች ወደ ሥልጣን ለሚመጡ መሪዎች የሚደረገውን የምርጫ አፈፃፀም ሥርዓትን ለብቻው፣ በአንዱ መንገድ ብቻ ወደ ሥልጣን የሚመጡትንም እንዲሁ ለብቻ ለማቅረብ ይሞከራል፡፡ በባሻ ሥርዓት ውስጥ የሚያልፉ ባህላዊ መሪዎችን ለመመደብ የሚደረጉት የምርጫ ሥርዓቶች በአብዛኛው ተመሣሣይ ናቸው፡፡ በመሆኑም ድግግሞሽን ለማስወገድ ሲባል አቀራረባችን በአንዱ የሥልጣን ቦታ ላይ የሚደረገውን ባህላዊ የምርጫ ሥርዓትን ብቻ እንደ ማቀንቀኛ ይዞ የሚተርክ፣ ሌሎቹንም በዚያ ዙሪያ በማምጣት አንድነታቸውንና ልዩነታቸውን እየጠቀመ አጠቃላይ ሥርዓቱን ለማሳየት የሚሞክር ይሆናል፡፡ የተለየ የምርጫ ሥርዓት ያላቸውን ግን ለይተን፣ ለብቻቸው እናቀርባቸዋለን፡፡

*ኤላዎች ማለትም ወማ፣ ዳይና፣ ማሻ (ፊዚ)፣ ጋናና ጃልዓባ* በምርጫና በባሻ ሥርዓት የሚሰየሙ ባህላዊ መሪዎች እንደሆኑ ተናግረናል፡፡ የሁሉም ባህላዊ መሪዎች የምርጫ ሥርዓት የሚካሄደው በተመሣሣይ ወቅት ይሆናል፡፡ የተወሰኑ ወገኖች ለወማ ሥልጣን በሚፎካከሩበት በዚያው ወቅት፣ በሌላ ወገን ለዳይናነት ወይም ለማሻነት ወዘተ. የሚወዳደሩ ክፍሎች ይኖራሉ፡፡

ከሁሉም በፊት በማንኛውም የሥልጣን ቦታ ላይ መወዳደር የሚፈልግ ሰው ‹‹ለዚህ ቦታ እንዲወዳደር ይፈቀድልኝ›› ወይም ‹‹ይህ ሥልጣን ይሰጠኝ›› የሚል ጥያቄ ይዞ ከሚመለከተው አካል ዘንድ ሊቀርብ ይገባል፡፡[39] የምልመላም ሆነ የምርጫ ሂደቶች የሚጀምሩት ከዚህ በኋላ ይሆናል ማለት ነው፡፡ *ሥልጣን ፈላጊው* ለቤተሰቡ የመጀመሪያ ልጅ ሲሆን ለወላጅ አባቱ፣ ታናሽ ሲሆን ደግሞ ጥያቄውን የሚያቀርበው፣ መልካም ፈቃዱን የሚጠይቀው በመጀመሪያ ለታላቅ ወንድሙ ቀጥሎ ለወላጅ አባቱ ይሆናል (ይህ ግን *ለማሽነት* ወይም *ለፊዜነት* *ሥልጣን* ሲሆን የማይሰራ መሆኑን ልብ ይሏል)፡፡ ከቤተሰቡ የ‹‹ፈቅደናል›› ምላሽ ካገኘ በኋላ እንደገና ጥያቄውን *ለኣንሽ* ወይም *ለጎሳንካ ኣናው* (ለጎሳ መሪው) ያቀርባል፡፡ በቡርጂ ባህላዊ የምርጫ *ሥርዓት* ውስጥ ጠንካራ መሰናክል አለ ቢባል ከዚህ ላይ ነው፡፡ *ጎሳንካ ኣናውም* ከሌሎች ከጎሳው ሹማምንትና ሽማግሌዎች ጋር በጥያቄው ዙሪያ ይወያያል፡፡ የጎሣው ሹማምንትም የጠያቂውን ባህርይ፣ የሥራ ብቃቱንና ችሎታውን፣ ወዘተ. በሚገባ ይገመግማሉ፡፡ ባህላዊ እውቀቱን፣ ጥንካሬውን፣ የንግግር ችሎታውንና ብልሃቱን ይመረምራሉ፡፡ ግለሰቡ ወደፊት በሥልጣን ዘመኑ የሚያገኘው ክብር የጎሳው ክብር፣ የእሱ ውርደት የጎሳው ውርደት ስለሚሆን፣ ለጎሳው ስምና ክብር ሲሉ፣ በጉዳዩ ላይ በእርጋታ ይመክራሉ፡፡ ለዚህ ሲሉም የጎሣውን ያለፈን ተያያዥ ታሪክ ወደ ኋላቸው ተመልሰው ይፈትሻሉ፡፡ በጎሣው ታሪክ ቀደም ሲል ባሻ የወሰደ (ሥልጣን የያዘ ሰው) መኖር አለመኖሩን ያጠናሉ፡፡ ካለ በሥልጣን ዘመኑ በህዝቡ፣ በአገሩ ላይ የደረሰ ክፉ ወይም ደግ ክስተት ምን እንደነበረ ያጣራሉ፡፡ አጣርተው ሲያበቁ ወይም ጠያቂው እነዚህንና ሌሎች መስፈርቶችንም ያሟላል ብለው ሲያምኑ አስጠርተውት ውጤቱን ይገልጹለታል፡፡ በጠየቀው የሥልጣን ቦታ ላይ እንዲወዳደር የጎሣው ፍላጎት እንደሆነ ይነግሩታል፡፡ ፍላጎቱና ምኞቱ እንዲሳካለትም መርቀውት ወደሚቀጥለው አካል ይሰዱታል፡፡

የአፈፃፀም ልዩነት ያለው ከዚህ ላይ ነው፡፡ ውድድሩ *ለማሽነት (ለፊዜነት)* እና ከዚያ በታች ላለው የስልጣን ቦታ ከሆነ ከጎሳው መሪ ቀጥሎ ጥያቄው መቅረብ ያለበት *ቢታናች* በሚል ማዕረግ ለሚጠራውና ዋነኛ የምርጫ አስፈጻሚ ለሆነው ሹም ይሆናል፡፡ *ለወማነትና ለዳይናነት (ለጋሪንታ ዳይናነት)* ሥልጣን የሚወዳደሩት ግን ጥያቄያቸውን ለቢታናች እንዲያቀርቡ

[39] ለዳይናነት ሲሆን ግን ይህ አባባል ሁልጊዜ ትክክል አይሆንም፡፡ ትክክል የማይሆነውም ዳይናነት ሣይፈለግም፣ ሣይጠየቅም የሚሰጥበት ሁኔታ (አሰራር) ስላለ ነው፡፡ በድሮ ዘመን ወማው፣ አንድን ሰው ‹‹ሀብታም ነው፤ በቂ ሀብት ንብረት አለው›› ብሎ ሲገምት የራሱን ሉብ (ፖሊስ) በፈረስ አድርጎ ከሀብታሙ ሰው ዘንድ ይልካል፡፡ ሉብም በፈረስ እየጋለበ መጥቶ ከሀብታሙ ሰው ላይ ሣር ይነሰንስበታል፡፡ በዚህም ሀብታሙ ሰው ለዳይናነት በወማው መታጨቱን ወይም መመረጡን ያበስርለታል፡፡ ሀብታሙ ሰው ሥልጣኑን ፈለገም አልፈለገ፣ መልዕክተኛውን በሚገባ አብልቶና አጠጥቶ ይሰዳል፡፡ ሀብታሙ ሰው በወማው ምርጫ የሚስማማ ከሆነ አስፈላጊውን መሰናዶ አድርጎ ከወማው ዘንድ ይሄዳል፡፡ ካልተስማማ ደግሞ ዝም ይላል፡፡ ዝም ብሎ ከቤቱ ይቀመጣል፡፡ ወደ ወማው አይሄድም፡፡ ወማው ከሀብታሙ ሰው ምላሽ ጠብቆ ካጣ እንደገና ሉባውን ከሀብታሙ ሰው ዘንድ ይልክበታል፡፡ ይህን ጊዜ ግን፣ ሀብታሙ ሰው ሥልጣኑን ባይፈልገውም፣ የወማውን ፈቃድ ለማሟላት ሲል ብቻ ምርጫውን ይቀበላል፡፡ ከወማው ዘንድ ወርዶ አስፈላጊውን ካሟላ በኋላ ለባሻው ሥርዐት መዘጋጀት ይጀምራል፡፡ ከዚያም ዳይና ሆኖ ይሰየማል፡፡ በቃ፡፡ በድሮ የምርጫ ደንብ እንዲህ አድርጎም ዳይና ይኮን ነበር፡፡

አይገደዱም። ባህላዊ የምርጫ ደንቡም አይፈቅድላቸውም። የእነርሱ ቦታ ሌላ ነው። ስለሆነም ከጎሳቸው ይሁንታ ያገኙትና ለወማነት ሥልጣን የሚወዳደሩት ጥያቄያቸውን የሚያቀርቡት *ለጉልጉቤይካ ጎርሶማው* ወይም *ለኣንሸ ጎርስ* ይሆናል። *በጎርሶማው* የተመረጠ እጩ ተወዳዳሪም የምርጫው አሸናፊ ይሆናል። ለቀጣዩ፣ *ለባሻ ሥርዓትም* ከወዲሁ መዘጋጀት ይጀምራል። ውድድሩ *ለዳይና ሥ*ልጣን ሲሆንም የአፈፃፀሙ *ሥ*ርዓት እንዲሁ ይለያል።

ለዳይና *ሥ*ልጣን የሚደረገው የምርጫ ስርዓት ሁለት መልክ አለው። አንደኛው የጥንቱ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የአሁኑ የምርጫ አፈፃፀም *ሥ*ርዓት ነው። የጥንቱ የሚባለው፣ ስርዓቱ ተቋርጦ እስከቆየበት እስከ 1995 ዓ.ም ድረስ ሲሰራበት የነበረው ሲሆን፣ የአሁን የሚባለው ደግሞ ስርዓቱ ተቋርጦ ከቆየ በኋላ፣ ዳግም ተግባራዊ መሆን ከጀመረበት ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ ወዲህ ያለውና አሁን የሚሰራበት ነው።

ከጎሳው ይሁንታ የተቸረው ግለሰብ፣ ከአሰበበት ለመድረስ ሁለት ወይም ሶስት ደረጃዎች ይቀሩታል። አንደኛው ግለሰቡን የወከለው አካባቢ ጎርሶማ ነው። ይህም ቢያንካ ጎርሶማ ይባላል። የቢያንካ ጎርሶማውን መልካም ፈቃድ ሲያገኝ ደግሞ ጋሪንካ ጎርሶማው ፊት ይቀርባል። እዚህ ድረስ ያለው የዳይና የምርጫ ስርዓት ጥንትም ሆነ ዛሬ ተመሳሳይ ነው። የሚለየው ከዚህ በኋላ ነው። ከጥንቱ እንጀምር።

በጥንቱ *ሥ*ርዓት፣ ከፍ ሲል የተጠቀሰውን ሂደት ያጠናቀቀ ዕጩ ተወዳዳሪ *ዳይና* ለመሆን *ከወማው* ዘንድ ሄዶ ደጅ ሊጠና፣ *በወማው* ሊመረጥ ይገባል። ለዚህ ሲልም *ከወማው* ቤት *ጉሱማ* (ውኃ ያልገባበት በቅል ያለ ድፍድፍ ቦርዴ) ወስዶ *ከጎላንዳው* (ሣሎኑንና ጓዳውን የሚለይ ግድግዳ) ላይ መስቀል ይኖርበታል። ከዚያ በፊት ግን ወማውን እንዲያግባቡለት የወማውን ረዳቶች ይማጸናል። ተማጽኖ ብቻ አይተውም። ደግሶ ሊያበላቸው፣ ሊያጠጣቸው ይገባል። ስጦታም እንዲሁ ይሰጣቸዋል። እነርሱም በፈንታቸው ‹‹እገሌ የሚባል ሰው ከአደባባይ ሊወጣ ፈልጎ ከደጅዎ እየዋለ ነው›› በማለት ግለሰቡ ስልጣን ፈላጊ መሆኑን ለወማው ይነግሩለታል። ወማውም ስለ ግለሰቡ ዝርዝር መረጃ እንዲነግሩት ይጠይቃቸዋል። በምላሻቸው ከረካ እጩ ዳይናው ከእሱ ዘንድ የሚቀርብበትን ቀን ቆርጦ ይነግራቸዋል። ምላሻቸው ካላረካው ደግሞ ስለ ግለሰቡ ዝርዝር ሁኔታ አጥንተው እንዲነግሩት ረዳቶቹን ያዛቸዋል። ለቦታው ጥያቄ ያቀረቡት ሰዎች ሁለትና ከዚያ በላይ ሲሆኑም እንዲሁ የተሻለውን መርጠው እንዲያቀርቡ ረዳቶቹን ያዛቸዋል።

ረዳቶቹም ከእያንዳንዱ እጩ ቤት ሄደው አኗኗራቸውን ይገመግማሉ፡፡ ያላቸውን የሀብትና የንብረት መጠን ያሰላሉ፡፡ በአካባቢው ህብረተሰብ ዘንድ ያላቸውን ተወዳጅነት፣ ተሰሚነት ያጠናሉ፡፡ የንግግር ችሎታቸውን ይመዝናሉ፡፡ ሌላም ሌላም ጉዳዮችን ይገመግማሉ፡፡ ሲመለሱም የግምገማቸውን ውጤት ለወማው ያሳውቃሉ፡፡ *ወማው* በሀሳባቸው፣ በምርጫቸው የተስማማ እንደሆነ ቀን ቀጥሮ ተመራጩን እጩ ዳይና ከቤቱ ያስጠራል፡፡

በቡርጂ ባህላዊ ህገ ደንብ መሰረት *የዳይናነት ሥልጣን* እንዲሰጠው *የወማውን* ደጅ የሚጠና ሰው ከወማው ዘንድ ሲሄድ *ካላችና ሊሶ* ይዞ ይሄዳል፡፡ ከወማው ፊት ሲቀርብም ወማው ‹‹ምን ፍለ*ጋ* መጣህ?›› ይለዋል፡፡ እሱም ‹‹ከአደባባይ ልወጣ ብዬ *መጣሁ*›› ይላል፡፡ ወማውም መልሶ ‹‹ደህና፡፡ እስቲ የደንባችንን አሰማና›› ይለዋል፡፡ ‹‹ባህላዊ የምርቃትና የፀሎት *ሥርዓቱን* አሰማን›› ወይም በቡርጂኛ ‹‹ሐሣዴ በል›› ሲለው ነው፡፡ በአጭሩ፣ ይህ ከወማው ዘንድ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚቀረብበት ዕለት ከባድ ፈተና ያለበት፣ የእጩ *ዳይናው* ብቃትና ችሎታ የሚፈተሽበት እለት ነው፡፡ እጩ *ዳይናው* ከወማው ግቢ ገብቶ አስፈላጊውን ባህላዊ *ሥርዓት* ፈጽሞ ወጥቶ እስከሚሄድ ድረስ የሚያደርጋቸው ማናቸውም ነገሮች ሁሉ አንድ በአንድ ይገመገማሉ፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ከወማው ቤት እንደገባ እንዲያኾጎደጉደው የሚጠየቀው ባህላዊው የምርቃትና የልመና *ሥርዓት (ሐሣዴ)* አከዋወኑ በሚገባ ይጠናል፡፡ አንዳች ሳያደናቅፈው፣ አንድ ቃል ሳይገድፍ፣ ቅደም ተከተሉን ሳያዛንፍ እንዲያነበንባቸው ይጠበቃል፡፡ ባለማወቅም ሆነ በአጋጣሚ *ሐሣዴ* በሚልበት ወቅት ቅደም ተከተሉን ያዛነፈ ወይም ቃል የገደፈ ወይም የሚባለው ጠፍቶት ያቋረጠ እንደሆነ ግን ከባድ ቅጣት ይጠብቀዋል፡፡ ባህላዊ ቅጣቱ ደግሞ ‹‹አንድ በሬ›› ወይም ስድስት የኢትዮጵያ ብር ነው፡፡ ልክ እንደዛሬው፣ በዚያ ዘመን ገንዘብ እንደልብ አይገኝም፡፡ ይህ ይሆናል ተብሎም ተይዞ አይኬድም፡፡ በዚህ ዓይነት ጥፋት የፈጸመ እጩ ዳይና አንድ በሬ (ስድስት ብር) እንዲቀጣ ይወሰንበታል፡፡ ቅጣቱን ወዲያው መክፈል ካልቻለ ደግሞ ታላቅ ክብር ያላቸውን፣ የስልጣኑ መለያ የሆኑትን *ካላቹንና ሊሶውን* አውልቆ፣ ለወማው ያስረክባል፡፡ ወይም ተወርሶበት ባዶ እጁን ወደ ቤቱ ይመለሳል፡፡ በዚህም ብዙ የለፋበት፣ የደከመበት፣ አንጡራ ሀብቱን ያሟጠጠበት *ሥልጣንና* ክብር ሁሉ መና ይቀራል፡፡ ይህን በመፍራትም በዚያን ዘመን በርካታ ስልጣን ፈላጊዎች ባህላዊ *ሥርዓቱን* ጠንቅቀው የሚያውቁ ሰዎችን እየያዙ ከወማው ዘንድ ይቀርቡ እንደነበር ይነገራል[40] ፡፡

---

[40] ተቋርጦ የነበረውን ፣ የባህላዊ አስተዳደር ስርዓትን እንደገና ለማስጀመር ሲባል በተካሄደው፣ በጉል ጉበይንካ ጎርሶማ ላይ ስሙ ያልተጠቀሰ አንድ የሌሞ ቦሄ ተወካይ የሆነ የጎርሶማው ተሳታፊ ከተናገረው የተወሰደና ተቀናብሮ የቀረበ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት *የዳይናን* ስልጣን የሚሰጥ *ወማ* የለም። ተቋርጦ የቆየው የወማ መዋቅር ዛሬም እንዳይቀጥል *‹‹ጉልጉቤይንካ››* *ጎርሶማው* ተስማምቷል። በመሆኑም *ጋሪንካ* ጎርሶማው *ወማውን* ተክቶ የዳይናን ስልጣን ለሚፈልጉት እንዲሰጥ ተወስኗል። አሁን የሚሰራው እንዲህ ነው። ለዳይናነት ‹‹ምረጡኝ›› የሚል ጥያቄ፣ በደረጃ ለሚገኙ የምርጫ አካላት አቅርቦ ይሁንታ የተቸረው፣ በምርጫ ያሸነፈው ግለሰብ፣ ጥያቄውን ይዞ ከጋሪንካ ጎርሶማው ፊት ቆሞ *ካራ ባኡዎ ሺንስ ዱሩ ቃደዶ* (ከአደባባይ መውጣት ፈልጌ ከፊታችሁ ቆሜያለሁ) በማለት ፍላጎቱን ያሳውቃል። ጎርሶማውም በጥያቄው ላይ ይመክራል። ግለሰቡ ከስር ያሉ ደረጃዎችን በአግባቡ አልፎ መምጣቱን የጎሳውን መሪ በማነጋገር ያጣራል። ከዚያ በኋላ ጉባኤተኛው ‹‹ሰምተንሀል። አይተንሃል። አንተ የእኛው ነህና ተቀብለንሃል›› በማለት ውሳኔያቸውን፣ መስማማታቸውን ያሣውቁታል። በመጨረሻም *ሃያ ሀራዳዴይ ኒንሣ አሴሲታ* ‹‹በላ! ከዚህ ከተቀመጥንበት አስነስተህ ሸኘና፣ አሰናብተና!›› ይሉታል። ይህን ማለታቸው አንድም፣ ‹‹ጋብዘን፤ እህል ውሃ በለን። ወይም በልተን፣ ጠጥተን የምንመርቅበትን ነገር አቅርብልን›› ማለታቸው ነው። በቡርጂ ባህላዊ ደንብ የሚመረቀው ተበልቶ፣ ተጠጥቶ ነው። በባዶ፣ በደረቁ እርግማን እንጂ ምርቃት የለም። አንድም፣ እንዲያውም በዋናነት፣ ‹‹ከአሁን ጀምረህ መሪያችን ነህ›› ማለታቸው፣ እውቅና መስጠታቸው ነው። *ጎርሶማው* የህዝብ ተወካዮችን ያሰባሰበ ሸንጎ ነው። የጎርሶማው ሰብሳቢ ደግሞ *ዳይናው* ነው። *ዳይናው*፣ ሰብሳቢው ሣያሰናብት ጉባኤው አይበተንም። ‹‹ከተቀመጥንበት አስነሳና›› ማለታቸውም ‹‹ከአሁን ጀምረህ የመሪነቱን *ሥ*ልጣን ተረክበህ ምራን›› ሲሉ እንጂ የምር እርቧቸው ወይም ጠምቷቸው አይመስለኝም። የአሁኑ *ዳይናነት* ብዙ ወጭ የለበትም። ከጥንቱ የሚለየው አንዱ ነጥብ ይህ ነው።

ይህን ሲሉ እጩ ዳይናው አንድ መቶ ብር አውጥቶ ይሰጣቸዋል። በብሩ በልተውበትና ጠጥተውበት ይመርቁታል። *ሱቡሮ* ወጥቶ ስልጣኑን በይፋ የሚረከብበትንም *(የባሻን)* ቀን ያሣውቁታል። እሱም ከዚያን ቀን ጀምሮ ለባሻው *ሥ*ርዓት ዝግጅት ማድረግ ይጀምራል።

ለወማነትና ለዳይናነት እንዲህ ምርጫ በሚደረግበት ወቅት *ከዳይናው* ወደታች ላሉት ቦታዎችም *(ለጋናነት፣ ለማሻነትና ለጃልዓባነትም)* እንዲሁ በሁሉም አካባቢዎች ምርጫ ይካሄዳል። ከፍ ተብሎ እንደተጠቀሰው በምርጫው ላይ ለመወዳደር የጎሣቸውን ይሁንታ ያገኙት የበታች ሹማምንት እንደ *ዳይናው* በቀጥታ *ከጎርሶማው* ፊት አይቀርቡም። ከዚያ በፊት *ጉሱማ* ይዘው *ከቢታናቹ* ቤት ይሄዳሉ። *ጉሱማውን* ከቤቱ *ጎላንዳ* ላይ ሰቅለው፣ ጎላንዳውን ስመው (ተሳልመው ማለትም ይቻላል) ይመለሳሉ። ውጤቱ እስከሚገለጽላቸው ድረስ ይህንን ተግባር ለበርካታ

ጊዜያት ይከውኑታል፡፡ ውድድሩ የሚካሄደው በተለያዩ አካባቢዎች ለሚገኙ የሥልጣን ቦታዎች የመሆኑን ያህል ጉሱማውም (አቤቱታውም) እንዲሁ የሚቀርበው በየአካባቢው ለሚገኙ ቢታና ይሆናል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለጸው ለአንድ ቦታ ሁለትና ከዚያ በላይ ተወዳዳሪዎች ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ በዚህ መልክ ለቢ ታናች ጥያ ቄ ከሚ ያቀርቡ ተ ወዳዳሪዎች መካከል ብዙው ን ጊዜ አሸናፊ ሆኖ የሚመረጠው ከሁሉም ቀድሞ ከቢታናቹ ቤት ጉሱማ ወስዶ የሰቀለ ሰው ይሆናል፡፡ ከሁሉም ቀድሞ ጉሱማ የሰቀለ እያለ ሌላው የሚመረጥበት ሁኔታም አልፎ አልፎ አለ፡፡ ይህ የሚሆነው በተለያዩ ምክንያቶች ግለሰቡ ለቦታው ብቁ አይደለም ወይም መመዘኛውን አያሟላም ተብሎ ሲታመን ነው፡፡ ቢታናቹ አሸናፊውን የሚመርጠው ከባለጋንና ከኣንሽ ጋር እየተማከረ ነው፡፡ መርጦ ሲያበቃ በደረጃ ላለው ጎርሶማ አቅርቦ ያፀድቃል፡፡ ሲፀድቅለትም ከአሸናፊው ቤት ሄዶ *ዳዋኖ* በመዝፈን ተወዳዳሪው በውድድሩ አሸናፊ መሆኑን፣ መመረጡን ያበስርለታል፡፡ ለባሻው ሥርዓት ከወዲሁ እንዲዘጋጅ ጭምር ይነግረዋል፡፡ በውድድሩ ለተሸነፈው ወገን ደግሞ ‹‹ለከርሞ ጠብቅ፣ ዘንድሮ አልተሳካልህም›› በማለት ይነገረዋል፡፡ ይህን ጊዜ ሁለቱም ወገኖች ውጤቱን (ውሳኔውን) በፀጋ ይቀበላሉ፡፡ ያሸነፈው ከቤቱ ደግሶ *ዳዋኖ* [41] የሚባል ዘፈን ያዘፍናል፡፡ *ወማ፣ ዳይና፣ ማሻ...ወዘተ* ሆኖ መመረጡን በይፋ ያሳውጃል፡፡ ለስልጣን እርክክቡም ከወዲሁ መዘጋጀት ይጀምራል፡፡ በምርጫው ውድድር የተሸነፈውም ቢሆን *‹‹ለምን ተሸነፍኩ?››* ብሎ ‹‹ዘራፍ!›› አይልም፡፡ ወይም ጦር አያነሳም፡፡ አይሸፍትም፡፡ አያምፅም፡፡ አያኮርፍም፡፡ ይልቁን መሸነፉን በጸጋ ተቀብሎ ምልስ ይላል፡፡ ከቤቱ ገብቶ ይቀመጣል፡፡ የአሸናፊውን አሸናፊነት ተቀብሎ፣ በእሱ ስር ይተዳደራል፡፡ በእነዚህ በሁሉም የሥልጣን ቦታዎች ላይ ውድድሩ የሚካሄደው ግን፣ የቀድሞዎቹ መሪዎች የስልጣን ዘመን ከማብቃቱ አስቀድሞ ነው፡፡

*ኣንሽ፣ ጎርስ፣ ሃዩ፣ ኣርጉማንቾ እና ኦለይንካ ኣና በባሻ ሥርዓት* ውስጥ ማለፍ ሣይጠበቅባቸው፣ በምርጫ ብቻ የሚመደቡ ባህላዊ የአስተዳደር መሪዎች መሆናቸውን ገልጸናል፡፡ *የኣንሽ ሥ*ልጣን ሁለት ዓይነት ነው፡፡ አንደኛው *ሥ*ልጣኑ በዘር ሀረግ ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍ ሲሆን፣ ሌላው በምርጫ የሚሰጥ *ሥ*ልጣን ነው፡፡ *ሥ*ልጣኑም እንዲሁ በጊዜ ያልተገደበ፣ የእድሜ ልክ ነው፡፡ ‹‹*ሥ*ልጣኑ የእድሜ ልክ ነው›› መባሉም *የኣንሽ* ስልጣን የሚያበቃው ግለሰቡ ሲሞት ብቻ መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን ሁሉም *ኣንሾች* ወደ ስልጣን የሚመጡት በምርጫ ነው

[41] በቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካ ሥዓት ውስጥ ወማ፣ ዳይና፣ ማሻ፣ ጋና፣ ጃልዐባ እና ኣንሽ ሆነው ለሚመረጡ ባለስልጣናት ክብር ሲባል የሚዘፈን የሀገረሰባዊ ዘፈን መጠሪያ ነው፡፡ *ዳዋኖ* የሚዘፈነው ሹማምንቱ ወደ ሥልጣን ሲመጡ (በባሻ ስርዐት ወቅት) እና ሲሞቱ (በቀብራቸው ወቅት) ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ በሌላ ጊዜና በሌላ ቦታ፣ ለሌላ ሰውና ለሌላ ዓላማ አይዘፈንም፡፡

ማለት አይደለም። ዘለዓለማዊ የሆነ፣ በዘር ሐረግ ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍ የኣንሽ *ሥልጣንም* እንዲሁ ቡርጂ ውስጥ አለ። በዚህ *ሥርዓት* የሚተዳደሩ *ኣንሾች* በቁጥር ሁለት ናቸው። እነዚህም፣ አንደኛው በተለምዶ *ቡርጂ* በሚባለው አካባቢ (ማለትም *ኦቶማሎን* ይዞ ወደ ታች እስከ *ክሊቾ* ድረስ ባለው አካባቢ)፣ ሁለተኛው በተለምዶ *ጉባ* በሚባለው አካባቢ ማለትም *ከኦቶማሎ* በላይ ባሉ *በሳድሼና በየበን* ውስጥ የሚገኙ *ኣንሾች* ናቸው። እነዚህ ሁለቱ የኣንሽ ስልጣኖች በዘር ሀረግ ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፉ፣ የማይሻሩ፣ የማይለወጡ፣ በምርጫ የማይሰጡ ናቸው። የአብዛኞቹ ኣንሾች *ሥልጣን* ግን በምርጫ የሚሰጥና በጊዜ የተገደበ ነው። በቦታቸው ሌላ ሰው የሚተካው ሲሞቱ ብቻ ሲሆን፣ ከጎሣው አባላት መካከል አንድ ሰው ተመርጦ ሁሉም የጎሳው አባላት በተገኙበት በታላቅ *ሥነ ሥርዓት* ይሆናል። ለሥርዓቱ ሲባል ቦርዴ ይጠመቃል። *ኣርካሌ* (የቆጮ እንኩሮ) ይዘጋጃል። ኮርማ በሬ ይታረዳል። ከአዲሱ *ኣንሽ* ደጅም *ኤሣና* ሶስት ድንጋዮች በጎሣው አባላት ይተከላሉ። በኤሣው ላይ ቦርዴና ደም በመርጨት *የሒጣኖ ሥርዓት* ይፈጸማል። ተመራጩም ከግንባሩ *ካላቻ* ያስራል። ከእጁ ሲሶ ይይዛል። ለክብሩም *ዳዋኖ* ይዘፈንለታል። *ሙላ ቡልኮና ግላንግሌ* የክብር አልባሳቱ ይሆናሉ። ከዚያን ቀን ጀምሮ ደጁ *ሓላሲንታ ካራ* እየተባለ ይጠራል። ‹‹የተቀደሰ፣ የተባረከ ደጅ›› እንደማለት ነው።

ቡርጂዎች አንድ ባህላዊ ልማድ አላቸው። ቀደም ሲል የህዝብ *መሪ (ወማ፣ ዳይና እና ማሻ)* የነበረ ሰው የ*ሥልጣን* ዘመኑ ሲጠናቀቅ ‹‹በቃ! አገልግሎቱን ጨርሷል። *ሥልጣኑ* አብቅቷል›› ብለው ያንን ሰው አያገሉትም። ከባህላዊ የአስተዳደርና የፖለቲካ ጉዳዮች አያርቁትም። ይልቁን ልምዱን እንዲያካፍለው፣ እንዲያማክረው፣ የአሰራርና የአመራር *ሥርዓቱን* እንዲያለማምደው ለአዲሱ ሹም አማካሪ (ጎርሳ) አድርገው ይመድቡታል። አንድ ሰው ጎርስ ሆኖ የሚመደበው በዚህ *መንገድ* ነው። እንዲህ ዓይነት ሰዎች በቁጥር አናሳ ስለሚሆኑ በአንዳንድ ጥቃቅን ምክንያቶች (ለምሳሌ በበሽታ) ካልሆነ በስተቀር ብዙውን ጊዜ ሁሉም ቀደምት *መሪዎች* ጎርስ ሆነው ይመደባሉ።

*ሃዩ*፣ ማህበረሰቡ ለዚህ *ሥልጣን* ከሰጣቸው ጎሳዎች መካከል እንደሚመረጥና የ*ሥልጣን* ዘመኑም የእድሜ ልክ እንደሆነ ቀደም ስል ተናግረናል። አዲስ ሃዩ የሚመረጠው የቀድሞው ሲሞት ብቻ ነው። የቀድሞው ሃዩ ሲሞት ተረኞቹ የሀግ አባላት እንዲሰበሰቡ ይደረጋል። የሚሰበሰቡትም በቡርጂኛ *ሀግንካ ባልባላ* በሚባለው በራሳቸው አደባባይ ወይም ጽህፈት ቤት ውስጥ ነው። ሁሉም አባላት እንደተሰበሰቡ ከመካከላቸው ለሃዩነትና ለኣርጉማንቾነት ሁለትና በላይ እጩዎችን መርጠው እንዲያቀርቡ በአካባቢው ሹማምንት ይጠየቃሉ። አባላቱም

የተጠየቁትን ይፈጽማሉ። ሹማምንቱም በአባላቱ ከቀረቡት እጩዎች መካከል ከፍ ሲል የተመለከቱ መስፈርቶችን ይበልጥ የሚያሟላውንና ለቦታው ብቁ ነው ያሉትን አንዱን *ሃዩ* አድርገው ይመርጡታል። ከቀረቡት እጩዎች መካከል *ሃዩ* ሆኖ የተመረጠው ማን እንደሆነ በቡርጂኛ *ባንኤይሽ* በሚባል (በአማርኛ ምን እንደሚባል አላውቅም) የእንጨት ቅጠል የተመራጩን ጀርባ በመጠብጠብ ለአባላቱ ያሣውቃሉ። ከዚያም ለተመራጮቹና ለህግ አባላቱ ‹‹አገሩም፣ ህዝቡም፣ ንብረቱም ይኸውላችሁ። ከዛሬ ጀምራችሁ ጠብቋቸው›› በማለት የመከላከያ ኃይልነቱን ሥልጣን ያስረክቧቸዋል። ከዚያ በኂላ ይታረድና ይበላል። ይጠጣል። ይዘፈናል። አባላቱም ለሥርዓቱ ሲባል ከታረደው እንሰሳ ቆዳ ትንሽ በትንሹ ቆራርጠው በመከፋፈል እንደቀለበት በጣቶቻቸው ላይ ያጠልቁታል። በዚህም የሥርዓቱ ፍፃሜ ይሆናል። ኦለይንካ ኣና እና ገሪኤንካ ኣና በምርጫ ብቻ ከሚመደቡ ባህላዊ የፖለቲካ መሪዎች መካከል ተጠቃሾች ናቸው። ሁለቱም ሹሞች የሚመረጡት በነዋሪዎቹ ነው።

በአጠቃላይ *ኣንሽ፣ ጎርስ፣ ሃዩ፣ ኣርጉማንቾ እና ኦለይንካ ኣና (ገሪኤንካ ኣና)* በሥልጣን ላይ የሚመደቡት በባህላዊ የምርጫ ሥርዓት ብቻ ይሆናል። የተቀሩት *ወማ፣ ዳይና፣ ፊዜ (ማሻ)፣ ጋና* እና *ጃልዓባ* ግን ምርጫውን ቢያሸንፉም ያሸነፉበትን ሥልጣን መረከብ አይችሉም። ያሸነፉበትን ወንበር ለመረከብ ግን *ባሻ* የሚባለውን ባህላዊ ሥርዓት መፈጸም ይጠበቅባቸዋል።

### 4.3.4. የባሻ ሥርዓት

*ባሻ* በቁሙ ሣር ማለት ነው[42]። በዚህ አገባቡ ግን *ባሻ*፣ *ወማ፣ ዳይና፣ ፊዜ፣ ማሻ፣ ጋና* እና *ጃልዓባ* ሆነው ለመመደብ፣ ከፍ ብለን በጠቀስነው ምርጫ ተወዳድረው ያሸነፉት ባህላዊ መሪዎች፣ ያሸነፉበትን ሥልጣን በይፋ የሚረከቡበት፣ የህዝብ መሪ መሆናቸውን ለሚመሩት ህዝብ በይፋ የሚያሣውቁበት፣ የሚያሣውጁበት ሥርዓት ነው። *ባሻ*፣ አዲሶቹ የህዝብ መሪዎች የህዝብ አደራ የሚረከቡበት፣ ኃላፊነት የሚሸከሙበት፣ የሥልጣን ዘመናቸው የሰላም፣

---

[42] ደረቅ ሳይሆን እርጥብ፣ ለምለም ሣር። እርጥብ፣ ለምለም ሣር በቡርጂዎች ዘንድ ከእንስሳት መኖነት ባሻገር ከፍተኛ ባህላዊ ፋይዳ አለው። ሣር በቡርጂዎች ዘንድ የተጣሉትን ማስታረቂያ፣ እምቢተኛውን መመለሻ፣ ኃይለኛውን ማለዘቢያ … ወዘተ መሣሪያ ነው። ‹‹ካልሄድኩኝ፣ ሄጄ ካልታነቅሁ፣ ሰው ካልገደልኩ፣ ካልተደባደብኩ፣ በአጠቃላይ እኩይ ተግባር ካልፈፀምኩ ሞቼ እገኛለሁ›› ብሎ ለገላጋይ ያስቸገረን፣ በስንት አማልዕክት ስም ተለምኖ አሻፈረኝ ያለን ሰው፣ ቡርጂዎች በሣር የመመለስ፣ ከእኩይ ተግባሩ እንዲቆጠብ የማድረግ ልማድ አላቸው። እንዲህ ዓይነት ሰው ሲኖር አንድ ሰው (ወንድም ሴትም ሊሆን ይችላል) ለምለም ሣር ነጭቶ፣ ሣሩን በሁለት እጆቹ ይዞ ከፊት ለፊቱ በመቆም *ታ ባሻንካ ማጋና* … (ለዚህ ሣር ስትል ከድርጊትህ ተቆጠብ…) ያለው እንደሆነ ያ ሰው አልፎት አይሄድም። ምልስ፣ በረድ፣ ቅዝቅዝ ይላል። ከተግባሩ ይቆጠባል። ይህ የሚሆነው ሣር እርጥብ፣ ለምለም ነገር ሲለሆነ፣ እርጥቡን፣ ለምለሙን ሣር አልፎት የሄደ ሰው ዘሩ አይለመልምም፣ አይዋለድም፣ የዘራው አይበቅልም፣ ቢበቅልም ፍሬ አይሰጥም ተብሎ ስለሚታመን ነው። የህዝብ ባህላዊ መሪዎች፣ አዛውንቶች ወይም የከፍተኛው የህዝብ ሸንጎ አባላት በአንድ ጉዳይ ላይ ለመወያየት ወይም ዳኝነት ለማየት ሲሰበሰቡ የሚቀመጡት ለምለም ሣር ካለበት ቦታ ላይ ነው። ይህ ሣር በቡርጂኛ *ሃራዳ* ይባላል። ለምለም የሰርዶ ሣር ማለት ነው። አዛውንቱ፣ ሹማምንቱ ከሣር ላይ መቀመጣቸው፣ አገሩ ምድሩ እንደ ሣሩ እንዲለመልም፣ ህዝቡ እንዲበለጽግ፣ ዐቡ እንዲበርድ፣ ወዘተ. በሚል ነው። በቡርጂ ባህላዊ ልማድ አዛውንቱ፣ ሹማምንቱ ከድንጋይ፣ ወይም ሣር ካላበቀለ ባዶ መሬት ላይ ተቀምጠው አይወያዩም፤ አይዳኙም። እንዲህ ዓይነት ደረቅ ነገር (ቦታ) ላይ የሚቀመጡት ግን ለእርግማን ሲሆን ብቻ ነው። እርጥብ ሣር ሌላም ባህላዊ ፋይዳ አለው (ግርጌማ ቁጥር 57 ተመልከት)።

የብልጽግና፣ የጥጋብ፣ የጤንነት ወዘተ እንዲሆን ከህዝቡ ምርቃትና በረከት የሚቀበሉበት ባህላዊ *ሥርዓት* ነው። ቡርጂዎች ለአንድ ሰው *ኤቤሎንኮ ባሻ ጎና* (እገሌ ሣር ወሰደ) ሲሉ ‹‹እገሌ ባለሥልጣን ሆነ ወይም የህዝብ መሪ ሆኖ ተመደበ›› ማለታቸው እንጂ፣ የእውነት ‹‹ሣር አጭዶ ተሸከመ›› ማለት አይደለም። ባህላዊ *ሥርዓቱን ባሻ* ብለው መሰየማቸውም ከዚህ በመነሳት ነው - በመሪዎቹ ላይ ሣር ስለሚነሰነስባቸው። በአጭሩ አንድ ተወዳዳሪ በምርጫው አሸናፊ መሆኑ ከተገለጸበትና ከቤቱ *ዳዋኖ* ካዘፈነበት ቀን ጀምሮ፣ *ሱቡሮ* ወጥቶ ባህላዊ *ሥርዓቱን* ፈፅሞ ወደ ቤቱ እስከሚመለስበት ጊዜ ድረስ ያለው ባህላዊ *ሥርዓት* ነው - *የባሻ ሥርዓት* የሚባለው።

ከፍ ተብሎ እንደተጠቀሰው እንደ ምርጫ *ሥርዓት* ሁሉ፣ *የባሻ ሥርዓት*ም የሚፈጸመው በአንድ ቀን በአንድ *ሥፍራ* ላይ ነው። ሁሉም ባህላዊ መሪዎች ተወዳድረው ያሸነፉበትን *ሥ*ልጣን በይፋ የሚረከቡት፣ የህዝቡን አደራና በረከት የሚቀበሉት በአንድ ቀን በአንድ ላይና ቦታ ነው። ይህ የባሻ *ሥርዓት* የሚፈፀመው በዓመት አንድ ጊዜ፣ በቡርጂዎች የወር አቆጣጠር *ሥርዓት* መሰረት የመጀመሪያ በሆነውና ዶጎሌ በሚባለው (በየካቲት) ወር አካባቢ ነው። *ሥፍራው* ግን ይለያያል። *የወማነቱ* ስልጣን *በጋሚዮ ቦሄ* ነዋሪዎች እጅ በነበረበት ጊዜ *የባሻው ሥርዓት* በጋሚዮ ቦሄ ውስጥ፣ *ወሚንታ ኡራ* (የንጉስ ተራራ) ከሚባል ስፍራ ላይ ይፈፀም ነበር። *የክሊቾ ቦሄ* ሰዎች ስልጣኑን ከያዙ በኂላ ደግሞ የባሻው *ሥርዓት በክሊቾ ቦሄ* ውስጥ ይካሄድ ነበር። ከዚያ በኂላ ስርዓቱ እታች *ሴጎ* መሆኑ ቀርቶ እላይ ከሱቡሮ ላይ መካሄድ ጀመረ። እስከ ዛሬም ድረስ የሚፈጸመው ሱቡሮ ላይ ነው።

የባሻ *ሥርዓት* በሚፈጸምበት ዕለት ቡርጂ ውስጥ ታላቅ በዓል ይሆናል። ለዚህ ሲባልም በሁሉም ተመራጮች ቤት በሰፊው ይደገሳል። *ኣርካሌ* የሚባል ባህላዊ ምግብ ከቆጮና ከቡላ ይዘጋጃል። *ብርቃ* የሚባል ባህላዊ መጠጥ (ቦርዴ) ይጠመቃል። እርድም እንዲሁ ይኖራል።

ልክ እንደ የምርጫው *ሥርዓት* ሁሉ የቡርጂዎች የባሻ *ሥርዓት* ሁለት መልክ አለው ማለት ይቻላል። አንደኛው *ወማ* የአስተዳደሩ ቁንጮ በነበረበት በጥንቱ ዘመን የነበረው ሲሆን፣ ሁለተኛው *ዳይና* የአስተዳደሩ ቁንጮ በሆነበት በአሁኑ ጊዜ የሚፈጸመው የባሻ *ሥርዓት* ነው። ልዩነቱ ግን ይኸን ያህል የሰፋ አይደለም። መጠነኛ የ*ሥርዓት* ልዩነት ነው ያለው።

በጥንቱ የባሻ *ሥርዓት*፣ ዳይናው ከክብረ በዓሉ ቀን ቀደም ብሎ ለወማው (*ሥ*ልጣኑን ለሰጠው ወማ ማለት ነው) የሚገባውን ያደርግለታል። ለመመረጥ ሲል የሰጠውን የእጅ መንሻ

ሣይጨምር፣ አምስት የቁም ከብቶችን አምጥቶ ለወማው ይሰጠዋል፡፡ ሱቡሮ ከመውጣቱ በፊት ሌሎች የበታች ሹማምንትን አስከትሎ ከወማው ግቢ ሄዶ ከወማው ደጅ ያለውን ኤሳ ሊያድስ ይገባል፡፡ በክብረ በዓሉ ዕለት ግን ከሁሉም ፊት የሚሆነው አዲሱ ወማ እንጂ ዳይናው አይደለም፡፡ በመሆኑም ሁሉም ሥርዓቶች የሚመሩት በወማው አማካይነት ይሆናል፡፡

በአሁኑ *የባሻ ሥርዓት* ግን ይህ ሁሉ የለም፡፡ በአሁኑ ወቅት ወማ ስለሌለ ዳይናው ለወማው የሚሰጠው ክብት፣ ከወማው ደጅ የሚተክለው ኤሳ አይኖርም፡፡ በአዲሱ የአስተዳደር መዋቅር ደንብ መሰረት፣ የሁሉም ቁንጮው ራሱ ዳይናው ስለሆነ፣ በዕለቱ ማናቸውም ባህላዊ ሥርዓቶች የሚመሩት በእሱ አማካይነት ይሆናሉ፡፡ ከዚህ ውጭ ያሉት *የባሻ ሥርዓቶች* በአብዛኛው ተመሣሣይ ናቸው፡፡ ስለሆነም፣ ቀጥለን በአሁኑ ጊዜ በዳይናው ፊታውራሪነት የሚፈጸመውን የባሻን ሥርዓት ብቻ እንተርካለን፡፡ ልዩነቶች ሲኖሩ ደግሞ ቆም እያልን የልዩነቶቹን ዓይነትና ምክንያት ለመግለጽ እንሞክራለን፡፡

የቡርጂዎች *የባሻ ሥርዓት* በይፋ የሚከናወነው *ሱቡሮ* ከሚባለው ስፍራ ላይ ነው፡፡ በዕለቱም አዳዲሶቹ ሹማምንት ወደ ሱቡሮ ከመውጣታቸው አስቀድመው ከቤታቸው የሚፈፅሟቸው ባህላዊ ስርዓቶች አሉ፡፡ ሁሉም ከራሳቸው፣ ከጎሣ መሪያቸው ደጅ፣ *(ዳይና ወይም ማሻ ሲሆኑ ደግሞ)* ከተሰየሙበት ቦሄ ወይም *ቢያ ባልባላ* ላይ *ኤሳ* ይተክላሉ፡፡ *ኤሳው* ተተክሎ እንዳበቃ ከኤሳው ሥር ፍየል በጦር ከአንገቱ ላይ በትንሹ ከተወጋ በኂላ በቢላዋ ይባረካል፡፡ ደሙንም በመጀመሪያ አዲሶቹ ሹማምንት፣ ቀጥለው ከዚያ ያሉ ሌሎች ሹማምንትና የበዓሉ ታዳሚዎች ተራ በተራ በኮባ አገዳ እያጣቀሱ ከግንባራቸው ላይ ይይዙታል ወይም ይቀቡታል፡፡ እንደገና የፍየሉ ደም በእቃ ይቀዳና ልክ እንደ ቦርዴው በኤሳው ላይ ይረጫል፡፡ ወይም *የሒጣኖ* እምነታዊ ሥርዓት ይፈጸማል፡፡ ይህ በሁሉም ባህላዊ መሪዎች አማካይነት የሚፈጸም ባህላዊ ሥርዓት ቢሆንም ግን አፈፃፀሙ የራሱ የሆነ ቅደም ተከተል አለው፡፡ ይህም እንደሚከተለው ይገለጻል፡፡

ከሁሉም በፊት ከፍ ሲል የተመለከተው ባህላዊ ሥርዓት የሚፈጸመው በታችኛው ሹም፣ በማሻ አማካይነት ነው፡፡ አንድ ማሻ ሆኖ የተመረጠ ሹም ከፍ ሲል የተ ጠቀሰውን ሥርዓት የሚፈጽመው ረዳቱ ጃልዓባ በተገኘበት ስለሆነ እስኪመጣለት ይጠብቃል፡፡ እሱም ተገቢውን ሥርዓት ከደጁ ከፈጸመ በኂላ በተራው ረዳቱን አስከትሎ ከእሱ ከፍ ብሎ ወደሚገኘው ባለሥልጣን ወደ *ፊዜው* ወይም ወደ *ዳይናው* ይሄዳል፡፡ ፊዜውም (የማሻዎቹ አለቃም) በተራው

የአካባቢው ማሻዎችና ጃልዓባዎች በተገኙበት በቤቱና በህዝብ ባልባላው ተመሳሳዩን ሥርዓት ከፈፀመ በኋላ የበታቾቹን ሹማምንት አስከትሎ ከእሱ ከፍ ወዳለው ዳይናው ዘንድ ይሄዳል።

ዳይና (ጋሪንታ ዳይና ማለቴ እንደሆነ ልብ ይሏል) የቡርጂዎች ቁንጮ የሆነ ባህላዊ መሪ ነው። ስለሆነም በእለቱ ሥርዓቱ ወደሚፈፀምበት፣ ወደ ሱቡሮ የሚወጣው በማሻዎች፣ በጃልዓባዎችና በህዝብ ታጅቦ ነው። ለዚህ ሲልም ‹‹በዚህ ቀን ሱቡሮ ስለምወጣ፣ ህዝባችሁንና ለኤሳ መትከያ የሚሆን እንጨት ይዛችሁ ድረሱብኝ›› በማለት ለሁሉም የቢያ መሪዎች ወይም ለማሻዎች (ለፊዜዎች) ይልክባቸዋል። መልዕክተኞቹ ደግሞ ሉብ የሚባሉ ‹‹ወታደሮቹ›› ናቸው። ፊዜዎችም በተራቸው መልዕክቱን በተዋረድ ለሚገኙ ለየቦሄ መሪዎች ማለትም ለማሻዎች ያስተላልፋሉ። ማሻዎችም በተራቸው መልዕክቱ ለነዋሪዎች እንዲደርስ በማድረግ የበዓሉን ቀን ያሳውቃሉ።

አብዛኞቹ ማሻዎችና ረዳቶቻቸው ወደ ሱቡሮ የሚሄዱት በሚያስተዳድሩት ህዝብ ታጅበው፣ በሚቀርባቸው መንገድ ነው። ለዳይናው ቅርብ የሆኑት ወይም ዳይናው በሚኖርበት ቢያ ውስጥ የሚገኙት ማሻዎች፣ ጋናዎችና ጃልዓባዎች ግን አለቃቸውን (አዲሱን ዳይና) አጅበው ወደ ሱቡሮ ይሄዳሉ። ለዚህ ሲሉም በበዓሉ ዕለት አንድ የፍየል ወጠጤ ይዘውና ማልደው ከዳይናው ቤት ይመጣሉ። ዳይናውም እነሱ ያመጡለትን ፍየል በማረድ ከፍ ሲል የተጠቀሰውን ባሕላዊ ስርዓት ከደጁ ላይ ይፈጽማል። ከዚያ በኋላ ከቤት ገብተው ይቀመጣሉ። እንደ ማዕረጋቸው ቅደም ተከተል ከቢታናቹ ፊት እየቀረቡ ከአናታቸው ላይ ቅቤ ይቀባሉ። ከእነሱ ቀጥለው እናቶቻቸውና ሚስቶቻቸውም እንዲሁ ተራ በተራ ከቢታናቹ ፊት እየቀረቡ ከደረታቸው፣ ከጡታቸው ላይ ቅቤ ይቀባሉ። በቅቤ የታሸ ካላቻ ከግንባራቸው ላይ ያስራሉ። በቀኝ እጃቸው ደግሞ ሊሶ ይይዛሉ። ሊሶውንም እንዲሁ በቅቤ ያሻሹታል። ከዚያን ቀን አንስቶ ሊሶውንና ካላቹን በቅቤ እሽት እሽት ማድረግ የሁሉም ሹማምንት የዕለት ተዕለት ተግባር ይሆናል።

ቅቤ (ጥሬ ቅቤ) በቡርጂ ባህላዊ ሥርዓት ውስጥ ከፍተኛ ፋይዳ አለው። ቅቤ በተፈጥሮው እርጥብ ነገር (ቅባት) ነው። ቅባት በመሆኑም ደረቁን ያርሳል። ሻካራውን ያለሰልሳል። አመዳሙን ያወዛል። የባህላዊ ሹማምንት ልዩ ምልክት የሆኑት፣ ሊሶና ካላችም ሁልጊዜ ቅቤ የሚቀቡት ለዚሁ ሲባል ነው። የመሪዎቹ የስልጣን ዘመን የልምላሜ፣ የብልፅግና፣ የሰላም እና የጤንነት ዘመን እንዲሆን። በአካባቢው ዝናብ እንዲዘንብ፣ ዘንቦ አገሩን፣ መሬቱን እንዲያርስ፣ ሀገሩን እንዲያለማ በሚል ምኞት ነው ሊሶውንና ካላቹን ዘወትር ቅቤ እየቀቡ ማስቀመጣቸው። ባህላዊ ቁሱ፣ በተለይ ሊሶው ቅቤ ካልተቀባ ክችች ይላል። ቆዳ ስለሆነ ድርቅ ይላል። አመድ

መስሎ ይነጣል፡፡ *ሊሰው* አመድ ከመሰለ ‹‹የሹሙ የስልጣን ዘመንም እንዲሁ አመዳም፣ የድርቅ ዘመን፣ ወዘተ. ይሆናል፡፡ በአገሪቱ ዝናብ ይጠፋል፡፡ ሳር ቅጠሉ ይደርቃል፡፡ በዚህም ህዝብ ይራባል፣ ወዘተ›› ተብሎ ይታመናል፡፡ ከዚህ እምነት በመነሳትም *ካላቹንና ሊሰውን* ቅቤ የመቀባቱ ተግባር ለአንድ ቀን እንኳን ችላ አይባልም፡፡

አዳዲሶቹ ሹማምንት ወደ ሱቡሮ ሊሄዱ ሲሉ ከቤታቸው የሚወጡት በሰው ታዝለው ነው፡፡ የሚያዝሏቸው ደግሞ *ሉብ* የሚባሉ፣ የፈረጠሙ ወጣቶች ናቸው፡፡ በዚህ ዓይነት ታዝለው ከቤት ሲወጡ ከውጭ እልልታው ይቀልጣል፡፡ ዘፈኑ ይደምቃል፡፡ ታዝለው ትንሽ መንገድ ከተወሰዱ በኋላ ወርደው በእግራቸው ይሄዳሉ፡፡ ሱቡሮ ሊደርሱ ጥቂት ሲቀራቸውም እንዲሁ ታዝለው እስከ ስርዓቱ ቦታ ድረስ ይወሰዳሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ወርደው በእግራቸው ይንቀሳቀሳሉ፡፡[43]

ዳይናው ሱቡሮ የሚወጣው ሁለት ነገሮችን ይዞ ነው፡፡ አንደኛው ኮርማ በሬ ሲሆን ሁለተኛው ቦርዴ ነው፡፡ ሁለቱም በ*ሥፍራው* ላይ ለሚፈጸመው ለሒጣኖ እምነታዊ *ሥርዓት* ማስፈጸሚያነት ይውላሉ፡፡ ሱቡሮ ሁሉም ቡርጂዎች *የባሽ* ስርዓቱን በጋራ የሚፈጽሙበት ስፍራ ነው፡፡ እያንዳንዱ የቢያና የቦሄ አስተዳደሮችም እንዲሁ የባሻ *ሥርዓት* የሚፈጽሙበት *ሥፍራ* በየግላቸው አሏቸው፡፡ *ሥርዓቱ* ቡርጂ አቀፍ ሲሆን ግን የሚፈጸመው ሱቡሮ ላይ ይሆናል፡፡ በመሆኑም በዕለቱ ሱቡሮ ላይ ታላቅ በዓል ይሆናል፡፡ የሁሉም አካባቢ ህዝቦች፣ የህዝብ ሹማምንት፣ *ኣንሾች፣ ጎርሶች፣ ቢታናቾች* እና ሌሎችም ማልደው ወደ ሱቡሮ ይመጣሉ፡፡


በዕለቱ ሱቡሮ ላይ ሶስት ዋና ዋና ባህላዊ ስርዓቶች ይፈፀማሉ፡፡ የአንድነት አርማ፣ የስልጣን ምልክት የሆነውን *ኤሳ* መትከል ወይም ማደስ ቀዳሚው ተግባር ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ *ሒጣኖ* የሚባለው እምነታዊ ስርዓት ይፈፀማል፡፡ በዕለቱ ሱቡሮ ላይ የሚፈፀመው ሶስተኛው ባህላዊ ስርዓት በአዳዲሶቹ ባህላዊ *መሪዎች* ላይ ሳር ነጭቶ መነስነስ ይሆናል፡፡

ከሱቡሮ ላይም ሆነ ከሌላ ስፍራ ላይ የሚተከለው *ኤሳ* የሚዘጋጀው ከተለያዩ የእንጨት ዓይነቶች ነው፡፡ እንጨቶቹም በዓይነት፣ ለወማ ሲሆን ስምንት፣ ለጋሪንታ ዳይና ሲሆን አምስት ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ኡቱባ[44] ይባላል፡፡ ረዥም እድሜ ካስቆጠረ ከግራር ግንድ ተጠርቦ የሚወጣ አጭርና ወፍራም ጠርብ ነው፡፡ ከመሃል ቆሞ ሌሎችን እንጨቶች አቅፎ የሚይዘው፣

---

[43] አሁን አሁን በእግር መሄዱ እየቀረ ያለ ይመስለኛል፡፡ ይህን ለማለት ያስቻለኝ በቅርብ ጊዜ ከተመረጡት ሹማምንት መካከል የተወሰኑት በበቅሎ ሲጠቀሙ በማየቴ ነው፡፡
[44] በአንዳንድ የቡርጂ አካባቢዎች ቢዶ እየተባለ ይጠራል፡፡ ቢዶ ማለት ምስሶ ማለት ነው፡፡ ቢዶ ማለታቸውም ከኤሳው መሀል ስለሚቆም ይመስለኛል፡፡

ወይም የሚሸከመው *ሉቱባው* ነው፡፡ *ሉቱባ የኤሳው* መሰረት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሁለተኛው *ብርብር* (የአበሻ ጥድ) ነው፡፡ ሶስተኛው የእንጨት ዓይነት ደግሞ *ሌይም* (ቀርከሃ) ነው፡፡ *ኤሳን* ለማዘጋጀት የሚያገለግለው አራተኛው የእንጨት ዓይነት *ጂርማሌይ* (ግራር) ሲሆን፣ አምስተኛው ደግሞ *ሆባኔ* ይባላል፡፡ ቆላ አካባቢ ብቻ የሚገኝ ጠንካራ የሀረግ ዓይነት ነው፡፡ ስድስተኛው *የገር* (ወይራ)፣ ሰባተኛው *ሚኤሳ* ሲሆን ስምንተኛው ደግሞ *ዶራሆ* ይባላል (*ሥዕል* ቁጥር 4 ተመልከት)፡፡



*ሥዕል ቁጥር 4፤* የጎሳ መሪ፣ ወማ፣ ዳይና፣ ማሻ እና ባለጋን በሆኑ ሹማምንት ደጅ፣ እንዲሁም ሱቡሮ ላይና በየባልባልው የሚተከለው፣ የቡርጂዎች የአንድነታቸው አርማ፣ የቃል ኪዳናቸው ማዕኛ የሆነው ኤሣ ይህ ነው፡፡

እነዚህ እንጨቶች ወደ ሱቡሮ የሚመጡበት መንገድ በራሱ *ሥርዓታዊ* ነው፡፡ ማንም ሰው በቅንነት ቆርጦ የሚያመጣቸው አይደሉም፡፡ ቢመጡም ለኤሳው ከተዘጋጀው ጉድጓድ አይገቡም፡፡ ቡርጂዎች ለዚህም ያበጁት ስርዓት አላቸው፡፡ ለኤሳው ዝግጅት ማን ምን ይዞ መቅረብ እንዳለበት ቀደም ተብሎ በባሻ *ሥርዓተ* ደንቡ ተደንግጓል፡፡ ደንቡ ዛሬም ይሰራበታል፡፡ በዚህ ህገ ደንብ መሰረት፣ ለኤሳ ዝግጅት የሚውለውን ብርብር (ጥድ) ማምጣት ያለበት *ራለይ* የሚባለው *የቢያ* አስተዳደር ነው፡፡ *ሌይም* (ቀርከሃ) *በሸይሸቤ ዳይና (ሀና* በሚባለው *የቢያ* አስተዳደር) አማካይነት ይመጣል፡፡ *ሆባኔ* የሚባለውን ሐረግ ሰገን ከሚባለው ከቡርጂ ቆላማ አካባቢ ቆርጦ እንዲያመጣ የተባለው ደግሞ የየበን አስተዳደር ነው፡፡ ሌሎቹም እንዲሁ አምጪ አላቸው[45] ፡፡

---

[45] በእኔ እምነት እንዲህ ለኤሳው ዝግጅት የሚውሉ እንጨቶችን የተለያዩ የአስተዳደር አካባቢዎች እንዲያመጡ መደረጉ ትልቅ ፖለቲካዊ መልእክት ያለው ይመስለኛል፡፡ ኤሳ በመሰረቱ የቡርጂዎች የአንድነት አርማ ነው፡፡ ለዚህ የሚሆን እንጨት በየአስተዳደሩ እንዲመጣ መደረጉ እውቅና ከመስጠት ጋር የተያያዘ ጉዳይ ይመስለኛል፡፡ ለምሳሌ ያህል ከሁሉም ቀድሞ ከጉድጓድ የሚገባው እንጨት ጥድ ነው፡፡ ጥድን ደግሞ የሚያመጡት ራለያዎች ናቸው፡፡ ጥድ አመጡ ማለት ለዳይናውም ሆነ ዳይናውን ለወከለው አካል እውቅና የመስጠት ያህል ሳይሆን አይቀርም፡፡ ጥድ ካልመጣ ኤሳው አይዘጋጅም ወይም አይቆምም፡፡ ጥድ ሳይገባ ቀርከሃው ከጉድጓድ ሊገባ አይችልም፡፡ ራለያዎች ጥድ ባላመጡበት ሁኔታ፣ ሌሎች ባመጡት ጥድ ኤሳው ቢዘጋጅ እንኳን፣ ስርዓቱ የተሟላ አይሆንም፡፡ ዳይናውም ‹‹የቡርጂ አስተዳዳሪ ወይም መሪ ነኝ ›› ማለት አይችልም፡፡ ለምን ቢባል፣ የአንድ ቢያ ህዝብ እውቅና ነፍጎታልና ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ እንጨቶች በቢያ እንዲመጡ የተደረጉት ‹‹እንጨቶቹ በእነዚህ አካባቢዎች ብቻ የሚገኙ ስለሆኑ ነው›› የሚል እምነት የለኝም፡፡ እጅግ ጠንካራ ፖለቲካዊ ይዘት እንዲኖረው ሲባል የተበጀ

ይህ ማለት ግን ሌላው አካል እንጨቶቹን ማምጣት አይችልም ማለት አይደለም፡፡ የፈለገ አንዱን ወይም ሁሉን ቆርጦና አዘጋጅቶ ሊያመጣቸው ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ እጅግ በተወሰነ አጋጣሚ ካልሆነ በስተቀር እንጨቶቹ አገልግሎት ላይ የመዋል ዕድል አያገኙም፡፡ ለኤሳው ከተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ ገብተው የመቆም እድል አይኖራቸውም፡፡ ለዚህ ቅድሚያ ያላቸው፣ የማምጣት (የማቅረብ) ስልጣን ባላቸው የቢያ አስተዳደሮች አማካይነት የቀረቡ እንጨቶች ብቻ ናቸው፡፡

‹‹ሱቡሮ ላይ ኤሳ ይተከላል›› ሲባል አዲስ ኤሳ ይዘጋጃል ማለት አይደለም፡፡ ቀድሞ የነበረው ኤሳ ፈርሶ ይታደሳል እንጂ፣ ሌላ አዲስ ኤሳ፣ ከሌላ ስፍራ ላይ አይቆምም፡፡ ነባሩ ኤሳ ፈርሶ በቦታው ላይ አዲስ ጉድጓድ ከመቆፈሩ በፊት ግን ቀደም ሲል በተገለጸው መልኩ ቦርዴ ይረጭበትና የሐጣኖ ስርዓት ይፈፀማል፡፡ ከሁሉም ቀድሞ ቦርዴውን የሚረጨው በጥንቱ ሥርዓት ወማው ሲሆን በአዲሱ ሥርዓት ግን ዳይናው ይሆናል፡፡ እሱም ቦርዴውን በእጆቹ እፍስ አድርጎ፣

*ሲርገን ! ሲርገን ! ( ቀዝቅዝ ! ቀዝቅዝ! )*
*ቢያጋ ሲርጋሃ ኡዊ ( ለህዝቡ፣ለሀገሩ ደህናውን፣ ልምላሜውን ስጥ )*
*ዳዶ ሲርገን ! ( መሬት፣ ቀዝቅዝ )*
*ጨና ጨሬ ! ( ዝናብ ይዝነብ ) . . . ወዘተ*

እያለ ይረጨዋል፡፡ እሱን ተክትለው ሌሎች ሹማምንትም እንዲሁ ያደርጋሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ነባሩ ኤሳ በፈረሰበት ቦታ ላይ ሌላ አዲስ ጉድጓድ ይዘጋጃል፡፡ ጉድጓዱ ተቆፍሮ እንዳበቃ ኤሳውን የመትከል ስልጣን ያላቸው ወገኖች እንጨቶችን ይዘው ከተቆፈረው ጉድጓድ ዙሪያ ክብ ሰርተው ይቆማሉ፡፡ በዕለቱ በባለስልጣናት የማይያዘው ወይም በአዲስ እንጨት የማይተካው፣ የሁሉም መሰረት የሆነው *ኡቱባው* ብቻ ነው፡፡ *ኡቱባ* አንዴ ከተተከለ አንዳች ነገር ሳይሆን ከ100 እስከ 150 ዓመት ድረስ ማገልገል ይችላል (ጌታሁን፣1999፣18)፡፡ በመሆኑም እሱ በቶሎ አይቀየርም፡፡ በአዲስ አይተካም፡፡ ባለስልጣናቱ እንጨቶችን ይዘው እንደቆሙ *ሉስ! ሉስ! ኡቱባ! ኡቱባ!* ይባላል፡፡ ይህን ጊዜ የያዙትን እንጨት ተራ በተራ ከጉድጓዱ ውስጥ ያቆማሉ፡፡ ከአሮጌዎቹ እንጨቶች መካከልም ደህና ደህናዎቹ፣ ያልበሰበሱት ይለዩና ከአዲሶቹ እንጨቶች ጋር ከጉድጓዱ

---

ባህላዊ ስርዐት ነው፡፡ በሐረጉ (በሆባኔ) ኤሳው ከወገብ ላይ ካልታሰረ በቀላሉ ይፈርሳል፡፡ የበኖዎች ሐረጉን አላመጡም ማለት ኤሳው የሳምንት እድሜ አይኖረውም፡፡ በሌላ አገላለፅ የቡርጂዎች አንድነት ይፈርሳል ማለት ነው፡፡ ዋናው ቁምነገር፣ እንጨቶቹ በቢያ እንዲመጡ የመደረጋቸው ምክንያት ለኔ ይህ ይመስለኛል፡፡

ውስጥ ይቆማሉ፡፡ ከዚያ በኋላ *ሆባነይ* በሚባለው ሐረግ ከወገባቸው ላይ ከሁለት ቦታ ሸብ ተደርገው ይታሰራሉ፡፡ በመጨረሻም አፈር ይመለስባቸዋል፡፡ በቃ! ኤሳው ተተከለ ማለት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ዳይናው የቡርጂ መሪ መሆኑን አረጋገጠ ማለት ነው፡፡ የቡርጂ ህዝቦች የአንድነታቸው ቃል ኪዳን ታደሰ ማለትም ሊሆን ይችላል፡፡ የኤሳ ትዕምርታዊነት ብዙ ነው፡፡ ለብቻው ቢጠና ራሱን የቻለ አንድ መጣጥፍ ሊወጣው የሚችል ይመስለኛል፡፡

ለኤሳው የተመረጡት እንጨቶችም ቢሆኑ ከተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ የሚገቡት በዘፈቀደ አይደለም፡፡ ለዚህም የተበጀ ባህላዊ *ሥርዓት* አለ፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለፀው ቀድሞ ከጉድጓዱ ውስጥ የሚገባው እንጨት (*ከሉቱባው ቀጥሎ ማለት ነው*) ጥድ ነው፡፡ ቀጥሎ ቀርከሃ ይቆማል፡፡ ሌላውም እንዲሁ ይከተላል፡፡ እንጨቶቹን ከጉድጓዱ ውስጥ የሚያቆሙ ሰዎችም እንዲሁ ተለይተው ይታወቃሉ፡፡ ማንም ተነስቶ ከጉድጓድ ሊያቆም አይችልም፡፡ በድሮ ስርዓት ከሁሉም በፊት ጥዱን አንስቶ ከጉድጓዱ ውስጥ ማቆም የሚችለው አዲሱ *ወማ* ነበር፡፡ ከወማው ቀጥሎ ዳይናው ቀርከሃ ያቆማል፡፡ ከዳይናው በኋላ ኣንሾች (የጎሳ *መሪዎች*) ይከተላሉ፡፡ ይህ ግን በድሮው ዘመን ወሚሶ ከግራዝማች ዳምጤ ዳዌ እጅ ከመግባቱ በፊት ይፈፀም ወይም ይሰራበት የነበረ ስርዓት ነው፡፡

ዳምጤ ‹‹ወማ›› በነበረ ዘመን ግን መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበታል፡፡ የእንጨቶቹ ቅደም ተከተል እንደ ተጠበቀ ሆኖ፣ እንጨቶቹን ከጉድጓድ በሚያቆሙ ሹማምንት አሰላለፍ ላይ መጠነኛ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡ በጥንቱ ዘመን *ሥርዓቱ* ሲፈፀም ከሁሉም በፊት የኤሳውን ቀዳሚ እንጨት (ጥዱን) የሚተክለው ወማው ነበር ብለናል፡፡ በዳምጤ ዘመን ግን ከሁሉ ቀድሞ ጥዱን ከጉድጓድ ያቆም የነበረው *የጋሻራ* ተወካይ የሆነው ሹም እንጂ ‹‹*ወማ*›› ዳምጤ አልነበረም፡፡ ይህ የሆነውም ስርዓቱ የሚካሄድበት ስፍራ (ሱቡሮ) የሚገኘው በጋሻራ ግዛት ውስጥ ስለሆነ ነው፡፡ በመሆኑም ከሁሉም ቀድሞ ኤሳውን (ጥዱን) ከጉድጓዱ የሚያቆመው ወማው መሆኑ ቀርቶ የጋሻራ ተወካይ ሆነ፡፡ ይህን በተመለከተ ከዚህ ቀደም በእውነት የሆነ፣ በአሁኑ ዘመን ላይ ግን፣ እንደ አፈ-ታሪክ የሚተረክ አንድ አጋጣሚ እንደነበር ይነገራል፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡፡

> ዳምጤ ዳዌ የቡርጂ ወማ ከሆነ በኋላ ነው፡፡ ወልዴ የሚባል ሰው *ዳይና ሆኖ* የሚሰየምበት ክብረ በዓል ሱብሮ ላይ ይካሄድ ነበር፡፡ ሁሉም ህዝብ ከሱቡሮ ላይ ተሰብስቧል፡፡ *ወማ* ዳምጤም ክብረ በዓሉ ላይ ተገኝቷል፡፡ ጉድጓድ ተቆፍሯል፡፡ *ኤሳ* ሊተከል ነው፡፡ ሹም እንጨት ማንሳት ጀመረ፡፡ ዳምጤም ‹‹የሁሉም የበላይ እኔ ነኝ፤ ወማ ነኝ›› ብሎ ጥዱን አነሳ፡፡ ከሁሉም ቀድሞ ጥዱን ከጉድጓድ ሊያቆም ወደ ጉድጓዱ አቀና፡፡ ይህን ጊዜ *ጉቼ ግና* የተባለው የጋሻራ ሰው ከሹማምንቱ መካከል እመር ብሎ በመውጣት ወደ በቅሎው ገሰገሰ፡፡ ከበቅሎው ላይ ዘሎ ከወጣ በኋላ ወደ ሰፈሩ (ወደቤቱ) ሸመጠጠ፡፡ ወማውም ‹‹ኧረ ነገሩ ምንድ ነው?›› አለ፡፡ ሹማምንቱም ህዝቡም ጮኸ፡፡ ‹‹ኧረ ያንን ሰው ምን ነካው? ስርዓቱ

> ሳያበቃ ወደ ቤቱ የሚሄድበት ምክንያቱ ምንድነው? ኧረ ጥሩት! መልሱት›› ተባለና ፈረሰኞች ተላኩበት፡፡ ጉቼ ግና ርቆ ነበር፡፡ ፈረሰኞቹ ግን ደረሱበት፡፡ ደረሱበትና ጉቼ ግናን መለሱት፡፡ ሲመለስ ‹‹ሰውዬ ምን ተፈጠረ? ስርዓቱ ሳያበቃ ወደ ቤትህ ልትሄድ የተነሳኸው ምን ሆንኩ ብለህ ነው?›› ተብሎ በወማው ተጠየቀ፡፡ ያ ዘመን ወማ እጅግ የሚፈራበት ዘመን ነበር፡፡ ለወማ መልስ  የማይሰጥበት ዘመን ነው፡፡ ጉቼ ግና ግን አልፈራም፡፡ ‹‹ኤሳውን ከሁሉም ቀድመህ ልትተክል ጥዱን አንስተህ የነበረው ከማን ደጃፍ ላይ ቆመህ ነው?›› በማለት ከወማ ዳምጤ ላይ አፈጠጠበት፡፡ ወማ ዳምጤ የሰማው ያልጠበቀውን መልስ ስለነበር ግራ ተጋባ፡፡ ወዲያው *ኣንሾች፣ ጎርሶች* እና *ሸማግሌዎች* በጉዳዩ ገቡበት፡፡ ሽማግሌዎቹም ‹‹*ወማ ዳምጤ*›› አሉት፡፡ ‹‹ወማ ዳምጤ! አንተ የቡርጂ ወማ መሆንህ እርግጥ ነው፡፡ ከዚህ ስፍራ ከአንተ በላይ ማንም የለም፡፡ በዚህ አንፃር ሲታይ ኤሳ ልትተክል ጥድ ማንሳትህ ስህተት የለውም፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ስርዓት የሚፈፀምበት፣ ኤሳው የሚተከልበት ስፍራ የጋሻራዎች ነው፡፡ ሱቡሮ የጋሻራ ደጅ ነው፡፡ በእኛ ልማድ ደግሞ ከሁሉም ቀድሞ ኤሳ የሚያቆመው፣ ለኤሳ ከተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ ጥድ የሚተክለው የስፍራው ባለቤት ወይም የእሱ ተወካይ ነው፡፡ የቤቱ ባለቤት እያለ ሌላ ሰው ከደጁ ላይ ኤሳ ሊያቆም አይችልም፡፡ ቤቱ፣ ደጁ የጋሻራ ነው፡፡ ጉቼ ግና ደግሞ የጋሻራ ተወካይ ነው፡፡ ያለንበት ይህ ቤት የእሱ ነው፡፡ ስለሆነም ከሁሉም ሰው ቀድሞ ኤሳውን ማቆም፣ ጥዱን መትከል  ያለበት እሱ፣ ጉቼ ግና ነው፡፡ ጉቼ ግና ጥዱን መጀመሪያ ይትከል፡፡ ወማ ዳምጤ አንተ ደግሞ ከእሱ ቀጥለህ ትከል›› አሉት፡፡ በዚህ መሰረት መጀመሪያ ጉቼ ግና ጥዱን አንስቶ ከተዘጋጀው ጉድጓድ ውስጥ አቆመ፡፡ ቀጥሎ ወማ ዳምጤ አቆመ፡፡ ከወማ ቀጥሎ ዳይና ወልዴ እንጨት አንስቶ ከኤሳው ጉድጓድ ውስጥ አቆመ ይባላል[46]፡፡

በአሁኑ ጊዜ ግን ይህ ዓይነቱ አሠራር ‹‹በሥርዓቱ ውስጥ የአንድ አካባቢ የበላይነት እንዲንፀባረቅ፣ አምባገነንነት እንዲሰፍን ያደርጋል›› በሚል እንዲቀር ተደርጓል፡፡ በአዲሱ የባሻ ሥርዓት ደንብ መሰረት ከሁሉ ቀድሞ ኤሳ የሚተክለው፣ ጥድ አንስቶ ከጉድጓድ የሚያቆመው፣ የሁሉ ቁንጮ የሆነው፣ አዲሱ *ዳይና* ነው፡፡ ከእሱ ቀጥሎ *ኣንሽ* የሚባሉ የየጎሳ መሪዎች ይተክላሉ፡፡ ከዚያም *ጎርስ* የሚባሉ አማካሪዎች፣ እንዲህ እንዲህ እያለ ይቀጥላል፡፡

*ኤሳው* በዚህ መልክ ከታደሰና ከቆመ በኋላ በላዩ ላይ ደም በመርጨት *ሒጣኖ* የሚባለው እምነታዊ ስርዓት ይፈፀማል፡፡ ለዚህ ሲባል *ከኤሳው* ስር አንድ ኮርማ በሬ *በዳይናው* አማካይነት ይባረካል (ይታረዳል)[47]፡፡ ደሙ በእቃ ይያዝና በኤሳው ላይ ይረጫል፡፡ ዳይናውን ጨምሮ ሁሉም ሹማምንት የበሬውን ደም በጣታቸው አሊያም በኮባ ቅጠል *(በጉርባ)* እያጣቀሱ ከግንባራቸው

---

[46] ይህ የባሻ ስርዓት፣ በተለይም ወሚሶ እና ዳይኖማ ከ1967-1995 ድረስ፣ ለ27 ዓመት ያህል ተቋርጦ ነበር፡፡ ከ27 ዓመት በኋላ ግን በ1996 ዓ. ም እንደገና እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡ እንዲቀጥል የተደረገው ግን የዳይኖማ ስርዓት እና ከእሱ በታች ያሉት ብቻ ናቸው፡፡ ህዝቡ ‹‹ያለፈው የወሚሶ ሥርዓት ጨቋኝ ነበር›› በሚል እንዲቀጥል ለጊዜው አልፈቀደም፡፡ ይህን የወሰኑት፣ ባህላዊ ስርዓቱ እንዲቀጥል ያደረጉት ደግሞ ‹‹ጉል ጉበይንካ ጎርሶማ›› የሚባለው የምክር ቤት ጉባኤ ነው፡፡ በዚህ ጉባኤ ላይ የዳይኖማ ስርዓት እንዲቀጥል ከተስማሙ በኋላ ‹‹ከየት ይጀምር? ከሁሉ በፊት የዳይና ስልጣን ለየትኛው የቢያ አስተዳደር ይሰጥ?›› የሚል ጥያቄ ለውይይት ቀርቦ ነበር፡፡ ይህ ትረካም ‹‹ የባሻ ሥርዐቱ የሚፈጸምበት ሥፍራ - ሱቡሮ የሚገኘው በጋሻራ ውስጥ ስለሆነ ከሁሉ  በፊት  ስልጣኑ  ለጋሻራ ቢያ ሊሰጥ ይገባል›› የሚሉ ወገኖች ከሰነዘሩት ሃሳብ ውስጥ የተወሰደ ነው፡

[47] በድሮ ጊዜ ከኤሳው ስር የሚታረደው ጥቁር መልክ ያለው በሬ እንደነበር ይነገራል፡፡ ጥቁር በሬ የሚታረደውም ሰማዩ ጠቁሮ ደመና ቋጥሮ ዝናብ በአገሩ ላይ እንዲዘንብ ያደርጋል በሚል እምነት ነው፡፡ ዝናብ ዘንቦ መሬቱን ያርሣል አገር ያለመልማል፡፡ ጥቁር በሬ ዝናብ የቋጠረ የጥቁር ደመና ተምሳሌት ነው፡፡ ጥቁሩ በሬ ሲባረክ (ሲታረድ) የሚፈሰው ደም ደግሞ ዝናብ ከአረገዘው ከጥቁሩ ሰማይ (ደመና) ላይ የሚወርደውን (የሚዘንበውን) ዝናብ የሚወክል ይመስለኛል፡፡ በዛሬ ላይ እንዲህ አይነቱ እምነት ያለ ቢሆንም፣ ከኤሳው ስር የሚታረደው በሬ መልኩ የግድ ጥቁር መሆን የለበትም፡፡ የሚፈለገው ኮርማ በሬ መሆኑ ብቻ ነው፡፡ ቀለም፣ መልክ አይፈለግም፡፡

ላይ ይይዙታል። ይህም በቡርጂኛ *ጨጂ ጋጋሪሳ* (ደም መያዝ) ይባላል። በዚህም *የሒጣኖ* ስርዓት ፍፃሜ ይሆናል። ከዚያ በኋላ ሁሉም መሪዎች በተለመደው ሁኔታ በሰው ታዝለው አዲስ የተተከለውን ኤሳ ሶስት ጊዜ ይዞራሉ።

*ሱቡሮ* ላይ በዕለቱ ከሚፈፀሙ ዋና ዋና ባህላዊ ስርዓቶች መካከል ሶስተኛው በአዲሶቹ ሹማምንት ላይ ‹‹ሳር የመነስነስ›› ስርዓት ነው። በቡርጂኛ *ባሻ ካራ* ይባላል። ለዚህ ሲባል ሁሉም ሹማምንት እንደ ማዕረጋቸው ቅደም ተከተል ከመሬቱ ላይ *(ሓራዷጋ)* በመደዳ እንዲቀመጡ ይደረጋሉ። ከመጀመሪያው ጫፍ ዳይናው (በድሮው *ሥርዓት* ወማው) ይቀመጣል፡ ፡ ቀጥሎ ፊዜዎች፣ *ማሻዎች…እያለ* ወደ መጨረሻው ደግሞ *ጃልዓባ* የሆኑ ሹሞች ይቀመጣሉ። ሳር የመነስነሱ ስርዓት ከመጀመሩ በፊት ግን ባህላዊው የልመናና የፀሎት *(ሓሣዳ)* ስርዓት ይከናወናል። እንደሌላው ጊዜ ሁሉ ይህም ስርዓት የሚጀመረው በዳይናው (በጥንቱ አሰራር በወማው) አማካይነት ነው። ዳይናውም የሚከተለውን በማለት የፀሎትና የምርቃት ስርዓቱን ያስጀምራል። እሱ ‹‹*ኣ! ሓራዳ ሓራዲንካ ኣናጋ ሓራዳ ሹል ኦይዶ!*›› ሲል ሌሎቹ ወይም ህዝቡ ‹‹*ኦይዶ!*›› ብሎ ይቀበለዋል።

*ኣ! ሓራዳ ሓራዲንካ ኣናጋ ሓራዳ ሹል ኦይዶ !*
*ሓራዳድ ኪሌንካ፣ ሚጨሪንካ ወንቶ ባሲቶ !*
*ካል ሂልኣሌይሃ ወንቶ ሂርቶ !*
*ሂልኣሌይንካ ሂርባ ወንቶ ዳብዶ !*
*ኣንሸ ሺታ ሂርባ ወንቶ ዳብዶ !*
*ጎርሶ ሺታ ሂርባ ወንቶ ዳብዶ !*
*ሂዲቲንካ ኦልቾ ሺታ ሂርባ ወንቶ ዳብዶ !*
*ሀቡራ ዲርቦ ሺታ ሂርባ ወንቶ ዳብዶ !*
*ሱቡሮ ሉሉኮ ወንቶ ሼ ሂርቶ !*
*ኒንታ ሱማ ወንቶ ሂርቶ !*
*ባርጉዳ ኒንታ ወንቶ ሳድ !*
*ጋፋንታ ወንቶ ጎድ !*
*ጨና ኒንሳ ኣንድ !*
*ጋላኒኖ ዳዋና ጋላኔይሽ፣ ባርጉዴይሽ፣ ኒንሳ ኣጊንታ ኢህ !*
*ካራ ኒንሳ ኣጊንታ ኢህ !*
*ሱማ ኒንሳ ኣጊኒታ ኢህ !*
*ሱማዴይ ሱሌይ ወንቶ ባሲቶ !*
*ሱቡሮ ኣጊኒታ ኢህ !*
*ኤሳ ዳሲካን !*

(የአማርኛው ትርጉሙ የሚከተለውን ይመስላል)

*ለህዝብ መሪ ስልጣኑ የተሳካ ይሁንለት !*

*እግዚአብሄር[48] ከህዝቡ መሀል ተንኮለኛውን ነገረኛውን ያጥፋው !*
*እግዚአብሄር ያንን፣ የሰማዩን ይፍታው !*
*የጎሳ መሪዎች እግዚአብሄር ይከተላችሁ !*
*አማካሪዎች እግዚአብሄር ይከተላችሁ !*
*ስምንቱ የአስተዳደር አካባቢዎች እግዚአብሄር ይከተላችሁ !*
*ሀቡራ እና ዲርቦ - እግዚአብሄር ይከተላችሁ !*
*ሰቡሮ እና ሉሉኮ እግዚአብሄር ይፍታችሁ !*
*መሰረታችንን እግዚአብሄር ይፍታው !*
*እግዚአብሄር ሆይ! የእኛን ባርጉዳ ክፈትልን !*
*እግዚአብሄር መልካሙን ያድርግልን !*
*ለእኛ ዝናብ አምጣልን !*
*ገላና እና ባርጉዳ ወዲህ የመጣንባቸው መንገዶቻችን ናቸውና የተባረኩ ይሁኑ !*
*ደጃችንን፣ መገኛችንን የተባረከ ያድርግልን !*
*መሰረታችንን የተባረከ ያድርግልን !*
*ከመሠረታችን ክፉውን እግዚአብሄር ያርቅልን !*
*ሰቡሮን የተባረከ ያድርግልን !*
*እነሆ አጠናቀቅሁ፡፡*

እንዲህ ብሎ ዳይናው ሲጨርስ ሌሎችም እንደ ማዕረጋቸው ተራ በተራ ምርቃቱንና ልመናውን ያዥጎደጉዱታል፡፡ ይህ እንደተጠናቀቀ ባለስልጣናቱን የመመረቅ ወይም ሹመታቸውን የማፀደቅ ባህላዊ *የባሻ ሥርዓት* ይቀጥላል፡፡ ይህም እንደ አቀማመጣቸው በእያንዳንዳቸው እራስ ላይ ሣር በመነስነስ ይፈፀማል፡፡

ከመሪዎቹ ራስ ላይ የሚነሰነሰው ለምለም ሳር ነው፡፡ ሣሩ አናቱ በከብት ያልተበላ፣ አሊያም በሰው ያልተቆረጠ ሊሆን ይገባል፡፡ ሳሩን ነጭተው እንዲያመጡ የሚላኩት ደግሞ *በክ* (ኣርጋሌ) በሚል *ማዕረግ* የሚታወቁ *የቢታናች ረዳቶችና ሉብ* የሚባሉ የመሪዎቹ ‹‹ፖሊሶች›› ናቸው፡፡ ከሁሉም በፊት ሳሩ የሚነሰነሰው በዳይናው (በጥንቱ *ሥርዓት* በወማው) እራስ ላይ ነው፡፡ ሣሩን የመነስነሱን ቅድሚያውን የሚወስዱት ደግሞ የጎሳ መሪዎች (ኣንሾች) ይሆናሉ፡፡ ከእነርሱ በመቀጠል የሚነሰንሱባቸው አማካሪዎች (ጎርሶች) ናቸው፡፡ እንዲህ እንዲህ እያለ፣ ሴቶቹ ሲቀሩ፣ ከዚያ የታደመው ሰው ሁሉ ‹‹ሺያ ሹል ቢያጋ ኦይዶ!›› (ግንባርህ ለህዝቡ መልካም ይሁን) እያለ በእያንዳንዱ ሹም ራስ ላይ ሳር ይነሰንስበታል፡፡ እንዲህ ከሚነሰነሰው ሣር መብዛት የተነሣ እያንዳንዱ ሹም ከመሬት ላይ የተቀመጠ ሰው መሆኑ ቀርቶ ታጭዶ የተቀመጠ የሳር ክምር የሚመስልበት አጋጣሚ ሞልቷል፡፡ *ሥርዓቱ ባሻ* (ሣር) መባሉም ከዚህ ተነስቶ ነው፡፡ በዚህም የ*ሥ*ልጣን ሽግግሩ *ሥርዓት* ተከናወነ፣ የባሻው *ሥርዓት* ተፈፀመ ይባላል፡፡

---

[48] ይህ አሁን ከዘመናዊ ሃይማኖቶች መስፋፋት በኋላ የመጣ አባባል ነው፡፡ በድሮ ጊዜ ግን ቡርጂዎች ‹‹ኣቦ! ኣኮ! ወዘተ›› (አባቴ! አያቴ! ቅድማያቴ›› ይሉ ነበር፡፡ ከዚያ ቀጥለው ‹‹ዋጭ›› በሚሉት ውቃቢ ማምለኩ ሲለመድ ‹‹ኣባካ ዋጮ!›› (የአባቴ ውቃቢ) ማለት ጀመሩ፡፡ በመጨረሻም በአካባቢው የዘመናዊ ሃይማኖትን መስፋፋት ተከትሎ ‹‹ወንቶ›› (እግዚአብሔር) ማለቱን ጀምረው ቀጠሉበት፡፡

ከዳይናው ጀምሮ ወደ ታች ባሉት ባህላዊ መሪዎች ዘንድ የሥልጣን ሽግግሩ የሚፈጸመው ከፍ ሲል በተገለጸው ሁኔታ ነው። አንዱ ለሌላው ሥልጣን ማስረከቡ የሚገለጽበት፣ አንዱ ለሌላው የሚሰጠው ወይም አንዱ ከሌላው የሚቀበለው አንዳች ነገር አይኖርም። በወማው የሥልጣን ሽግግር ሥርዓት ወቅት ግን ከዚህ ለየት ያለ ሁኔታ ይካሄድበታል። ተሰናባቹ *ወማ* ለአዲሱ *ወማ ፊኒና* ወይም *ሺጊዳ* የሚባለውን ባህላዊ ቁስ በመስጠት የሥልጣን ሽግግር ሥርዓቱ ይፈፀማል። በዚህም የባሻ ሥርዓት ፍጻሜ ይሆናል።

ከዚህ በኋላ ቀሪው ወደ መንደር ተመልሶ ለበዓሉ ሲባል የተዘጋጀውን ድግስ ከፍቶ የመብላትና የመጠጣት ስነ ስርዓት ነው። በእያንዳንዱ ሹም ቤት የተደገሰ ቢሆንም ግን ሁሉም ሹማምንት ቀድመው የሚጋበዙት ከወማው ቤት ይሆናል። በመሆኑም በጥንቱ ልማድ ዳይናውን ጨምሮ የሁሉም ቢያና የቦሄ መሪዎች፣ *ኣንሾችና ጎርሶች*፣ *ቢታናቾችና* ሌሎች ሹማምንት በሙሉ ተያይዘው ከወማው ደጅ ይገባሉ። ወማውም በእለቱ ከምግብና ከቦርዴ ሌላ ለእያንዳንዱ ቢያ በነፍስ ወከፍ አንድ አንድ በሬ ያቀርብላቸዋል። ለስምንቱ የቢያ አስተዳደሮች ስምንት በሬዎች፣ በክብረ በዓሉ ቦታ ከኤሳው ሥር የሚታረደውን በሬ ጨምሮ ወማው ብቻ ጠቅላላው ዘጠኝ በሬዎችን በዕለቱ ያቀርባል ማለት ነው። ዳይናው ሲሆን ደግሞ የበሬዎቹ ቁጥር ወደ ስድስት ዝቅ ይላል። ይህም የሚሆነው ዳይናው (ክብረ በዓሉ በሚፈፀምበት ቦታ ከኤሳው ሥር የሚታረደውን በሬ ሣይጨምር) አንዳንድ በሬ የሚሰጠው ለሚያስተዳድራቸው ለአምስቱ የቢያ አስተዳደሮች ብቻ ስለሆነ ነው።

*የየቢያ* ሹማምንት ብዛት በርግጥ አንዱ ከሌላው ሊበልጥ ይችላል። ይሁን እንጂ፣ ቁም ነገሩ ይህ አይደለም። በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ የሚቆጠረው የቢያ አስተዳደር እንጂ ሰው አይደለም። በቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር ህገ-ደንብ መሰረት፣ ሁሉም የቢያ አስተዳደሮች በየትኛውም ደረጃ እኩል ናቸው። *በጉልጉባው ጎርሶማ* ውስጥ እያንዳንዳቸው ያላቸው የመቀመጫ ብዛት አንድ አንድ ሲሆን የሚኖራቸው ድምፅም እንዲሁ እኩል አንድ ይሆናል። በቢያ ደረጃ አንዱ የበላይ ሌላው የበታች የሚሆንበት ሁኔታ የለም። ‹‹ይህ *ታላቅ* ነው። *ያ ታናሽ* ነው›› የሚባል የአስተዳደር አካባቢ ቡርጂ ውስጥ የለም። በመሆኑም የአንዱ ቢያ ሹማምንት ብዛት 20፣ የሌላው 60 ቢሆን እንኳን ለባለ ሃያውም ሆነ ለባለ ስልሳው የሚሰጠው እኩል አንድ፣ አንድ በሬ ነው። ምግቡም፣ መጠጡም እንዲሁ እኩል ይቀርብላቸዋል። የፈለገው የተሰጠውን በሬ ከዚያው አርዶ ሲበላ፣ ሲጠጣ፣ ሲዘፍን ያድራል። ያልፈለገው አርዶ ከበላ በኋላ ወደ ቤቱ

ያቀናል። ወይም ስጋውን ተከፋፍሎ፣ ድርሻውን ቋጥሮ ወደቤቱ ይሄዳል። መብላት መጠጣቱም እስከ ሣምንት ድረስ ሊዘልቅ ይችላል።

ባህላዊ መሪዎቹ፣ በተለይም ወማውና ዳይናው ወደ ባልባላቸው (ጽህፈት ቤታቸው) ለመግባት፣ ገብተው መደበኛ ሥራቸውን ለመጀመር ግን አንድ ተግባር ይቀራቸዋል። ሁለቱም ባለሥልጣናት መደበኛ ሥራቸውን ከመጀመራቸው በፊት በመንፈሳዊ መሪዎች *(በባለጋኖች)* ሊመረቁ፣ ሊባረኩ ይገባል። የሚመረቁት ደግሞ *በሣጋናንካ ወማው (ጋን)* እና *በባንባልንካ ወማው (ጋን)* አማካይነት ይሆናል። ለዚህ ሲሉም *ወማውና ዳይናው ለባንባልንካ ወማ* የሚያቀርቡት ገፀ በረከት የለም። *ለሳጋናንካ ወማው* (ለዝናቡ ንጉስ) ግን አንዲት ጊደር የመስጠት ግዴታ አለባቸው። ለወማው ጊደር ሰጥተው የሥልጣን ዘመናቸው የብልጽግና፣ የጥጋብ፣ የሰላም…ወዘተ እንዲሆን ይመረቃሉ። ይህቺም ጊደር በቡርጂኛ *ወሚንታ ሙዳ* ትባላለች። ‹‹የወማው ቅቤ›› እንደማለት ነው። በቡርጂ እምነታዊ ሥርዓት መሰረት አንድ *ባለጋን* የሚመርቀውም ሆነ የመረቀው የሚሰምረው ከአናቱ ላይ ቅቤ የተቀባ እንደሆነ ነው። ከፍ ተብሎ እንደተገለጸው ቅቤው የባለጋኑን አናት ሲያርስ ዝናብ ይዘንባል። ዝናብ ዘንቦ ምድሪቷን ያርሳል። አገር ይለመልማል። የተቆጣው ይረግባል። የጋለው ይቀዘቅዛል። ህዝብ ይጠግባል ተብሎ ይታመናል። የተቀሩት ሹማምንትም እንዲሁ ሥራ ከመጀመራቸው በፊት በየአቅራቢያቸው ወዳሉት *ባለጋኖች* ዘንድ ሄደው ምርቃትና ቡራኬ ይቀበላሉ። ከረዳቶቻቸው ጋር በመሆን ወደ ጽህፈት ቤታቸው የሚገቡት፣ ስራቸውን የሚጀምሩት ከዚያ በኋላ ይሆናል። እንዲህ ሣይመረቁ በፊት ሥራ የጀመሩ እንደሆን የሥልጣን ዘመናቸው የችግር የመከራ፣ የጦርነት…ወዘተ ይሆናል ተብሎ ይታመናል። *ሙሳ ቡልኮ የወማ* የክብር ልብስ ሲሆን፣ *ካላችና ሊሶ* ደግሞ የሁሉም መሪዎች መለያ ምልክቶቻቸው ይሆናሉ። *ዳዋና* ለሁሉም ሹማምንት ክብር ሲባል የሚዘፈን ባህላዊ ዘፈን ነው።

## 4.4. የባህላዊ መሪዎች ተግባር

አብዛኞቹ የህዝብ መሪዎች ወደ ሥልጣን የሚመጡት በምርጫና በባሻ ሥርዓት እንደሆነ ከፍ ሲል ተመልክቷል። የአብዛኞቹ የሥልጣን ዘመንም እንዲሁ በጊዜ የተገደበ ነው። እያንዳንዱ መሪም በሥልጣን ዘመኑ ውስጥ የሚያከናውናቸው ተግባራት አሉት። ተግባራቱ ግን በእያንዳንዱ የማህበረሰቡ አባል ልቦና ውስጥ ተጽፈውና ታትመው ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል ሲተላለፉ ከዚህ የደረሱ እንጂ፣ በቀለም ተጽፈው ወይም በወረቀት ታትመው የተቀመጡ አይደሉም። ቡርጂ ውስጥ አንድ ባህላዊ መሪ ወደ ሥልጣን ሲመጣ ምን መሥራት እንዳለበት

ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ የሥልጣን ድንበሩ እስከየት ድረስ እንደሆነ በሚገባ ይገነዘባል፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ የህዝብ መሪ የሌላውን ድንበር ሣይጋፋ የራሱን ሥራ ለይቶና ጠብቆ ሲያከናውን ይታያል፡፡ ይህ ማለት ግን፣ እያንዳንዱ ባህላዊ መሪ የሚሠራው ሥራ ልክ በዘመናዊ የሥራ ተቋማት ውስጥ እንደሚደረገው የአንዱ ከሌላው እንዳይዛነቅ፣ እንዳይገናኝ፣ እንዳይመሣሰል ሆኖ የተበጀ ነው ማለት አይደለም፡፡ ከዚህ ከቡርጂዎች ዘንድ ያለው ግን ፈፅሞ የተለየ ነው፡፡

የቡርጂ ባህላዊ መሪዎች፣ እንደሚያስተዳድሩት አካባቢ ስፋትና ጥበት በሥልጣን ደረጃቸውና በማዕረግ ስማቸው ይለያዩ እንጂ፣ አብዛኞቹ የሚያከናውኑት ተግባር ተመሣሣይ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን በምርጫና በባሻ ሥርዓት ወደ ሥልጣን የሚመጡ የህዝብ መሪዎች (ማለትም የወማ፣ የዳይና፣ የማሻ፣ የፊዜ፣ የጋና እና የጃልዓባ) ዋና ተግባር ተመሣሣይ ብቻ ሣይሆን አንድ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህም በቡርጂ ህዝብና አካባቢ ላይ ወደፊት ይከሰታሉ ወይም ይደርሳሉ የተባሉት ክፉ አጋጣሚዎች (ማለትም ወረርሺኝ፣ ጦርነት፣ ድርቅ፣ ረሃብ፣ በሽታ ወዘተ) እንዳይደርሱ መከላከል ነው፡፡ በምርጫ ሥርዓት ብቻ ወደ ሥልጣን የሚመጡ የህዝብ መሪዎች ተግባራት ግን ከዚህ የተለዩ፣ የአንዳቸው ከሌላው ጋር እንዳይመሳሰሉ ተደርገው የተበጁ ናቸው፡፡ በመሆኑም የመሪዎቹ ተግባር ምን እንደሆነ? እንዴት እንደሚሠሩ? ቀጥሎ በዝርዝር ይቀርባል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከፍ ብለን እንደጠቀስነው፣ በባሻ ሥርዓት ስልጣን የሚይዙ መሪዎች (የኤላዎች) ተግባር በአብዛኛው ተመሣሣይ ስለሆነ የሁሉም ተግባራት በአንዱ ሹም ተግባር (በተለይም በዳይናው ተግባር) ሥር ተካተው እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡ የተለዩ ተግባራት ሲኖሩ ወይም ለአንዱ ሹም ብቻ የተወሰኑ ተግባራት ሲያጋጥሙ ግን ለብቻቸው ተብራርተውና ተለይተው ይቀርባሉ፡፡ በምርጫ ብቻ የሚመደቡ መሪዎች ተግባር ግን አንዱ ከሌላው ስለማይመሳሰል ብቻ ለብቻ ለማቅረብ ይሞከራል፡፡

### 4.4.1 የኤላዎች ተግባር

ኤላ፣ በባሻና በምርጫ ሥርዓት ሥልጣን የሚይዙ፣ አስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ተግባራትን የሚያከናውኑ ባህላዊ መሪዎች *(ማለትም ወማ፣ ዳይና፣ ፊዜ፣ ማሻ፣ ጋና* እና *ጃልዓባ)* በጥቅል የሚጠሩበት ስም ነው፡፡ እነዚህ ሹማምንት በማህበረሰቡ እምነታዊ እና መንፈሳዊ ተግባራት ውስጥ አይገቡም፡፡ ተግባራቸውን ለማከናወን የሚጠቀሙበት ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይልም የላቸውም፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኞቹን ተግባራት የሚያከናውኑት *በባለጋዎች፣* በጠንቋዮችና በተንባዮች በመታገዝ ነው፡፡

ወማ ተጠሪነቱ ለጉል ጉብይንካ ጎርሶማ ሲሆን የጎርሶማው ሰብሳቢ በመሆን ይሠራል፡፡ ጋሪንታ ዳይናም እንዲሁ ተጠሪነቱ ለጋሪንካ ጎርሶማ፣ ላዋጋንካ ዳይና ለላዋጋንካ ጉርሶማ፣ ፊዜ ለቢያንካ ጎርሶማ፣ ማሻ ደግሞ ተጠሪነቱ ለቦሄንካ ጎርሶማ ሲሆን እያንዳንዳቸው ተጠሪ ለሆኑበት ጎርሶማ ሰብሳቢ በመሆን ይሰራሉ፡፡ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ጎርሶማውን ጉባኤ ይጠራሉ፡፡ የኤላዎች የአገልግሎት ዘመን አንድ ዓመት ብቻ ነው፡፡ ሆኖም ከወማው በስተቀር የተቀሩት በስልጣን ዘመናቸው መልካም የሰሩ እንደሆነ ለሌላ ተጨማሪ ዓመት እንዲያገለግሉ ይደረጋሉ፡፡ ወማው ሲሆን ግን፣ የቱንም ያህል መልካም ቢሰራ ከአንድ ዓመት በኂላ ሥልጣኑ ለሌላ ሰው ተላልፎ ይሰጣል እንጂ፣ ለሌላ ተጨማሪ ዓመት በስልጣን ላይ እንዲቆይ አይደረግም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ የወማነት ሥልጣን በአምስት ጕሣዎች ዘንድ ተራ በተራ ይሄድ ስለነበር ነው፡፡

ሙሉ ቡርጂን ማለትም ስምንቱንም የቢያ መስተዳድሮችን ማስተዳደር ለወማ ብቻ የተሰጠ ተግባር ነው፡፡ ጋሪንታ ዳይና ደግሞ ከስምንቱ የቢያ መስተዳድሮች መካከል ጋሻራ፣ የበን፣ ኦቶማል፣ ወርጼይና ራለይ የሚባሉ አምስት የቢያ መስተዳድሮችን (ወይም አንዳንዴ ጋሪንታ ቢያ እየተባለም ይጠራል) በበላይነት ያስተዳድራል፡፡ ላዋጋንታ ዳይና ከስምንቱ አንዱ የሆነውን የላዋጋንታ ቢያ ብቻ የሚያስተዳድር መሪ ሲሆን፣ ሼይሽንታ ዳይና ደግሞ ሀና የሚባል የአንድ ቢያ መሪ በመሆን ይሰራል፡፡

በጋሪንታ ቢያ (ራስ ገዝ) አስተዳደር ውስጥ፣ ፊዜ የአንድ ቢያ፣ ማሻ ደግሞ የአንድ ቦሄ መሪ በመሆን ይሰራሉ፡፡ በቡርጂ የቢያ (የራስ ገዝ) እና በላዋጋ የቢያ (የራስ ገዝ) አስተዳደር አካባቢዎች ውስጥ ግን፣ ማሻ በወሚንካ ባልባላና በዳይናንካ ባልባላ ውስጥ የወማ ወይም የዳይና ረዳት በመሆን ያገለግላል፡፡ ጋና በወሚንካ ባልባላና በዳይናንካ ባልባላ ውስጥ የወማና የዳይና ተላላኪና ጉዳይ አስፈፃሚ ሆኖ ለሚሰራ ሰው የሚሰጥ ሥልጣን ነው፡፡ በዚህም ወሚንካ ጋና፣ ዳይናንካ ጋና እየተባለ ይጠራል፡፡ የጋናው ዋና ተግባርም ወማውና ዳይናው ወደ ስልጣን በሚመጡበት በወሚሶና በዳይኖማ ሥርዓት ወቅት ለክብራቸው ሲባል የሚዘፈነውንና ዳዋዎ የሚባለውን ሀገረሰባዊ ዘፈን ማስጀመርና መምራት ነው፡፡ ይህ ግን በድሮ ጊዜ ይሰራበት የነበረ ነው፡፡ በአሁኑ የአስተዳደር መዋቅር መሰረት በወሚንካ ባልባላም ሆነ በዳይናንካ ባልባላ ውስጥ ጋና አይመደብም፡፡ በርግጥ በአሁኑ ወቅት የወማ አስተዳደር ባለመኖሩ ጋናም አለመኖሩ ትክክል ነው፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ የዳይና አስተዳደር ቡርጂ ውስጥ ተግባራዊ እየተደረገ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዳይናንካ ባልባላ ውስጥ ጋና የለም፡፡ ወይም አይመደብም፡፡ በአዲሱ መዋቅር መሰረት፣

በዳይናንካ ባልባላ ውስጥ ሁለት አባላት ብቻ ይመደባሉ፡፡ እነሱም ዳይና እና ጃልዓባ የሚባሉ ናቸው፡፡

ጃልዓባ ደግሞ በወማ፣ በዳይና፣ በፊዜና በማሻ ባልባላዎች ውስጥ የወማ፣ የዳይና፣ የፊዜና የማሻ አማካሪና ረዳት ሆኖ የሚሰራ ሹም ነው፡፡ በዚህም ወሚንካ ጃልዓባ፣ ዳይናንካ ጃልዓባ፣ ማሼንካ ጃልዓባ እየተባለ ይጠራል፡፡ በመሪዎቹ ሲታዘዝ ወደ ጠንቋዮችና ተንባዮች በመሄድ ስለ ህዝቡ መፃኢ ሁኔታ ማስጠንቆል፣ ማስተንበይና ውጤቱን ለላከው አካል ማሣወቅ ዋና ተግባሩ ነው፡፡ ከዚህ በተለየ ግን፣ በድሮ ጊዜ፣ ወሚንካ ጃልዓባ በአመት አንድ ጊዜ፣ ከዳይናው ዘንድ በመሄድ እንደ ግብር የመሰሉ ስጦታዎችን ከዳይናው ተቀብሎ ለወማው ያስገባ ነበር፡፡ ከዚህ በተረፈ ግን በሁሉም ደረጃ ያሉ ጃልዓባዎች ተግባር ተመሳሳይ ነው፡፡

ቡርጂዎች መጪው አዲስ ዓመት የሰላም፣ የደስታ፣ የብልጽግና...ወዘተ እንዲሆንላቸው በሚል በወርሃ ዶጎሌ (የካቲት) የሚፈጽሙት ሒጣኖ የሚባል እምነታዊ ሥርዓት አላቸው፡፡ ምኞቱ ለሁሉም ቡርጂ ሲሆን ሥርዓቱ በወማው አማካይነት ይፈጸማል፡፡ ጋሪንታ ዳይናው በጋሪንታ ቢያ፣ ላዎጋንታ ዳይናው በላዎጋንታ ቢያ፣ ፊዜው በቢያ፣ ማሻው በቦሄ፣ ጌሪንካ ወይም ኦለይንካ ኣናው በጌሪኤ ወይም በኦላ ደረጃ የሚፈጸሙ የሒጣኖ ባህላዊ ሥርዓቶችን ይመራሉ፡፡ እምነታዊ ሥርዓቱም የሚፈጸመው በየአካባቢዎቹ ባሉት ባልባላዎች ውስጥ ይሆናል (ምዕራፍ አምስትን ተመልከት)፡፡

ሁሉም የህዝብ መሪዎች ማንኛውንም ተግባር የሚያከናውኑት ብቻቸውን አይደለም፡፡ አንዳቸውም በግላቸው የሚወስኑት ውሳኔ፣ የሚፈፅሙት ተግባር የለም፡፡ ወይም የወማው፣ የዳይናው፣ የማሻው...ወዘተ ብቻ ተብለው የተሰጡ፣ ተከልለው የተቀመጡ ተግባራት የሉም፡፡ ሁሉም ውሳኔዎች የሚሰጡት በጋራ፣ በምክክር ነው፡፡ ማናቸውንም ተግባራት የሚያከናውኑት ጐርሳ ከሚባሉ አማካሪዎቻቸው ጋር እየተመካከሩ፣ በእነርሱ እየታገዙ ነው፡፡ አማካሪዎቻቸው ደግሞ የየጎሳ መሪዎች (ኣንሾች) እና ቀደም ሲሉ በአመራር ላይ የነበሩ፣ የሥልጣን ዘመናቸውን አጠናቀው የተቀመጡ ሰዎች (ጎርሳዎች) ናቸው፡፡ ምንም ነገር ሊያደርጉ ሲፈልጉ ከአማካሪዎቻቸው ጋር ተማክረው ነው፡፡ የአማካሪዎቹን ምክር የማይቀበል፣ ተቀብሎ ተግባራዊ የማያደርግ መሪ በጽህፈት ቤቱ ውስጥ ወይም በሥልጣኑ ላይ ብዙ አይሰነብትም፡፡ በትህትና በታጀበ አሰራር ከቦታው ላይ እንዲነሳ ይደረጋል፡፡ በቦታው ላይ ሌላ መሪ ይመደባል (ክፍል 5.5 ተመልከት)፡፡ ጋሪንታ ዳይናን መምረጥ የወማ ተግባር ነው፡፡

የህዝቡንና የሀገሩን መጻኢ ሁኔታ ጠንቋዮችንና ተንባዮችን በማስጠየቅ፣ ተገቢ በሆነ ጊዜ ጎዴ የሚባለውን እምነታዊ ሥርዓት በማስፈፀም (ምዕራፍ 5 ተመልከት) የህዝቡንና የሀገሩን ደህንነት መጠበቅ አንድ የህዝብ መሪ ሆኖ የተሰየመ ሰው የሚፈጽመው ዋናው ተግባር ነው። በቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓት ደንብ መሰረት፣ አንድ መሪ ሥልጣን ከተረከበበት ማግስት ጀምሮ በህዝቡ ወይም በሀገሩ ላይ ወደፊት ምን ምን ክፉ ነገሮች ሊደርሱ እንደሚችሉ ማነፍነፍ አለበት። ‹‹ይደርሳሉ›› የተባሉት ክፉ አጋጣሚዎች ከመድረሣቸው በፊት መሪዎቹ ሊያውቋቸው፣ አውቀው ሊከላከሏቸው ይገባል። ለህዝብ መሪዎች፣ ወደፊት የሚሆነውን የሚነግሯቸው ደግሞ ትንቢት ተናጋሪዎች ወይም ጠንቋዮች ናቸው[49]። ከተንባዮችም ሆነ ከጠንቋዮች ዘንድ የሚሄዱት ግን ራሳቸው ዋና ዋና መሪዎቹ (ማለትም *ወማው፣ ዳይናው፣ ፊዜው ወይም ማሻው*) ሣይሆኑ *ጃልዓባ* የሚባሉ ረዳቶቻቸው ናቸው። በአካባቢው ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ ያልዘነበ እንደሆነ ከ*ሣጋናንካ ወማ (ከሣጋናንካ ጋን)* ዘንድ በመሄድ ዝናብ እንዲያዘንብ ባለጋኑን መለመን፣ ወማና ዳይና የሆኑ የህዝብ መሪዎች ብቻ ከሚያከናውኗቸው ተግባራት መካከል ተጠቃሽ ነው[50]።

በተለያዩ የቡርጂ ጎሳዎች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን መፍታት የሁሉም ባህላዊ መሪዎች ተግባር ነው። ይሁን እንጂ፣ ከፍ ያሉ የሰው ሞትንና መቁሰልን ያስከተሉ የጎሣ ግጭቶች ሲሆኑ ግጭቶቹን መፍታት በተለይ (የባለጋኖቹም ተግባር መሆኑ ሣይዘነጋ ማለት ነው) የወማው ወይም የዳይናው ተግባር ይሆናል። በመሠረቱ ማናቸውም የጉሣ ግጭቶች እንደተከሰቱ ከዳይናው ወይም ከወማው ዘንድ አይቀርቡም። በግጭቶቹ ምክንያት የሰው

[49] ጥንቆላ ወይም ማስጠንቆል የቡርጂዎች ልማድ እንደልነበር ሁሉም መረጃ ሰጪዎቹ (ቡኬ፣ 27፤ ጫሜ፣ 69፤ ማኒኦ፣ 59፤ ቱኬ፣ 60፤ 2002) አስረግጠው ይናገራሉ። እንደ መረጃ ሰጪዎች አባባል ጠንቋይም ሆነ ጥንቆላ አጉራባች ከሆነው ከኮሬ ብሔረሰብ የተኮረጀ ባዕድ እምነት ነው። ቡርጂ ውስጥ ተግባራዊ መሆን የጀመረው በቅርብ ጊዜ ነው። ከዚያ በፊት ቡርጂዎች ራጅ በሚሉዋቸው፣ በተለይ ስለ ቡርጂ በመተንበይ የሚታወቁትን፣ ኮንሶ ውስጥ የሚገኙትንና ጋዬካ ጆራ የሚባሉ ተንባይ ቤተሰቦችን ይጠቀሙ ነበር። ለዚህ ሲሉም ጥንት ኮንሶ ድረስ ይኬድ እንደነበር ይናገራሉ። የኋላ ኋላ ግን ጠንቋዮች ዘንድ መሄዱ ተጀመረና ተለመደ። በአሁኑ ጊዜ ስለ መፃኢ ሁኔታ ለማወቅ በሁለቱም፣ ማለትም በጠንቋዮችና በተንባዮች ይገለገላሉ። ‹‹መተንበይ ይችላሉ ወይም ይተነቢያሉ›› ተብለው የሚታመኑት ደግሞ በዕድሜ የገፉ አረጋዊያን ናቸው።

[50] የወማ ዋነኛ ተግባር ህዝቡን መዝረፍና ማዘረፍ ነው ብለው የሚሞግቱ ወገኖች አሉ። ‹‹የወማ ተግባር ምንድነው›› ብዬ ላቀረብኩለት ጥያቄ ‹‹መብላት መጠጣት ብቻ›› ብሎ በእርግጠኛነት ስሜት የመለሰልኝ መረጃ ሰጪ (ቱኬ፣ 2002፣ 45) አለ። የወማነት ሥልጣን በተወሰኑ አካባቢዎችና ጐሳዎች ብቻ ተይዞ በነበረበት ዘመን ይህ ዓይነት ተግባር በይፋ ይፈጸም እንደነበር ያስረዳሉ። ይዘረፍ የነበረው ደግሞ በደጋማው አካባቢ ይኖር የነበረው የቡርጂ ህዝብ ነበር። ወማው በዚያ አካባቢ የራሱን ሠራዊት ይልካል። መጥተው ያገኙትን እንስሳ አርደው ሥጋውን ጭነው ለወማው ያስገባሉ። የእህል ክምር አፍርሰው፣ ጉተራ ገልብጠው ይወስዳሉ። ከልካይ አልነበራቸውም። ይህ በዘመኑ የአንድ ወማ የዕለት ተዕለት ተግባር ነበር። በዚያ ዘመን የማይነካው፣ የማይደፈረው፣ የማይዘረፈው ልዕለ ተፈጥሮአዊ ሃይል አላቸው የሚባሉ የባንባላ ጉሳ ንብረት ብቻ ነበር። በመሆኑም አብዛኞቹ የማህበረሰቡ አባላት እንዳይዘረፍባቸው ሲሉ ምርቶቻቸውን ከባንባላ ጉሣ ዘንድ ያስቀምጡ እንደነበር ይነገራል። ከደጋው አካባቢ የሆኑ ሴቶች ቅቤ ሊሸጡ ገበያ የወጡ እንደሆነ ቅቤውን ይዘው ብቻቸውን አይቀመጡም። በወማው ሠራዊት ወዲያው ይነጠቃሉ። ይህን በመፍራትም የባንባላ ጎሳ አባል የሆኑ ሴቶችን ፈልገው፣ ከእነሱ ዘንድ ተጠግተው ቅቤአቸውን የባንባላ ሴቶች ሊሸጡ ከዘረጉት ዕቃ ወይም ቅቤ ጋራ ቀላቅለው በማስቀመጥ ለመሸጥ ይገደዱ ነበር። በእነዚህና በመሣሰሉ ምክንያቶች በዚያን ዘመን የወማ ዋንኛው ተግባር የህዝቡን ደህንነት መጠበቅና ማስጠበቅ ሳይሆን፣ ህዝቡን መዝረፍና ማዘረፍ ነበር ብለው ይሞግታሉ። በእነዚህ ወገኖች እምነት ወማው የህዝብን ደህንነትና ንብረት ይጠብቃል ቢባል እንኳን በተወሰነ አካባቢ የሚኖሩ የተወሰኑ ጉሳዎችን ብቻ የሚመለከት ሊሆን ይችላል እንጂ አብዛኛውን ቡርጂን የሚመለከት አይደለም።

ህይወት ጠፍቶ እንደሆነ ግን በርግጥም ይህ ከፍ ያለ ግጭት፣ ላቅ ያለ ጉዳይ ነው። በመሆኑም በጉዳዩ ዳይናው ወይም ወማው ሊገባበት ይችላል። ይህም ቢሆን የሚፈጸመው ወዲያው ግጭቱ እንደተከሰተ አይደለም። የራሱ የሆነ የአፈፃፀም ሥርዓት አለው። ጉዳዩ ከዳይናው ወይም ከወማው ዘንድ ከመቅረቡ በፊት በአካባቢው ሽማግሌዎችና በበታች ሹማምንት አማካይነት ለመፍታት ይሞከራል። በእነርሱ ደረጃ ችግሩን መፍታት ካልተቻለና ‹‹በዚህ ሰበብ በሁለቱ ጕሣዎች መካከል ከፍ ያለ ግጭት ሊቀሰቀስ ይችላል›› ተብሎ ሲታመን የወቅቱ ከፍተኛ ባለሥልጣን የሆነው ዳይናው ወይም ወማው በጉዳዩ እንዲገባበት ይደረጋል ወይም ይጠየቃል። ሁለቱን ወገኖች አቀራርቦ እንዲያስታርቅ፣ ግጭቱን እንዲፈታ የተጠየቀው ሹምም (ዳይናው ወይም ወማው) ግጭቱን የሚፈታው በሚከተለው መንገድ ነው።

በመጀመሪያ ረዳቱን (ጃልዓባውን) አስከትሎ ከተጐጂ ወገኖች ዘንድ ይሄዳል። ከቤታቸው እንደደረሰ ዘው ብሎ ከቤታቸው አይገባም። ከውጭ ቆሞ በአገሩ ልማድ ‹‹እኔ ልሙትለት፣ እኔ ልደፋለት፣ የእኔ ደም ይፍሰስ…ወዘተ›› እያለ በተጐጂው ቤተሰብ ላይ በደረሰው ጉዳት እጅግ ማዘኑን ይገልጻል። በመቀጠልም ተጎጂ ወገኖች ለበቀል መነሣሣታቸውን ትተው ወደ እርቅ እንዲመጡ ይማፀናቸዋል። "እኔን እዩኝ። በእኔ ላይ ያለውን ካላች እና ሊሶ ተመልከቱ። በእላዩ ላይ ስላለው ስለ ካላቹ እና ስለ ሊሶው ስትሉ እሺ በሉኝ" እያለ ይለምናቸዋል። ልመናውና ተማፅኖው ለሚቀጥሉት ቀናትም አይቋረጥም። ተጎጂዎቹ ወገኖች እሺ እስከሚሉ ድረስ ይቀጥላል።

ተጐጂዎቹ ወገኖች በአንድና በሁለት ቀን ልመና፣ ወዲያው "እሺ" ላይሉት ይችላሉ። ይሁን እንጂ፣ ወማው ወይም ዳይናው እንዲህ በየቀኑ ከቤታቸው መጥቶ፣ ከደጃቸው ቆሞ ሲለምናቸው "እሺ" ማለታቸው፣ ችግሩን በእርቅ ለመፍታት መስማማታቸው የማይቀር ነው። በዚህ ዓይነት ዳይናው (ወማው) ተጎጂውን ወገን እሺ ካሰኘ በኋላ ከረዳቱ፣ ከጃልዓባው ጋር በመሆን ሌሎች የአገር ሽማግሌዎችንና የጎሳ መሪዎችን ይዞ ሁለቱን ወገኖች ያቀራርባል። አቀራርቦ ያስማማቸዋል። የተበደለው እንዲካስ፣ የበደለው እንዲክስ አድርጎ ያስታርቃቸዋል። በግጭቱ ምክንያት በህግ ፊት ሊቀርብ የታሰረም ካለ ከእስር ያስፈታል። በዘመናዊ የዳኝነት አካላት፣ በፍርድ ቤት የተጀመረ የክስ ሂደት ካለም እንዲቋረጥ ያደርጋል። በመጨረሻም ሞጨ የሚባለውን ባህላዊ ሥርዓት በመፈፀም በደል የፈጸመው (የገዳይ) ወገን ከእርኩሰቱ፣ ከኃጥኣቱ እንዲነፃ ያደርጋል። እንዲሁም ሁለቱም ወገኖች ወደ ፊት በክፉ እንዳይፈላለጉ፣ ቦርቶማ በሚባለው ባህላዊ ሥርዓት አማካይነት ሁለቱንም ወገኖች አንድ ጎሣ በማድረግ

ያስተሳስራቸዋል፡፡ ለግጭቱ ማስሪያ ያበጅለታል (*ምጩ* እና *ቦርቶማ* ስለሚባሉ እምነታዊ ሥርዓቶች ምንነትና አፈጻጸም ምዕራፍ አምስትን ተመልከት)፡፡

የቡርጂ ህዝብ አብዛኛው አርሶ አደር ነው፡፡ በእርሻና በከብት እርባታ ይተዳደራል፡፡ በመሆኑም ከምንም በላይ በአካባቢያቸው ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ እንዲዘንብላቸው ይፈልጋሉ፡፡ ዝናብ ሲዘንብ የዘሩት ይበቅላል፡፡ የበቀለው ያፈራል፡፡ በዝናብ ሣር ይበቅላል፡፡ ከብቶች ጠግበው ይበሉታል፡፡ በሬው ጠግቦ ከበላ በሚገባ ያርስላቸዋል፡፡ ላም ደግሞ ወተት ትሰጣቸዋለች፡፡ አካባቢው ይለመልማል፡፡ ጥጋብ እንጂ ድርቅ፣ ረሀብ አይኖርም፡፡ ዝናብ ከሌለ ደግሞ ይህ ሁሉ አይኖርም፡፡ የሚያርስ በሬ፣ የምትታለብ ላም አትኖርም፡፡ የተዘራው አይበቅልም፡፡ የበቀለው አያፈራም፡፡ በአጭሩ የቡርጂዎች ህይወት የተቆራኘው ከዝናብ ጋር ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ቡርጂዎች ከምንም በላይ የዝናብ መጥፋትን ይፈራሉ፡፡ ወቅቱን ጠብቆ እንዲዘንብላቸው መመኘት፣ መጸለይ የዘወትር ተግባራቸው ነው ፡፡

አሁን አሁን እየቀነሰ ይምጣ እንጂ፣ ጥንት ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ ያልዘነበ እንደሆን ቡርጂዎችን ብዙም የሚያስጋቸው ነገር አልነበረም፡፡ ለምን? ቢሉ ባሻቸው ጊዜ ዝናብ የሚያዘንብላቸው *ሣጋናንካ ወማ* ወይም *ሣጋናንካ ጋን* የሚባል የእምነት መሪ ወይም ‹‹የዝናብ ንጉስ›› ስላላቸው ነው፡፡ ዝናብ ሣይዘንብ ከቆየና ወደፊትም ላይዘንብ ይችላል ብለው ሲሰጉ፣ የደንቡን ይዘው ወደ ሣጋናንካ ወማ *(ሣጋናንካ ጋን)* ዘንድ ይሄዳሉ፡፡ *ሣጋናንካ ጋን* የጠየቁትን የማይነሣ መንፈሳዊ መሪ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በእንዲህ ዓይነቱ ችግር ወቅት ጥንት *ከሣጋናንካ ወማው* ዘንድ የሚሄዱት፣ ሄደው ዝናብ እንዲያዘንብላቸው የሚለምኑት ደግሞ ወማ ወይም ዳይና የሆኑ ባህላዊ መሪዎች ብቻ ነበሩ፡፡ ከእነሱ ውጪ ሌላ ሰው ሄዶ ቢለምን *ሣጋናንካ ወማው* አይሰማም፡፡ ጠብታ ዝናብ አይሰጥም፡፡ ስጦታም አይቀበልም፡፡ ዛሬ ዛሬ ግን ማንም መሄድ ጀምሯል፡፡ *ሣጋናንካ ወማውም* ቢሆን ያመጡትን ተቀብሎ የጠየቁትን ይሰጣቸዋል፡፡

ዳይናው ወይም ወማው *ከሣጋናንካ ወማው (ጋን)* ዘንድ የሚሄደው ብቻውን አይደለም፡፡ የራሱን ጃልዓባ አስከትሎ ነው፡፡ በድሮ ጊዜ ወደ ሣጋናንካ ወማ ሲኬድ ጥሬ ቅቤና ጨው ተይዞ ይኬድ ነበር፡፡ ቅቤና ልብስ ተይዞ የሚኬድበት ጊዜም ነበር፡፡ ዛሬ ግን የአልኮል መጠጥና (የአበሻ አረቄና) ገንዘብ ይዞ መሄድ ተጀምሯል፡፡ ሹማምንቱ እነዚህን ይዘው በመሄድ ችግራቸውን ያጫውቱታል፡፡ በዝናብ እጦት ህዝቡ ሊራብ መሆኑን፣ የመጡትም ዝናብ ፍለጋ እንደሆነ ይነግሩታል፡፡ የሣጋናንካ ወማውም የሚሉትን ያዳምጣል፡፡ አዳምጦም "እውነት የአባቶቻችን፣ የአያቶቻችን፣ የቅድመ አያቶቻችን ልማድ፣ ደንብ ዛሬም ያለ እንደሆነ የጠየቃችሁትን ይሰማል፡፡

እነርሱ የት ሄደው ነው ህዝቡንና አገሪቱን ድርቅ የሚመታው?" ብቻ ነው የሚለው፡፡ ከዚህ ውጭ ዝናብ ለማዘነብ ብሎ የሚፈፅመው እምነታዊ ሥርዓት የለም፡፡ እጣን አያጨስም፡፡ ማህሌት አይቆምም፡፡ ውዳሴ መዝሙር አያሰማም፡፡ ጠያቂዎቹ ከእሱ ዘንድ ወጥተው ወደ መንደራቸው የሚመለሱት በዝናብ በስብሰው እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህን በተመለከተ አንዱ መረጃ ሰጪ ያጫወተኝን፣ ‹‹በእውነት ተፈፀመ›› ያለውን ከዚህ መጥቀሱ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ይህን የነገረኝ መረጃ ሰጪ ከሁለት፣ ከሶስት ዓመት በፊት የቡርጂ ዳይና ሆኖ ያገለገለ ሰው ነው፡፡ በሥልጣን ዘመኑ ራሱ የፈጸመውን፣ ‹‹በእውነት ፈፀምኩ ያለውን›› እንዲህ በማለት ይተርካል፡፡

> እኔ ዳይና ሆኜ በአገለገልኩበት ዓመት ውስጥ ነው፡፡ በአካባቢው፣ በሀገሩ ዝናብ ጠፋ፡፡ ቡቃያው ሊደርቅ ሆነ፡፡ በአጭሩ በወቅቱ መጣል የነበረበት ዝናብ ሣይጥል ቀረ፡፡ በዚህ የተነሣ ከሣጋናንካ ወማው ዘንድ ሄድኩኝ፡፡ ስሄድ ብቻዬን አልነበረም የሄድኩት፡፡ የእኔ ጃልዓባም አብሮኝ ነበር፡፡ ጃልዓባው በጀሪካን አረቂ ይዞ ነበር አብሮኝ የሄደው፡፡ እኔም ደግሞ ወደ ስምንት የሚሆን ብር ይዤአለሁ፡፡ እነዚህን ይዘን ወደ ሣጋናንካ ወማው ቤት ሄድን፡፡ ከቤታቸው ደረስን፡፡ ወደ ውስጥ ዘለቅን፡፡ "ተቀመጡ" ተባልንና ተቀመጥኩኝ፡፡ እኔ ከተቀመጥኩ በኋላ ጃልዓባው "አባቴ" ብሎ ወማውን ጠራቸው፡፡ "አቤት" አሉት፡፡ "አቤት" ሲሉት ጊዜ "ከታችኛው በኩል እዞራለሁ" አላቸው፡፡ ሲላቸው "ለምድነው የምትዞረው?" ብለው መልሰው ጠየቁት፡፡ "ከታች በኩል ዞሬ የመጣሁበትን ጉዳይ እናገራለሁ" አላቸው፡፡ ይህን ሲላቸው "ተው አትዙር፡፡ አትዙር፡፡ ዝም ብለህ ጉዳይህን ተናገር" ብለው ከለከሉት፡፡ ይኸነ ጃልዓባው ‹‹በድሮ ጊዜ ቢሆን እጅ ተነስቶ፣ ብዙ ነገር ተኩኖ ነበር የመጡበት ጉዳይ የሚነገረው›› ሲላቸው "ተወው፣ ተወው፡፡ ‹እኔ አፈር ልብላልህ› ማለት ድሮ ቀረ፡፡ ሌላ ሌላውን ትታችሁ የመጣችሁበትን ጉዳይ ብቻ ተናገሩ" አሉ፡፡ ይህን ጊዜ የእኔ ጃልዓባ " ይኸውልዎት አባቴ፣ እንደው ስናየው ይህ ዓመት ጥሩ ዓመት አልሆን እያለ፣ እየከፋ መሄድ ሲጀምር ጊዜ፣ ዝናብ ምናምኑ….."ብሎ ንግግሩን ገታ ሲያደርግ /ሲያቆም/ እኔ ደግሞ እሱ፣ ጃልዓባው ካቆመበት ቀጥዬ "……ሲቋረጥብኝ ጊዜ ነው እኔ የመጣሁት ንጉሥ ሆይ" አልኩኝ፡፡ እኔ እንግዲህ እንደረዳቴ፣ እንደ ጃልዓባው ከታች በኩል አልዞርም፡፡ ከታች አልቀመጥም፡፡ እኔ ቁንጮ ላይ ያለሁ የሀገር መሪ ስለሆንኩኝ ከእሳቸው፣ ከሣጋናንካ ወማው አጠገብ ነው አልፌ የተቀመጥኩት፡፡ የምናገረውም እዚያው ከተቀመጥኩበት ሆኜ ነው፡፡ እንዲህ ስላቸው "ይኸውልህ፣ በእርግጥም ድሮ ዝናብ ይጠየቅ ነበር፡፡ ጥንት በአባቶቻችን፣ በአያቶቻችን ዘመን ዝናብ አዘንብልን እየተባለ የምር ይጠየቅ ነበር፡፡ በዚያን ዘመን ታዲያ ዝናብ ጠያቂዎቹ ዝናብ ሲጠይቁ ገና ከቤታቸው እንደ ወጡ ነበር ይዘንብ የነበረው፡፡ ከዚህ ደርሰው እስከሚጠይቁ አይጠብቅም ነበር" አሉን፡፡ እንዲህ ሲሉን እኛ ደግሞ "ዛሬም ቢሆን ይህ የጥንቱ ልማዳችን መቼ ጠፋ? ዛሬም ይኖራል" አልናቸው፡፡ ይህን ብለን ስናበቃ ጃልዓባው ተነስቶ ከሳማቸው በኋላ አረቂውን ሰጣቸው፡፡ እነርሱ ያንን አረቂ ለሁለት ጠጡት፡፡ እኔ ቀድሞውኑ ስለማልጠጣ አልተካፈልኳቸውም፡፡ እንዲሁ ቁጭ ብዬ ሳወራ ቡና ተፈላልኝ፡፡ ምግብም ተሠርቶ ቀረበልን፡፡ በልተን ከጠጣን በኋላ "ንጉሥ ሆይ! እንግዲህ ወደ ቤታችን ልንሄድ ነው" አልናቸው፡፡ "እሺ ሂዱ፡፡ ሂዱ፡፡ የአባቴ፣ የአያቴ ልማድ ዛሬም ያለ ከሆነ እግዜር በላያችሁ ላይ ጥላ ይያዝላችሁ፡፡ መሬቱ ይቀዝቅዝ" አሉን፡፡ ተሰናብተናቸው ከቤታቸው ስንወጣም "ከመንገዳችሁ ላይ የዘነበባችሁ እንደሆነ ከማንም ቤት ጐራ እንዳትሉ ፡፡ የትም እንዳትጠለሉ፡፡ የቱንም ያህል ቢያበሰብሳችሁ ዝም ብላችሁ መበስበስ እንጂ ከማንም ቤት ጐራ አትበሉ፡፡ አትጠለሉ፡፡ ከቤታችሁ ግቡ" ብለው ሸኙን፡፡ የዚያኑ ዕለት ገና ከቤታቸው ወጥተን ወዲህ እንዳዘቀዘቅን ለስንት ጊዜ ጠፍቶ የከረመው ዝናብ ወደ ራስያ አካባቢ ማካፋት ጀመረ፡፡ በርግጥም ይህ ቤተሰብ ያለው ነገር አለው፡፡ ይህን ወደ ራስያ አካባቢ የጠቆረውን ነገር እየተመለከትን ‹‹ያ ነገር ደመና ነው? ወይስ ዝናብ ነው?›› እያልን ስንጠያየቅ ነበር፡፡ ትንሽ ወደፊት ሄደን የበን አካባቢ ልንደርስ ስንል ወርዴይ አካባቢም ይዘንብ ጀመረ፡፡ ትንሽ ቆይቶ ዝናቡ ከመንገድ ላይ ያዘን፡፡ ገና ላንሴ ከሚባል አካባቢ እንደደረስን ዶፉን አወረደብን፡፡ በተሰጠን ማስጠንቀቂያ መሠረት የትም ሳንጠለል፣ ከማንም ቤት ጐራ ብለን ሳናባራ፣ በዝናቡ ዶፍ እየተደበደብን፣ እየተመታን ብስብስ ብለን ከመንደራችን ደረስን፡፡ ከቤታችን ገባን፡፡ በዚህ አይነት በዚያን እለት ለምነን የተሰጠንና ወዲያውኑ መዝነብ የጀመረው ያ ዝናብ ሳያቋርጥ ለረዥም ቀናት

> በሁሉም የቡርጂ አካባቢዎች ዘንቦ፣ እስከ ሰገን [ቆላማ አካባቢ ] ድረስ ሁሉ ሳይቀር በሚገባ ዘንቦ፣ ህዝቡ ጥሩ ምርት እንዲያገኝ አደረገ። ህዝቡን ከአንዣበበበት አደጋ የታደገው እንዲህ ተለምኖ የዘነበ ዝናብ ነው። በሥልጣን ዘመኔ ይህን የመሠለ ሥራ ለህዝቤ ሠርቻለሁ (ማኒአ፣ 2ዓዓ2፣100-103)።

በማህበረሰቡ ሰብሎች ላይ ተምች የወረደበት፣ አንበጣ የዘመተበት እንደሆነ እነዚህን የማጥፋት ሥልጣን ወይም ልዕለ ተፈጥሮኣዊ ሀይል አላቸው ወደሚባሉ *ባለጋኖች* ዘንድ በመሄድ *ባለጋኖቹ* ወጥተው ተምቹንና አንበጣውን እንዲያወግዙ ማድረግ የእያንዳንዱ ባህላዊ መሪ የሥራ ድርሻ ነው። ይሁን እንጂ አንዳቸውም ይህን  ተግባር በቀጥታ መፈፀም አይችሉም። ከባለጋኖቹ ጋር በቀጥታ ተገናኝተው ችግራቸውን እንዲናገሩ እምነታዊ ሥርዓቱ አይፈቅድላቸውም። ይህን ሥራ የሚሠራ፣ የፖለቲካ እና የእምነት መሪዎችን ወይም ተቋማትን የሚያገናኝ *ቢታናች* የሚባል ባለስልጣን አለ። የህዝብ መሪዎቹ ማድረግ የሚችሉት ችግራቸውን፣ ጉዳያቸውን ለቢታናቹ መንገር ብቻ ነው (ምዕራፍ አምስትን ተመልከት)። ቢታናቹም ከህዝብ መሪዎች የቀረበውን ጥያቄ ወስዶ ለባለጋኑ ይነግረዋል። ባለጋኑም ከተራራ ላይ ወጥቶ ክስተቱን ያወግዛል[51] ። አውግዞ ተምቹም ሆነ አንበጣው በህዝቡ ሰብል ላይ ጉዳት ሳያደርሱ ከአካባቢው እንዲጠፉ፣ እንዲሠወሩ ያደርጋል።

ከፍ ሲል ማሻ ሁለት ዓይነት እንደ ሆነ ገልፀናል። አንደኛው በቦሄ ደረጃ፣ ራሱን ችሎ፣ የቦሄ አስተዳዳሪ ሆኖ የሚመደበው *ማሻ* ነው። ይህ በአብዛኞቹ የቡርጂ አካባቢዎች የሚሰጥ ሥልጣን ነው። ሁለተኛው ከወማ እስከ ኦላ ድረስ ባሉት በአስፈፃሚ ተቋማት ውስጥ ላሉ ኃላፊዎች ረዳት ሆነው የሚመደቡ፣ በተወሰኑ የቡርጂ አካባቢዎች ብቻ ተግባራዊ የሚደረጉ ማሻዎች ናቸው። እነዚህም *ወሚንካ ማሻ፣ ዳይናንካ ማሻ፣ ኀሳንካ ማሻ፣ ገሬንካ ማሻና ኦለይንካ ማሻ* በመባል ይታወቃሉ። ተግባራቸውም እንደስማቸው የተለያየ ነው። የመጀመሪያውን *ማሻ (ቦሄንካ ማሻ)* ተግባር ከሌሎች ሹማምንት ጋር ከፍ ብለን ነግረናል። ከዚህ የሁለተኛውን *ማሻ* ተግባር ብቻ እናቀርባለን።

*ወሚንካ ማሻ በወሚንካ ባልባላ* ውስጥ የወማ ረዳት ሆኖ የሚሰራ ሹም ነው። ተጠሪነቱ *ለወማው* ሲሆን የአገልግሎት ዘመኑም ልክ እንደ ወማው አንድ ዓመት ነው። ዋነኛ ተግባሩም እምነታዊ ስርዓቶችን ማስፈፀም ነው። በድሮ ጊዜ ቡርጂን አቋርጠውም ሆነ ከቡርጂ ጋር በቡርጂ ገበያ ይገበያዩ ከነበሩት ከቦረናና ከሶማሌ ታላላቅ ነጋዴዎች ላይ ቀረጥን የመሰለ ነገር

---

[51] ግን አይራገምም። አይሳደብም። መራገም፣ መሳደብ የባለጋን ባህርይ፣ የባለጋን ተግባር አይደለም። እርሱ መመረቅ እንጂ መራገም አያውቅም። እርሱ ክፉውንም በጎውንም ነገር ይመርቃል። ይህ ምርቃቱ ግን ክፉ ሀሳብ ይዘው ለሚመጡት እርግማን፣ ደግ ሀሳብ ለሰነቁት ደግሞ በረከት ይሆናል። እንደ መረጃ ሰጪዎቹ (አሊስ፣ 2002፣ 8፤ቱኬ፣ 2002፣ 17) ውግዘቱም ቢሆን በረዳቱ በቢታናች ጉትጎታ ነው ከአንደበቱ የሚወጣው። ይህም ቢሆን እጅግ የተቆጠበና ጥንቃቄ የተሞላበት ነው። ለምሳሌ ሰብል የወረረውን የአንበጣ መንጋን ለማውገዝ ሲፈልግ "የአያቶቼ፣ የቅድመ አያቶቼ ካልሆንክ በመጣህበት አኳኋን ወደ መጣህበት ገስግስ" ነው የሚለው። እንጂ ባለጋን «እንዲህ ያድርግህ፣ ይፍለጥህ፣ ይቁረጥህ...ወዘተ» አይልም። ይህን ማለት የባለጋን ባህሪ፣ የባለጋን ተፈጥሮ አይደለም።

መሰብሰብ የወሚንካ ማሻ ሌላው ተግባር ነበር። ከነጋዴዎች ላይ የሰበሰበውንም ከወማው ጋር እኩል ይካፈላል (Amborn and kellners, 1999፣ 62)::

*ጎሳንካ ማሻ* በሁለተኛው የማሻ ምድብ ስር የሚጠቀስ ሌላው ባለ ስልጣን ነው። ጎሳንካ ማሻ በጕሣንካ ባልባላ ውስጥ ለጎሳ መሪው ረዳት ሆኖ ለሚሰራ ሹም የሚሰጥ ማዕረግ ነው። የጎሳ መሪውን ዓላማ ማሳካት ዋነኛ ተግባሩ ይሆናል። በዚህም ከጎሳ መሪው ለጎሳው አባላት የሚተላለፉ መልዕክቶችን ያደርሳል። እንዲሁም ከጎሳው አባላት ለጎሳ መሪው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ወይም አቤቱታዎችን ተቀብሎ ለጎሳው መሪ ያቀርባል ወይም ያሰማል። በአጭሩ በጎሳ መሪውና በጎሳው አባላት መካከል አገናኝ ወይም ድልድይ ሆኖ ይሰራል። ጎሳንካ ማሻ ከጎሳው አባላት መካከል አንድ ሰው የሞተ እንደሆነ የአባሉን ሞት ለጎሳው አባላት የማሳወቅ ወይም የማርዳት ተግባር ይፈፅማል። በጎሳው መሪ ሲታዘዝም ለተለያዩ ባህላዊና ማህበራዊ ጉዳዮች የጎሳውን አባላት ይጠራል፤ ይሰበስባል። በየዓመቱ በጎሳ ደረጃ በሚፈፀመው *በሐጣኖ ሥርዓት* ላይ በመገኘት የጎሳ መሪውን ይረዳል። ለስርዓቱ የሚታረደውን የእንስሳ *ሥጋ* (እንስሳው በግ፣ ፍዬል ወይም በሬ ሊሆን ይችላል) ለጎሳው አባላት እኩል ያከፋፍላቸዋል። ከታረደው እንስሳ ቆዳ ላይ ትንሽ ቆርጦ በክንዱና በጣቱ ላይ ያጠልቃል። ጕሳውን በሚመለከቱ በማናቸውም ጉዳዮች ላይ ከጎሳ መሪው (ከኣንሽ ወይም ከጎሳንካ ኣና) ጋር የቅርብ አማካሪና ረዳት በመሆን ይሳተፋል። የጎሳንካ ማሻ ተጠሪነቱ ለጎሳንካ ኣናው ሲሆን የአገልግሎት ዘመኑም ልክ እንደ ኣንሽ የእድሜ ልክ ይሆናል።

ሌላው ገሬንካ[52] ማሻ ይባላል። ለገሬንካ ኣና (ለገሪኤው መሪ) ረዳት ሆኖ የሚሰራ ሰው የሚጠራበት ማዕረግ ነው። ተጠሪነቱ ለገሪኤው መሪ ሲሆን ዋና ተግባሩም በማናቸውም ጉዳዮች የገሪኤውን መሪ መርዳት ነው። በገሪኤው ነዋሪዎች አማካይነት በህብረት የሚከናወኑ ተግባራት ሲኖሩ፣ ለሚሰራው ስራ ሁኔታዎችን በማመቻቸትና ስራውን በመቆጣጠር የገሪኤውን መሪ ያግዛል። ከዚህም በላይ የገሪኤው መሪ መልዕክተኛ በመሆን ይሰራል። በመሪው ሲታዘዝም ልዩ ልዩ ማስታወቂያዎችን ለነዋሪዎቹ ያውጃል። ነዋሪው ማወቅ ያለበትን ያሳውቃል። መፈፀም

[52] በተወሰኑ የቡርጂ አካባቢዎች ብቻ (በተለይም በቡርጂ የቢያ አስተዳደር ውስጥ) ተግባራዊ የሚደረግ መዋቅር ነው። ገሪኤ ከቦሄ (ከቀበሌ) አነስ፣ ከኦላ (ከጎረቤት) ደግሞ ከፍ ብሎ የሚዋቀር የመኖሪያ አካባቢ ነው። ቀደም ሲል በነበረው ልማድ ገሪኤም ሆነ ኦላ የሚመሰረተው ቤተሰባዊ ዝምድና ወይም ትስስር ባላቸው ሰዎች አማካይነት ነው። በሌላ አገላለፅ የአንድ ገሪኤ ወይም ኦላ ነዋሪዎች አብዛኞቹ የአንድ ቤተሰብ ወይም ጎሳ አባላት ናቸው። ወይም በአንድ አዲስ በሚመሰረተው ገሪኤ ውስጥ ቀድመው የሚሰፍሩት ወይም አዲስ ገሪኤ የሚመሰርቱት ቤተሰባዊ ዝምድና ያላቸው ሰዎች ይሆናሉ። የሌላ ጎሳ ወገን የሆኑት የሚመጡትና የሚሰፍሩት ከዚያ በኋላ ነው። በአሁኑ ወቅት ግን እንዲህ ዓይነት አሰራር የቀረ ይመስላል። ይሁን እንጂ የዚህ ዓይነቱ መዋቅር (ገሪኤ) በአብዛኞቹ ቡርጂዎች ዘንድ ጥንትም ሆነ ዛሬ አልተለመደም።

ያለባቸውን እንዲፈጽሙ ያዛል፡፡ ነዋሪውን ለስራና ለስብሰባ ይጠራል፡፡ ከሁሉም በላይ ግን በገሪኤው የሚከናወኑ ማናቸውንም እምነታዊ ስርዓቶችን በሃላፊነት መምራት ወይም መፈፀም *የገሪኤይንካ ማሻ* ትልቁ ተግባር ነው፡፡ በዚህም በገሪኤ ደረጃ በአመት አንድ ጊዜ በሚፈጸመው በሐጣኖ ስርዓት ላይ ከፍተኛ ተሳትፎ ያደርጋል (Amborn and Kellners, 1999, 53):: *ኦለይንካ ማሻ* ተጠሪነቱ *ለኦለይንካ ኣና* ሲሆን ተግባሩም ከፍ ሲል ከተጠቀሰው *ከገሪኤንካ ማሻ* ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

### 4.4.2 የሌሎች ባህላዊ መሪዎች ተግባር


በቡርጂ ባህላዊ አስተዳደር ውስጥ ከፍተኛ ሚና ያላቸው፣ ነገር ግን በባሻ *ሥርዓት* የማይካፈሉ ባህላዊ መሪዎች መኖራቸውን ቀደም ብለን ጠቅሰናል፡፡ እነዚህም *ኣንሸ፣ ሃዩ፣ ኣርጉማንቾ፣ ኦለይንካ (ገሪኤንካ) ኣና እና ሉብ* ናቸው፡፡ የእያንዳንዳቸው ተግባርም ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

#### 4.4.2.1 የኣንሸ ተግባር

ኣንሸ ለአንድ ጎሳ መሪ ለሆነ ሰው የሚሰጥ ማዕረግ ነው፡፡ በጎሳ መሪነቱም የጎሳውን ማናቸውንም ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በበላይነት ይመራል፡፡ የጎሳውን የዕለት ተዕለት ጉዳዮችን ይቆጣጠራል፡፡ በጎሳው አባላት መካከል የሚከሰቱ አለመግባባቶችን ያረግባል፡፡ ከጎሳ አባላት የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ተቀብሎ ያስተናግዳል፡፡ ዳኝነት ያያል፡፡ የተበደለው እንዲካስ፣ የበደለው እንዲክስ ያደርጋል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ጥፋተኛውን ይመክራል፡፡ ይገስጸዋል፡፡ ከጎሳው ስርዓትና ደንብ ያፈነገጡ (የሚያፈነግጡ) የጎሳው አባላት ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ይመክራል፤ ያስመክራል፡፡ በእምቢተኝነታቸው የቀጠሉ (የሚቀጥሉ) ሲኖሩ ደግሞ ከቀላል ቅጣት እስከ *ጪርዳ* (ከጎሳው ብሎም ከማህበረሰቡ ማግለል) በመባል እስከሚታወቀው ከፍተኛውን ቅጣት ድረስ ሊቀጣቸው ይችላል፡፡ እንዲሁም *ኣንሸ* በከፍተኛው የህዝብ ሸንጎ *(በጎርሶማ)* ውስጥ ጎሳውንና የአካባቢውን ህዝብ ወክሎ ይሳተፋል፡፡

*ኣንሸ፣ በጎርሶማ* አባልነቱ በቡርጂ የአስተዳደርና የእምነት *ሥርዓት* ውስጥ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ ማህበረሰቡ የሚመራበትን ባህላዊ የፖለቲካ *ሥርዓት* ያበጃጃል፡፡ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ተግባራትን በበላይነት ይመራል፡፡ ማህበረሰቡ የሚተዳደርበትን ደንብ ያወጣል፡፡ አዲስ *ሥርዓት* ይቀርፃል፡፡ ነባሩን ያሻሽላል፡፡ ከላይ ሆኖ አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡ ወይም አስፈፃሚ አካላትን ይቆጣጠራል፡፡ በአስፈጻሚ ተቋማት ውስጥ በአመራር ላይ የተቀመጡ የህዝብ መሪዎች እንዴት መስራት እንዳለባቸው፣ ህዝብንና አገርን እንዴት ማስተዳደርና መምራት እንዳለባቸው

ይመክራቸዋል። መንገዱን ያሳያቸዋል። የህዝብ መሪዎች በተሳሳተ መንገድ እንዳይጓዙ፣ ህዝቡን እንዳይበድሉ፣ በስልጣን እንዳይባልጉ የሚጠብቀው፣ ሲሣሣቱ የሚያርማቸው፣ ሲጣመሙ የሚያቃናቸው በዋናነት *ኣንሽ* (ሌላው *ጎርስ* መሆኑን ልብ ይሏል) ነው።



<u>ሥዕል ቁ. 5</u>፣ ተመራማሪው፣ የኣናቡራ ጎሣ መሪ ከሆኑት፣ ከኣንሽ ቱኬ ሀርቦ ጋር፣ አዳያ በሚባለው አካባቢ በሚገኘው በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ የቃል መጠይቅ ሲያደርግ፤

ከጎሳው አባላት መካከ ል ለባለጋን ረዳት ሆ ኖ የሚሰራውንና ቢ ታናች የሚባለውን ሹም የሚመድበው ኣንሽ ነው። የኣንሽ ተግባር ይህ ብቻ አይደለም። አንድ ባለጋን ለህዝብ ሸንጎ (ለጎርሶማ) መቅረብ ያለበት ጉዳይ ካለውና ጉዳዩ ፖለቲካዊ ይዘት ያለው ከሆነ፣ ይህንን የባለጋኑን ጉዳይ ባለጋኑን ወክሎ ለጎርሶማው (ለህዝብ ሸንጎ) የሚያቀርብለት፣ አቅርቦ ጉዳዩን የሚናገርለት፣ የሚያስወስንለት፣ አስፈላጊም ሲሆን የሚከራከርለት ኣንሽ እንጂ ራሱ ባለጋን አይደለም። ባለጋን በህዝብ ካልተጠየቀ በስተቀር በፖለቲካ ጉዳዮች ውስጥ አይሳተፍም። በህዝባዊ ስብሰባዎች ላይ አይገኝም። የእሱ ተግባር መንፈሳዊ ብቻ ነው። በመሆኑም ለህዝብ ሸንጎ መቅረብ ያለበት ጉዳይ ሲኖረው ረዳቱ ለሆነው *ለቢታናቹ* ይናገራል። *ቢታናቹ* ደግሞ የባለጋኑን ጉዳይ አምጥቶ ለኣንሹ ያሳውቃል። ለምሣሌ ባለጋኑም ሆነ ሚስቱ በአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ስድብ፣ ዛቻ፣ ወዘተ. ደርሶባቸው እንደሆነ ‹‹እገሌ ወይም እነ እገሌ እንዲህ እንዲህ አሉኝ፣ እንዲህ እንዲህ አድርገው በድለውኛልና ስሙልኝ፣ ጠይቁልኝ፣ ወዘተ.›› የሚል አቤቱታ ለአካባቢው ጎርሶማ ሊያቀርብ፣ አቅርቦ ግለሰቡን ወይም ቡድኑን ሊያስቀጣ፣ ግለሰቡ የህዝብ መሪ የሆነ እንደሆነ ደግሞ ከሥልጣኑ ሊያስወርደው ይፈልጋል እንበል። ይሁን እንጂ

ራሱ አቤቱታውን ይዞ ከጎርሶማው ፊት መቅረብ ስለማይችል ጉዳዩን ለቢታናቹ ያሳውቃል። ቢታናቹም በተራው የባለጋኑን አቤቱታ ለኣንሽ ያቀርባል። ኣንሹም አቤቱታው ተገቢ መሆን አለመሆኑን ይመረምራል። ፖለቲካዊ ይዘት ይኑረው አይኑረው ይገመግማል። ተገቢ ነው ብሎ ሲያምን አቤቱታውን ራሱ ይዞ ከጎርሶማው ፊት ይቀርባል። አቅርቦ ያስወስናል። ውሳኔውንም በቢታናች አማካይነት ባለጉዳዩ (ባለጋኑ) እንዲያውቅ ያደርጋል። ጉዳዩ ፖለቲካዊ ይዘት የሌለውና ከጎርሶማው ፊት መቅረብ የማይችል መሆኑን ሲረዳ ደግሞ ጉዳዩን ለባለጋኑ ይመልሰዋል። በዘመናዊ የህግ ቋንቋ ‹‹መዝገቡን ዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ይመልሰዋል›› የማለት ያህል ነው። አቤቱታውን ውድቅ ያደርግበታል። በዚህም ኣንሽ በቀጥታም ባይሆን በተዘወርዋሪ መንገድ ባለጋንን ይቆጣጠራል ማለት ይቻላል።

በአጠቃላይ በቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካ ስርዓት ውስጥ ቁልፍ ሚና ካላቸው ከከፍተኛ ሹማምንት ፊት የሚሆነው ኣንሽ ነው። ይህ በመሆኑም በማናቸውም ደረጃ በሚጠሩ የጎርሶማ ጉባኤዎች ላይ መገኘት ከነበረባቸው ኣንሾች መካከል አንድ ኣንሽ እንኳን ቢቀር፣ ጉባኤው አይካሄድም። ለሌላ ቀን ይቀጠርና ይበተናል እንጂ ሁሉም ኣንሾች ባልተገኙበት ሁኔታ ማንኛውም የጎርሶማ ጉባኤ አይካሄድም።

ኣንሽ *በጎርሶማው* ላይ የሚካፈለው ጎሳውን ብቻ ሣይሆን የአካባቢውንም ህዝብ ወክሎ ነው። በድሮውም ሆነ በአሁኑ አሰራር የጉልጉባው ጎርሶማ ጉባኤ ሲቀመጥ ከእያንዳንዱ ቢያ አንድ አንድ ኣንሽ ተሳታፊ ይሆናል። በዚህም *ኦቶማሊንካ ኣንሽ (የኦቶማል ኣንሽ)፣ ወርዴይንካ ኣንሽ (የወርዴይ ኣንሽ)*…ወዘተ እየተባሉ ይጠራሉ። ወደ ሥልጣን ለመምጣት ሲባል በሚቀርቡ በ‹‹ስልጣን ይሰጠኝ›› ጥያቄዎችና በምርጫ ውጤቶች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከሚሰጡት ሹማምንት መካከል አንዱ ኣንሽ ነው። በአጭሩ ኣንሽ የቡርጂን ባህላዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ህገ ደንብ የሚያወጣ፣ አፈፃፀሙን ከላይ ሆኖ የሚቆጣጠር፣ በፖለቲካ እና በእምነት ተቋማት መካከል ድልድይ ሆኖ የሚሰራ ከፍተኛ ሹም ነው። በቡርጂ የፖለቲካና የእምነት ስርዓት ውስጥ *ኣንሽ* ሳያውቅ የሚፈፀም አንዳች ጉዳይ የለም። ሁሉም ጉዳይ *ኣንሽን* ይመለከተዋል። ሁሉም የህዝብና የአካባቢ ጉዳዮች በመዳፉ ውስጥ ናቸው ማለት ይቻላል።

#### 4.4.2.2. የሃዩ ተግባር

ከፍ ሲል ሃዩ የህግ መሪ መሆኑ ተጠቅሷል። እንዲሁም ህግ በቡርጂ ባህላዊ የግርዛት ስርዓት ውስጥ የሚመሰረት፣ በወጣት ወንዶች የተገነባ ተቋም መሆኑ ተገልጿል። ይህ ማህበራዊ

ተቋምም በቡርጂዎች ዘንድ እንደ መከላከያ ኃይል ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ስለሆነም ይህን በወጣት ወንዶች የተገነባውን የመከላከያ ሃይልን መምራት፣ ማዘዝ፣ መቆጣጠርያ፣ አጥፊውን መቅጣት ከሃዩ ተግባራት መካከል ጥቂቶቹ ይሆናሉ፡፡

የሃዩ ዋና ተግባር የማህበረሰቡንና የአካባቢውን (የቡርጂን) ደህንነት መጠበቅና ማስጠበቅ ነው፡፡ በመሆኑም የህዝቡን ሰላም የሚያደፈርስ፣ ደህንነቱን የሚፈታተን ሁኔታ በተፈጠረ ጊዜ በሥሩ ያለውን የመከላከያ ኃይል (ሉብ) ይዞ በሁኔታው ላይ ፈጥኖ ይደርሳል፡፡ ወይም ይዘምታል፡፡ ዘመቻውንም በበላይነት እየመራ ከህዝቡ ችግር ጋር ፊት ለፊት ይጋፈጣል፡፡ (ጦርነትም ቢሆን ያዋጋል፡፡ ይዋጋል) ህዝቡን ከችግር ይታደጋል፡፡ ከዘመቻው የቀረ፣ ትዕዛዝ የጣሰ አባል ካለ ይቀጣል፡፡ ቅጣቱ ከተግሳጽ እስከ ንብረት መውረስ፣ ከፍ ሲልም ከማህበረሰቡ እስከ ማግለል ድረስ ሊደርስ ይችላል፡፡

የሃዩ ተግባር በዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ ከፖለቲካዊ ጉዳች በተጨማሪ፣ መንፈሳዊ (እምነታዊ) ጉዳዮች ላይም ይሳተፋል፡፡ በዚህም ህዝቡን ወደፊት ከሚመጡበት ክፉ አጋጣሚዎች (ከበሽታ፣ ከረሃብ ፣ ከጦርነት፣ ወዘተ.) ለመከላከል ሲባል በሚፈጸመው *በጎዴ* እምነታዊ ስርዓት ላይ ከፍተኛ ተሳትፎ ያደርጋል (ስለ ዝርዝር አፈፃጸሙ ክፍል 5.4.2 ተመልከት)፡፡ አብዛኛው የቡርጂ ህዝብ ኑሮ የተመሰረተው በግብርና ነው፡፡ የሚኖረውም በገጠር አካባቢ ነው፡፡ እንደ ከተሜዎቹ የሞተን የሚያስቀብር፣ የሞተበትን የሚያስተዛዝን እድር ወይም ማህበራዊ ተቋሚ የለውም፡፡ ይሁን እንጂ እድሩን ተክቶ የሚሰራ ማህበራዊ ተቋሚ አለው፡፡ ይህም በሃዩ የሚመራው ህግ ነው፡፡ በአካባቢው ሰው የሞተ እንደሆነ ሰው የሞተባቸው ቤተሰቦች፣ ሰው የሞተባቸው መሆኑን ለሃዩው ይነግሩታል፡፡ እሱም ከህግ አባላት መካከል ለአካባቢው ህዝብና ለሟች ወገኖች መርዶ የሚያደርሱትን ይመድባል፡፡ ህዝቡ ወጥቶ መቃብር ሟቹን እንዲቀብር ያደርጋል፡፡

ሃዩ፣ ለመገረዝ የደረሱ፣ ግን ገና ያልተገረዙ፣ ከሰባት ዓመት እድሜ ጀምሮ ወደ ላይ ያሉ የማህበረሰቡን ልጆች ሰብስቦ አደን ያለማምዳቸዋል፡፡ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ስርዓቶችን ያስጠናቸዋል፡፡ በዚህም ልጆቹ በማህበረሰቡ ልማድና ሥርዓት ተኮትኩተው እንዲያድጉና ወደፊት በማህበረሰቡ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት ውስጥ በብቃት እንዲሳተፉ ከወዲሁ ያዘጋጃቸዋል፡፡ ሃዩ ሌላም ተግባር አለው፡፡ የእርሻ መሬት ለሚፈልጉ የማህበረሰቡ አባላት የእርሻ መሬት እየለካ የሚያከፋፍለው እሱ ነው፡፡ በወሰንተኛ ባለ ይዞታዎች መካከል የድንበር ይገባኛል ክርክር በሚነሳበት ጊዜም ቢሆን ሁለቱን ወገኖች የሚዳኘው ሃዩው ነው፡፡

በአጠቃላይ፣ *ሃዩ የመከላከያ* አዛዥ በመሆን ህዝቡንና አካባቢውን ከጥቃት ይከላከላል። ድንበር አስከባሪ፣ ደህንነት አስጠባቂ ነው ሃዩ። በየደረጃው ባሉ የህዝብ ጎርሶማዎች ውስጥ የመከላከያ ተጠሪ በመሆን ይሳተፋል። ተግባሩን የሚፈጽመው፣ *ሥራውን* የሚሰራው ያለ አንዳች ጣልቃ ገብ አካል፣ በነፃነት ነው። ከላይ ሆኖ በቀጥታ የሚያዘው አካል የለም። ሃዩ ራሱን ችሎ የሚንቀሳቀሰውን የሀግ ተቋም የሚመራ ታላቅ መሪ ነው። ይህንንም ማህበረሰቡ *ሃዩ ጋሊቶን፣ ሂጋሃ አሉቦን* በማለት የሃዩን ታላቅነት፣ ወሳኝ ባለሥልጣን መሆኑን ይገልጻል። ትርጉሙም *ሃዩው ይግባ* (ከጦርነት ወይም ከዘመቻ ማለት ነው)፣ *ሌላው ይለቅ* እንደ ማለት ነው። በአንድ ጦርነት ላይ አንድ ሃዩ ከሚሞት ሌላው ጦር (የመከላከያ ሃይል) ሞቶ ቢያልቅና እሱ ቢተርፍ ይመረጣል እንደ ማለት ነው።

ሃዩ የህዝቡን ደህንነት ብቻ ሣይሆን ንብረቱን የመጠበቅና የማስጠበቅ ኃላፊነት አለበት። በዚህም ዝንጀሮና ጦጣ የመሳሰሉ ፀረ ሰብል የዱር እንስሳት መንጋ በአካባቢው ሲታዩ የሀግ አባላትን አሰባስቦ በእንስሳቱ ላይ ያዘምታል። እንስሳቱ ከአካባቢው እንዲርቁ በማድረግ የህዝቡን ሰብል ከጥፋት ይታደጋል። የተከለሉ የግጦሽ መሬቶችን ያስጠብቃል። መንገዶችን፣ ድልድዮችን፣ የመሳሰሉትንና ለህዝቡ ማህበራዊ አገልግሎት የሚሰጡ ሌሎች በርካታ ነገሮችን ያሰራል፣ ይሰራል።

*ኣርጉማንቾ በሀግንካ ባልባላ* ውስጥ *የሃዩ* ረዳትና መልዕክተኛ ሆኖ የሚሰራ ሰው የሚጠራበት ማዕረግ ነው። የኣርጉማንቾ ዋና ተግባርም ከሃዩ ጋር በመሆን፣ የህዝቡን ደህንነት፣ የሀገርን ዳር ድንበር መጠበቅና ማስጠበቅ ነው። የመከላከያው ሃይል ለአንድ ተግባር ወይም ዘመቻ በተፈለገ ጊዜ፣ በሃዩው ሲታዘዝ አባላቱን ለዘመቻ ይጠራል። *ኣርጉማንቾ ከሃዩው* የታዘዘውን የሚፈጽመው፣ የሀግ አባላትን ለሥራ፣ ለዘመቻ የሚጠራው፣ *ኣያማ* የሚሰኘውንና ከድኩላ ቀንድ የሚሰራውን ጡሩምባ በመንፋት ይሆናል። ኣርጉማንቾ ተጠሪነቱ ለሃዩው ሆኖ የአገልግሎት ዘመኑም ከሃዩው ጋር እኩል የእድሜ ልክ ነው።

#### 4.4.2.3. የሉብ ተግባር

*ሉብ* በቡርጂ የትውልድ አመዳደብ *ሥርዓት* (Generation Grading System) ማለትም *በሀግ* ውስጥ የተካተቱ ወጣት ወንዶች የሚጠሩበት ማዕረግ ነው። *ሉብ* በሁሉም ደረጃ ባሉት *ባልባላዎች* ውስጥ ለባ ህላዊ የህዝብ *መሪዎች* እንደ ስርአት አስ ከባሪ ‹‹ *ፖሊስ*›› ወይም ‹‹ወታደር›› በመሆን *ያገለግላሉ*። *የሉብ* ተግባር በአብዛኛው ጎልቶ የሚታየው በባህላዊ የባሻ

ስርዓት ወቅት ነው፡፡ መሪዎቹ ለባሻ ሥርዓት ወደ ሱቡሮ ሲሄዱ ሲሉ ከመኖሪያ ቤታቸው የሚወጡት፣ ሱቡሮ ሊደርሱ ትንሽ መንገድ ሲቀራቸውም እንዲሁ እስከ ቦታው ድረስ የሚሄዱት በሰው ታዝለው ነው፡፡ ሱቡሮ ላይም ኤሳውን ሶስት ጊዜ የሚዞሩት በሰው ትከሻ ላይ ሆነው ነው፡፡ ይህን ሁሉ ተግባር የሚያከናውኑት፣ የህዝብ መሪዎችን የሚሸከሙት ወይም የሚያዝሉት ሉብ ሆነው የተመደቡላቸው ወጣት ወንዶች ናቸው፡፡ ሉባዎች ከሱቡሮ መልስ በእያንዳንዱ ሹም መኖሪያ ቤት በሚኖረው የግብዣ ሥነ ሥርዓት ላይ ለሚታደሙ እንግዶች ምግብና መጠጥ በማቅረብ ያስተናግዳሉ፡፡ እስከ ሥነ ሥርዓቱ ፍጻሜ ድረስ በየአለቆቻቸው ግቢ፣ ቤት… ወዘተ ውስጥ ሥርዓት የሚያስከብሩት፣ የሰው፣ የእንስሳትና የንብረት ደህንነት የሚጠብቁት፣ ከዚያ ያለውን ስራ የሚሰሩት፣ የሚቆጣጠሩት ሉብ የሚባሉ «ፖሊሶች» ናቸው፡፡

ሉባዎች የባህላዊ መሪዎችን መልዕክት ወደተለያዩ አካባቢዎች (በተለይም እጅግ አስቸኳይ መልዕክቶችን፣ ብርቱ ትዕዛዞችን) ያደርሳሉ፡፡ ከፍ ብለን እንደጠቀስነው ወማው አንድን ሰው ያለውድድር ጋሪንታ ዳይና አድርጎ ሲሰይም ወደ ግለሰቡ የሚላከው፣ ወደቤቱ ሄዶ በተመራጩ ግለሰብ ላይ ሣር የሚነሰንሰው ለወማው ሉብ ሆኖ የተመደበ ወጣት ነው፡፡ በአለቆቻቸው ሲታዘዙም የማህበረሰቡን ደንብ የሚጥሱ፣ የመሪዎቻቸውን ትዕዛዝ የማይፈፀሙ ግለሰቦችን ይዘው ለሸንጎ ያቀርባሉ፡፡ ወይም የአጥፊዎችን ንብረት በመዝረፍ ይቀጣሉ፡፡

### 4.4.2.4 የኦለይንካ ኣና ተግባር

ኦላ፣ በኦለይንካ ኣና የሚመራ ዝቅተኛው የአስተዳደር ተቋም መሆኑን ቀደም ብለን ተናግረናል፡፡ የኦለይንካ ኣና ዋነኛው ተግባር በሚያስተዳድረው ኦላ ውስጥ ሰላም እንዲሰፍን፣ ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡ በዚህም በኦላ ውስጥ የሚከሰቱትን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ችግሮችን ይፈታል፡፡ አለመግባባቶችን ያረግባል፡፡ የኦላ ነዋሪዎች በጋራ የሚያከናውኗቸው ተግባራት (ለምሳሌ አውድማ፣ መንገድ ማዘጋጀት፣ ድልድይ መሥራት…ወዘተ) ሲኖሩ ነዋሪዎችን አስተባብሮ ያሰራል፡፡ ይቆጣጠራል፡፡ ከበላይ ሹማምንት የሚሰጡ ትዕዛዞችን፣ መመሪያዎችን ያስፈፅማል፡፡ ነዋሪዎቹ የሚተዳደሩበት ደንብ (Code of conduct) በነዋሪዎቹ እንዲቀረጽ ያደርጋል፡፡ ደንቦቹ ሲወጡም ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ አፈፃፀማቸውን ይቆጣጠራል፡፡ ደንቦቹን የሚጥሱ ሲኖሩም በደንቡ መሰረት ይቀጣቸዋል፡፡ ቅጣቱም አጥፊውን ከኦላው ህብረተሰብ እስከ ማግለል ሊደርስ ይችላል፡፡ ኦለይንካ ኣናው ይህን ሁሉ ተግባር የሚፈጽመው ግን ከረዳቶቹ (ከኦለይንታ ጪማዬ - ከኦላ ሽማግሌዎች) ጋር በመሆን እንጂ ብቻውን አይደለም፡፡

## 4.5 የስብሰባና የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት

በቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥ *ጎርሶማ* የሚባል ከፍተኛ የሕዝብ ሸንጎ መኖሩ ቀደም ሲል ተጠቅሷል። *ጎርሶማው* የሚመራበት የስብሰባና የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት አለው። ይህ ንኡስ ክፍልም የዚህን፣ በተለይም *የጉልጉቤይንካ ጎርሶማውን* የስብሰባና የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓቶችን ጠቅለል አድርጎ ለማሣየት የሚሞክር ነው።

### 4.5.1. የስብሰባ ሥርዓት

ስብሰባ ሲጠራ የመሰብሰቢያ ሥፍራና ጊዜ፣ እንዲሁም ተሰብሳቢዎች አብረው ይነሳሉ። የመሰብሰቢያው ሥፍራም ዘመናዊ አዳራሽ፣ ደሳሳ ጎጆ፣ ዋሻ ወይም ሌላ ሊሆን ይችላል። ሥፍራው ምንም ሆነ ምን ሊኖር ግን ግድ ይላል። የቡርጂ ጎርሶማዎችም ለዚህ ተግባር የሚገለገሉባቸው የታወቁ የመሰብሰቢያ ሥፍራዎች አሏቸው። ይህም ሥፍራ፣ ከፍ ብለን እንደጠቀስነው *ባልባላ* ይባላል። የቡርጂ *ባልባላ*፣ ቤት ወይም ዋሻ አይደለም። እነርሱ *ሓራዳ* የሚሉት ለምለም ሣር ያለበት፣ ገላጣ ሜዳ እንጂ። በመሆኑም ስለ ስብሰባው ሥርዓት ከመናገራችን በፊት *የጉልጉቤይንካ ጎርሶማ* እስከዛሬ ድረስ የት? የት? እንደተሰበሰበ፣ እነዚያ ቦታዎች ለምን? እንደተመረጡ...ወዘተ ማስተዋወቁ ተገቢ ስለመሰለኝ ቅድሚያውን ሰጠሁት።

የቡርጂ *ጎርሶማ* እስከ ዛሬ ድረስ ሶስት የመሰብሰቢያ ሥፍራዎችን ለመሰብሰቢያነት ተጠቅሟል። ለመጀመሪያ ጊዜ መቀመጥ የጀመረው፣ ወይም ይቀመጥ የነበረው በቡርጂ ቦሄ፣ በኣባያ ገሪኤ ውስጥ በሚገኘውና *ካራሬ* በሚባለው ሥፍራ ላይ ነበር። ቀጥሎ በጋሻራ የቢያ አስተዳደር፣ በ*ዳሊያ* ቦሄ ውስጥ፣ ሱቡሮ ላይ መቀመጥ ጀመረ። እንደገና ለሶስተኛ ጊዜ ከዳሊያ ተነስቶ፣ በተለምዶ ሻቻ ከሚባለውና *በኦቶማል የቢያ* አስተዳደር ውስጥ የሚገኘውን ሥፍራ ዋና መቀመጫው አደረገ። ዛሬም ድረስ የሚቀመጠው ሻቻ ላይ ነው። በአጭሩ ጎርሶማው እስከዛሬ ሶስት የተለያዩ ቦታዎችን ወይም አካባቢዎችን ለመሰብሰቢያነት ተጠቅሟል። ቀያይሯል። እንዲህ ቦታ ለመቀያየራቸው እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው የቀለብ አቅርቦት ችግር እንደሆነ፣ በብሔረሰቡ አፈ ታሪክ ውስጥ እንዲህ ይተረካል።

> በቡርጂ ልማድ ወደ ጎርሶማ ሲኬድ ስንቅ (ቀለብ) አይያዝም። ለተሰብሳቢዎች አስፈላጊውን የሚያደርገው፣ እህል ውኃ የሚያቀርበው ጎርሶማው የተቀመጠበት አካባቢ ሕዝብ ነው። ስለሆነም ሁሉም ባዶ እጁን ይሄዳል። በአካባቢው ሕዝብ ተስተናግዶ ይመለሳል። ጎርሶማው መጀመሪያ ቡርጂ (ካራሬ) ይቀመጥ ነበር። ከዚያ ለምን ተነሣ? ተሰብሳቢውን ረሃብ ፈጀው። ቡርጂዎች የሚበላ ብዙም አልነበራቸውም። ቢኖራቸውም ለተሰብሳቢው በቂ ምግብ አያቀርቡም። ይህም ጎርሶማው ወደ ዳሊያ (ሱቡሮ) እንዲዛወር ምክንያት ሆነ። ዳሊያ ያን ጊዜ ስንዴ በብዛት የሚመረትበት ቦሄ ነበር።

> ይሁን እንጂ ዳሊያም ቢሆን እንደታሰበው አልሆነም። በርግጥ መጀመሪያ አካባቢ ምግብ በገፍ ይቀርብላቸው ነበር። እየቆዬ ግን የምግቡ መጠን እየቀነሰ መጣ። በፊት ዳሊያዎች ለአንድ ቀን የጎርሶማ ቆይታ አንድ የስንዴ ክምር ወቅጠው፣ ፈጭተውና አብስለው ያቀርቡ የነበሩት፣ የኋላ ኋላ ሁለትና አምስት ነዶ ብቻ እስከማቅረብ ደረሱ። ይህም አልዳረስ ቢላቸው ስንዴውን ከአፈር ጋር ቀላቅለው እየፈጩና እያበሰሉ ያቀርቡ ጀመር። በዚህም ጉባኤተኛው ተማረረ። ረሀቡም ፀናባቸው። ይህን የተመለከተ አንድ የኦቶማል አስተዳደር ተወካይ ተነስቶ *‹‹ሳንሲ የታም ሳ ያድነይ››* (ለም አፈር እያለ ለረሀብ አንሰጋም) በማለት ጎርሶማው መቀመጫውን ወደ ኦቶማሎ እንዲያዛውር ሀሳብ አቀረበ። ሀሳቡም በአባላቱ ስለተደገፈ የጎርሶማው መቀመጫ ከዳሊያ ወደ ኦቶማል፣ በተለምዶ ሻቻ ከሚባል ሥፍራ ሲዛወር ቻለ።
>
> ያ ዘመን ኦቶማሎዎች በእንሰት ተክል የሚታወቁበት ዘመን ነበር። እንሰቱን ቆፍረውና ከታትፈው ከእሳት ላይ ይጥዱታል። ሲበስል በኮባ ቅጠል አድርገው ለጉባኤተኛው በገፍ ያቀርቡለታል። ይህን ካደረጉ በኋላ እንደገና በቀረበው እንሰት ላይ የበሶ ዱቄት ያርከፈክፉበታል። ሁሉም እስኪጠግብ በልቶ ይተርፋል። በዚህም የነበረው የምግብ ችግር ተወገደ። እስከዛሬም ጎርሶማውን ችግር አላገኘውም። የጎርሶማው መቀመጫም እስከዛሬ ድረስ ከኦቶማል፣ ከሻቻ ላይ አልተነሳም (ማኒኦ፣ 2002፣ 78-82)።

*የጉልጉባ ጎርሶማ* ስብሰባ የሚጠራው በወማው ነው። ጉባኤው የሚመራው *ቆማች* (አፈ ጉባኤ) በሚል ማዕረግ በሚጠራ ሹም ሲሆን፣ የመወያያ ርዕሶች (አጀንዳዎች) ደግሞ በወማው ተቀርፀው፣ በወማው አማካይነት ለጉባኤተኛው ይቀርባሉ። የቆማች ተግባርም ውይይቱን መምራት ነው። በጉባኤው ማጠናቀቂያ ላይ ጉባኤው የተወያየባቸውን አጠቃላይ ፍሬ ሀሳቦችን ጨምቆ ያቀርባል። በጉባኤው የተላለፉ ውሳኔዎችንም ለጉባኤተኛው ያሣውቃል።

የጎርሶማው አባላት ስብሰባ ሲቀመጡ ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ አዙረው ነው። ይህን የሚያደርጉትም ምሥራቅ *ከሊበን* ወደ ቡርጂ የመጡበት አቅጣጫ (መንገድ) በመሆኑ፣ ወይም የቡርጂ ዋና *ባልባላ* በመሆኑ ነው። አቀማመጣቸውም እንደማዕረጋቸው ነው። ወማ ከሁሉም ፊት ይቀመጣል። ከእሱ ቀጥሎ ከግራውና ከቀኙ ወደ ኋላው ትንሽ ገባ ብለው ረዳቶቹ ይቀመጣሉ። ከወማው ረዳቶች ቀጥሎ *ጋሪንታ ዳይና*፣ ከጋሪንታ ዳይናው ግራና ቀኝ ረዳቶቹ ይቀመጣሉ። ከእነዚህ ቀጥለው የሚቀመጡት ደግሞ ማሻዎችና (ፊዜዎችና) ረዳቶቻቸው ይሆናሉ። ቀጥለው ኣንሾችና ጎርሶች ይቀመጣሉ። እንዲህ እንዲህ እያለ ይሄዳል። በአጭሩ ኤላዎች ከፊት፣ ሌሎቹ ከኋላቸው ሆነው ይቀመጣሉ። በቡርጂ ባህላዊ ደንብ መሰረት ኤላ ያልሆነ ሰው ከኤላ ፊት አልፎ እንዲቀመጥ አይፈቀድም። ምክንያቱ ደግሞ ኤላዎች ሊሶና ካላች ስላላቸው፣ ከሊሶውና ከካላቹ ፊት አልፎ መቀመጥም ሆነ መቆም (በተለይ በባህላዊ የምርቃት *ሥነ ሥርዓት* ወቅት) ለከፋ አደጋ ይዳርጋል ተብሎ ስለሚታመን ነው።

*ጎርሶማው* ወደ ውይይቱ የሚገባው ምልዓተ ጉባኤው ሲሟላ ነው። በቡርጂ ባህላዊ ደንብ መሰረት የጎርሶማው ምልዓተ ጉባኤ ተሟልቷል የሚባለው ሁሉም *ኣንሾች* ተሟልተው ሲገኙ ነው። አንድ ኣንሽ በዕለቱ ያልተገኘ እንደሆነ ጎርሶማው ሌላ ተለዋጭ ቀጠሮ ይዞ ይበተናል እንጂ፣ በምንም ሁኔታ ወደ ውይይት አይገባም። ወይም ጉባኤው አይካሄድም። ኣንሾች

ተሟልተው፣ ከተቀሩት አባላት መካከል አንዱ ቢጎድል እንኳን፣ ጉባኤው አይበተንም። ምልዓተ ጉባኤው ተሟልቷል ተብሎ ውይይቱ እንዲቀጥል ይደረጋል።

ውይይቱ የሚጀምረው በባህላዊ የምርቃት ሥርዓት (ሐሳዪ) ይሆናል። በሌሎች አጋጣሚዎችና ባህላዊ ሥርዓቶች ላይ ለወትሮው ሓሳዬ የሚለው ከአባላቱ መካከል ከፍተኛ ሥልጣን ያለው ባህላዊ መሪ (ወማ፣ ዳይና፣ ማሻ...ወዘተ) ነው። በዚህ፣ በጉል ጉባ ጎርሶማው ላይ ግን ሓሳዬ የሚለው፣ ጉባኤውን በባህላዊ ምርቃት የሚከፍተው ጎርሶማው የተቀመጠበት አስተዳደር መሪ ይሆናል። በሌላ አገላለጽ፣ በአሁኑ ወቅት የጉልጉባው ጎርሶማ ጉባኤ የሚቀመጠው ሻቻ በሚባለው በኦቶማል የቢያ አስተዳደር ውስጥ ነው። በመሆኑም ሀሳዬ በማለት ጉባኤውን የሚከፍተው የኦቶማል ቢያ አስተዳዳሪ የሆነው ማሻ (ፊዜ) ይሆናል ማለት ነው። ከዚያ በኋላ የዕለቱ የመወያያ ርዕስ በወማው አማካይነት ለጎርሶማው አባላት ይገለፃል። ጎርሶማውም በቀረበው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ይሰጥበታል። በመጨረሻም የዕለቱ ውሳኔና የውይይቱ ፍሬ ነገር በቆማች አማካይነት ተጠቃሎ ከቀረበ በኋላ በባህላዊ የምርቃት ሥርዓት ጉባኤው ይጠናቀቃል።

### 4.5.2. የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት

በቡርጂ የአስተዳደር ሥርዓት ውስጥ አንድ ሰው ወይም አንድ ሹም ብቻውን የሚሰጠው ወይም የሚያስተላልፈው ውሳኔ አለመኖሩን ከፍ ብለን ገልጸናል። ሁሉም ውሳኔዎች የሚሰጡት በጋራ፣ በጎርሶማው ጠቅላላ ጉባኤ አማካይነት ነው።

አብዛኞቹ የጎርሶማ የመወያያ ርዕሶች፣ የመሰብሰባቸው ምክንያት በህዝቡ ወይም በአካባቢው ላይ የሚከሰቱ ችግሮች ወይም ክፉ አጋጣሚዎች ናቸው። ከፍ ባሉት ክፍሎች እንደተመለከተው፣ በአካባቢው የሚቀሰቀስ ጦርነት፣ ወረርሽኝ፣ ረሀብ፣ ወዘተ. አለ ተብሎ ሲታመን ጎርሶማው እንዲሰበሰብ፣ ተሰብስቦ የተባለው እንዳይደርስ ማድረግ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ እንዲመክር፣ መክሮ እንዲወስን ይጠራል። ወይም ግጭቶች ሲኖሩ ግጭቶቹን ለመፍታት ወይም መፍታት በሚቻልበት ስልት ላይ ለመወያየት ሲባል ጎርሶማው ይቀመጣል።

በቡርጂ ባህላዊ የስብሰባ ሥርዓት መሰረት፣ ውሳኔዎች የሚሰጡት ወይም የሚተላለፉት ካለ አንዳች ተቃውሞና ድምፀ ተሐቅቦ፣ በሙሉ ድምፅ ነው። ከጉባኤተኛው መካከል (ቁጥራቸው የቱንም ያህል ቢሆን) አንድ አባል ሀሳቡን (ውሳኔውን) ቢቃወም ያ ጉዳይ አይፀድቅም። የቀረበው ሀሳብ ፀድቆ ተግባራዊ እንዲሆን ከተፈለገ ሁሉም የጎርሶማው አባላት ያለ ልዩነት

በተነሳው ጉዳይ ላይ መስማማት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም በጉባኤው የሚተላለፉ ውሳኔዎች ካለአንዳች ሣንካ በሁሉም አካባቢዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ አስችሏቸዋል ብዬ አስባለሁ፡፡ በአጭሩ በቡርጂ ባህላዊ የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት ውስጥ አብላጫ ድምፅ ብሎ ነገር የለም፡፡ አይሰራምም፡፡ ጥንትም ሆነ ዛሬ የሚሰራው እንደዚሁ ነው፡፡

## 5. የቡርጂ ባህላዊ ሃይማኖት

በዛሬ ላይ ሆነን ስንናገር፣ አብዛኞቹ ቡርጂዎች የዘመናዊ ሃይማኖት ተከታይ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ዘመናዊ ሃይማኖቶች ወደ አካባቢው ከመግባታቸው በፊት ግን ቡርጂዎች የሚከተሉት *ጋን* የሚባል ባህላዊ እምነት (ሃይማኖት) ነበራቸው፡፡ *ጋን* ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ተከታይ ያላጣ፣ ለዘመናዊ ሃይማኖቶች ወይም እምነቶች ሙሉ በሙሉ ያልተንበረከከ የቡርጂ ባህላዊ ሃይማኖት ነው፡፡ ህዝቡ ለሚከተላቸው ለሌሎች *ሒጣና*፣ *ጎዬ*፣ *ኡስ*፣ *ራጅና* ለመሳሰሉት እምነቶች መነሻና ምንጫቸው *ጋን* ነው፡፡ ይህ ምዕራፍ ይህን የሚመለከቱ አምስት ዋና ዋና ነጥቦችን ያነሣል፡፡

በመጀመሪያ የቡርጂ ህዝቦች *በጋን* መቼ? እንዴት? እና ለምን? ማመን እንደጀመሩ የሚያወሳ ታሪክ ይቀርባል፡፡ በመቀጠል የባህላዊ እምነት መዋቅሩ ምን እንደሚመስል በገለፃና በምስል ለማስረዳት ይሞክራል፡፡ በዚህ የእምነት ተቋም ውስጥ የሚሠሩ አባላት እንዴት እንደሚመደቡ? ምን እንደሚሠሩ? እና እንዴት እንደሚሠሩ? ይህ ምዕራፍ ከሚያነሳቸው ነጥቦች መካከል ናቸው፡፡ ከባህላዊ አስተዳደር ጋር ተያይዘው የሚፈፀሙ ባህላዊ እምነቶችና የአፈፃፀም ሥርዓታቸውም እንዲሁ የዚህ ምዕራፍ ትኩረቶች ይሆናሉ፡፡ በመጨረሻም ባህላዊ የፖለቲካና የእምነት መሪዎች ገደቦች የቁጥጥር ሥርዓቶች ይቀርባሉ፡፡

### 5.1. የጋን እምነት ታሪክ

*ጋን* የቡርጂ ህዝቦች "ከፈጣሪ የተቸረን፣ ከአያት ከቅድመ አያቶቻችን የተሰጠን ፀጋ ነው" ብለው የሚያምኑትን ልዕለ ተፈጥሯዊ ኃይል (Super Natural Power) የሚጠሩበት ስም ነው፡፡ ይህ፣ ልዕለ ተፈጥሯዊ ሀይል (ጋን) ያደረባቸው፣ የሚገለጥባቸው ሰዎች ደግሞ *ወነይ*፣ *ወማ* ወይም *ቃሉ* ይባላሉ[53] (ስለ *ወማ* ዓይነትና ልዩነት የምዕራፍ አራትን መግቢያ ተመልከት)፡፡ ልዕለ ተፈጥሯዊ ሀይሉ (ጋን) ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው እንዲተላለፍ የሚደረግበት ባህላዊ የንግሥና ስርዓት ደግሞ *ጋኖማ* ተብሎ ይጠራል፡፡ *ወነይ* በዚህ፣ በንግሥና ሥርዓት ወቅት ለአዲሱ ነጋሲ ባለጋን የሚሰጥ የንግስና ስም ነው፡፡ ትርጉሙም ቀዳማዊ እንደማለት ነው፡፡

---

[53] እኔ ግን በነጠላው ባለጋን፣ ሲበዛ ደግሞ ባለጋኖች ብያቼዋለሁ፡፡ ለዚህ መነሻ የሆነኝ አንድም፣ ሁሉም በጋራ የሚጠሩበት አንድ የጥቅል ስም የሌላቸው መሆኑ ነው፡፡ አንዳንዶቹ ለምሳሌ *ሢጋናንካ* ጋን እና *ባንባልንካ ጋን* (የሁሉም ታላቅ ነው የሚባለው) ወማ ተብለው ሲጠሩ፣ ሌሎቹ ባንባልንካ ጋኖች ደግሞ *ቃሉ* በሚል የጥቅል ስም ይጠራሉ፡፡ የተቀሩት ደግሞ *ወነይ* በሚል ማዕረግ ሲጠሩ ይሰማል፡፡ ስለሆነም ሁሉንም *ባለጋን* ወይም *ባለጋኖች* በሚል በአማርኛው ስልት ለመጥራት ተገደድኩ፡፡ አንድም፣ አማርኛው መንፈሳዊ ኃይሉን ‹‹ውቃቢ›› ብሎ፣ ይህ መንፈሳዊ ኃይል ያደረበትን ሰው ደግሞ ‹‹ባለውቃቢ›› ብሎ ስለሚጠራ፣ እኔም ‹‹ጋን›› ብዬ ‹‹ባለጋን›› ስል ምን ማለቴ እንደሆነ አንባቢዬ ለመረዳት አይቸገርም በሚል ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ‹‹ጋን›› ረቂቅ መንፈሳዊ ኃይል ሲሆን፣ ‹‹ባለጋን›› ደግሞ ይህ ኃይል ያደረበት ሰው ማለት እንደሆነ ልብ ይሏል፡፡

ጋን ረቂቅ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ሀይል እንጂ ግዑዝ ፍጡር ወይም ሰው አይደለም። ሰው ስላልሆነም አይታይም፤ አይዳሰስም። ሁሉን የሚያደርገው፣ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ሀይልነቱን የሚገልጠው በሰው አድሮ ነው። ይህ ረቂቅ ሀይል ያደረባቸው ባለጋኖች ግን የሚታዩ፣ የሚዳሰሱ፣ የሚናገሩ፣ የሚንቀሳቀሱ፣ ወዘተ. ሰዎች ናቸው። ሰው ሆነው ግን፣ ከሌላ ሰው የተለየ መንፈሣዊ ሀይልና ችሎታ አላቸው ተብሎ ይታመናል። ልዕለ ተፈጥሮአዊ ሀይልና ችሎታ ሰላላቸውም ህዝቡን ችግር ያገኘው እንደሆነ ፈጥነው ይደርሱለታል። ደርሰው ከህዝቡ ችግር ጋር ፊት ለፊት ይጋፈጣሉ። ተጋፍጠው የህዝቡን ችግር ይፈታሉ። የህዝቡን ጥያቄ ይመልሣሉ። ህዝቡን ከችግር ይታደጋሉ። በዚህም በህዝቡ ዘንድ እንደ ቅዱስ ይቆጠራሉ፤ ይፈራሉ፤ ይከበራሉ። መንፈሣዊ መሪ ሆነው መንፈሣዊ አገልግሎት ይሰጣሉ። እምነታዊ ተግባራትን ብቻ ያከናውናሉ። ፖለቲካዊ በሆኑ ጉዳዮች ውስጥ አይገቡም። ሥልጣኑም ከአባት ወደ ልጅ፣ በዘር ሐረግ የሚተላለፍ ነው ( ክፍል 5.3.1. ተመልከት)።

ጋን ብዙ ነው። በቁጥር አስራ ሁለት ናቸው። ሁሉም የሚጠሩት በጎሣ ስማቸው ነው። "የዚህ ጎሣ ጋን፣ የዚያ ጎሣ ጋን" እየተባሉ ይጠራሉ። ባለጋኖቹም የነዚሁ ጎሣ አባላት ናቸው። ይሁን እንጂ፣ መንፈሣዊ አገልግሎታቸው በጎሣ የተከለለ፣ ለዚያ ጎሣ ብቻ የተሰጠ አይደለም። ለሁሉም፣ ለሚያምናቸውም፣ ለማያምናቸውም፣ ጋን ሌለላቸው ሌሎች ጎሣዎች[54]፣ በአጭሩ ለቡርጂ ህዝቦች እንጂ። በቡርጂ ህዝቦች ዘንድ የሚታወቁት አስራ ሁለቱ ጋኖችም የሚከተሉት ናቸው።

- *ጊነይንካ ጋን (የጊነ ጎሣ ጋን)*
- *ባንባልንካ ጋን (የባንባላ ጎሣ ጋን)፣ በሌላ ስሙ ዋዋያንካ ጋን በመባል ይታወቃል*
- *ሣጋናንካ ጋን (የሣጋና ጎሣ ጋን)*
- *ቃዳዲንካ ጋን (የቃዳዶ ጎሣ ጋን)*
- *ማንጋዳንካ ጋን (የማንጋዳ ጎሣ ጋን)*
- *ኣናቡራንካ ጋን (የአናቡራ ጎሣ ጋን)*
- *ኮቦሌይሽንካ ጋን (የኮቦሌይሽ ጎሣ ጋን)*
- *ያቢንካ ጋን (የያቢ ጎሣ ጋን)*
- *ጋቤይንካ ጋን (የጋቤይ ጎሣ ጋን)*
- *ጣሜይንካ ጋን (የጣሜይ ጎሣ ጋን)፣ በሌላ ስሙ ዳረይሽንካ ጋን (የአንበጣ ጋን) በመባል ይታወቃል*
- *ሎማሌይንካ ጋን (የሎማሌይ ጎሣ ጋን)*
- *ቢሬይሌንካ ጋን (የቢሬይሌ ጎሣ ጋን)*

---

[54] ቡርጂ ውስጥ በጠቅላላው ከዘጠና በላይ ጎሣዎች አሉ (አበበ፣ 2002)። ከእነዚህ መካከል ጋን ያላቸው በቁጥር 12 ጎሣዎች ብቻ ናቸው። በመሆኑም ጋን የሌላቸው በርካታ ጎሣዎች ቡርጂ ውስጥ መኖራቸውን ልብ ይሏል።

በቁጥር አስራ ሁለት ይሁኑ እንጂ፣ በአሁኑ ጊዜ ያሉት (አገልግሎት የሚሰጡት) ጋኖች ግን አስራ አንድ ብቻ ናቸው፡፡ ከመጀመሪያው ላይ የተጠቀሰው፣ *ጊኒይንካ ጋን* በአሁኑ ጊዜ አገልግሎት አይሰጥም፡፡ ጨርሶ ቡርጂ ውስጥ የለም፡፡ እምነቱ ብቻ ሣይሆን ራሱ ጎሣውም የለም፡፡ ሁለቱም ጠፍተዋል፡፡ ይህ *ጎሣ በዘመኑ* ከሁሉም የበለጠ ረቂቅ ሀይል የነበረው፣ ከሁሉም የበለጠ የሚፈራና የሚከበር *ጋን* ነበረው (ለዝርዝሩ ክፍል 4.1.1 ተመልከት)፡፡ እንዲሁም እንደ *መረጃ* ሰጪ አባባል (ቱኬ፣ 2002) ይህ *ጎሣ* በባህርው ኃይለኛና ጦረኛ ስለነበረ ከዚህም ከዚያም እርስበርሱም እየተዋ*ጋ* ተሳለቀ፡፡ የተቀሩት በሙሉ ዛሬም ድረስ አሉ፡፡ ለህዝቡም *መ*ደበኛ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

የእያንዳንዱ *ጎሣ ጋን* እንዴት *መ*ቼ እንደ ጀመረ፣ ወዘተ. የሚያስረዳ የየራሱ *ታ*ሪክ (አፈ*ታ*ሪክ) አለው፡፡ የሁሉንም ከዚህ ማቅረብ አይቻልም፡፡ ስለሆነም ከዚህ፣ ‹‹ከሌላው ይበልጥ ይፈራል፣ ይከበራል›› ስለሚባለው ስለ *ባንባልንካ ጋን አጀማመር* የሚተርክ አፈ*ታ*ሪክ ብቻ ይቀርባል፡፡

*ባንባልንካ ጋን* ቡርጂ ውስጥ ካሉት ሁሉ ‹‹ብልጫ›› *ያ*ለው *ጋን* ነው ተብሎ ይ*ታ*መናል፡፡ ከሌሎች የበለጠ የሚፈራው፣ የሚከበረው እሱ ነው፡፡ ቡርጂን በሙሉ የሚመለከቱ እምነታዊና ባህላዊ *ሥ*ርዓቶች ሲኖሩ፣ ከሁሉ ፊት የሚሆነው፣ ቀድሞ የሚመርቀው፣ ቡራኬ የሚሰጠው የባንባላ *ጎሣ ባለጋን (ወማ)* ነው፡፡ የቡርጂ ህዝቦች ከአጎራባች ህዝቦች *ጋ*ር ጉባኤ በሚቀመጡበት ወቅት፣ የቡርጂን ባህላዊ የእምነት ተቋምን ወይም ባለ*ጋ*ኖችን ወክሎ ጉባኤውን የሚመርቀው *ባንባልንካ ጋን (ወማ)* እንጂ ሌላ ማንም አይደል፡፡

*ባንባልንካ ጋን* በአንድ *ወማ* እና በአራት *ቃሎዎች* የሚመራ የእምነት ተቋም ነው፡፡ እንደ አብዛኞቹ የቡርጂ *ጎሣ*ዎች፣ የባንባላ *ጎሣ*ም ሆነ እምነቱ፣ ከሲበን መጥተው ቡርጂ የሠፈሩ አይደሉም፡፡ ከዚሁ ከቡርጂ ምድር፣ *ቆሌ* ከሚባል አካባቢ የተገኙ ወይም የተፈጠሩ እንደሆኑ ይነገራል፡፡ ይህ ስለመሆኑም፣ በቡርጂ አፈ*ታ*ሪክ እንዲህ ይተረካል፡፡

> በድሮ ጊዜ ከወቴይቫ ጎሣ የሆነች አንዲት ልጃገረድ ነበረች፡፡ ከብቶች ልትጠብቅ ይዛቸው ከዱር ሄደች፡፡ ልጃገረዲቱም አንድም ወንድ ሣታውቅ፣ ከወንድ ጋር ግንኙነት ሣታደርግ አረገዘች፡፡ አርግዛ፣ ከዚያው ከዱር ወንድ ልጅ ተገላገለች፡፡ ልጇን ከወንዝ ጨምራው ከመንደር ተመለሰች፡፡ እንዲሁም በከብቶች መካከል ልትወልድ የደረሰች አንዲት ጥቁር ላም ነበረች፡፡ ላሚቷ ከዚያው ከዱር ጥጃ ወለደች፡፡[55] እሷም ጥጃዋን ከዱር ጥላ ከመንደር ተመለሰች፡፡
> ይህ ከሆነ ሣምንት፣ ሁለት ሣምንት አለፈ፡፡ የላሚቱዋ ግት ግን አይቀንስም፡፡ ወር ሁለት ወራትም አለፉ፡፡ ግቷ አሁንም ካለመቀነሱም በላይ፣ ጧት ላይ ጥጃ እንደሚታጠባ ሁሉ ‹‹ሂ! ሂ! ሂ!›› እያለች

[55] አንድ ጓደኛዬ (ግሮ፣ ህዳር 12 ቀን፣ 2003 ዓ ም፣ ግላዊ ግንኙነት፣ ሶየማ) ‹‹ሰው ወለደች›› ብሎ ተርኮልኛል፡፡ ይህን የእሱን ተረክ ይዘን ‹‹ባለጋን ሲሞት፣ ወደ ላም ሆድ ተመለሰ እንጂ፣ ሞተ አይባልም›› ከሚለው አባባልና ሲቀበር ደግሞ ከጊደር ጋር መቀበሩን ስናስብ ‹‹ላም ሰው ወለደች›› የሚለው ተረክ ሚዛን የሚደፋ ይመስላል፡፡ ብቻ የቡርጂ የጋን እምነት ብዙ ትዕምርቶች ያሉበት፣ ለብቻው ሰፊ ጥናት የሚሻ ስለመሆኑ እነዚህ በቂ መረጃዎች ናቸው፡፡

ትጣራለች፡፡ ሲፈቷት ደግሞ ወደ ዱር ትገሰግሣለች፡፡ ከዚያው ውሳ ማምሻውን ወደ መንደር ትመለሣለች፡፡ እንዲህ መሆኑን የተመለከቱት የህዝብ መሪዎችና አዛውንቶች በክስተቱ ግራ ተጋቡ፡፡ ‹‹እንዲህ ያለ ነገር እንዴት ያለ ነገር ነው?›› ብለው ተጠያየቁ፡፡ በመጨረሻም ከተንባዮች ዘንድ ሄዱ፡፡ ‹‹የዚህች ላም ነገር ግራ አጋባን፡፡ ጧት ስንፈታት ወደ ዱር ትሮጣለች፡፡ ግን ወዴትና ለምን? እንደምትሄድ አናውቅም፡፡ ወልዳ ጥጃዋን ከገደለች ብዙ ቆየች፡፡ ግን ግቷ እስከ ዛሬ አልቀነሰም፡፡ ይህ ምን የሚሉት ነገር ነው? ምንስ እናድርግ?›› በማለት ምክር ጠየቁት፡፡ ተንባዩም እንዲህ አድርጉ አላቸው፡፡ ‹‹እስቲ ሣትታዩ ተከታተሉዋት፡፡ ተደብቃችሁ የምትሄድበትንና የምታደርገውን ተመልከቱ፡፡›› በማለት ምክር ለገሣቸው፡፡ እንደተመከሩት አደረጉ፡፡ ላሚቷን ተከትለዋት ወደ ዱር ሄዱ፡፡ ላሚቷ ከዱር ካለው ከአንድ ወንዝ አጠገብ ስትደርስ ቆመች፡፡ ቆማም እንደ ልማዷ ‹‹ሂ! ሂ! ሂ!.›› ብላ ተጣራች፡፡ ይህን ጊዜ፣ አንድ ሰው የሚመስል ነገር ከወንዙ ውስጥ ወጣ፡፡ ወጥቶ ወደ ላሚቷ መጣ፡፡ በሁለት እጆቹም የላሚቱዋን የኋላ እግሮች ይዞ ሲጠባት ተመለከቱ፡፡ ጠብቶ ሲያበቃ፣ ተመልሶ ከወንዙ ግብት አለ፡፡ ላሚቱዋም ተረጋግታ ሣር መጋጥ ጀመረች፡፡ ሰዎቹ ከመንደር ተመልሰው ያዩትን ሁሉ ለአዛውንቱ አጫወቷቸው፡፡ እነርሱም በፈንታቸው ለተንባዩ ሰው ነገሩት፡፡ ‹‹እሱ ምን የሚሉት ጉድ ነው? ምንድነው የምናደርገው?›› በማለት ሌላ ምክር ጠየቁት፡፡ እሱም ‹‹አንዳች ነገር አታድርጉት፡፡ ለአሁን ዝም ብላችሁ ተውት፡፡ ሁሉም በጊዘው ይሆናል›› አላቸው፡፡ ህዝቡም ዝም ብሎ የሚሆነውን መጠባበቅ ጀመረ፡፡

ከዕለታት በአንዱ ቀን በአከባቢው ከባድ መናወጥ ሆነ፡፡ ሰማይ ምድሩ ተንቀጠቀጠ፡፡ ህዝቡ ተደናገጠ፡፡ የነገሩን ምንነት ለማጣራት ብለው ድርጊቱ ይበልጥ ወደ ተሰማበት፣ ወደ ዱር ሄዱ፡፡ ከውሃው አጠገብ እንደደረሱም፣ ያኔ ላሚቷን ሲጠባ የተመለከቱት ፍጡር ከውሃው ወጥቶ ከመሬት ላይ ተቀምጦ ተመለከቱት፡፡ ግን አይናገርም፤ አይጋገርም፡፡ ልጁን ፊት ለፊት የሚመለከቱ፣ ዓይን ለዓይን የሚጋጩ ሰዎች ካሉበት ሙትት፣ ድርቅ ይሉ ጀመር፡፡ ከእሱ ጋር አይን ለአይን ያልተያዩት ሰዎች ግን አንዳች ነገር አያገኛቸውም፡፡ ሰዎች ይበልጥ ተደናገጡ፡፡ ፈሩ፡፡ ግን ፈርተው አልሸሹም፡፡ ካሉበት ተሸሽገው መጨረሻውን ለማየት ይጠባበቁ ጀመር፡፡ ልጁ፣ ከዚያ ትንሽ ተቀምጦ ከቆየ በኋላ ተነሣ፡፡ ተነስቶ መሄድ ጀመረ፡፡ ሄዶ ሄዶ ጋምቦ አካባቢ ኮቼ ከሚባለው *ሥፍራ* ላይ ሲደርስ እንደገና ተቀመጠ፡፡ እንደተቀመጠ ወደ ቀኙ ዞሮ ተመለከተ፡፡ ይህን ጊዜ አይኖቹ ያረፉባቸው ሰዎች ካሉበት ድርቅ ብለው ቀሩ፡፡ እሱ ባላየበት አቅጣጫ ያሉ ሰዎች አሁንም ምንም አልሆኑም፡፡ ፊቱን መለስ እንዳደረገ *ኢልማ ቆሌ* (የቆሌ ልጅ) ብሎ ፎከረ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲናገር መሰማቱ ነበር፡፡ ‹‹ እንዴ! ለካስ ይህ ነገር ሰው ኖሮአልን?›› አሉና አሁንም ተደብቀው የሚሆነውን መከታተል ቀጠሉ፡፡ እንደገና ከኮቼ ተነስቶ ጉዞ ቀጠለ፡፡ መጥቶ *ሐራቼ* ከሚባል አካባቢ ተቀመጠ፡፡ *ከሐራቼ* ወዲያ ማዶ ገባ፡፡ ስሙም ያያ ይባላል፡፡ ከዚያ በኋላ ያያ መኖሪያውን ከዚያው አደረገ፡፡ እዚያው ከተቀመጠበት ሆኖ መመረቅ፣ መባረክ ጀመረ፡፡ እሱ የባረከው በረከት መሙላት፣ እሱ የመረቀው ምርቃት መሣካት ጀመረ፡፡ እሱ የሚለው፣ ‹‹ይሁን›› ያለው ከመሬት ጠብ አይልም፡፡ ለመሆን ጊዜም አይፈጅም፡፡ ሰዎች ይበልጥ ግራ ተጋቡ፡፡ የዚህን ልጅ ሚስጢር ሊያውቁ አልቻሉም፡፡

በዚህ ዓይነት ያያ ሲኖር ሲኖር ተመልሶ የእውነት ሰው ሆነ፡፡ ከሰውም ባለጋን ሆነ፡፡ ባለጋን ሆኖ መባረክ፤ መመረቁን ቀጠለበት፡፡ እህል ሲባርክ ጎተራው ሙልት ይላል፡፡ ጦርነት ያወገዘ እንደሆነ ጦርነት አይኖርም፡፡ ፀጥ፣ እረጭ ይላል፡፡ ይህን ያየ ህዝብም ‹‹ይህ ሰው እንዴት ያለ ሰው ነው?›› ይል ጀመረ፡፡ በመጨረሻም ያያ *ባለጋን* መሆኑን ህዝቡ አወቀ፡፡ ይህን ሲያውቁም ወስደው አነገሱት፡፡ *ወማ* አደረጉት፡፡ ወማ አድርገው ሾሙት፡፡ ይህ ያያ የተባለው ወማም ከዚያ በኋላ ሰባት ሚስቶችን አገባ፡፡ ከሰባቱ ሚስቶቹም ሰባት ወንድ ልጆች ወለደ፡፡ ስድስቱን *ቃሉ* አደረጋቸው፡፡ ሰባተኛውና የሁሉም ታላቅ የሆነው ደግሞ *ወማ* ሆነ፡፡ ከእነዚህ ከሰባቱ መካከል አንዱ ኮንሶ[56] ገባ፡፡ ሌላኛው ደግሞ ጊዶሌ ተቀመጠ፡፡ የተቀሩት አምስቱ ከቡርጂ ቀሩ፡፡ በዚህም ያያ የመጀመሪያው የባንባላ *ጋን* እና የባንባላ ጎሣ መስራች ሆነ (ጫሜ፣ 2002፣ 48-52)፡፡

ይህ የአንድ ጎሣ *ጋን* ታሪክ ነው፡፡ የተቀሩትም እንዲሁ የየራሣቸው የአጀማመርና የአነሣስ ታሪክ አላቸው፡፡ የሁሉን ከዚህ ማቅረብ አይቻልም፡፡ ይህ በራሱ ለብቻው ጥናት የሚሻ አንድ ርዕሰ ጉዳይ ስለሆነ ለማሣያነት ከፍ ሲል የቀረበው የሚበቃ ይመስለኛል፡፡

[56] ኮንሶ ውስጥ ካሉት ከሶስት ታላላቅ ክልላዊ ቄሳውስት (regional priests) ወይም (poqullaa) መካከል አንዱ Bamalle (በጥንታዊ ድርሳናት ውስጥ ደግሞ Bamalla) ተብሎ እንደሚጠራ Hallpike (1972, 44) ጽፏል፡፡ የዚህ ክልላዊ ቄስ መስረቱም ወይም አመጣጡ ከቡርጂ እንደሆነ፣ ጥንት አያት ቅድማያቶቹ ከቡርጂ መጥተው ኮንሶ እንደተቀመጡ ጸሐፊው ይናገራል፡፡ ስለሆነም በአፈ ታሪኩ የተነገረው እውነት ሊሆን ይችላል ብለን ልንገምት እንችላለን፡፡

## 5.2 የጋን እምነት መዋቅር

የቡርጂ ባህላዊ እምነት፣ ይህ ነው የሚባል መዋቅር የለውም። ስርጭቱም ሆነ ተግባሩ ማህበረሰቡ ሰፍሮ በሚኖርበት አካባቢ ላይ የተመሠረተ ነው። እያንዳንዱ የቡርጂ *የቢያ* አስተዳደር (የ*ሀና* ቢያ ሲቀር) የራሱን ችግር የሚፈታለት ባህላዊ ቄስ ወይም *ባለጋን* አለው። እነዚህ *ባለጋኖች* ወይም የእምነት ተቋማት እያንዳንዳቸው የሚሠሩት፣ የሚንቀሳቀሱት ራሳቸውን ችለው ነው። አንዱ ሌላውን አያዝም። ‹‹ይህ በእሱ ደረጃ የሚፈፀም ወይም የሚፈታ አይደለም›› የሚባል ችግር የለም። እያንዳንዱ *ባለጋን* ያለውን ችሎታና ልዩ ኃይል ተጠቅሞ የተጠየቀውን ይፈጽማል። የፈፀመው ባይዝለት እንኳን ‹‹እሱ አልቻለም›› ተብሎ የሚኬድበት፣ የእሱ የበላይ የሆነ ባለጋን የለም። በአጭሩ በቡርጂ ባህላዊ የእምነት *ሥርዓት* ውስጥ ማዕከላዊነት (Centralism) ብሎ ነገር ቦታ የለውም። አንዱ ሌላውን የሚያዝበት፣ የ*ሥራ መመሪያም* ሆነ ትዕዛዝ ከላይ ወደታች የሚፈስበት *ሥርዓት* የለም። ሁሉም በራሱ ጌታ፣ በራሱ ንጉስ፣ ነው። ሁሉም ላለበት አካባቢ አዛዥ፣ ታላቅ ባህላዊ የእምነት መሪ ነው።

ይህ ማለት ግን የሁሉም የበኩር የሆነ ባለጋን የለም ማለት አይደለም። እያንዳንዱ ባለጋን ባለበት አካባቢ፣ በሚፈፀሙ እምነታዊ *ሥርዓቶች* ላይ ግንባር ቀደም ተሳታፊ ቢሆንም ግን፣ ሁሉም በአንድ ላይ በሚገናኙበት ወቅት፣ ከሁሉም ፊት የሚሆነው፣ ከሁሉ ቀድሞ የሚመርቀው *ባንባልንካ ጋን* እንደሆነ ከፍ ብለን ጠቅሰናል። ይህ ማለት ግን *ባንባልንካ ጋን* ከላይ ሆኖ ሌሎችን ያዛቸዋል ማለት እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል።

ከእነዚህ፣ ከአስራ አንዱ ባለጋኖች መካከል አንዳቸውም በፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ አይሳተፉም። ባህላዊ የፖለቲካ ተቋማትን በቀጥታ የሚያዙበት ሁኔታም ያለ አይመስልም። ይሁን እንጂ፣ በመዋቅሩ ከፖለቲካ ተቋማት ከፍ ብለው የሚቀመጡት ባለጋኖች፣ በተለይም *ባንባልንካ ጋን* እና *ሢጋናንካ ጋን* ናቸው። ለምን? ቢባል፣ ከፍ ሲል እንደተመለከተው ከፍተኛ የፖለቲካ ሹማምንት የሆኑት *ወማውና ዳይናው* ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ መንበረ *ሥልጣኑ* ሲመጡ፣ አስተዳደራቸው መልካም እንዲሆንላቸው ሲሉ ከሁለቱም ባለጋኖች ምርቃትና ቡራኬ የሚቀበሉ በመሆኑ ነው።

## 5.3 በጋን የእምነት ተቋም ውስጥ የአባላት አመዳደብ፣ ተግባርና የአሠራር ሥርዓት

የ*ጋን* እምነት ተቋም *ወማ፣ ቃሉ ወይም ወነይ* በሚል የማዕረግ ስም በሚጠራ *ባለጋን* ይመራል። እንዲሁም፣ በተለያዩ እምነታዊ *ሥርዓቶች* ላይ ባለጋኑን የሚረዱ *ቢታናችና ኣላልች* በሚል የማዕረግ ስም የሚጠሩ ሁለት ከፍተኛ ሹሞች በተቋሙ ውስጥ ይመደባሉ። እንዲሁም

ቦክ (በአንዳንድ አካባቢዎች *ኣርጋሌይ)* በሚል ማዕረግ የሚጠራ አንድ ሌላ ሹም፣ የቢታናች ረዳት ሆኖ ይመደባል። በአጠቃላይ በአንድ *የጋን* እምነት ተቋም ውስጥ በትንሹ አራት አባላት ይኖራሉ ማለት ነው። እነዚህ ሹማምንት በቦታው ላይ እንዴት እንደሚመደቡ፣ ማን እንደሚመድባቸውና የሥልጣን ዘመናቸው ስንት ዓመት እንደሆነ በዚህ ክፍል ሥር አንድ ባንድ ይቀርባል። በመቀጠልም የእያንዳንዱ ሹም ተግባር ምን እንደሆነ፣ እያንዳንዳቸው ምን እንደሚሠሩና እንዴት እንደሚሰሩ በገለፃና በትንታኔ መልክ ለማቅረብ ይሞከራል።

### 5.3.1 የባለጋን አመዳደብና ተግባር

በድሮ ጊዜ፣ በጥንቱ ዘመን ባለ*ጋን* በሰው ለሰው፣ በምርጫ ወይም በሹመት የሚሰጥ፣ ከሰው የሚገኝ ሥልጣን አልነበረም። በድሮ ዘመን ‹‹አንድን ሰው ባለ*ጋን* አድርጎ የሚፈጥረው፣ ፈጥሮ የሚመድበው ፈጣሪ እንጂ ሰው አይደለም›› ተብሎ ይታመናል። በቡርጂ እምነት መሰረት፣ በአንድ *የጋን* ጎሳ ውስጥ፣ ወደፊት *ባለጋን* የሚሆነው ሰው የሚታወቀው ገና ሲወለድ ጀምሮ ነው። እሱም ገና ሲወለድ በእጆቹ የወይራ ቅጠል፣ ዳና[57] እና የተለያዩ የእህል ዘሮችን (በተለይ ስንዴ) ይዞ ይወለዳል።[58] በዚያ ጎሣ ውስጥ ወደፊት ባለ*ጋን* የሚሆነው፣ በትረ ሥልጣኑን የሚጨብጠው፣ እንዲህ ሆኖ የተወለደ ወንድ ልጅ እንጂ፣ ሌላ ማንም *ባለጋን ሆኖ* ሊመደብ አይችልም ተብሎ ይታመናል።

ይህ የቡርጂዎች ያለፈ እምነት፣ የጥንት *ታሪክ* ነው። በአሁን ጊዜ ግን እንዲህ ሆኖ የሚወለድ ሰው የለም፤ ይኖራል ተብሎም በቡርጂዎች አይታመንም። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ የአሁኖቹ

---

[57] በአማርኛ ሰንደዶ የሚባለው የሣር ዓይነት ነው። በቡርጂዎች ዘንድ ከፍ ያለ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ፋይዳ ያለው፣ ከሣሮች ሁሉ የሚበልጥ ሣር ነው። ባለጋኖች ለሕዝበቡ ጤናና ሠላም ሲፀልዩ፣ ቡራኬ ሲሰጡ ከሚይዟቸው ቁሶች መካከል አንዱ ዳና ነው። እንዲሁም ዳና በሟቹ እግር የሚተካውን የአዲሱን ባለጋን ማንነት ማመላከቻ ምልክት በመሆንም ያገለግላል። የባለጋን ሥልጣን ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፈው ቀዳሚው ባለጋን ሞቶ ከመቀበሩ በፊት ነው። ለዚህም ሲባል ወራሹ የሚሆነው የሟች ወንድ ልጅ ከአዲሷ ሚስቱ ጋር በመሆን በተዘጋጀላቸው ቦታ ላይ እንዲቀመጡ ይደረጋሉ። እዚያ በተቀመጡበት እንዳሉ፣ የዋንዛና የወይራ ቅጠሎች ከዚህ ዳና ከሚባለው ሣር ጋር በአንድ ላይ ይታሰሩና በላያቸው ላይ እንደ ጃንጥላ ከፍ ተደርገው ይያዝላቸዋል። በዚህም ሕዝቡ የአዲሱን ባለጋንና የሚስቱን ማንነት ይለያል። ይህ ጃንጥላም በቡርጂኛ ማላልቱ ይባላል። ዳና በባህላዊ የጋብቻ ሥርዐት ውስጥም የሚሰጠው ባሕላዊ ፋይዳ ቀላል አይደለም። በቡርጂ ባህላዊ የጋብቻ ሥርዐት ውስጥ ዳንቃሣ የሚባል የመተጫጨት ሥርዐት አለ። ዳንቃሣ አንዲት ገና ጡት ያልጣለች ሴት ህፃን ልጅን ለሌላ ወንድ ህፃን ልጅ አጭቶ የማቆየት ባህላዊ ሥርዐት ነው። የመተጫጨቱ ሥርዐት የሚፈፀመው ግን እንደ መደበኛው ‹‹ልጃችሁን ለልጃችን›› በሚል ሥርዐት ከሴቷ ወላጆች ቤት በመመላለስ አይደለም። ህፃኗ በታዘለችበት ወይም ከእናቷ ማዕቀፍ ውስጥ እንዳለች ዳና ቀጥፎ ፀጉር ካላት ከህፃኗ ፀጉር ውስጥ በመሰካት ወይም በማዘያው ውስጥ በመጣል ብቻ ይፈፀማል። በዚህ መልክ የተያዘች ሴት ልጅ በምንም መንገድ ለሌላ ወንድ አትዳርም። ወንዱ በህይወት እስካለ ድረስ እድሜዋ ለጋብቻ እስከሚደርስ ድረስ ከወላጆቿ ዘንድ ሆና እሱኑ ጠብቃ ለእሱ ትዳራለች። አራስ ለመጠየቅ ሲኬድ ዳና ይዞ መሄድም እንዲሁ በቡርጂዎች ዘንድ የተለመደ ነው። አራሷን በማህበረሰቡ ልማድ ‹‹ሙጋ ባንቱ›› (በሰላም ተገላገልሽ እንደ ማለት ነው) ብለው ከሣሟት በኋላ የያዙትን ዳና ከአራሷ አጠገብ ያስቀምጡታል። ‹‹ማህፀንሽ እንደዚህ ሣር ይለምልም›› እንደማለት ነው፡ ፡ በጎሣ ደረጃ በየዓመቱ በሚፈፀመውና ሒጣኖ በሚባለው እምነታዊ ሥርዐት ላይም እንዲሁ፣ ዳና ይፈለጋል። የጎሣ መሪ የሆነ አንድ ሰው፣ በሥርዐቱ ላይ ለጎሣው ሠላምና ልማት አምላኩንና ሙታን ወገኖቹን የሚማፀነው በእጆቹ ዳና ይዞ ነው። ልመናው ሲያበቃም ዳናውን ከቤቱ በር ላይ፣ በውስጠኛው በኩል ይሰካዋል። ዳና ቡርጂዎች ‹‹ጎዴ›› ለሚሉት እምነታዊ ሥርዐት ማስፈጸሚያነት የሚያውሏትንና ቆኖሶ የሚሏትን እንስሳ መያገርነትም ይጠቀሙታል (ክፍል 5.4.2 ተመልከት) ።

[58] በሌሎች የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዘንድም ከዚህ ጋር የሚቀራረብ እምነት መኖሩን ልብ ይበሉ። አንዱን ብቻ ልጥቀስ። የሞስዬ ብሔረሰብ ‹‹ዳማ›› የሚባል ባህላዊ መሪ አለው። የ‹‹ዳማ›› ሥልጣን በዘር ሐረግ ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍ ነው። ወደፊት በአባቱ እግር ተተክቶ ወራሽ (ዳማ) የሚሆነው የሟቹ ወንድ ልጅም ገና ሲወለድ በእጆቹ የተለያዩ የእህል ዘሮችን ጨብጦ እንደሚወለድ ይታመናል (ደ.ብ.ብ.ሕ.ፕ፣ 2001፣ 193)።

ባለጋኖች የእምነቱን ደንቦች ሙሉ ለሙሉ ስለማያከብሩ፣ ገደቦችን ስለሚጥሱ፣ ወዘተ. ነው ተብሎ ይታመናል (ስለ ገደቦችና የቁጥጥር ሥርዓት ክፍል 5.5 ተመልከት)። የዚህ ዓይነቱ እምነትና የአመዳደብ ሥርዓት ከቀረ ብዙ ዓመታት ተቆጥረዋል። በአሁኑ ጊዜ፣ በሁሉም የቡርጂ አካባቢዎች፣ አንድ ሰው ባለጋን ሆኖ የሚመደበው *ከወናዋ* (ቀዳማዊት እመቤት) የተወለደ፣ የመጀመሪያ ወንድ ልጅ ሲሆን ብቻ ነው። እንዴት? ቢባል ይህ ራሱን የቻለ ሰፊ ርዕሰ ጉዳይ ነው። ቢሆንም ግን እጅግ አሳጥሬ ለማቅረብ እሞክራለሁ።

በቡርጂ የእምነት ሥርዓት፣ *የአንድ ባለጋን ሥ*ልጣን በዘር ሐረግ ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍ ነው። ይህም የሚሆነው አባቱ (የቀድሞው ባለጋን) የሞተ እንደሆን ብቻ ነው። ሥልጣኑ የሚተላለፍለት ልጅም፣ ባለጋን ከመሆኑ በፊት ሚስት አግብቶ፣ ጎጆ ቀልሶ፣ ልጆች ወልዶ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ፣ አባቱን ተክቶ *ባለጋን* እንዲሆን ከታሰበ (ከታጨ) ሌላ አዲስ፣ ልጃገረድ ሚስት ሊያገባ ወይም ተይዛ ልትመጣለት ይገባል። ለአዲሱ ባለ*ጋን* አዲስ ሚስት ለመዳር ግን ማጨት አያስፈልግም። የልጅቷንም ሆነ የወላጆቿን ፈቃድም መጠየቅ የለም። በተገኘችበት አፈፍ አድርጎ መያዝና ማምጣት ብቻ ነው። ይህን የሚፈጽሙት፣ ለአዲሱ *ባለጋን* አዲስ ሚስት የሚያመጡለት፣ በ*ጋን ባልባላ* ውስጥ *ቢታናች* እና *ኣላልች* ሆነው የሚሰሩ ሰዎች ናቸው። የአፈጻጸም ሂደቱም የሚከተለውን ይመስላል።

ሂደቱ የሚጀምረው የቀድሞው ባለ*ጋን ነፍሱ* ከስጋው እንደተለየች ነው። የቀድሞው ባለ*ጋን* እንደሞተ ሁለቱ ሹማምንት (*ቢታናች* እና *ኣላልች)* ለአዲሱ ባለ*ጋን* ሚስት የምትሆን ልጃገረድ ፍለጋ ይወጣሉ። ለዚህ ደግሞ የተቀመጠ መስፈርት አለ። መስፈርቱም እንደ ባለጋኑ ጎሣ ሊለያይ ይችላል። ለምሳሌ ነጋሲው የባንባላ ጎሣ ከሆነ ለእሱ ሚስት የምትሆነው ልጃገረድ የምትመረጠው ከወቴይሽ ጎሣ ውስጥ ይሆናል። ለሌሎቹ ጎሣ ባለጋኖችም እንዲሁ የተቀመጠ መስፈርት አለ። በዚህም ሁለቱ ሹማምንት፣ በተለያዩ የቡርጂ አካባቢዎች ውስጥ እየተዘዋወሩ መስፈርቱን የምታሟላ ልጃገረድ ያፈላልጋሉ። ከዱር ከብት ስትጠብቅም ይሁን ወይም ሰፈር ተልካ ስትመለስ፣ ብቻ የሚፈልጓትን ልጃገረድ ሲያገኙ፣ በተገኘችበት ቦታ ይይዟታል። ነገር ግን አያስገድዷትም። ወይም አፍነው አይወስዷትም። ሁኔታውን በስነ ስርዓት፣ በእርጋታ ዘርዝረው ያስረዷታል። እነርሱ እነማን እንደሆኑ? ለምን እንደፈለጓት? በትህትና ይነግሯታል። ማህበረሰቡ ስለሚከተለው የእምነት ስርዓት፣ እነርሱ እያራመዱት ስላለው ባህላዊ ልማድ አንድ በአንድ ያስረዷታል፤ ይሰብኳታል። እንዲህ አስረድተው ሲያበቁ ይዘዋት ወንዝ ይወርዳሉ። እዚያም ከሆዷ ያለውን፣ ቀደም ሲል የበላችውን፣ የጠጣችውን በሙሉ እንድታስመልስ ያደርጓታል።

በውኃ ጽድት አድርገው ሁለመናዋን ያጥቧታል። በሌላ አገላለጽ ‹‹ያጠምቋታል።›› ይህንን ከፈፀሙ በኋላ ይዘዋት ወደ መንደር ይመጣሉ። ለአዲሱ *ነጋሲ ባለጋን* ሚስት ትሆን ዘንድ የተመረጠችው ልጃገረድ፣ *በቢታናች* እና *በኣሳልች* ተይዛ ስትመጣ በባህላዊ የፖለቲካ ተቋማት ውስጥ ቁልፍ ሚና ያላቸው *ኣንሾች፣ ጎርሶች፣ ኤላዎች* እና ሌሎች ሹማምንት በክብር ይቀበሏታል። ከአዲሱ ቤቷ እንደደረሰች ከቤቱ መግቢያ በር ላይ ጠቦት አርደው ተራምዳው እንዲታልፍ ያደርጓታል። ከዚያ በኋላ ከባሏ ጋር ያነግሷታል። የንግስና ስሟንም *ወናዋ* (ቀዳማዊት እመቤት) ይሏታል። ባልዋን ደግሞ ወነይ (ቀዳማዊ) ይሉታል። ለክብራቸውም ሐዬሞ[59] የሚባል ባህላዊ ዘፈን ይዘፈንላቸዋል። ከዚያን ቀን ጀምሮ የሁለቱም ፀጉር አይቆረጥም፣ አይላጭም። እንግዲህ፣ ወደፊት ይህ አዲሱ *ባለጋን* ሲሞት በትረ ስልጣኑን መውረስ፣ እሱን ተክቶ ባለጋን መሆን የሚችለው ከዚህች፣ ተይዞ ከተዳረችለት፣ ከአዲስቷ ሚስት *(ከወናዋ)* መጀመሪያ የሚወለደው፣ የሚቹ ወንድ ልጅ ይሆናል ማለት ነው። በቡርጂ ባህላዊ ደንብ መሰረት፣ ሚቹ *ባለጋን* ከመሆኑ በፊት ከመጀመሪያ ሚስቱ የሚወልዳቸው ልጆች የአባታቸውን ስልጣን መውረስ፣ ባለጋን መሆን አይችሉም። እናታቸውም ብትሆን፣ *የወናዋዋን* ያህል በህዝብም ሆነ በባለጋኑ ቤተሰቦች ዘንድ ክብር አይኖራትም።

የሥልጣን ሽግግሩ የሚፈፀመው ሚች ከመቀበሩ አስቀድሞ፣ በምሽት (ማታ) ላይ ነው። ሽግግሩ የሚፈፀመውም የባለጋን ልዩ መለያ የሆኑትንና ቡራ[60] እና ማልዳቾ [61] የሚባሉ ባህላዊ ቁሶችን

---

[59] ለባለጋን ብቻ የሚዘፈን ነው። የሚዘፈነውም በንግሥናው፣ በሞቱና ህዝቡ የእሱን ሥራ በሚሰራበት ወቅት ብቻ ነው። ከዚ.ህ ውጭ ለማንም፣ በማንም፣ ለምንም አይዘፈንም።

[60] የተለያየ ቅርጽ ያላቸው፣ የባለጋን ልዩ የኃይል ምንጭ የሆኑ ጨሌዎች ወይም ዶቃዎች ናቸው። የሚደረጉት ወይም የሚታሰሩት ከአንገት ላይ ነው። Anborn እና Kellner, (1999, 28) ቡርጂዎች ከሊበን አመጣን ብለው እንደሚናገሩ፣ ነገር ግን ዶቃዎቹ ነጋዴ በሆኑ ቦረናዎች አማካይነት ከሱማሌ እንደመጡ ጽፈዋል። አንዱ መረጃ ሰጪ (ጫሜ፣ 2002፣ 57) ጥንት የሚሰሯቸው ቤተሰቦች እንደነበሩ፣ ቡራው በእነዚህ ወገኖች ከተሰራና አስፈላጊው እምነታዊ ሥርዐት ከተፈፀ በኋላ (ከተባረከ በኋላ ማለት ይቻላል) አገልግሎት ላይ እንደሚውል ይናገራል። ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል የሚኖረውም ከዚ.ህ በኋላ እንደሆነ ያስረዳል። በዘመናዊ የእምነት ቋንቋ ‹‹ውኃ በካህን ከተባረከ በኋላ ፀበል ይሆናል›› እንደሚባለው ማለቱ ይሆን

[61] ሌላው ለባለጋን ልዩ መለያና የኃይል ምንጭ በመሆን የሚያገለግል፣ እንደወርቅ የሚያንፀባርቅ ባህላዊ ቁስ ነው። ማልዳቾ ሁለት ዓይነት ነው። አንደኛው እንደቀለበት በጣት ላይ የሚጠለቅ ሲሆን ሁለተኛው ዓይነት ደግሞ እንደ አንባር በክንድ ላይ ይደረጋል። Anborn እና Kellner, (1999, 52) ከነሐስ ሣይሰራ አይቀርም የሚል መላምት ሰንዝረዋል። እኔ ያነጋገርኳቸው መረጃ ሰጪዎች ግን ማልዳቾ ከምንም፣ በማንም የማይሰራ፣ ከተፈጥሮ የሚገኝ እንደሆነ ይናገራሉ። አንዱ መረጃ ሰጪ (ጫሜ፣ 2002፣ 56) ማልዳቾ የሚገኘው ከዘንዶ እንደሆነ ይናገራል። በባለጋን ቤት ለዘንዶ ተብሎ የሚዘጋጅ እምነታዊ ሥርዐት ወይም ድግስ አለ። እምነታዊ ሥርዐቱን ሲፈጸምለት ዘንዶው ይመጣል። መጥቶ ድግሱን ለመብላት ሲል ማልዳቾውን ከአፉ አውጥቶ ከመሬት ያስቀምጣል። አስቀምጦት ይሄዳል። ማልዳቾ በዚ.ህ መልክ ከዘንዶ እንጂ ከየትም አይገኝም። በባለጋኖች ዘንድ እንጂ ከሌላ ሰው ዘንድ እንደማይገኝ አያት ቅድም አያቶቹን ዋቢ በማድረግ ያብራራል። ማልዳቾ የጋን ቤተሰቦች ሲፈጠሩ አብሮአቸው የተፈጠረ ባህላዊና እምነታዊ ቁስ መሆኑን የነገረኝ የመረጃ ሰጪም አለ (ቱኬ፣ 2002፣ 28)። በሌላ በኩል ደግሞ የያቢ ጎሣ ጋን (ያቢንካ ጋን) የሚገለገለው ማልዳቾ ከሊበን የመጣ መሆኑን የሚናገር መረጃ ሰጪ አለ (ቡቄ፣ 2002፣ 7-8)። እንደ መረጃ ሰጪው አባባል የያቢ ጎሣ ባለጋን የሆነበት ማልዳቾ በመሰረቱ የባላንባሌ ጎሣ ንብረት ነበረ። ከያቢ ጎሣ እጅ እንዴት ሊገባ እንደቻለ፣ የሚከተለውን አፈ ታሪክ በመተረክ ያስረዳል። ነገሩ እንዲህ ነው። የባላንባሌ ጎሣ አባላት ከሊበን ወዲህ ወደ ቡርጂ ሲመጡ ማልዳቾና ሉሌ ይዘው ነበር። ሲመጡ ደክሟቸው ‹‹ቀባርቶ›› ከሚባል አካባቢ ከአንድ ዛፍ ጥላ ሥር አረፉ። ሲነሱ ማልዳቾውን ከዚያው ረስተው ሉሌውን ግን ይዘው ጉዞ ጀመሩ። ብዙ ከተጓዙ በኋላ ማልዳቾውን ካረፉበት መርሳታቸውን አስታወሱ። ወደ ኋላቸው ተመልሰው ከቦታው ሲደርሱ በቦታው ላይ የያቢ ጎሣ አባላት ተቀምጠውበትና ማልዳቾውንም አንስተውት አገኙ። ‹‹ማልዳቾው የእኛ ነው። መልሱልን›› ባሏቸው ጊዜ የያቢ ጎሣ አባላት ‹‹ማልዳቾውን አንመልስላችሁም። ከፈለጋችሁ አንድ ጎሣ ሆነን በጋራ እንጠቀመው›› በማለት መለሱላቸው። ይህን ጊዜ የባላንባሌ ጎሣ አባላት ‹‹ከጠቀማችሁ ውሰዱት። ማልዳቾ ተራ ነገር ነው። እኛ ከእሱ የበለጠ ሉሌ ይዘናል›› ብለው ማልዳቾውን ለያቢ ጎሣ ትተው ሉሌውን ይዘው ቡርጂ መጥተው ሲሰፍሩ፣ የያቢ ጎሣ አባላትም ማልዳቾውን ይዘው ቡርጂ መጥተው ሰፈሩ። በማልዳቾው አማካይነትም ከቡርጂ ባለጋን ጎሣዎች መካከል አንዱ ሊሆኑ ቻሉ። ማልደቾ የሚደረገው በሁለት መልክ (በጣት ወይም በክንድ ላይ )ነው። ይህ ሲባል ግን ሁሊጊዜ ይደረጋል

ከሟቹ ወደ ወራሹ በማዛወር ወይም እንዲዛወሩ በማድረግ ይሆናል፡፡ ቡራ ለዚህ ሥልጣን ባለው ጎሣ አማካይነት ከሟች አንገት ላይ ተፈቶ ከወራሹ አንገት ላይ ይታሰራል፡፡ ማልዳኞ ግን ከሟች ወደ ወራሹ የሚዛወረው በሰው አማካይነት ሣይሆን በራሱ ጊዜ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህም የራሱ የሆነ የአፈፃፀም ሥርዓት አለው፡፡

በቅድሚያ እሳት ይቀጣጠላል፡፡ እሣቱ መንቦግቦግ ሲጀምር እየተዘፈነ ማልዳኞው ያለበት የሟች እጅና የወራሹ እጆች ተስበው ከእሳቱ በላይ እንዲቀራረቡ፣ እንዲገናኙ ይደረጋል፡፡ ይህን ጊዜ፣ በሟቹ ባለጋን እጅ ላይ የነበረው ማልዳኞ ማንም ሳይነካው፣ በራሱ ጊዜ ከሟቹ እጅ ወልቆ፣ ወደ ወራሹ እጅ (ክንድ ወይም ጣት) ይዛወራል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ ሲሆን የሥልጣን ሽግግሩ ሥርዓት ተፈፀመ፣ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይሉ በአዲሱ ባላጋን ላይ አደረ፣ ወራሹ በኃይል (በመንፈስ) ተሞላ ተብሎ ይታመናል፡፡[62]

የሥነ ሥርዓቱ አስፈፃሚዎች ደግሞ የባህላዊ እምነትና የአስተዳደር ከፍተኛ ሹማምንት ናቸው፡፡ ከዚህ በኋላ በነጋሲው ወንድሞች፣ እህቶችና በሌሎች ሰዎች ለአዲሱ ባለጋን ይዘፈንለታል፡፡ በሌላ ወገን ደግሞ ለሟቹ ባለጋን በሟቹ ወንድሞች፣ እህቶችና በሌሎች ሰዎች ይለቀስለታል፡፡ በአንድ ጊዜ በአንድ ቤት፣ በአንድ ግቢ፣ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ለቅሶና ዘፈን ይሆናል፡፡ በአባቱ እግር ተተክቶ ባለጋን የሚሆነው ወይም የሆነው የሟቹ ልጅም ቢሆን ‹‹አባቴ ሞተ›› ብሎ አያለቅስም፡፡ እንዲያውም የአባቱ አስከሬን ሊቀበር ከቤት ሲወጣ ባንቶ ኣቦ ጋላሽ! (የወጣኸው አባቴ አትመለስ) ነው የሚለው፡፡ የሟች አስክሬን የሚቀበረው ከዚህ በኋላ ነው፡፡

---

ማለት አይደለም፡፡ የሚደረገው ተገቢ የሆነ እምነታዊ ሥርዐት (ምርቃት ወይም ውግዘት) ለመፈፀም ሲባል ብቻ ነው፡፡ ሥርዐቱ ከተፈጸመ በኋላ ለሁልጊዜው ከሚቀመጥበት ቦታ ይቀመጣል፡፡ የሚቀመጠው በቆዳ በተለበጠ ከዋንዛ እንጨት በተሰራ ሣጥን ውስጥ ተቆልፎበት ነው፡፡ የሚወጣው እንደተባለው ለእምነታዊ ሥርዐት ሲፈለግ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ በማንኛውም ጊዜም ሆነ ቦታ አይወጣም፡፡ ማንም ሰው እንዲያየውም አይፈቀድም፡፡ የአንድ ባለጋን ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል በዋናነት ያለው በዚህ ባህላዊ ቁስ ላይ እንደሆነ ይታመናል፡፡

[62] መሪዎች አሏቸው የሚባለውን ልዕለተፈጥሮአዊ ኃይል ከአንዱ ወደ ሌላው፣ ከሟች ወደ ተተኪው መሪ እንዲተላለፍ የሚደረግበት መንገድም ሆነ እምነት ከማህበረሰብ ማህበረሰብ ይለያያል፡፡ ወይም ይመሳሰላል፡፡ ሁለት ምሳሌዎችን ብቻ ልጥቀስ፡፡ አንድ ከናይጀሪያ፣ አንድ ከኢትዮጵያ፡፡ ናይጀሪያ ውስጥ Yoruba የሚባል ማህበረሰብ አለ፡፡ ማህበረሰቡ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል አለው በሚባል ባህላዊ መሪ (Chief) ይመራል፡፡ አንዱ (Chief) ሞቶ አዲስ (Chief) ሲተካ በቀዳሚው (Chief) ላይ የነበረው ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል ወደ አዲሱ (Chief) ሊተላለፍ ይገባል፡፡ ለዚህ ሲባልም አዲሱ (Chief) የቀዳሚውን (Chief) ልብ እንዲበላ ይደረጋል፡፡ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይሉ ከቀዳሚው (Chief) ወደ አዲሱ (Chief) ተላለፈ የሚባለውም አዲሱ (Chief) የቀዳሚውን ልብ በከፊል የበላ እንደሆነ ነው ተብሎ እንደሚታመን "…the Yoruba custom in which each successive Oba was required to eat part of the heart of his predecessor" በማለት Cowan (1959) በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 4፣ ገጽ 5 ላይ ጽፏል፡፡ ሌላው የሱርማ ብሔረሰብ ነው፡፡ ሱርማዎች ‹‹ዶሌቲ›› የሚባል ባህላዊ መሪ አላቸው፡፡ ‹‹ዶሌቲ›› ከፖለቲካዊ ሥልጣን በተጨማሪ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይልም አለው ተብሎ ይታመናል፡፡ ሥልጣኑ በዘር ሐረግ፣ ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍ ሲሆን ሽግግሩ በዋናነት የሚፈጸመው በቀዳሚው ዶሌት ላይ የነበረው ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይልን ወደ ወራሹ ልጅ እንዲተላለፍ በማድረግ ነው፡፡ ይህም በሚከተለው መንገድ ይከናወናል፡፡ በቅድሚያ ለሟቹ የሚሆን የመቃብር ጉድጓድ ይቆፈራል፡፡ በተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥም ወራሹ ገብቶ ቁጢጥ ብሎ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡ ከዚያም በመቃብሩ አፍ ላይ እንጨቶች ይረበረቡና በላዩ ላይ ፍየል ይታረድበታል፡፡ የሟቹ አስከሬንም ከርብራቡ ላይ ተደርጎ በፍየሉ ደምና ፈርስ ይታጠባል፡፡ እጣቢውም ከመቃብሩ ውስጥ በተቀመጠው ወራሽ ላይ እንዲፈስ ይደረጋል፡፡ ይህ ሲሆን ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይሉ ከሟች ወደ ወራሽ ተላለፈ ተብሎ ስለሚታመን ልጁ ከመቃብሩ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ ከጉድጓዱ ከወጣ በኋላ የዶሌት መለያ ምልክት የሆነው ጨሌ ከሟቹ አንገት፣ አንባሩ ደግሞ ከእጁ ላይ ወጥቶ ለአዲሱ ዶሌቲ ይደረግለታል፡፡ በዚህም የሥልጣን ሽግግር ሥርዐቱ ይፈጸማል፡፡

በቡርጂ የእምነት ሥርዓት መሠረት አንድ ባለጋን የነበረ ሰው ነግሶ በቆየበት መኖሪያ ቤቱ ውስጥ እንዲሞት (ነፍሱ ከስጋው እንድትለይ) አይፈቀድም። በቡርጂ የእምነት ሥርዓት፣ የአንድ ባለጋን መኖሪያ ቤት (ኢባ) እንደ ቅዱስ ሥፍራ ተደርጎ ይቆጠራል። በዚህ በቅዱስ ሥፍራ ላይ ነፍሱ ብትወጣ ሥፍራው እንደረከሰ ስለሚቆጠር ሲሞት ሲያጣጥር ከጎረቤት ቤት ይወሰዳል። ነፍሱ ከጎረቤት ከወጣች በኋላ አስከሬኑ ተመልሶ ይመጣል። ከመኖሪያ ቤቱ እንዳለ ነፍሱ ቢትወጣ ግን፣ የሟቹ አስከሬን የሚወጣው ቤቱ ከጀርባ በኩል ተቀዶና ሌላ መውጫ በር ተበጅቶለት፣ በጓሮ በኩል እንጂ፣ በፊት ለፊት፣ በዋናው በር *(በባልባላው)* በኩል አይወጣም። ይህ የሚሆነው በሁለት ምክንያቶች ይመስለኛል። አንደኛው እንደ መኖሪያ ቤቱ፣ ግቢው ወይም ባልባላው እንዳይረክስ በሚል ነው። ሁለተኛው ምክንያት ቡርጂዎች በአንድ ባልባላ ላይ ሥልጣን ያለው መሪ (ኣና) የሆነ ሰው ነው ብለው ስለሚያምኑ ነው። ሟቹ ባለጋን በርግጥ ቀደም ሲል በባልባላው ላይ ኣና ነበር። አሁን ግን አይደለም። አሁን ኣናው፣ ወማው ወይም ባለጋኑ፣ አዲሱ ባለጋን እንጂ ሟቹ (አሁን አስከሬን የሚባለው) አይደለም። በዚህ እምነት መነሻም የሟቹ አስከሬን እንደ እርኩስ ተቆጥሮ፣ የተቀደሰውን ሥፍራ እንዳያረክስ ሲባል በጓሮ በኩል እንዲወጣ ይደረጋል። በመጨረሻም ነፍሱ የወጣበት ቤትና ግቢ *ምጨ* (እንዲነፃ) ይደረጋል።

አንድ ባለጋን ሲሞት፣ መሞቱ ወዲያው ለሕዝብ ይፋ አይደረግም። እንዲሁም ወዲያውም አይቀበርም። መሞቱ ይፋ የሚደረገውም ሆነ የቀብር ሥነ ሥርዓቱ የሚፈጸመው ከአምስት ወይም ከሰባት ቀናት በኋላ ነው። ይህ የሚደረገውም አንድም፣ ለሥልጣን ሽግግሩ በቂ ጊዜ ለማግኘት ሲባል ነው። አንድም፣ በቀብሩ ላይ መገኘት ያለባቸው ክፍሎች በተለይ እባብ፣ ዘንዶ፣ አንበሣ፣ ነብር፣...ወዘተ የመሣሰሉት የዱር አራዊትና የማህበረሰቡ ከፍተኛ ሹማምንት፣ ተጠቃለው እስከሚገቡ፣ ከሟቹ ቤት ለለቅሶ እስከሚመጡ ድረስ ለመጠባበቅ ሲባል ነው። አንድ ባለጋን ሲሞት አራዊት ሁሉ ሣይቀሩ ከሟቹ ቤት ድረስ ይመጣሉ ተብሎ ይታመናል። ከሁሉም በላይ ግን እባብና ዘንዶ ባለጋን የሆኑ ሰዎች ሲሞቱ ብቻ ሣይሆን በህይወት እያሉም ከመኖሪያ ቤታቸው አካባቢ የማይጠፉ፣ የቅርብ ወዳጆቻቸው እንደሆኑ ይታመናል[63]።

[63] ይህንን በተመለከተ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ አንድ ገጠመኝ አለው። ገጠመኙ ከዛሬ ከ20 ዓመት በፊት የሆነ ነው። ፀሐፊው ጋን አላቸው ከሚባሉ ከባንባላ ጎሣ የሚወለድ አንድ ጓደኛ ነበረው። ሁለቱም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጋሞ ጎፋ ውስጥ ሲከታተሉ ቆይተው ትምህርት ቤቱ ለክረምት ሲዘጋ ወደ ቡርጂ ይመጣሉ። ክረምቱን የሚያሳልፉት ቀንም ሆነ ማታ ሣይለያዩ ነው። ዛሬ ከጓደኛው ወላጆች ቤት ካደሩ ነገ ደግሞ ከፀሐፊው ወላጆች ቤት ያድራሉ። አንድ ማታ እንደተለመደው ከጓደኛው ወላጆች ቤት ያድራሉ። ከጓደኛው ጋር እንደ ቆጥ በተሰራ ሰቀላ አልጋ ላይ በተኛበት በዚያ ውድቅት ሌሊት ላይ፣ አንድ ነገር ይጫነዋል። የጓደኛው እግር መስሎት ገፋ ቢያደርገው መንቀሳቀስ፣ እላዩ ላይ መሄድ ጀመረ። ጓደኛውን ቀስቅሶ ‹‹እስቲ ባትሪውን አብራ። በላዬ ላይ የሚሄድብኝ ነገር ምንድነው?›› ሲለው ‹‹ዝም ብለህ ተኛ። ምንም አያደርግህም›› ይለዋል ጓደኛው። ‹‹ምኑ?›› መልሶ ጓደኛውን ጠየቀው። ጓደኛውም እየሳቀ ‹‹የቤታችን ደንብ ነዋ! እስከዛሬ አጋጥሞህ

ሟቹ ባለ*ጋ*ን የሚቀበረው ብቻውን አይደለም። ከጊደር *ጋ*ር አብሮ ይቀበራል። በመጀመሪያ መቃብሩ ሰፋ ተደርጎ ይቆፈራል። በመቃብሩ ወለል ላይ አንድ ቋሚ እንጨት ይተከልና ጊደር ገብታ ትታሰርበታለች። ሣር ታጭዶ ከፊቷ ይጣልላታል። ከእሷ በላይ ትንሽ ከፍ ብሎ እንጨት ይረበረብና ለሟች አስከሬን ማረፊያ የሚሆን ቦታ ከወገቡ ላይ ይዘጋጅለታል። አስከሬኑ ከአረፈ በኋላ አፈር ይመለስበትና ግብዓተ መሬቱ ይፈፀማል። በቡርጂ ልማድ፣ አንድ ባለ*ጋ*ን ሲሞት ‹‹ሞተ›› አይባልም። *‹‹ሣለይንካ ሣሉና ርቃን››* (ከላሚቷ ሆድ ተመለሰ) ነው የሚባለው።

አንድ ባለ*ጋ*ን ሲሞት ‹‹ከላሚቷ ሆድ ተመለሰ›› እንጂ፣ እንደ ተራ ሰው ‹‹ሞተ›› የማይባለው፣ በርግጥም መረጃ ሰጪዎቹ (ቱኬ፣ 23፤ አደን፣ 35፤ 2002) ሞቱን ከተራ ሰው ሞት ለመለየት፣ ከሰው (ከፍጡር) ከፍ ያለ፣ ከፈጣሪ ዝቅ ያለ መሆኑን ለማመልከት፣ ለማክበር ሲባል ሊሆን ይችላል። እኔ ግን አባባሉ ከዚህም በላይ የሆነ ሌላም ፍች አለው ብዬ እገምታለሁ። ፍችው፣ በአንድ በኩል፣ ቀደም ሲል ስለ *ባንባላ ጎሣ ጋን* እምነት አጀማመር ከተተረከው አፈ ታሪክ *ጋ*ር የሚያያዝ ይመስለኛል። በአፈ ታሪኩ መሰረት፣ *ለባንባልንካ ጋንና ጎሣ* መፈጠር ምክንያት የሆነው፣ *ያያ* ተባለው ባለ*ጋ*ን የተወለደው ከሰው (ከድንግል) ቢሆንም፣ ያደገው ግን የላም ጡት እየጠባ ነው። ላሚቷ ባትወልደውም፣ እያጠባች አሣድገዋለችና ‹‹እናቱ›› ነች ማለት ይቻላል። ሲሞት ‹‹ከላሚቷ ሆድ ተመለሰ›› መባሉም አንድም፣ (ለሁሉም ላይሰራ ቢችልም) ይኸንኑ አፈጣጠሩን ለማመልከት ሲባል ይመስለኛል። አንድም፣ የ*ጋ*ኑን ሕያውነት፣ ዘለዓለማዊነት ለመጠቆም ሲባል ነው ብዬ እስባለሁ። እንደ እምነቱ ተከታዮች፣ *ጋን* በሰዎች የሚያድር ልዩ መንፈሳዊ ችሮታ እንጂ፣ በራሱ ሰው አይደለም። መንፈስ በመሆኑም አይሞትም። የሚሞተው፣ ሞቶ የሚቀበረው ማደሪያው የነበረው፣ *ሥጋ* ለባሹ ሰው እንጂ እሱ፣ መንፈሱ አይደለም። እሱ ሕያው ስለሆነ አንዱ ማደሪያው ሲሞት በሌላ ማደሪያው (በሌላ ሰው) አድሮ እንደገና የሚገለጥ ቋሚ እንጂ ሟች፣ አላፊ፣ ጠፊ፣ ያለመሆኑን ለማመልከት ሲባል ይመስለኛል። ከጊደር *ጋ*ር መቀበሩም፣ አባባሉ እውነትነት፣ እምነቱ ተጨባጭነት እንዲኖረው ለማድረግ ታስቦ ሣይሆን አይቀርም ብዬ እገምታለሁ።

---

አያውቅም አይደል?›› አለው። ነገሩ የገባው ፀሐፊም በድንጋጤ የሌሊት ልብሱን ከላዩ ላይ ወርውሮ ዘሎ ከአልጋው ላይ ወረደ። ጓደኛውም እየሳቀ ባትሪውን አበራለት። ትልቅ ጥቁር እባብ ከሌሊት ልብሳቸው ውስጥ መሰስ ብሎ ወጥቶ በአልጋው ቋሚ አድርጎ ወደ መሬት ሲወርድ ተመለከተ። ሌሎቹ ያላዩ መስሎት ‹‹እባብ! እባብ!›› ሲል በድንጋጤ ጮኸ። ጓደኛውን ጨምሮ የቤቱ ሰው ሁሉ ይስቅበት ጀመር። የጓደኛው አባት (ባለጋኑ) ግን ተነስተው ኃይዞህ! አትፍራ! ሰውን አይነካም›› ብሎ አረጋጋው። ከዚያም በማይሰማ ድምፅ የሆነ ነገር አሉ። እባቡም ወዲያው ተሰወረ። በሌላ ቀን ከዚሁ ቤት ውስጥ ነው። ከጧቱ ወደ አራት ሰዓት አካባቢ ቡና እየጠጡ ሳለ ፀሐፊው በማያውቅ ምክንያት ሌላው ሰው ሁሉ ወደ እሱ እየተመለከተ ይስቅ ጀመረ። ጎንበስ ብሎ ቢመለከት በእባቦች ተከቧል። በድንጋጤ ዘሎ በትር አንስቶ እባቦቹን ሊመታቸው ሲል የጓደኛው እናት እየሳቀች በትሩን ተቀበለችው። ‹‹ገና ምኑን አይተህ። ሰውን አይተናኮልም። ያንተን ማንነት ሊያጣራ የመጣ ነው›› ብላ አጉመተመተች። እባቦቹም ተሰወሩ። ፀሐፊውም ለመዳቸው። በባለጋኑ ግቢ ውስጥ እባቦቹ ሲርመሰመሱ መመልከት የዘወትር ተግባሩ ሆነ።

በቡርጂ ህዝብ፣ በንብረቱና በሀገሪቱ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ወይም የደረሰውን እኩይ ነገር *መከላከልና እንዲጠፋ ማድረግ፣* የሕዝቡን ደህንነት መጠበቅ ከባለ*ጋን ተግባራት መካከል* ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ *መባረክ፣ መመረቅና ‹‹ማውገዝ››* ከሁሉም ቅድሚ*ያ ያላቸው* የባለ*ጋን* ተግባራት ናቸው፡፡ ባለጋን የተዘሩ ሰብሎች እንዲበቅሉ፣ በቅለው ፍሬ እንዲሰጡ፣ እንዲበረክቱ፣ ላሞች እንዲወልዱ፣ እንዲታለቡ፣ ዝናብ ዘንቦ ሀገሩ እንዲለማ ይመርቃል፡፡ ይባርካል፡፡ እንደ በሽታ፣ ጦርነት፣ ወዘተ. *የመሳሰሉ፣* ህዝብን የሚጎዱ ነገሮች በአካባቢው ሲከሰቱ ደግሞ *ያወግዛቸዋል፡፡* ይህ ሲባል ግን ሁሉም ባለጋኖች ከላይ የተመለከቱትን ሁሉ ማድረግ ይችላሉ ማለት አይደለም፡፡ አንዱ ያለውን ችሎታ አብዛኞቹ አይኖራቸውም፡፡ ወይም አንዱ የሚፈጽመውን ሌላው *መፈጸም* አይቻለውም፡፡ በሌላ አገላለጽ እያንዳንዱ *ባለጋን* ከአያት ከቅድመ አያቶቹ የወረሰው፣ የየራሱ የተለየ ችሎታና ስጦታ ወይም ሰማያዊ ፀጋ አለው፡፡ የአንድ ባለጋን ተግባር የሚወሰነውም በዚህ ‹‹አለው›› በሚባለው ልዩ ስጦታና ችሎታ ይሆናል፡፡ በዚህም፣ *ሢጋናንካ ጋን* በአካባቢው ዝናብ እንዲዘንብ ወይም ተቃራኒው እንዲሆን የማድረግ ተግባር ይፈጽማል፡፡ *ቀዳዲንካ ጋን* ደግሞ የዘንጋዳ ሰብል ፍሬ እንዲሰጥ፣ እንዲበረክት ይመርቃል፡፡ ይባርካል፡፡ በበሽታ እንዳይጠቃ ይከላከላል፡፡ ወይም ተቃራኒው እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ሌላው *ማንጋደንካ ጋን የሚ*ባለው ነው፡፡ ተግባሩም የስንዴና የማሽላ ሰብሎች እንዲበረክቱ፣ በአንበጣና በትናንሽ ነፍሳት እንዳይጠቁ *መከላከል* ወይም ተቃራኒውን ማድረግ ነው፡፡ የተዘራው የስንዴ ዘር እንዲበቅል፣ የበቀለው እንዲያፈራ፣ ምርቱ እንዲበረክት የማድረግና በስንዴ ሰብል ላይ የሚከሰቱ በሽታዎችን የመከላከል ወይም ተቃራኒውን የመፈጸም ተግባር ደግሞ *አናቡራንካ ጋን* ይሆናል፡፡ የማሽላ ሰብሎችን *መመረቅ፣* ከጥቃት *መከላከል* ወይም ተቃራኒው እንዲሆን *መሥራት ያቢንካ ጋን* ተግባር ነው፡፡ *ቢሬይሌንካ ጋን* የሚባለው ደግሞ ተምችን ጨምሮ ሰብል የሚያጠቁ ሌሎች በሽታዎችን ይከላከላል፡፡ ወይም ተቃራኒውን *ሥራ* ይሠራል፡፡ በጦርነቶችና በሁሉም በሽታዎች ላይ *ሥ*ልጣን ያለው *ባንባልንካ ጋን* ነው፡፡ በሌላ ስሙ *ዋዋያንካ ጋን* እየተባለም ይጠራል፡፡ ጦርነቶችን ፀጥ ማድረግ፣ በሰው፣ በቤት እንስሳትና በእፅዋት ላይ የሚከሰቱ በሽታዎችን *መከላከል* ወይም ተቃራኒውን ማድረግ ዋነኞቹ ተግባራቱ ናቸው፡፡ በማህበረሰቡ ሰብል ላይ አንበጣ ወይም ፌንጣ የዘመተበት እንደሆነ አንበጣውን ወይም ፌንጣውን እንዲያባርር የሚጠየቀው *ጣሚይንካ ጋን* ያላቸው ቤተሰቦች ናቸው፡፡ *ጣሚይንካ ጋን፣ ዳሬይሽንካ ጋን* (የአንበጣ ጋን) በሚል ስሙም ይታወቃል፡፡ በማናቸውም ዓይነት በሽታዎች ላይ *ሥ*ልጣን አለው ተብሎ የሚታመነው ሌላው *ጋን* ደግሞ *ኮበሌይሽንካ ጋን* ነው፡፡ *ጋቤይንካ ጋን* የሚባልም አለ፡፡ ተግባሩም ተምችን ጨምሮ ሁሉንም የሰብል በሽታዎችን፣ የቤት እንስሳትን የሚያጠቁ የዱር አራዊትን የማዘዝ፣ ሰብሉና እንስሳቱ

በእነዚህ እንዳይጠቁ መከላከል ወይም ተቃራኒውን ማድረግ ነው። በሰማይ የሚበሩ አዕዋፍትን እንዳሻው የሚያዘው ደግሞ *ሎማሌይንካ ጋን* በመባል ይታወቃል።

አንድ ባለጋን ሲመርቅም ሆነ ሲያወግዝ በእጆቹ የሚይዛቸው ባህላዊ ቁሶች ይኖራሉ። ባለጋን ሲመርቅ አራት ነገሮችን ይይዛል። ከእነዚህ መካከል አንዱ *ሊሶ* ነው። ሁለተኛው ቡርጂዎች *ዳና* የሚሉት ለምለም ሣር ነው። ሶስተኛው ቅጠል ያለው የወይራ እንጨት ሲሆን አራተኛው ከእህል ዘሮች መካከል አንዱን (በተለይም ስንዴን) ይዞ ይመርቃል። የሚፈጸመው እምነታዊ *ሥርዓት* ውግዘት ሲሆን *ቃራ* የሚባለው ጦርና *ሊሶ* ብቻ ይያዛሉ። ካላች በሁለቱም ወቅት ከግንባር ላይ ይታሰራል።

ባለጋን ከቤቱ አይወጣም። ከቤቱ ቁጭ ብሎ ህዝብን፣ ሀገርን፣ እንስሳትን፣ ዘመንን፣ ሰብልን፣ ወዘተ. ይመርቃል። ይባርካል። እንዲህ የሚባርከውም ሆነ የሚመርቀው እንዲመርቅና እንዲባርክ ሲጠየቅ ብቻ ነው። የሚጠይቀው ደግሞ ለዚህ ተግባር የተመደበው *ቢታናች* ነው። በዚህም ህዝቡ ማሳውን አርሶ ከመዝራቱ በፊት፣ የተዘራው ሰብል ደርሶ ከመታጨዱ ወይም ከመበላቱ አስቀድሞ፣ በሚመለከተው ባለጋን ሊመረቅ ይገባል (ስለዝርዝሩ ቀጣዩን ክፍል ተመልከት)። ይህ ሳይፈፀም፣ ማንም ሰው እህል እንዲዘራም ሆነ ያሸተውን  እንዲበላ አይፈቀድለትም። ባለጋን (ሚስቱን ጨምሮ) የጉልበት ስራ እንዲሰራ አይፈቀድለትም። እርሻ አያርስም። እህል አያጭድም። ሁሉን የሚሠራለት ህዝቡ ነው ። የእሱ *ሥራ* ለህዝቡ ሠላምና ብልፅግና መፀለይ፣ ህዝቡንና የህዝቡን ንብረት መመረቅ፣ ክፉውን ማውገዝ ብቻ ነው። ይህንንም የሚያከናውንበት የተለየ *ሥፍራ* አለው። ለውግዘት ሲሆን ብዙውን ጊዜ *ሥርዓቱ* ከአካባቢው ከፍ ባሉ ተራራማ *ሥፍራዎች* ላይ ይከናወናል። የምርቃት *ሥርዓቶች* ግን የሚከናወኑት ከዚያው ከባለ ጋኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ ለዚህ ሲባል በተዘጋጀ ቦታ ላይ ነው። ይህም *ሥፍራ ዋያ* ይባላል። *ዋያ* ሁሉም *ባለጋኖች (ከሣጋናንካ  ጋን* በስተ ቀር) ተቀምጠው የሚመርቁበት  *ሥፍራ* ነው፡ ፡ *ሥፍራ* ው የሚገኘው በባለጋኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ ነው።

ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል፣ ሁሉም ባለጋኖች፣ ከማህበረሰቡ ህይወት ጋር በእጅጉ  የተቆራኙ ተግባራትን ስለሚያከናውኑ በህዝቡ ዘንድ እጅግ ይከበራሉ። ከፍ ተብሎ እንደተጠቀሰው ጥሩ ጥሩውን፣ መልካም መልካሙን፣ ህዝቡን የሚጠቅሙትን ብቻ ሳይሆን ክፉ ክፉውንም፣ ህዝብን የሚጎዱ ተግባራትንም ጭምር የማድረግ መንፈሳዊ ኃይል አላቸው ተብለው ስለሚታመኑ ይፈራሉ። ይህን የሚያደርጉት ግን፣ ህዝቡ ያስቀየማቸው፣ ሕዝቡ ያስከፋቸው እንደሆን ብቻ ነው። ለምሳሌ ያህል፣ የዱር አራዊትን የማዘዝ *ሥ*ልጣን ያለውን ባለጋን ህዝቡ አስከፍቶት

እንደሆነ፣ በቤት እንስሳቱ ላይ የዱር አራዊት እንዲዘምቱባቸው ያዛቸዋል። ይህን ጊዜ የዱር አራዊቱ ካሉበት እየወጡ፣ እንስሳቱን መፍጀት ይጀምራሉ ተብሎ ይታመናል። ይህን ማን? ለምን? እንደፈፀመ ስለሚታወቅ *ባለጋሉ* አራዊቱን ጠርቶ እንዳስመጣቸው ጠርቶ እንዲያስወጣቸው *በቢታናች* አማካይነት ይጠየቃል። እሱም የጠየቁትን ይፈፅምላቸዋል። እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች የሚከሰቱት ግን እጅግ በአነስተኛ ደረጃ ነው።

### 5.3.2 የቢታናች አመዳደብና ተግባር

ከፍ ተብሎ እንደተጠቀሰው፣ *ቢታናች* በሁለቱም (በፖለቲካዊና በመንፈሳዊ) መዋቅሮች ውስጥ የሚሳተፍ ከፍተኛ ባለስልጣን ነው። *ቢታናች* የሚመደበው በምርጫ ሲሆን፣ የሚመርጠው ደግሞ *ኣንሽ* ነው። የምርጫ *ሥ*ርዓቱም የሚከተለውን ይመስላል።

የቀድሞው *ቢታናች* የ*ሥ*ልጣን ዘመኑ እንደተጠናቀቀ፣ ‹‹አዲስ *ቢታናች* መድቡ›› የሚል መልዕክት፣ ከእምነት ተቋሙ ተረኛ ለሆነው ጎሣ መሪ *(ለኣንሽ)* ይደርሰዋል። መልዕክቱን የሚልከው *ባለጋሉ* ሲሆን፣ *ለኣንሽ* የሚያደርሰው ደግሞ *ኣላልቻ* (ቀጣዩን ክፍል ተመልከት) ይሆናል። መልዕክቱ የደረሰው *ኣንሽም* የሚመለከታቸውን የጎሳውን ሹማምንት ጠርቶ በጉዳዩ ላይ ይመክራል። ከጎሳው አባላት መካከል፣ የእምነት *ሥ*ርዓቶችንና ደንቦችን ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ በማህበረሰቡ ወይም በጎሣው ዘንድ ጥሩ ስም ያለውን፣ ኃላፊነቱን በአግባቡ ሊወጣ የሚችለውን፣ ወዘተ. በአጭሩ ለቦታው ተገቢ የሆነን አንድ ሰው መርጦ *ለኣላልቻ* ያቀርባል። በመጨረሻም *ኣላልቻ* ‹‹አዲሱ *ቢታናች* ይኸውልህ። ለአንተ ይላላክልህ›› በማለት ተመራጩን ሰው ወስዶ *ለባለጋሉ* ይሰጠዋል።

*ቢታናች* ከሁሉም ጎሳ አይመረጥም። *ቢታናች* መርጦ መመደብ ለተወሰኑ ጎሳዎች ብቻ የተሰጠ *ሥ*ልጣን ነው። ዛሬ ከአንድ ጎሳ የተመረጠ ከሆነ፣ በሚቀጥለው የ*ሥ*ልጣን ዘመን ደግሞ ከሌላ ጎሳ ይመረጣል። *ቢታናች* ተጠሪነቱ ለባለጋሉ ሲሆን፣ የአገልግሎት ዘመኑ እንደ አካባቢው ይለያያል። ለምሳሌ ያህል *በክሊቾ ቦሄ* አካባቢ አንድ *ቢታናች* በ*ሥ*ልጣን ላይ የሚቆየው ለአንድ ዓመት ብቻ ነው። *በጋሻራ* አካባቢ የቢታናች *ሥ*ልጣን በሰባት ዓመት ሲገደብ፣ የበን ውስጥ ደግሞ *የቢታናች ሥ*ልጣን የእድሜ ልክ ይሆናል። በሌሎች አካባቢዎችም እንዲሁ ይለያያል።

ለልዩነቱ (በሌሎች ባህላዊ ደንቦች ላይም እንዲሁ ይንፀባረቃል) ምክንያቱ ምን እንደሆነ በእርግጠኛነት ለመናገር፣ በራሱ ጥናት የሚሻ ቢሆንም ግን፣ አስተዳደራዊ መዋቅሩ አንዱ ምክንያት ሣይሆን አይቀርም ብዬ አስባለሁ። ከፍ ባሉት ምዕራፎች እንደተመለከተው፣ የቡርጂ

ክልላዊ ተቋም፣ ራሣቸውን ችለው በሚተዳደሩ በአራት የራስ ገዝና በስምንት የቢ.ያ አስተዳደሮች የተዋቀረ ነው። የእያንዳንዱ የቢ.ያ ፖለቲካዊም ሆኑ እምነታዊ ደንቦች የሚቀረጹት በቢ.ያንካ ጎርሶማ አማካይነት መሆኑ ከፍ ሲል ተመልክቷል። ደንቦች ሲወጡ የቡርጂን እምነት መሰረት የሚያደርጉ ቢሆንም፣ ለአካባቢያቸው እንዲመች አድርገው ይቀርጹታል። አስተዳደራዊ መዋቅሩ፣ ለቢ.ታናች የአገልግሎት ዘመንም ሆነ ለመሣሰሉት መለያየት አንዱ ምክንያት ሣይሆን አይቀርም ያልኩትም ይህንኑ መሰረት በማድረግ ነው።

*ቢ.ታናች በባለጋን* እና በህዝብ፣ *በባለጋን እና በኣንሽ፣* እንዲሁም *በባለጋን* እና *በኤላዎች* መካከል አገናኝ ሆኖ ይሠራል። አገናኝ በመሆኑም፣ የህዝቡን ጥያቄ ተቀብሎ ለባለጋኑ ያደርሳል። *የባለጋኑን* መልዕክት ወስዶ ለህዝብ ያሰማል። እንዲሁም *የባለጋኑን* ጉዳይ ተቀብሎ *ለኣንሽና ለኤላዎች፣ የኣንሽንና* የኤላዎችን ሀሳብ ወስዶ *ለባለጋኑ* ያቀርባል። በአጭሩ *ቢ.ታናች፣ ከባለጋን* ወደ *ኣንሽ፣ ወደ ኤላዎችና* ወደ ህዝብ፣ ከህዝብ፣ *ከኤላዎችና ከኣንሽ* ወደ *ባለጋን* ይመላለሳል። ይላላካል።

ይህ ሲባል ግን፣ ህዝቡ በቡድንም ሆነ በግል *ከቢ.ታናቹ ጋር* በቀጥታ ይገናኛሉ ወይም ፍላጎታቸውን ይነግሩታል ማለት አይደለም። ህዝቡን ወክለው *ከቢ.ታናች ጋር* የሚገናኙት፣ የህዝቡን ፍላጎት የሚገልጹት፣ ጥያቄ የሚያቀርቡት፣ ለህዝቡ በረከትና ምርቃት እንዲቀበል *ቢ.ታናቹን* ወደ *ባለጋኑ* የሚልኩት *ኣንሾች፣ ጎርሶችና ኤላዎች* ናቸው። ለምሳሌ ያህል፣ የአንበጣ *መንጋ* በህዝቡ ሰብል ላይ ዘምቶበት ከሆነ የዚህ *ሥ*ልጣን ያለው ባለጋን አንበጣውን እንዲያስወግድላቸው ህዝቡ ይፈልጋል። ይህንን የሕዝቡን ጥያቄ የሚያቀርቡት ደግሞ *ኣንሾችና* ኤላዎች ይሆናሉ። እነርሱም *ራሣቸው* ቢሆኑ ጥያቄውን ይዘው ከባለጋኑ ዘንድ መቅረብ አይችሉም። ይህን እንዲያደርጉ እምነታዊ ደንቡ አይፈቅድላቸውም። እነርሱ *ለቢ.ታናች* ይነግሩታል። ወይም *ቢ.ታናቹን* ወደ *ባለጋኑ* ይልኩታል። አሊያም *ቢ.ታናቹን* ከፊት አድርገው፣ እሱን ተከትለው፣ ጥያቄያቸውን ይዘው፣ *ከባለጋኑ* ዘንድ ይሄዳሉ።

እንዲህ ወደ *ባለጋኑ* የሚኬደው ባዶ እጅ አይደለም። በርግጥ ቡርጂዎች ከባለጋኖች ለሚያገኙት እምነታዊ አገልግሎት የሚከፍሏቸው አንዳች ክፍያ የለም። ሁሉንም አገልግሎት የሚያገኙት በነፃ ነው። ይሁን እንጂ፣ የሚኬደው ለምርቃት፣ ለበረከት ሲሆን፣ ከባለጋን ዘንድ ጥሬ ቅቤ፣ ትኩስ ወተትና ቦርዴ *(ጉሱማ)* ተይዞ ይኬዳል (የሚኬደው ‹‹ዝናብ የመዝነብ ኃይል አለው›› ተብሎ ወደሚታመነው ወደ *ሣጋናንካ ጋን* ከሆነ ደግሞ፣ በሚወሰደው ነገር ላይ መጠነኛ ልዩነት መኖሩን በምዕራፍ አራት ላይ ልብ ይሉዋል)። የህዝቡ ጥያቄም በቢ.ታናች አማካይነት

ይቀርብለታል። እሱም ጥያቄውን ከመመለሱ በፊት ከሄደለት ቅቤ ትንሽ አንስቶ በቅድሚያ ለራሱ፣ ከአናቱ ላይ ይቀባል። ቀጥሎ የቢታናቹን አናት ይቀባል። ከዚያ የተገኘን ሰው ሁሉ ቅቤ ከአናት አናታቸው ላይ ይቀባቸዋል። በመጨረሻም በሥርዓቱ ላይ የሚያዙ ባህላዊ ቁሶችንም እንዲሁ ቅቤ ከቀባቸው በኋላ የህዝቡን ጥያቄ ይመልሣል። ይመርቃል። ይባርካል ወይም ያወግዛል። ለውግዘት ሲሆን የራሱ ሥርዓትና ሥፍራ አለው። የህዝቡ ጥያቄ፣ አንድን ክፉ ክስተት እንዲያርቅላቸው፣ እንዲከላከልላቸው ሲሆን፣ ባለጋኑ ከቤቱ እንዲወጣ ይደረጋል። አስፈላጊውን ባህላዊ ቁስ ይዞ በአካባቢው ባለ ተራራማ ስፍራ ላይ ይወጣል።

*ባለጋን* ይህን ሁሉ በሚያደርግበት ሰዓት *ቢታናች* ከሥር ከሥሩ ነው። ከባለጋን ሥር ፈፅሞ አይጠፋም። እነዚህን ቁሶች ለባለጋን የሚያቀብለው እሱ ነው። ሥርዓቱ ከሚፈጸምበት ተራራ ላይ ከተወጣ በኋላም ቢሆን ባለጋኑን ‹‹እንዲህ በል! እንዲህ በል!›› እያለ የሚመራው ቢታናቹ ነው። ባለጋን በራሱ ጊዜ፣ በራሱ ፍላጎት የሚለው አንዳች ነገር የለም። ምርቃቱንም፣ ‹‹ውግዘቱንም›› ‹‹እንደዚህ በል›› የሚለው ቢታናች ነው። ‹‹በአካባቢው እንዲህ፣ እዲህ ያለ የተከሰተ ነገር አለ የህዝብ ሰብል በአንበጣ ተወሯልና አውግዘው›› የሚለው ቢታናቹ እንጂ ማንም አይደለም። ለምሳሌ ያህል በአካባቢው ጦርነት ተቀስቅሶ እንደሆነ ‹‹እንዲህ ያለኸው፣ እንዲህ የሆንከው ጦርነት ከአካባቢው ጥፋ በል!›› እያለ ቢታናቹ ይመራዋል። ይወተውተዋል።

*‹‹ኣባካ፣ ኣኪንካ ኒንካ ጆሪሃ ኢተይ ወጋ››* *(የአባታችን፣ የአያታችን የቤተሰቦቻችን ካልሆንክ)*

*‹‹ዲሪም! ዲሪም!* ( ጥፋ ጥፋ! )

*ሁራ ጋል! ኣርባ ጋል!* ( ሁራ ግባ አርባ ግባ )[64]

*የሬው! የሬው!...››* ይላል እንጂ፣ ባለጋኑ ግን ብዙውን ጊዜ ቢታናቹ በል ያለውን ሁሉ አይልም። ‹‹ይፍለጥህ! ይቁረጥህ! ወዘተ.›› አይልም። እንዲህ ሲልም *ቃራ* የሚባለውን ጦር፣ ጦርነቱ ወይም የሚወገዘው ነገር ወዳለበት አቅጣጫ ቀስሮ ይይዘዋል። እንዲህ አይነቱ ቃል (ቃሉ አዎንታዊም አሉታዊም ሊሆን ይችላል) ባለጋን ከሆነ ሰው አንደበት ቶሎ አይወጣም። ከወጣ ደግሞ ከመሬት ጠብ አይልም። ሁሉም ነገር ወዲያውኑ፣ እሱ እንዳለው ይሆናል ተብሎ ይታመናል። ይህ ማለት ክስተቱ ጦርነት ከሆነ፣ ባለጋኑ ወጥቶ ካወገዘው በኋላ አይኖርም፤ አንበጣውም ቢሆን ከአካባቢው ይጠፋል።

---


[64] የአማርኛው ትርጉሙ (ትርጉሞቹ ብል ይሻላል) ትክክል ስለመሆናቸው እርግጠኛ አይደለሁም። ትንሽ ይቀራረቡ እንደሆን እንጂ አቻ ይሆናሉ የሚል እምነትም የለኝም። ለምን? በሁለት ምክንያቶች። አንደኛው፣ ቡርጂኛው አፌን የፈታሁበት ቋንቋ ቢሆንም ስላልገባኝ ትርጉማቸውን እንዲነግረኝ መረጃ ሰጪውን፣ ራሱን ጠይቄው ነበር። እሱም ምን ማለት እንደሆነ ቡርጂኛውን በሌላ ቡርጂኛ ፈቶ ነግሮኛል። ይህም አልገባኝም። ሁለተኛው ትርጉማቸውን የሚያውቅ ሌላ ሰው በመታጣቱ ነው (እኔ ከጠየኳቸው መካከል ማለቴ እንጂ የሚያውቅ ጨርሶ የለም ማለቴ እንዳልሆነ ልብ ይሏል) ሌሎችን ጠይቃቸው እነርሱም አያውቁትም። ቢያውቁትም ለእኔ በሚገባኝ ቋንቋ ማስረዳት አልቻሉም። ወይ ደግሞ እኔ ልረዳቸው አልቻልኩም።

*ቢታናች ከባለጋኑ* ዘንድ ሄዶ ለህዝቡ ምርቃት፣ በረከት የሚቀበል ሹም ነው። የህዝቡ አዝመራ ደርሶ ከመበላቱ ወይም ከመታጨዱ በፊት ከባለጋን ዘንድ ወስዶ እንዲባርክላቸው ማድረግ የቢታናች ሌላው ተግባር ነው። ሰብል ደርሶ ከመታጨዱ፣ ከመበላቱ በፊት ቢታናቹ በየአካባቢው እየዞረ ከደረሰው ሰብል ከየዓይነቱ፣ በኩር በኩሩን ትንሽ በትንሹ ይሰበስባል። የሰበሰበውን ይዞ ከኣላልች ዘንድ ይመጣል። ከኣላልች ጋር በመሆን፣ ሰብሉን ይዞ *ከባለጋኑ* ዘንድ ይሄዳል። *ባለጋኑም* ሰብሉን ከባረከ በኋላ ህዝቡ እንዲበላ፣ አጭዶ እንዲያስገባ ያደርጋል።

ከፍ ሲል፣ *ባለጋን* ከቤቱ ቁጭ ብሎ ከመመረቅ፣ ቡራኬ ከመስጠት፣ ለህዝቡ ከመፀለይ በስተቀር ሌላ *ሥራ* እንደማይሰራ፣ የእሱን *ሥራ* (እርሻውን የሚያርስለት፣ ሰብሉን የሚያጭድለት፣ ወዘተ.) የሚሰራለት ሕዝቡ እንደሆነ ነግረናል። ለዚህ *ሥራ* ሕዝቡን የሚጠራው ደግሞ *ቢታናች* ነው። እንዲሁም፣ በዓመት አንድ ጊዜ ለሚፈፀመው *ለሐጣና ሥርዓት* ማስፈጸሚያ የሚሆን እንስሳ ከህዝቡ ያፈላልጋል። ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ *በኣንሽ* አማካይነት ከከፍተኛው የህዝብ ሸንጎ ፊት ቀርቦ ውሳኔ ያገኘውን *የባለጋኑን* ጉዳይ ወይም የተሰጠውን ውሳኔ ወስዶ፣ *ለባለጋኑ* የሚያሣውቀው፣የሚነግረው እሱ ነው።

*የቢታናች* ተግባር ይህ ብቻ አይደለም። በባህላዊ የፖለቲካ ተቋማት ውስጥ የሚመደቡ ከፍተኛ ባለስልጣናትን የሚመርጠው፣ የሚመለምለው *ቢታናች* የሆነ ሰው ነው። በእሱ ተመልምለውና ተመርጠው *ሥልጣኑ በጎርሶማው* የፀደቀላቸውን ባለሥልጣናት ቅቤ ቀብቷቸውና መርቋቸው ለባሻ *ሥርዓት* ወደ ሱቡሮ የሚሸኛቸው ቢታናች እንጂ ማንም አይደለም። ዳይና ሆኖ የሚሾም ሰው ከቤቱ ደጃፍ ላይ ፍየል አርዶ ወይም በጦር ወግቶ፣ ደሙን ለወማ ሊወስድለት እንደሚገባ ከፍ ተብሎ ተጠቅሷል። በዚህ መልክ የታረደውን፣ የፍየሉን ደም በእንስት ቅጠል አቃፊ (በቡርጂኛ *ጉርባ* ይባላል) ጫፍ አጣቅሶ በመያዝ ለወማው የሚወስድለት ዳይናው ሳይሆን *ቢታናች* የሆነ ሰው ነው።

*የቢታናች* ተግባር እንዲህ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም። በቡርጂ መንፈሳዊና ፖለቲካዊ ተቋማት ውስጥ ቁልፍ ሰው በመሆኑ፣ ተግባራቱም በርካታ ናቸው። ሁለቱ ከፍተኛ ተቋማት ማለትም፣ ባህላዊ የአስተዳደርና የእምነት ተቋማት የሚገናኙት በቢታናች አማካይነት ነው። ሁለቱም ተቋማት አንዳቸው በሌላው *ሥራ* ጣልቃ አይገቡም። በባለስልጣናት ደረጃም፣ ፊት ለፊት፣ በቀጥታ አይገናኙም። የሚያገናኛቸው *ቢታናች* ነው። በሁለቱ ተቋማት መካከል የተዘረጋ ድልድይ ነው - *ቢታናች* ማለት። ይህን ሁሉ በሚከተለው *ሥዕላዊ* መግለጫ ማሳየት ይቻላል።




ሥዕል ቁጥር 6፣ የቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካና የእምነት ተቋማት የግንኙነትና የአሰራር ሥርዓት

### 5.3.3 የኣላልች አመዳደብና ተግባር

*ኣላልች፣* በቡርጂ የእምነት ተቋም ውስጥ ተመድቦ የሚሰራ ሶስተኛው ባለስልጣን ነው። ይህ ባለስልጣን በሁሉም የቡርጂ አካባቢዎች ባሉት የእምነት ተቋማት ውስጥ አይመደብም። Amborn and Kellner (1999, 90) በ1955 እና በ1973/74 በ*Straube* አማካይነት ከመስክ የተሰበሰበውን መረጃ ጠቅሰው እንደፃፉት *የያብ፣ የቀዳደ፣ የኣናቡራ፣ የጋማዮና የካራማ* ጎሳዎች በጋራ አንድ ኣላልች እንዳላቸው የሥልጣን ዘመኑም ስድስት ዓመት ሲሆን በየስድስት ዓመቱ፣ አንድ አንድ ኣላልች ከየጎሳው እየተመረጠ እንደሚመደብ ጽፈዋል።

*ኣላልች የጋንን* እምነታዊ ሥርዓቶችንና ደንቦችን ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ የሚያራምድ፣ የሚያስፈጽም ሹም ነው። የተዛቡ እምነታዊ ደንቦችና ልማዶች እንዲቃኑ ያደርጋል። ከፍ ሲል

እንደተመለከተው አዲስ *ቢታናች* እንዲመድብ ለተረኛው *ጎሳ መሪ ያሳውቃል*። ሲመደብም ወስዶ *ለባለጋት* ይሰጣል። *ከቢታናች ጋር* በመሆን አዲስ *ለሚሰየመው ባለጋን* ሚስት የሚትሆን ልጃገረድ መርጦና ይዞ *ያመጣል*። *በባለጋት* የምርቃትና የቡራኬ *ሥርዓት* ላይ *ከቢታናች ጋር* በመሣተፍ ለህዝቡ ምርቃት ይቀበላል። *በባለጋን* እና በህዝቡ መካከል የሚፈጠሩ ችግሮችን ወይም አለመግባባቶችን *ከቢታናች ጋር* በመሆን *ያረጋጋል*። ይፈታል። ወይም የሚፈቱበትን መንገድ *ያመቻቻል*። *ለባለጋን* ከህዝብ የሚመጡ (እንደ ወተትና ቦርዴ የመሳሰሉ) ስጦታዎችን እየተቀበለ *ለባለጋት* መስጠት *የኣላልቻ* ሌላው ተግባር ነው። በአጭሩ፣ *ኣላልችና ቢታናች* በቡርጂ የእምነት ተቋም ውስጥ በተመሣሣይ መንገድና መመዘኛ ተመርጠው የሚመደቡ፣ ተመሣሣይ ተግባር የሚፈጽሙ ባለስልጣናት ናቸው።

## 5.4 ከባህላዊ አስተዳደር ጋር ተያይዘው የሚፈፀሙ እምነታዊ ድርጊቶችና የአፈፃፀም ሥርዓታቸው

ከፍ ባሉት ምዕራፎች ላይ እንደጠቀስነው፣ እንደ አብዛኞቹ የአፍሪካ ህዝቦች ሁሉ የቡርጂዎች ባህላዊ አስተዳደርና እምነት፣ ሁልጊዜ አንዱ በአንዱ ውስጥ ሆነው፣ ተደጋግፈው የሚኖሩ ናቸው። አንዱ ያለ ሌላው ማህበራዊ ፋይዳ ወይም ህልውና ሊኖረው አይችልም። አስተዳደራዊ ሥራዎች እምነታዊ ሥርዓቶች በሌሉበት አይፈጸሙም። አይጀመሩምም። ባህላዊ የፖለቲካ መሪዎች ሥራቸውን የሚጀምሩት፣ ስብሰባ የሚከፍቱት፣ *ሓሣዬ* በሚባለው በምርቃት፣ በቡራኬና በፀሎት ባህላዊ ሥርዓት ነው። *የጋንን* እምነት የሚራምዱት፣ ዋነኛ ተግባራቸው ህዝቡን መመረቅ፣ መባረክና ለህዝቡ መፀለይ የሆናቸው *ባለጋኖችም* ቢሆኑ፣ ይህንን የሚያከናውኑት፣ በባህላዊ የአስተዳደር መሪዎች ሲጠየቁ ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ ግን ከቤታቸው ነው ቁጭ የሚሉት። በአጭሩ የቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደርና የእምነት ሥርዓቶች ሁልጊዜ አብረው የሚሄዱ፣ የማይለያዩ ናቸው። አንዱ በሌለበት ሌላኛው ተግባራዊ አይሆንም። ቢሆንም ተከታይ አይኖረውም። እድሜው አጭር ይሆናል። ሁለቱም ባህላዊ ሥርዓቶች ከትናንት እስከ ዛሬ ሣይጠፉ ሕያው ሆነው ከዚህ ሊደርሱ የቻሉትም የሚደጋገፉ በመሆናቸው ነው። እያንዳንዱ ፖለቲካዊ ተግባር በእምነታዊ ድርጊቶች የታጀበ፣ የደመቀ ነው። እያንዳንዱ እምነታዊ ሥርዓትም እንዲሁ በፖለቲካ ተግባራትና መሪዎች የታጀበ ነው። የዚህ ክፍል ዋነኛው ትኩረትም ከቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካ ሥርዓቶች ጋር ተያይዘው የሚፈፀሙና *ሒጣኖ፣ ጎዴ፣ ቦርቶማ* እና ሞጨ የሚባሉ እምነታዊ ድርጊቶችን ከነአፈፃፀማቸው ማቅረብና ማሳየት ነው።

### 5.4.1. ሒጣኖ

ሒጣኖ፣ የቡርጂ ህዝቦች ቦርዴን ወይም የእንስሳትን (የኮርማ በሬን ወይም የፍዬልን) ደም ወይም ትኩስ የላም ወተትን፣ ሦስቱን ወይም ሁሉቱን ወይም አንዱን ብቻ በኤሣ በባልበላ (በጽህፈት ቤት) ወይም በስራ ቦታ ላይ በመርጨት ለሚፈፅሚቸው የእምነት ሥርዓቶች የተሰጠ የጥቅል ስም ነው[65] ። በሌላ አገላለፅ ሒጣኖ፣ ቡርጂዎች ‹‹ከፈጣሪ ጋር ያገናኙናል፣ ፈጣሪን ያማልዱልናል›› ብለው ለሚያምኗቸው ለሙታን ወገኖቻቸው *(Ancestral worship)* በአመት አንድ ጊዜ የሚያቀርቡት የመስዋዕት ሥርዓት ነው።

ቡርጂዎች ዱርጋ *(duurga)* በሚሏቸው፣ በሙታን ወገኖቻቸው ያምናሉ። ጎመስ *(goomes)* ደግሞ የሙታን መናፍስት የሚጠሩበት ስም ነው። የእያንዳንዱ ጎሣ፣ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ዕጣ ፋንታ የተመሠረተው በሙታን ወገኖቻቸው መልካም ፈቃድ እንደሆነ ተደርጎ ይታመናል። የዘሩት የሚበቅልልላቸው፣ በቅሎ የሚያፈራላቸው፣ ወዘተ ከሟች አባቶቻቸው፣ አያት ቅድመ አያቶቻቸው ቡራኬና ምርቃት ሲያገኙ ብቻ ነው። ከሙታን ወገኖቻቸው ምርቃትና ቡራኬ የሚያገኙት ደግሞ በዘመኑ ሰርተው ካገኙት፣ ‹‹የበኩሩን›› ለሙታን ወገኖቻቸው በመስጠት፣ ሒጣኖ የሚባለውን እምነታዊ ሥርዓት የፈፀሙ እንደሆነ ብቻ ነው።

ይህ የሒጣኖ ሥርዓት በአብዛኛው በጎሣ ደረጃ ይፈፀማል። ከዚህ ሌላ በአንድ አካባቢ (በኦላ፣ በገሪኤ፣ በቦሄ፣ ወዘተ.) በሚኖሩ፣ ነገር ግን በስጋና በደም በማይገናኙ ህዝቦች አማካይነትም ይፈፀማል። በባሻ ሥርዓት ላይም ሒጣኖ ተግባራዊ ይደረጋል። በሌላ ቦታም እንዲሁ ሊፈፀም

---

[65] እነ አምቦር (1999) ሒጣኖ፣ ቡርጂዎች ቦርዴ፣ ትኩስ ወተትና የእንስሳት ደም በአንድነት በመቀላቀል በሰው ወይም በዕቃ ላይ በመርጨት ለሚፈፅሚቸው አጠቃላይ እምነታዊ ሥርዓቶች የተሰጠ ጥቅል ስም ነው ይላሉ(አፅንኦቱ የራሴ ነው)። ከእነዚህ አባባሎች መካከል ‹‹ሥርዓቱ እምነታዊ ነው›› የሚለው ያስማማኛል። በሥርዓቱ ላይ ቦርዴ፣ ትኩስ ወተት እና ደም የሚቀርቡ መሆናቸውም እንዲሁ የምስማማበት ነጥብ ነው። ነገር ግን የሶስቱም በአንድ ጊዜ መቅረብ የግድ አይደለም። በቦርዴ ብቻ የሒጣኖ ሥርዓቱን መፈፀም ይቻላል። እንስሳ አርዶ በእንስሳት ደም ብቻ ሥርዓቱን ማከናወንም እንዲሁ ይቻላል። ትኩስ ወተት ግን በሁሉም አካባቢ ህዝቦች (ቡርጂዎች) ዘንድ እምብዛም የተለመደ አይደለም። ለሥርዐቱ ሲል ፍየል ወይም በሬ የሚያርደው ያለው ሰው፣ ያለው ቤተሰብ ነው። የሌለው በቦርዴ ብቻ ሥርዓቱን መፈፀም ይችላል። እርድም የግድ አይደለም። ቦርዴ መጥመቅም ቢሆን እንዲሁ የግድ የማይሆንበት ሁኔታ አለ። ቦርዴ መጥመቅ ያልቻለ ቤተሰብ ብቅል ፈጭቶ፣ ዱቄቱን በውሃ በጥብጦ በመርጨት የሒጣኖን ሥርዓት መፈፀም እንደሚችል አንዳንድ መረጃ ሰጪዎች (ቡኬ፣ 45፤ ቱኬ፣ 2002፣ 56) ይናገራሉ። ከነ አንቦር ሀሳብ የማያስማማኝ አንዱ ነጥብ ይህ ነው፣ ለሒጣኖ ሥርዓት ቦርዴ፣ ደምና ትኩስ ወተት፣ ሶስቱም የግድ ሊኖሩ የሚገቡ ናቸው የሚለው። የማያስማማኝ ሁለተኛው ሀሳብ፣ እነዚህ ሦስቱም (ቦርዴ፣ ደምና ወተት) በአንድነት ይቀላቀላሉ የሚለው ነው። እኔ ግን ይህ በሁሉም የቡርጂ ህዝቦች ዘንድ የተለመደ አሠራር ነው የሚል እምነት የለኝም። ነገር ግን ፈፅሞ አይቀላቀሉም ብዬ መከራከር አልችልም። እንደሚቀላቀሉ የነገረኝ መረጃ ሰጪ (አደን፣ 2002፣ 21) ስላለ ማለት ነው። የእኔ ሙግት አንድም፣ መቀላቀል የግድ አይደለም የሚል ነው። መቀላቀልም ቢሆን በተወሰኑ የቡርጂ ህዝቦች ዘንድ እንጂ በሁሉም የቡርጂ ህዝቦች ዘንድ የተለመደ አይደለም የሚል ነው። ተቀላቅለው ሲረጩም አላየሁም። አብዛኞቹ መረጃ ሰጪዎቼም ይህን አልነገሩኝም። ከፀሀፊዎቹ ጋር የማያስማማኝ ሶስተኛው ነጥብ ደግሞ፣ እነዚህ ሶስቱ ‹‹በሰው ወይም በዕቃ ላይ ይረጫሉ›› የሚለው ነው። በአነርሱ እምነት የሒጣኖ ሥርዓት፣ ቦርዴን ደምንና ወተትን ቀላቅሎ፣ በሰው ወይም በዕቃ ላይ በመርጨት የሚፈፀም ሥርዓት ነው። ፀሐፊዎቹን የሒጣኖና የሞጩ እምነታዊ ስርዓቶች የተቀላቀሉባቸው ይመስለኛል። የአንዱን የአፈፃፀም ስርአት ከሌላው መለየት የቻሉ አይመስለኝም። በመሰረቱ የሚረጨው ከተጠቀሱት ከሶስቱ አንዳቸውም ባይሆኑም፣ ውሃን በእቃ ወይም በሰው ላይ በመርጨት የሚፈፀም የቡርጂዎች እምነታዊ ስርአት ሞጩ እንጂ ሒጣኖ አይደለም። የሒጣኖ ሥርአት ቦርዴም ሆነ ደም በተለይ በኤሣ ላይ በመርጨት የሚፈፀም ስርአት ነው። ከዚህ ውጭ በሰው ላይም ሆነ በዕቃ ላይ አይረጭም። መጀመሪያ በኤሳው ቀጥሎ በግቢው ግራና ቀኝ ይረጫል። ከዚህ በተለይ፣ የእንስሳውን ደም ሹመኞች ወይም ህዝቡ ከግንባራቸው ላይ ይይዛሉ። ወይም ይቀባሉ። ከዚህ ውጭ ደሙም ሆነ ቦርዴው በሰው ላይ የሚረጭ አይመስለኝም - ይህንን ከግንባራቸው የሚያዘውን ደም ከሰው ላይ ይረጫል ብለው እንደሆን ብዬ ነው።

ይችላል፡፡ ያም ሆነ ይህ፣ በሁሉም ደረጃና አካባቢ፣ የሒጣኖ ሥርዓት የሚፈፀመው በአመት አንድ ጊዜ፣ በወርሃ ዶጎሌ (በየካቲት ወር) ውስጥ ነው፡፡

*ሒጣኖ* በጎሣ ደረጃ፣ በአመት አንድ ጊዜ ይፈፀማል ብለናል፡፡ *ሥርዓቱ* በዚህ ደረጃ የሚከናወነው፣ ሁሉም የጎሳው አባላት በተገኙበት፣ በጎሳ መሪው ቅጥር ግቢ ውስጥ ይሆናል፡፡ ይህ፣ የሒጣኖ ሥርዓት የሚፈፀምበት የጎሣ መሪው ግቢም *ሓላሲንታ ካራ* በመባል ይታወቃል፡፡ ‹‹የተቀደሰ፣ የተባረከ ደጅ ወይም ግቢ›› ማለት ነው፡፡ አፈፃፀሙም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ወቅቱ ሲደርስ የጎሳ መሪው ከቤቱ ቦርዴ አስጠምቆ፣ የእርድ በሬ ወይም ፍየል አዘጋጅቶ የጎሳውን አባላት ይጠራል፡፡ የጎሳው አባላትም ከቤታቸው ቦርዴ በቅል *(ጉሱማ)* ይዘው በመምጣት ከጎሳ መሪው ቤት ይሰበሰባሉ፡፡ ያመጡት ቦርዴም ከጎሳ መሪው ቤት ከተጠመቀው ጋር ይቀላቀላል[66]፡፡ ለሥርዓቱ ማስፈፀሚያ የሚሆን ከአናቱ ተወስዶ ይቀመጣል፡፡ እምነታዊ ሥርዓቱ ሳይፈፀም መብላትም ሆነ መጠጣት አይፈቀድም፡፡

ሥርዓቱ የሚጀመረው በጎሳ መሪው አማካይነት ነው፡፡ በሥርዓቱ ላይም ቦርዴ፣ *ካሾ* ወይም *ሒጣኒታ ቆሬ* የሚባል (ለዚህ ተግባር ብቻ የሚያገለግል) ገበቴ፣ ለመርጨያነት ደግሞ በቡርጂኛ *ባኒዔይሸ* (በአማርኛ ምን እንደሚባል አላውቅም) የሚባል ቅጠል ይቀርባል፡፡ የግድ ባይሆንም ኮርማ በሬ ወይም ፍየል ይዘጋጃል፡፡ እነዚህ ከቀረቡ በኋላ የጎሳ መሪው ሚስት ቀደም ሲል በቅል የተቀመጠውን ቦርዴ አምጥታ ለባሏ ትሰጠዋለች፡፡ እሱም ይቀበላትና ወደ *ሒጣኒታ ቆሬ* (ወደ ገበቴው) ይገለብጠዋል፡፡ ሚስትም ወደ ገበቴ የተገለበጠውን ቦርዴ አንስታ በመያዝ ከጐሣ መሪው ፊት ትቆማለች፡፡

የጎሳው መሪም ቦርዴውን *በባኒዓይሸ* ቅጠል እያጣቀሰ ወይም በእጆቹ እያፈሰ መጀመሪያ ከደጁ ካለው *ኤሳ* ላይ በመርጨት *የሒጣኖን* (ለሙታን ወገኖቹ የመስጠቱን) ሥርዓት ይጀምራል፡፡ ቦርዴውን በሚረጭበት ወቅትም፣

---

[66] ከዚህ በተለየ መንገድ የመቀላቀሉ ስርዓት የሚፈፀምበት ሁኔታም አለ፡፡ ወቅቱ ከመድረሱ ቀደም ብለው የጎሳው አባላት ከቤታቸው ትንሽ ስንዴ፤ ዘንጋዳና ገብስ የመሳሰሉ የእህል ዓይነቶችን ይዘው ከጎሳ መሪያቸው ቤት ይመጣሉ፡፡ ሁሉም ያመጣው እህል ከጎሳ መሪው ቤት ወለል ላይ በአንድ ላይ ይቀላቀላል፡፡ ለወደፊቱ ለሒጣኖ ስርዐት የሚሆነው ቦርዴም የሚጠመቀው፣ በዚህ ዓይነት አንድ ላይ በተቀላቀለው እህል ይሆናል፡፡ የተጠመቀውን ቦርዴን ብቻ ሣይሆን ለቦርዴ መጥመቂያነት የሚሆኑ የእህል ዘሮችንም መቀላቀልና በእሱ ለሥርዐቱ የሚሆን ቦርዴ መጥመቅም ይቻላል ማለት ነው፡፡

*ዎ ኣቦ! ዎ ኣኮ!* *( አባቴ! አያቴ)*
*ዎ ሜኢሃና! ዎ ሜይሲሃና!* *(ቅድም አያቴ! ምንጂላቴ!)*
*ዎ ዱራካኖ! ዎ ዱራናካኖ!* *(የጥንቱ! የጥንት ጥንቱ (ፊተኛው የፊት ፊተኛው)*
*ኒንካ ጆሮ! ዱራካኖ! ዱራናካኖ!* *( የእኛ ቤተሰቦች! የፊተኞቹ! ቀዳሚዎቹ!)*
*ኦኒ ኢተይ! ዱጊይ!* *(ይኼውላችሁ ብሉ! ጠጡ!)*
*ዎ ኢት ኢያ ኣቦ! ኢያ ኣኮ!* *( አባቴ! አያቴ ብላ!)*
*ኒንካ ጆሮ! ዱራካኖ! ዱራናካኖ!* *(የእኛ ቤተሰቦች! የፊቶቹ! ፊተኞቹ!)*
*ወይዳ ጆሮ! ኒንካኖ!* *( የእኛ የጥንት ቤተሰቦች!)*
*ኦኒ እሺ ዱግ!* *(ይሄው በልተህ ጠጣ)!*
*ኦኒን ኣንጋላኖ ባስ አሺን ኣኒጋላን!* *( እኔ ያገኘሁትን ነገር አንተም አግኝ!)*
*ኒካ ጆሮ! ...ወዘተ* *( የእኛ ቤተሰቦች! ...ወዘተ )*

እያለ ከኤሳው ላይ ይረጫል፡፡ ለአያት፣ ለቅድማያቶቹ ይሰጣል፡፡ ቦርዴውን ሲረጭ ለጎሣው ሟች አባቶች፣ አያት ቅድምአያቶች፣ መስዋዕት አቀረበ፣ ሰጠ ማለት ነው፡፡ የጎሣው አባላት በዘመኑ ከአገኙት ሀብት፣ ከአፈሩት ንብረት የበኩሩን፣ ለጎሣው መገኘት መሰረት ለሆኑ ነገር ግን ጥንት ለሞቱት ወገኖቻቸው እንደሰጡ ይቆጠራል፡፡ በዘመናዊ ቋንቋ ‹‹አስራት›› መሆኑ ነው፡፡ በጥንቱ የቡርጂ እምነት መሰረት፣ የሟቾች መናፍስት (ጣዕረ ሙታን) በራባቸውና በጠማቸው ጊዜ፣ በአሳቻ ሰዓት ከጎሳው መሪ ቤት ይመጣሉ፡፡ መጥተው፣ እንዲህ በጎሳ መሪው የተሰጣቸውን (የተበተነላቸውን) በልተውና ጠጥተው፣ ጠግበውና ተደስተው፣ ጎሳውን መርቀው ይመለሳሉ፡፡ እንዲህ መጥተው አንዳች የሚላስ የሚቀመስ ነገር ያጡ እንደሆነ ደግሞ አዝነው፣ ተክዘው፣ ጎሳውን ረግመው ይመለሳሉ፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ የጎሳውን አባላት ክፉ ያገኛቸዋል፣ መከራ ይወርድባቸዋል፣ ሞት ይዘምትባቸዋል ተብሎ ይታመናል፡፡

በቡርጂዎች እምነት እንዲህ ሲርባቸውም ሆነ ሲጠማቸው ከጎሳ መሪው ቤት የሚመጡት የሙት መናፍስት የጎሣው ብቻ አይደሉም፡፡ የአጎራባች ቤተሰቦች የሙት መናፍስትም ጭምር ይመጣሉ፡፡ መጥተው የሚበላ፣ የሚጠጣ ይፈልጋሉ፡፡ ካገኙ መርቀው፣ ካጡ ተራግመው ይሄዳሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ የጎሳው መሪም እነዚህም መጥተው እንዳያጡ፣ አጥተው ጎሣውን እንዳይራገሙ ሲል ከቤቱ ግራና ቀኝ ዞሮ፡-

*ዎ ኦሌይሃኖ ! ሂነይካ የቶሃኖ !* *(ጎረቤቴ ! ከታች በኩል ያለኸው !)*
*ሆጎለይካ የቶሃኖ !* *( ከላይ በኩል ያለኸው ! )*
*ኣሸን ኦላና ! ኦሌይሁን ኢት ! ዱግ !* *( አንተም ጎረቤት ነህና ! ከጎረቤትህ ጋር ብላ ! ጠጣ !)*

እያለ የያዘውን ይረጫል፡፡ ለእነርሱም ይሰጣቸዋል፡፡ መስጠቱ በዚህ ብቻ አያበቃም፡፡ ቡርጂዎች፣ በማንኛውም ጊዜ የሟች ወገኖቻቸውን መናፍስት ተከትለው የሚመጡ፣ ሌሎች መናፍስትም እንዳሉ ያምናሉ፡፡ እነዚህም፣ እንዲህ ደግሰው ማብላት ማጠጣት ከማይችሉ፣ ከደሃው ጎሳ

(ቤተሰብ) ወገን የሆኑ፣ የተራቡ የተጠሙ፣ ጣዕረ ሙታን ናቸው። የሚመጡት ደግሞ ሣይታዩ በጓሮ በኩል ተደብቀው ነው ይባላል። በመሆኑም የጎሳ መሪው ለወገኖቹ እና ለጎረቤቶቹ ሲሰጥ እነዚህንም ያስባቸዋል። ለእነሱም ሊሰጣቸው እንደገና ወደጓሮው ይዞራል። ከቤቱ ጀርባ ዞሮ፡-

| | |
|---|---|
| *ቃሬይ ኢንተይታ ሜኖ !* | *(ተከትላችሁ የምትመጡ)* |
| *ኣሸን ኢት ! ዱግ !* | *(አንተም ብላ ! ጠጣ !)* |
| *ላስ፣ደቦች ኢንተይሼቶ ወጋ !* | *(እርቦህ፣ ጠምቶህ መጥተህ እንደሆነ !)* |
| *ጎንቱ ኢንተይሼቶ ወጋ !* | *(ለእርግማን መጥተህ እንደሆነ !)* |
| *ኦኒ ! ኣሸን ኢት ! ዱግ !* | *(ይሄውልህ ! አንተም ብላ ! ጠጣ !)* |
| *ኦኒ ! ኣሸን ፉሬይሽ ጋል !* | *(ይሄውልህ ! አንተም ጠግበህ ግባ !)* |

እያለ ያዘጋጀውን ይረጫል። ሰጪ፣ ቀላቢ ለሌላቸው፣ ተርበው፣ ተጠምተው ለሚመጡ ለሙታን መናፍስት ይሰጣል። በዚህም የሥርዓቱ ፍፃሜ ይሆናል። ፍየል ወይም በሬ (ኮርማ) ታርዶ ከሆነም ሥርዓቱ የሚፈፀመው በተመሳሳይ ሁኔታ የእንስሳቱን ደም በመርጨት ነው። ልዩነት ቢኖር፣ ሁሉም የጎሳው አባላት ደሙን ከግንባራቸው ላይ የሚቀቡ (የሚይዙ) መሆናቸው ብቻ ነው። ከሥርዓቱ ፍፃሜ በኋላ ለክብረ በዓሉ የተዘጋጀው ምግብና መጠጥ ቀርቦ ይበላል። ይጠጣል። እርድ ካለ ግማሹ ለጎሳ መሪው ተትቶ ግማሹ በአባላቱ ተጠብሶ ይበላል። ወይም ለሁሉም እኩል ይከፋፈላል። እንዲህ ሲበሉ ሲጠጡ አድረው፣ በማግስቱ መጪውን ዘመን የሠላም፣ የብልጽግናና የፍቅር እንዲያደርግላቸው አያት ቅድም አያቶቻቸውንና አምላካቸውን ለማምነው *ወንቶ ኒንሣ ጣዳላያ ናቱራ ጎቶ* (እግዚአብሔር እኛን በሰቢላና ጤናዳም ያድርገን) ተባብለውና ተመራርቀው ይለያያሉ።

ከፍ ብለን እንደጠቀስነው፣ *ሒጣኖ* የሚፈፀመው የአዝመራ ወቅት ሲቃረብ ነው። በመሆኑ፣ ሥርዓቱ ሣይፈፀም ማንም ወደ እርሻው አይሄድም። ሄዶ አይዘራም። ከመዝራቱ በፊት ለሟች ወገኖቹ መስዋዕት ማቅረብ፣ መጪው ዘመን የሠላም፣ የብልጽግና እንድሆንለት መለመን ይኖርበታል። የጎሳው አባላት ወደ ማሳቸው የሚሄዱት፣ ሄደው የሚዘሩት ክብረ በዓሉ ከተጠናቀቀ፣ ከሦስት ቀናት በኋላ ነው።

*በሒጣኖ* እምነታዊ ሥርዓት ላይ የማይሳተፍ የጎሳ አባል አይኖርም። ከአቅም በላይ በሆነ ችግር (ለምሳሌ በበሽታ ምክንያት) በክብረ በዓሉ ላይ ያልተገኘ አባል ሲኖር ለሥርዓቱ ሲባል የታረደው እንስሳ ደም እስከ ቤቱ ድረስ ይወሰድለታል። ደሙንም እንደለሎቹ ከግንባሩ ላይ እንድይዝ ይደረጋል። በዚህ እምነታዊ ሥርዓት ላይ የማይገኝ፣ በተለይም ደሙን ከግንባሩ የማይዝ (የማይቀባ) የጎሳው አባል ቢኖር ‹‹*ሙልቃ ጉያ*›› ብለው ቡርጂዎች ያምናሉ። ‹ክፉ ያገኘዋል፣ መከራና ስቃይ ይፈራረቁበታል፣ በመጨረሻም ይሞታል›› ማለት ነው።

ይህ እምነታዊ ሥርዓት በኦላ፣ በገሬሌ፣ በቦሄ...ወዘተ ደረጃ በሚኖሩ ሕዝቦች አማካይነትም ይፈፀማል፡፡ ልዩነቱ የክብረ በዓሉ ታዳሚዎች የአንድ ጎሳ አባላት አለመሆናቸው ብቻ ነው፡፡ ለሁሉም የቡርጂ ህዝቦች ሲሆን ሥርዓቱ በወሚንካ ባልባላ ውስጥ የአካባቢው ሕዝብና ሹማምንት በተገኙበት በወማው አማካይነት ይፈፀማል፡፡ ለቦሄው ነዋሪዎች ሲሆን ደግሞ ሥርዓቱ የቦሄ ነዋሪዎች በተገኙበት በቦሄንካ ባልባላ ውስጥ በማሻው አማካይነት ይፈፀማል፡፡ ከዚህም ሌላ ሐጣኖ፣ በባሻ ሥርዓት ላይም፣ በተመሣሣይ ሁኔታ፣ ቦርዴን ወይም የእንስሳትን ደም ከኤሳው ላይ በመርጨትና ደሙን ከግንባር ላይ በመቀባት (በመያዝ) ይፈፀማል (ክፍል 4.3.4ተመልከት)፡፡

### 5.4.2 ጎዴ

ጎዴ ከቡርጂ ባህላዊ አስተዳደር ጋር ተያይዞ የሚፈፀም ሌላው የእምነት ሥርዓት ነው፡፡ ግልፅ ባለ አነጋገር ጎዴ ቡርጂዎች ከራሳቸው ላይ ክፉ ነገሮችን ለመከላከል፣ በሌላው ወገን ላይ ክፉ ነገሮች እንዲደርሱ ለማድረግ ሲሉ የሚፈጽሙት የመተት እምነታዊ ሥርዓት ነው፡፡

ጎዴ በሁለት መልክ ይፈፀማል፡፡ አንደኛው በግለሰብ ደረጃ የሚፈፀመውም ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በቡድን ወይም በህብረተሰብ ደረጃ ይፈጸማል፡፡ በግለሰብ ደረጃ የሚፈፀመው ጎዴ፣ አንዱ ግለሰብ ሌላውን ግለሰብ ለማጥቃት ወይም በሌላው ግለሰብ ላይ ክፉ እንዲደርስ ለማድረግ ሲል የሚፈጽመው የመተት ሥርዓት ነው፡፡ ይህን በሚመለከት ‹‹በእውነት ተፈፅሟል›› ተባለውን አንድ ምሳሌ እንመልከት፡፡

> በድሮ ጊዜ ነው አሉ፡፡ አቶ ህርቦ የሚባል ሰው ነበረ፡፡ አንዲት የሚትታለብ ላም ከነጥጃዋ፣ ቦዳ በሚባል ሰው አለአግባብ ይወሰድበታል፡፡ በዚህ የተነሣ ቦዳን ሊበቀለው ፈለገ፡፡ ከጠንቋይ ዘንድ ሄደ፡፡ ቦዳ ያደረሰበትን በደል ዘርዝሮ ለጠንቋዩ ነገረው፡፡ ፍላጎቱ ላሚቷ ከነጥጃዋ ሞታ ማየት እንደሆነም አስረዳ፡፡ በመጨረሻም ምን ቢያደርግ ምኞቱ እንደሚሣካለት ጠየቀው፡፡ ጠንቋዩም ‹‹ከተወሰደችብህ ላም ጭራ ላይ የተወሰደውን ፀጉር፣ ከዱር ከመጣ የጅብ አይነምድር ጋር አድርገህ በጨርቅ፣ አንድ ላይ ቋጥራቸው፡፡ ማንም ሣያይህ፣ ቋጠሮውን ወስደህ ላሚቷ ከምታድርበት ስፍራ ላይ ጣለው፡፡ ይህንን በትክክል የፈፀምክ እንደሆነ፣ ከጥቂት ሣምንታት በኋላ ምኞትህ ተሳክቶልህ፣ ላሚቷ በጅብ ተበልታ ታያታለህ›› አለው፡፡ ህርቦም እንደተባለው አደረገ፡፡ ይህን ከፈፀመ ከወራት በኋላ፣ ላሚቷ ከዱር ሣር ሲትግጥ ከገደል ገብታ፣ ማታ የጅብ እራት መሆኗን ሰማ ይባላል (ጡኬ፣ 2002፣ 6)፡፡

በግለሰብ ደረጃ የሚፈፀም ጎዴ በቡርጂዎች ዘንድ እምብዛም የተለመደ አይደለም፡፡ በቡርጂ ህዝቦች ዘንድ የተለመደው፣ ከጥንት እስከ ዛሬም ሣያሰልስ ተግባራዊ እየሆነ ያለው በቡድን ወይም በህብረተሰብ ደረጃ የሚፈፀመው ጎዴ ነው፡፡ ይህም ቡርጂዎች በሚኖሩበት አካባቢ፣ ወደ ፊት ይደርሳል የተባለውን መጥፎ ክስተት (በሽታ፣ ጦርነት፣ ረሀብ፣ ወዘተ) አስቀድሞ ለመከላከል

ወይም የደረሰውን መጥፎ ክስተት ለማክሸፍ፣ ለማጥፋት ሲባል ይፈፀማል፡፡ በዚህ ደረጃ የሚፈፀመውን የጎዴን እምነታዊ ሥርዓት በዋናነት የሚያስፈፅሙት ባህላዊ የአስተዳደር መሪዎች (ኤላዎች) ናቸው (ክፍል 4.4. ተመልከት)፡፡

ጎዴ ጥንትም ሆነ ዛሬ የሚታመንበትና የሚፈፀምበት ዓላማ፣ ምክንያትና የአፈፃፀም ሥርዓቱ በአብዛኛው ተመሳሳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በጥንቱና በዛሬው የአፈፃፀም ሥርዓቶች መካከል አነስተኛ ልዩነቶች ይታያሉ፡፡

የመጀመሪያው ልዩነት የጊዜ ነው፡፡ በድሮ ጊዜ ጎዴ ይፈፀም የነበረው በዓመት አንድ ጊዜ፣ በቡርጂዎች አዲስ ዓመት መግቢያ (በጎዶሴ ወይም በየካቲት ወር) አካባቢ ነው፡፡ ከፍ ባሉት ክፍሎች እንደተመለከተው፣ በዚህ ወቅት መፈፀሙ በተያዘው አመት ውስጥ በአካባቢው ይከሰታሉ የተባሉት (ማለትም እንደ ጦርነት፣ በሽታ፣ ወረርሽኝ ወዘተ) ክፉ ነገሮች ከመድረሳቸው በፊት ለመከላከል ነው፡፡ በአጭሩ የጎዴ እምነታዊ ሥርዓት በአዲሱ ዓመት ዋዜማ ላይ መፈፀሙ፣ ዘመኑ የሠላም፣ የጤና፣ የፍቅር፣ የጥጋብ፣ የብልፅግና ወዘተ እንዲሆን ሲባል ነው፡፡ የአፈፃጸም ሥርዓቱም እንደሚከተለው ነው፡፡

ከፍ ተብሎ ስለ *ወማ*፣ ስለ *ዳይና* እና ስለ *ሃዩ* ሥልጣንና ተግባር በሚዘረዝረው ክፍል ሥር እንደተጠቀሰው አዲሱ ዘመን ሊገባ ሲቃረብ የወቅቱ *ዳይና ሃዩውን* አስጠርቶት፣ የቡርጂ እጣ ፋንታ በመጪው አዲስ ዘመን ምን ሊሆን እንደሚችል አስተንብዮ እንዲመጣ ወደ ኮንሶ ይልከዋል፡፡ ሃዩውም ኮንሶ ወዳሉትና ስለ ቡርጂ ይተነብያሉ ተብለው ከሚታመኑ *ጋዬካ ጀራ* (ከጋዬ ቤተሰቦች) ዘንድ ይሄዳል፡፡ በመጪው ዘመን በቡርጂ ህዝብና ሀገር ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ምን ምን ክፉ አጋጣሚዎች (ክስተቶች) እንደሚኖሩ ይጠይቃል፡፡ ተንባዮም የታየውን ይነግረዋል፡፡ ‹‹በዘመኑ በቡርጂ ህዝብና ሀገር ላይ የሚደርስ አንዳች መጥፎ ነገር የለም ወይም አይታየኝም›› ብሎ ሊነግረው ይችላል፡፡ ወይም የዚህን ተቃራኒ ሊነግረው ይችላል፡፡ በመጪው ዘመን የሚደርስ ክፉ ነገር አለ ካለ የመከላከያ መንገዱንም ጭምር ይጠቁማል፡፡

ብዙውን ጊዜ ግን ይደርሣል የተባለውን መጥፎ ክስተት ለመከላከል ሲባል ለሚፈፀመው ለጎዴ እምነታዊ ሥርዓት የሚመረጡት እንስሳት ናቸው፡፡ እንስሳቱ የቤት ወይም የዱር ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከቤት እንስሳት መካከል *ኣራሾ* (ሴት በግ) ወይም *ሱቤይንቾ* (ያልወለደች ሴት ፍየል) ተጠቃሾች ናቸው፡፡ መልካቸውም እንዲሁ ተለይቶ ይነገራል፡፡ *ሱቤይንቾ ቢያንታ ቢሻታ* (አፈርማ መልክ ያላት ሴት ፍዬል) ወይም ሌላም ሊባል ይችላል፡፡ *ቆኖሶ* እና *ዴጤ*

(በእንግሊዝኛው *hyrax* ይሉታል) ደግሞ ለጎዴ ተግባር ከሚፈለጉ ከዱር እንስሳት መካከል ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ተንባዩም እምነታዊ ሥርዓቱን ከእነዚህ እንስሳት በአንዱ እንዲፈጽሙ ሊመክራቸው ይችላል፡፡ ይህንን በተመለከተ፣ ጥንት ‹‹ተፈፀመ›› የተባለውን ጎዴ እንመልከት፡፡

> በድሮ ጊዜ ነው አሉ፡፡ ሃዩው ስለቡርጂ መጪ ሁኔታ ተንባዩን ጠየቀ፡፡ ተንባዩም ‹‹በመጪው ዘመን፣ የአንበጣ መልክ *(ዳሬይሽንታ ቢሻ)* ያላቸው ሁለት የቡርጂ ታላላቅ ሹማምንት በውጭ ጠላት ይገደላሉ፡፡ የእነርሱን ሞት ተከትሎ ቡርጂ በከባድ ድርቅ ትመታለች፡፡ በድርቁም ብዙ ህይወት ይጠፋል›› ይላል፡፡ በማከልም ‹‹ይህ እንዳይሆን እንዲህ አድርጉ፡፡ *ቆኖሶን* ያዟት፡፡ ይዛችሁ ግደሏት፡፡ ሁለት ዓይኖቿን አውጥታችሁ ድንበር አሻግራችሁ፣ ቅበሯት›› አለው፡፡ ሃዩውም ሲመለስ የተነገረውን ለዳይናው ነገረው፡፡ ዳይናው ጎርሶማውን ሰበሰበ፡፡ ሰብስቦ የተባለውን አሳወቀ፡፡ ጎርሶማውም በዝርዝር አፈፃፀሙ ላይ መከረ፡፡ ቆኖሶዋን ካላችበት አሳድኖ እንዲያስመጣ ሃዩው ታዘዘ፡፡ ሃዩውም የተመረጡ ጥቂት ሉባዎችን ይዞ ቆኖሶዋ ትገኝበታለች ወደሚባለው አካባቢ ዘመተ፡፡ ቆኖሶዋንም አድነው ከገደሏት በኋላ ዳና በሚባለው ሳር ውስጥ አስረዋት ወደ ሰፈር አመጧት፡፡ ሃዩው ቆኖሶዋን ለዚህ ሲባል ከተዘጋጀው ሥፍራ ላይ ካኖራት በኋላ፣ የታዘዘውን ፈጽሞ መመለሱን ለዳይናው አሳወቀ፡፡ እምነታዊ ሥርዓቱ (ጎዴ) እንዲፈፀም በተወሰነው ቀንም የአካባቢው ሕዝብና ሹማምንት በሥርዓቱ ላይ እንዲገኙ ተነገራቸው፡፡ በዕለቱም ታላቅ በዓል ሆነ፡፡ ቆኖሶዋ ዓይኖቹዋ እንዲጠፉ ከተደረገ በኋላ በዘፈን፣ በእልልታና በጭፈራ ታጅባ ወደተባለው ስፍራ ተወሰደች፡፡ ከሥፍራው ሲደረስም ‹‹ይደርሣል›› የተባለው ክስተት በባህላዊ መሪዎች ከተወገዘ በኋላ ተቀበረች፡፡ ህዝቡም በሄደበት ሁኔታ ወደ መንደር ተመለሰ፡፡ በዚህም ይደርሣል የተባለው ሣይደርስ ቀረ፡፡ በዘመኑ ሰውም አልሞተም፡፡ ድርቅም አልገባም (ቡኬ፣ 2002፣ 28-31)፡፡

በእንዲህ ዓይነቱ እምነታዊ ሥርዓት ወቅት፣ እንደ ቆኖሶ ‹‹ይቀበር፣ ይጣል፣ ወዘተ›› የተባለው ነገር ምን ጊዜም ተወስዶ መቀበር ወይም መጣል ያለበት ውሃ ከማይጠጣበት (ውሃ ከሌለበት) አካባቢ፣ ከራስ ድንበር በጣም አርቆ ነው፡፡ ከራስ ግዛት ውስጥ ወይም የሚጠጣ ውኃ በሚገኝበት አካባቢ የተጣለ (የተቀበረ) እንደሆነ ግን ‹‹የታለመው አይሰምርም፤ በሌላ ወገን ላይ እንዲደርስ የታሰበው በራስ ላይ ይደርሳል›› ተብሎ ይታመናል፡፡ ከተባለው አንዳች እንኳን ሳይጎድል በተባለው መንገድ የተፈፀመ እንደሆነ ‹‹ይደርሳል የተባለው መጥፎ ነገር አይደርስም፡፡ ዘመኑም የሰላም፣ የደስታ፣ የብልጽግና፣ የጤና፣ የጥጋብ፣... ወዘተ ዘመን ይሆናል›› ተብሎ ይታመናል፡፡ ጎዴ የሚባለው እምነታዊ ሥርዓት፣ በጥንቱ ዘመን እንዲህ፣ በዓመት አንድ ጊዜ፣ በግልጽ ይፈፀም ነበር፡፡

*የጎዴ* እምነታዊ ስርዓት በዛሬ ጊዜም በቡርጂዎች ዘንድ ይፈጸማል፡፡ የሚፈፀመው ግን እንደ ጥንቱ በዓመት አንድ ጊዜ አይደለም፡፡ ወይም ስርዓቱ በጊዜ አይገደብም፡፡ ‹‹እንዲህ ያለ ክፉ ነገር ይከሰታል›› በተባለ ቁጥርና ጊዜ ሁሉ እምነታዊ ስርዓቱ ተግባራዊ ይሆናል፡፡ በዚህም ጎዴ በዓመት ወይም በወር ወይም በሳምንት ከሁለትና ከሶስት ጊዜ በላይ የሚፈፀምበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ የአሁኑ *የጎዴ* አፈፃፀም ሥርዓት ከጥንቱ የሚለይበት ሌላም ነጥብ አለ፡፡ በጥንቱ ዘመን ሹማምንቱ ረዳቶቻቸውን ወደ ተንባዮች የሚልኩዋቸው በአመት ለአንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡

በአሁን ጊዜ ግን ዳይናውም ሆነ ማሻው ረዳቶቻቸውን ወደ ተንባዮች ወይም ወደ ጠንቋዮች የሚልኩዋቸው በየቀኑ፣ በየሳምንቱ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ የአካባቢው ፀጥታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየባሰበት መሄዱ ነው፡፡ በድሮ ጊዜ ቡርጂዎች የሚፈሩት ነገር ቢኖር አንዱ *ሙዳሙዴ* (ኩላሊትን እያሳበጠ ይገድል የነበረ በሽታ) ነው፡፡ ይህም ቢሆን የሚከሰተው ከስንት ዓመት በአንዱ ነው፡፡ ሌላው *ማቴ* የሚባል ጠላት ነበራቸው፡፡ እነዚህም ቢሆኑ በዓመት በሁለት ዓመት ለአንድ ወይም ለሁለት ጊዜ መጥተው ቢወጓቸው ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን በሽታውም፣ ጠላትም በዛ፡፡ በተለይ ከሚጎራበቷቸው፣ ከጉጂ ኦሮሞ ህዝቦች ጋር የነበራቸው ቅራኔ እጅግ ቢሶበታል፡፡ ሁለቱ ህዝቦች፣ በአሁኑ ጊዜ ቢያንስ ቢያስ በየወሩ፣ በየቀኑ ይጋጫሉ፡፡ በግጭቱም የበርካታ ንጹሐን ሰዎች ሕይወት ይቀጠፋል፡፡ ሰው በየቀኑ ይገደላል፡፡ ከብት ይዘረፋል፡፡ በአጭሩ ህዝቡ የሚኖረው የስጋት ኑሮ ነው፡፡ ይህም፣ በባህላዊ ሹማምንት ላይ ሥራ አበዛባቸው፡፡ ስለ ሕዝባቸው ደህንነት ተግተው እንዲሰሩ፣ ረዳቶቻቸው በየቀኑ ከተንባዮችና ከጠንቋዮች ዘንድ እንዲሄዱ ምክንያት ሆነ፡፡

እንደ መረጃ ሰጪዎች (ማኒኦ፣ ጫሜ፣ ቱኬ፣ 2002)፣ በጥንቱ ዘመን ቡርጂዎች ስለ ወደፊቱ ማስተንበይ እንጂ ማስጠንቆል አያውቁም፡፡ ማስጠንቆል ለቡርጂዎች የቅርብ ጊዜ ክስተት ነው፡፡ ከአጎራባች ሕዝቦች የተኮረጀ እንጂ የቡርጂዎች ልማድ አይደለም፡፡ ድሮ ለእንዲህ ዓይነቱ ተግባር የሚሄዱት ከተንባዮች ዘንድ ብቻ ነበር፡፡ በአሁን ጊዜ ግን በሁለቱም ይገለገላሉ፡፡ ይህም የዛሬውን ጎዴ ከጥንቱ የሚለይ ሌላው ነጥብ ነው፡፡ እንዲሁም በድሮ ጊዜ ጎዴ በግልጽ፣ በክብረ በዓል መልክ ይፈፀም ነበር፡፡ የዛሬው ጎዴ ግን የሚፈፀመው፣ እንዲህ በግልጽ ሣይሆን፣ እጅግ ሚስጥራዊ በሆነ መልክ ነው፡፡ ስርዓቱ ሲፈፀም ከፈጻሚዎቹ በስተቀር ማንም አያውቅም፡፡ አያይም፡፡ የሚፈጸመውም በአብዛኛው በሌሊት ነው፡፡ ለመፈጸሙም ዋነኛው ምክንያት ከፍ ሲል የተጠቀሰው፣ ከጉጂ ኦሮሞ ጋር ያለው መልካም ያልሆነው ግንኙነት ነው፡፡ ይህን በተመለከተ፣ አንዱ መረጃ ሰጪ በቅርብ ጊዜ በሁለቱም አጎራባች ህዝቦች ማለትም በቡርጂና በጉጂ ህዝቦች አማካይነት ‹‹ተፈፀመ›› ያለውን ወይም ‹‹አንዱ በሌላው ላይ ሲፈፅም ተመለከትኩ›› ወይም ‹‹ተሳታፊ ነበርኩ›› ያለው የጎዴ እምነታዊ ሥርዓት እንደሚከተለው ይተረካል፡፡

> አንድ ሌሊት ነው፡፡ ከመንደር ወጥተን ጥበቃ ላይ ነበርን፡፡ ከምሽጋችን ውስጥ አድፍጠናል፡፡ እዚያው አድፍጠን ባለንበት አካባቢ፣ በቅርብ ርቀት ላይ ባትሪ ብልጭ ሲል ተመለከትን፡፡ የጥበቃውን ሁኔታ ለመፈተሽ የወጡ የእኛው የቡርጂ ሰዎች ናቸው ብለን ዝም አልን፡፡ በበነጋታው ጧት፣ ማታ ባትሪ የበራበትን አካባቢ ለመፈተሽ ሄድን፡፡ ለካስ ጠላት ኖሮአል፡፡ ጉጂ፣ ሴት ይዞ መጥቶ፣ እዚያው ከመንገዱ ላይ፣ ከአፍንጫችን ሥር ተቀምጦ አሩን አርቶ፣ የሥጋ ዘር አልቀረም፣ ጨጓራ፣ ጉበት፣ ኩላሊት፣...ወዘተ በትንንሹ ከታትፎ፣ የምላጭና የምናምን ስብርባሪ ቀላቅሎበት፣ ከተፀዳዳው ከዓይነምድሩ አጠገብ ቁጭ

አድርጎት፣ ፊልፊላ ጥሎብን ሄዷል፡፡ ‹‹ወይኔ! ማታ ከዚያው የምናስቀረው ጠላት አመስጠን›› ብለን ተቆጨን፡፡ የተሰራብንን ጎዴ ወዲያው ወስደን በጭድ ውስጥ አድርገን በእሣት አቃጠልነው፡፡ እንዲህ ወዲያው ያቃጠልከው እንደሆነ ጎዴው ይከሽፋል፡፡ ከዚያም ማን? ለምን? እንዳደረገብን ለመጠየቅ ወደ ተንባዮች ሄድን፡፡ ተንባዩም ‹‹ይህን ያደረገባችሁ ጉጂ ነው፡፡ እናንተ ደግሞ አፈርማ መልክ ያላትን ፍየል *(ቢያንታ ቢሻታ ሶቤይንቾ)* ወስዳችሁ ‹ህዝቡን ማርልን› ብላችሁ፣ አንገቷን ጠምዝዛችሁ፣ እንዲሁም አንድ መልክ ብቻ ያላትን ዶሮ ይዛችሁ ‹ዓይንህ እንዲህ ይወጋ› ብላችሁ በአንዱ ዓይኗ ወግታችሁ በሁለተኛው ዓይኗ እንዲዘልቅ ከአደረጋችሁ በኋላ አንገቷን ጠምዝዛችሁ፣ ሣትታዩ ወስዳችሁ፣ ድንበር አሻግራችሁና አርቃችሁ ጣሏቸው›› አለን፡፡ እኛም እንደተባለው አድርገን፣ በሌሊት ወስደን፣ ከተባለው ሥፍራ ላይ በጥንቃቄ ጥለን ተመለስን (ጫሜ፣2002፣69)፡፡

‹‹የተባለው አንዳች ሣይጓደል በተባለው መንገድ በትክክል ከተፈፀመ ወይም ከተከናወነ፣ ስኬቱ መቶ በመቶ ነው፡፡ የተባለው በትክክል ካልተፈጸመ ግን የታሰበው አይሰምርም፡፡ የተፈራውም አይቀርም›› ብለው ቡርጂዎች ያምናሉ፡፡ ለዚህ እምነታቸው ትክክለኛነትም የሚከተለውን እውነተኛ ታሪክ በአስረጅነት ያቀርባሉ፡፡ ተራኪው ደግሞ በአንድ ወቅት ዳይና ሆኖ ያገለገለ ባህላዊ ሹም ነው፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፤

በእኔ የሥልጣን ዘመን፣ እዚያ ራሰያ አካባቢ አንድ ወርቄ ቦባ የሚባል ተንባይ (ጠንቋይ) ሰው ነበረ፡፡ ስለ ሀገራችንና ስለ ሕዝባችን መፃኢ ሁኔታ እንዲያስተነቢዩ ጃልዓባዬን ከሌላ አንድ ሰው ጋር አድርጌ ከዚህ ሰው ዘንድ ላኳቸው፡፡ እነርሱም ሄደው ሲመለሱ፣ ተንባዩ በአካባቢው ከባድ ጦርነት ሊቀሰቀስ መቃረቡን እንደነገራቸው ነገሩኝ፡፡ ‹‹ከላይ ከሰሜኑ የቡርጂ አካባቢ የሚጀምር፣ በፀሐይ መውጫ አቅጣጫ አድርጎ ሣያባራ እስከ ክሊቾ የሚዘልቅ ከባድ ጦርነት ይኖራል፡፡ በጦርነቱም ብዙ ሰዎች ይሞታሉ፡፡ ስለሆነም ሕዝቡ ከዚህ ጦርነት እንዲተርፍ የሚከተሉት ሶስት ተግባራትን ፈጽሙ፡፡ በመጀመሪያ ቡርጂ ውስጥ ያሉ የሁሉም ሃይማኖት መሪዎችና ምእመናን፣ የመንግስት ሹማምንትና ባሕላዊ የሕዝብ መሪዎች፣ የመንግስት ሰራተኞችና ሁሉም ሕዝቦች በሶያማ ከተማ ላይ ይሰብሰቡ፡፡ ተሰብስበው፣ ከለምለም ሣር ላይ ተቀምጠው፣ ‹ለሕዝቡ በረከትን፣ ምህረትን አምጣልን፡፡ ሕዝቡን ማርልን› ብለው በአንድነት ይፀልዩ፡፡[67] በመቀጠልም ጉጂ በእናንተ ላይ ጎዴ (ፊልፊላ) ሰርቶባችኋል፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱ የአስተዳደር አካባቢ (ቢያ) ‹‹ጀሲንታ አራሾ››

---

[67] አሁን ገና ትዝ አለኝ፡፡ በቡርጂ ልዩ ወረዳ ውስጥ ነው፡፡ ለዚህ ጥናት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ቡርጂ በነበርኩበት ወቅት ማለት ነው፡፡ አውራ አቀባዮቼን የቃል መጠይቅ ከማድረጌ በፊት በልዩ ወረዳው ባህል፣ ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ውስጥ ያሉትን በርካታ የድምፅና የምስል መረጃዎችን በርብሬያቸዋለሁ፡፡ በርካታ የቴፕ ካሴቶችን አዳምጫቸዋለሁ፡፡ በዚህን ወቅት ቡርጂ ውስጥ ያሉ የዘመናዊ ሃይማኖት ተከታዮችና መሪዎች፣ የመንግስትና የሕዝብ ሹማምንት፣ እንዲሁም ሌሎች ሕዝቦች፣ በሶያማ ከተማ ላይ በአንድ ላይ ተሰብስበው ሲፀልዩ፣ ሲዘምሩ፣ ሲያሸበሽቡ…ወዘተ በቴፕ የተቀዱ ጥቂት ካሴቶች አጋጥመውኝ ነበር፡፡ በወቅቱ ለሥራዬ ጠቀሜታ ስላልነበራቸው ጨርሼ አላዳመጥኳቸውም፡፡ ያን ጊዜ የፀሎቱ ዓላማ ስላልገባኝ ትኩረት አልሰጠኋቸውም፡፡ እንዲያውም ‹‹አሁን ይህን የሚቀርጹት ምን ያደርግልናል ብለው ነው›› ብዬ ሣልተቻቸው የቀረሁ አይመስለኝም፡፡ … አሁን ገና ገባኝ፡፡ ያን ጊዜ ፀሎቱ፣ ልመናው፣ እግዚኦታው…ወዘተ የተካሄደው ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ በወቅቱ ባህላዊ መሪ በነበረው በዳይናው ትዕዛዝ ወይም ማሳሰቢያ መሆኑን ስረዳ ግን እጅግ እጅግ አድርጎ ገረመኝ፡፡ ‹‹እነዚያን ካሴቶች ምነው ጨርሼ ባዳመጥኳቸው ኖሮ! ወይም እንዴሌሎቹ ካሴቶች ወደ እራሴ ካሴቶች ገልብጨ በያዝኳቸው ኖሮ!›› ብዬ ተቆጨሁ፡፡ የኦርቶዶክስ ካህናት፣ ዲያቆናትና ምዕመናን አልቀሩም፡፡ የሙስሊሞችና የፕሮቴስታንት እምነት መሪዎችና ተከታዮችም እንዲሁ የቀሩ አይመስለኝም፡፡ የመንግስት ከፍተኛ ሹማምንትና ሰራተኞችም እንዲሁ በጉባኤው አሉበት፡፡ ሌላው ተራው ሕዝብም በሥፍራው ተገኝቷል ብዬ እገምታለሁ፡፡ የተወሰኑ የእምነትና የፖለቲካ መሪዎች ተራ በተራ ንግግር ሲያሰሙ፣ ቡራኬ ሲሰጡ፣ ሲፀልዩ፣ ….ወዘተ ያዳመጥኳቸው መሰለኝ፡፡ ይህ ሁሉ ቡራኬ፣ ይህ ሁሉ ምልጃ፣ ይህ ሁሉ ምልዐተ ጉባኤ ግን ራሰያ ውስጥ የሚኖር አንድ ጠንቋይ (ተንባይም በሉት) ‹‹እንዲህ ይሆናል፡፡ እንዲህ እንዳይሆን እንዲህ አድርጉ…›› ብሎ ያሳሰበውን ማሳሰቢያ፣ የሰጠውን ማስጠንቀቂያ (ትዕዛዝም በሉት) መነሻ ያደረገ፣ በእሱ ማስጠንቀቂያና ማሳሰቢያ (በእሱ ትዕዛዝም በሉት) መሰረት የተፈፀመ መሆኑን፣ እውነት እውነት እላችኋለሁ! ፈፅሞ አላውቅም ነበር፡፡ እፁብ ድንቅ ተግባር ነው፡፡ ግን፣ ግን፣ ብዙ ከማለቴ በፊት አንድ ጥያቄ ላንሣ፡፡ ‹‹ለመሆኑ እነዚህ ሰዎች ይህን ሲያደርጉ፣ ተሰብስበው ሲፀልዩ (ለህዝብ ሰላምና ደህንነት መፀለያቸው መልካም ቢሆንም) መነሻው፣ መንስኤው የጠንቋዩ ንግር፣ የተንባዩ ማስጠንቀቂያ መሆኑን በእርግጥ ያውቁ ኖሯልን? እኔ ግን አብዛኞቹ የሚያውቁ ቀርቶ የሚጠራጠሩ አይመስለኝም፡፡ የነገሩን መነሻና መድረሻ፣ ዓላማና ግብ፣ ምክንያትና ውጤት የሚያውቁት በጣት የሚቆጠሩ ጥቂት ሰዎች ብቻ ይሆናሉ ብዬ እገምታለሁ፡፡ ግምቴም ትክክል እንዲሆን እመኛለሁ፡፡ እናንተም ተመኙልኝ፡፡ ግን ፀልዩልኝ አላልኳችሁም፡፡ አልላችሁምም፡፡ ለነገሩ ፈቃደ (1991፣14) ሀገረሰባዊ እምነት የሚለው እንዲህ እንዲህ ዓይነቱን አይደል ሰዎች በዋናነት ከሚከተሉት ሃይማኖት፣ በቅዱሳን መጻሕፍት ውስጥ ከተፃፈው ውጭ የሚያራምዱት እምነትና እምነታዊ ድርጊት ነው ሀገረሰባዊ እምነት የሚባለው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ከዚህ የሚነሣ ሌላም ትልቅ ጥያቄ አለኝ፡፡ ‹‹ለመሆኑ ቡርጂን የሚያስተዳድረው፣ ሕዝቡን የሚመራው ማነው? መንግሥታዊ ወይንስ ባህላዊ የፖለቲካ ተቋማት?›› ለአሁኑ በዚህ ይብቃኝ፡፡

የሚባል ቅጠል ከደጋው አካባቢ በማምጣት ገላና ወስዶ ከጫካው ውስጥ ይጣል፡፡ በሶስተኛ ደረጃ፣ እያንዳንዱ የቢያ አስተዳደር ከራሱ በስተግራው ባለው ቦሄ ውስጥ ከሚኖሩ ሸክላ ሰሪዎች ላይ የገብስ ገለባ (ሆሻራ) ያምጣ፡፡ አምጥቶ ወዲያ ማዶ ድንበር አሻግሮ ይጣል›› ተብለናል ብለው ነገሩኝ፡፡ ይህን እንደነገሩኝ ጊዜ አላጠፋሁም፡፡ ጎርሶማውን ስብሰባ ጠራሁ፡፡ ስብሰባ ጠርቼ ‹‹እንዲህ ተብለናል›› ብዬ ሁሉንም በዝርዝር ነገርኳቸው፡፡ ጉባኤተኛውም በጉዳዩ ላይ ከተወያየ በኋላ የተባለው በሁሉም አካባቢ በተባለው መሰረት እንዲፈጸም ወስኖ ተበተነ፡፡ ይሁን እንጂ የተባለው ጦርነት አልቀረም፡፡ ፊነዱ፡፡ ልክ እንደተባለው በቅድሚያ ከሰሜኑ የቡርጂ አካባቢ ጀመረ፡፡ ከዚያ የጀመረው ጦርነት አንዳች ፋታ ሣይሰጥ እስከ ክሊቾ ድረስ ዘለቀ፡፡...እንደዚያ ጊዜም ጫን ያለ ጦርነት ኖሮም አያውቅም፡፡ በጦርነቱም ብዙ ሰዎቻችን ተጎዱ፡፡ ሞቱ፡፡ ይህ የሆነው የህዝቡ ባህላዊ ሹማምንት እንዲያስፈጽሙ (እንዲፈጽሙ) የተነገራቸውን ነገር (የጎዴውን እምነታዊ *ሥርዓት*) በተነገራቸው መሰረት በትክክልና በአግባቡ ባለመፈጸማቸው ነው፡፡ እንዲፈጽሙ የተባሉትን ባህላዊ ደንብ ለመፈጸም ቀን ከማታ ሲባክኑ በመካከላቸው አለመግባባት ተፈጠረ፡፡ የሀሳብ ልዩነት ተከሰተ፡፡ በዚህ የተነሳ ደንቡን በተባለው ጊዜና ሁኔታ ሣይፈፅሙ ቀሩ፡፡ ይህ እንደተነገረኝ እንደገና ሁሉንም ሰበሰብኳቸው፡፡ ሁሉም አካባቢዎች ከተባለው አንድ ሣያጓድሉ እንዲፈጽሙ እንደገና ጥብቅ ትዕዛዝ ከአደራ ጋር ሰጠኋቸው፡፡ ‹‹ሁሉም የተባለውን በረቡዕ ቀን ይፈፅም›› ብዬ አዘዝኳቸው፡፡ ቅዳሜ ሁሉንም ጠርቼ የተባለውን ፈፅመው እንደሆነ ጠየኳቸው፡፡ ሁሉም በትክክል መፈጸማቸውን አረጋገጡልኝ፡፡ ይህ ከተደረገ በኋላ ግን ሁሉም ነገር ፀጥ፣ እረጭ አለ፡፡ ጦርነቱ ቆመ፡፡ ሕዝቡም ከእልቂት ተረፈ (ማኒአ፣ 2002፣ 61-64)፡፡

### 5.4.3 ሞጨ

*ሞጨ*፣ አንድን ነገር ወይም ሰውን ከኃጥያቱ፣ ከእርኩሰቱ ለማንፃት ሲባል የሚፈፀም እምነታዊ *ሥርዓት* ነው፡፡ *ሥርዓቱ* የሚፈፀመው ውሃን ወይም የበግን ፈርስ በሰው ወይም በዕቃ ላይ በመርጨት ወይም በመቀባት ይሆናል፡፡ *ኣራሾ* (ሴት በግ)፣ *ቆም*[68] ወይም *ሃባ* ወይም *ማ* (ደረቅ የእንሰት ግንድ ልባስ)፣ ከሁለት ወራጅ ወንዞች *(ባንኬ)* በማለዳ የተቀዳ ውሃ *የሞጨን* ስርዓት ለመፈፀም የሚያስፈልጉ (የሚቀርቡ) ነገሮች ናቸው፡፡

*ሞጨ* ሁለት ዓይነት ነው፡፡ አንደኛው በአንድ ቤተሰብ ውስጥ አባትና ልጅ ወይም የጎሳ መሪውና የጎሳው አባላት ተጣልተው በሚታረቁበት ጊዜ የሚፈፀመው *ሞጨ* ነው፡፡ እንዲሁም ሴት ልጅ ተድራ ልጅ አልወልድ ስትል እንድትወልድ ሲባል የሚፈፀመው *ሞጨም* ከዚሁ የሚመደብ ነው፡፡ ሁለተኛው *የሞጨ* ዓይነት ደግሞ ከዚህ ከፍ ባለ ደረጃ በተጋጩና በተገዳደሉ በሁለት ጎሳዎች ወይም ማህበረሰቦች መካከል ዕርቅ በሚወርድ ጊዜ የሚፈጸም ነው፡፡ የሁለቱንም የአፈጻጸም ስርዓት፣ በቀረቡበት ቅደም ተከተል፣ ተራ በተራ እንመልከት፡፡

---

[68] ገና ያልጠነከረ፣ጮርቃ የቅል ፍሬ ወይም የቅል ተክል አካል በአጠቃላይ የሚጠራበት ስም ነው፡፡ በቡርጂ ልማድ፣ *ቆም* እንደ ሴት በግ (እንደ ኣራሾ) ወይም *ከኣራሾ* እኩል ይቆጠራል፡፡ *ለሞጨ* ስርዓት መፈፀም ምክንያት ከሆኑ ወገኖች መካከል አንዱ ለስርዓቱ ማስፈፀሚያ ሴት በግ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ ይሁን እንጂ፣ በግ እንዲያቀርብ የተጠየቀው ወገን የእውነት በግ ማቅረብ ካልቻለ፣ በበግ ምትክ *ቆም* ይዞ ይቀርባል፡፡ ‹‹በጉ የት አለ›› ተብሎ ሲጠየቅም ‹‹ይኸውና›› ብሎ *ቆሞውን* ከሽማግሌዎቹ ፊት ቁጭ ያደርጋል፡፡ ሽማግሌዎችም ቢሆኑ ‹‹ለምን *ቆም*›› አይሉም፡፡ *ቆሞውን* ይቀበሉትና ከታትፈው ከውሃ ጋር ከቀላቀሉት በኋላ በመርጨት ስርዓቱን ይፈፅማሉ፡፡ *ቆሞውን* መከታተፍ፣ በግ እንደማረድ ይቆጠራል፡፡ ውኃው ደግሞ የበጉ ደምና ፈርስ መሆኑ ሣይሆን ይቀራል?

በድሮ ጊዜ የቡርጂ ሴቶች በቶሎ አይወልዱም። ሴት ልጆች አድገው፣ ለአካለ መጠን ደርሰው፣ ለባል ከተዳሩ በኋላም ቢሆን፣ በቀላሉ ዘር አያፈሩም። የሚወልዱት *ምጨ* ከተደረጉ በኋላ ነው ተብሎ ይታመናል። የዚህ ዓይነት፣ *ያለመውለድ* ችግር በተከሰተ ጊዜ አልወልድ *ያለችዋ* ሴት አንድ እንስራ ሙሉ ቦርዴ ይዛ ከወላጅ አባቱዋ ቤት እንድትመጣ ትደረጋለች። ቤተሰብ በሙሉ ይጠራል። ከአባቱዋ ቤት ስትመጣ *ቆሞና ሃባ* ይቀርባሉ። ውሃ ከሁለት ወንዞች ተቀድቶ ይመጣና በአንድ ላይ ይቀላቀላል። *ቆሞውና ሃባው* ይከተፉና ከውሃው ውስጥ ይጨመራሉ። ከዚያም *ሲርጊን! ቃልማን አሊቾታኖ! ያይእ ወንቶ! ወንቶ ቃሲ! ጋልች ቃልማኒ!*...(ልጂት ቀዝቀዝ በይ! ተዋለጂ! እግዚአብሔር[69] ሆይ! እግዚአብሔር ውሰድ! ገብተሽ ተዋለጂ ወዘተ.) እየተባለ የተቀላቀለው ውኃ፣ *ሥርዓቱን* በሚፈጽመው ሰው አማካይነት ከጀርባዋ፣ ከደረቷ፣ ከጡቷና ከሆዷ አካባቢ ይረጫል። ይህ ከተፈፀመ በኋላ ልጅ ሳይወልዱ የቆዩ ሴቶች ልጅ መውለድ ይጀምራሉ ተብሎ ይታመናል። ይህን የሚፈፅመው ደግሞ የአንድ ቤተሰብ፣ ወይም የጎሣ፣ *የቦሄ፣* ወዘተ መሪ የሆነ ሰው ነው። በአጭሩ *የምጨ ሥርዓት* በማንኛውም ደረጃ መሪ *(ኣና)* ባልሆኑ ሰዎች አይፈፀምም።

ሌላው *ምጨ*፣ ተጋጭተው በተገዳደሉ ወገኖች መካከል እርቅ ከወረደ በኋላ የሚፈፀመው ነው። *ሥርዓቱ* የሚፈፀመው የሁለቱም ወገኖች ወይም ተወካዮች በተገኙበት በባህላዊ *መሪው* (ባህላዊ *መሪው* የፖለቲካ ወይም የእምነት *መሪ ሊሆን* ይችላል) እና *በአምቢቻው* (ከሁለቱም ወገኖች *ጋር* የጋብቻ ዝምድና ባለው ሰው) አማካይነት ይሆናል። ከዚህ ደረጃ ከመደረሱ በፊት ግን፣ ሁለቱ ወገኖች በሽምግልና እንዲቀራረቡና እርቅ እንዲያወርዱ ይደረጋሉ። የበደለው ወገን እንዲክስ፣ የተበደለው እንዲካስ ተደርጎ በሁለቱ ወገኖች መካከል እርቅ ይወርዳል። ሁለቱን ወገኖች ከኃጥያታቸው የማንጻቱ፣ ቂም በቀል የማጥፋቱ፣ ቁጣ የማብረዱ (የሞጨ) ስርዓት የሚፈፀመው ከዚህ በኋላ ነው። እርቅ ወርዶ እንዳበቃ በግጭቱ የተጎዳው (የተበደለው) ወገን ሴት በግ (ኣራሾ)፣ ጎጂው (በደል አድራሹ) ወገን ደግሞ ኮርማ በሬ (ሃሪኣይ) እንዲያቀርብ ይደረጋል። በግጭቱ ሰው የሞተበት ወገን በግ እንዲያቀርብ የሚደረገው እነዚያን፣ እጃቸው በደም የበከለውን፣ በኃጥያት የጎደፈውን የገዳይ ወገኖችን በበጉ ደም፣ በበጉ ፈርስ ለማጠብ፣ ለማንፃት ሲባል ነው። የሟች ወገኖች ጥፋት፣ ኃጥያት የለባቸውም። በግጭቱ ሰው ሞቶባቸዋል። ተጎድተዋል። ይህ ሆኖ ሳለ ግን፣ ‹‹በሽምግልና እርቅ አውርደናል፣ ይቅር ለእግዜር ብለናል፣ ቂም በቀል ትተናል›› ብለዋል። ይሁን እንጂ፣ ገዳይ ወገኖችን ከልብ ይቅር

[69] ስለ ዝርዝር ማብራሪያው የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 48 ተመልከት።

ማለታቸውን፣ ዳግም ለበቀል የማይነሳሱ መሆናቸውን የሚያረጋግጡት በግ ሲያቀርቡ ነው። በግ ሲያቀርቡ ለእነዚያ፣ ለገዳይ ወገኖች ታላቅ መሪ መሆናቸውን ማስመስከራቸውም ነው። በቡርጂ ልማድ አባትና ልጅ ተጣልተው በሚታረቁበት ወቅት ጥፋተኛው አባት ቢሆን እንኳን በግ እንጂ በሬ እንዲያቀርብ አይደረግም። አንዳች ጥፋት ባይኖርበትም፣ ኮርማ በሬ የሚያቀርበው ልጁ ይሆናል።

ከሌላ እንስሳ ት መካከ ል በግ መመረ ጧም እንዲሁ የ ራሱ የሆነ ባህላዊ ፋይዳ አለው። በቡርጂዎች እምነት በግ የዋህ፣ ገር፣ ንጹህ፣ ቀዝቀዝና ረጋ ያለች ፍጡር ናት። ንጹህ በመሆንዋ ገዳይ ወገኖችን ከኃጥያታቸው ታነጻለች። ቀዝቀዝና ረጋ ያለች በመሆንዋ ደግሞ የሟች ወገኖ ችን ቁጣና የ በቀል ስሜት ታ በርዳለች። ተ ብሎ ይታመናል። በግ ለስርዓቱ መመረጥዋም ከዚህ እምነት በመነሳት ነው። ከዚህ በኋላ *አምቢቻ* የሆነ ሰው እንዲመጣ ይደረጋል። የእርቁን *ሥርዓት* የመራው የህዝብ መሪም እንዲሁ ይቀርባል። ሁለቱም ቀርበው በግዋን በጋራ ይባርኩዋታል። የበጓ ሆድ ይቀደድና ፈርሷ ይወጣል። ከዚያ በኋላ *ሲርገን! ሲርገን!* (ቀዝቀዝ፣ በረድ በል!) እየተባለ የሁለቱ ወገኖች አፍ በፈርሱ ይጠረግበታል። በዚህም የ*ሥርዓቱ* ፍፃሜ ይሆናል። በዚህ ዓይነት በግ አርደው የፈሰሰውን የሰው ደም የሚያደርቁበት፣ በዚህ ሰበብ የተቀሰቀሰውን ንዴትና ቁጣ የሚያበርዱበት፣ ቂም በቀል የሚያስወግዱበት፣ ኃጥያተኞችን ከእርኩሰታቸው የሚያነፁበት ባህላዊ የእምነት ስርዓት ነው ሞጨ የሚባለው።

### 5.4.4. ቦርቶማ [70]

*ቦርቶማ* በቁሙ መዋደድ፣ መፋቀር፣ አንድ መሆን ወይም መስማማት ማለት ነው። የሁለት ባላንጣ ወገኖች (ጎሳዎች) እርስ በርስ መዋደድ፣ አንድ መሆን ማለት ነው። ቦርቶማ ከባህላዊ አስተዳደር ጋር ተያይዞ የሚፈጸም የቡርጂ እምነታዊ ስርዓት ነው። *ሥርዓቱ* የሚፈፀመው ደግሞ ተጋጭተውና ተገዳድለው የነበሩ ሁለት ወገኖች እርቅ ከአወረዱ በኋላ ነው።

ቦርቶማ እና ከፍ ሲል የተመለከተው ሞጨ፣ በአብዛኛው ተመሳሳይና ተያያዥ የሆኑ እምነታዊ ስርዓቶች ናቸው። አፈጻጸማቸውም እንዲሁ ይመሳሰላል። ልዩነቱ ወደ መጨረሻው የ*ሥርዓቱ* ፍፃሜ አካባቢ ነው። የሁለቱ ወገኖች አፍ በበጉ ፈርስ ሲጠረግ የሞጨ (የማንጻቱ) እምነታዊ ስርዓት ያበቃል። ከዚያ በኋላ የሚኖረው *የቦርቶማ* ወይም *የኣምቦማ ሥርዓት* ይሆናል።

---

[70] ቦረናዎችና ጉጂ ኦሮሞዎች ‹‹ጎንዶሮ›› ይሉታል። አብዛኞቹ ቡርጂዎችም ቢሆኑ ይህን እምነታዊ ስርዓት የሚጠሩት በኦሮምኛው ቃል ‹‹ጎንዶሮ›› ወይም ‹‹ጎንዶርሳ›› ብለው ነው። ቃሉም (ጎንዶሮ) የቡርጂኛ ቃል ይመስላቸዋል። ግን አይደለም። ቡርጂኛው ቦርቶማ ወይም አምቦማ ነው የሚለው። ‹‹ወሲጋና ቦርቶማንከ›› ሲል፣ ሁለቱም አንድ ሆኑ ሲል ነው በቡርጂኛው።

ለቦርቶማ ሥርዓት ማስፈጸሚያነት ከሚቀርቡ ነገሮች መካከል አንዷ ሴት በግ ስትሆን ሌላዋ ያረጀች ላም ናት፡፡ ላም የምትቀርበው ግጭቱ የውጭ፣ ከሌላ ህብረተሰብ ጋር ሲሆን ነው፡፡ ለውስጥ ግጭት ማለትም ግጭቱ በቡርጂዎች መካከል ሲሆን ደግሞ ሴት በግ ትቀርባለች፡፡ ሁለቱም በአንድ ላይ በአንድ ጊዜ የሚቀርቡበት ሁኔታም አለ፡፡

ለቦርቶማም ሆነ ለሞጨ እምነታዊ ስርዓት ሰበቡ የሁለት ወገኖች (ጎሳዎች) ግጭት እንደሆነ፣ ሁለቱም ወገኖች በሽምግልና እንዲቀራረቡ፣ እንዲታረቁ ከተደረጉ በኋላ፣ አፋቸውን በበጉ ፈርስ በመጥረግ የሞጨ ሥርዓት እንደሚፈጸም ከፍ ሲል ጠቅሰናል፡፡ ከዚህ በኋላ ደግሞ *የቦርቶማ* እምነታዊ ሥርዓት ይፈፀማል፡፡

*ቦርቶማ* ሲፈፀም የአካባቢው ሕዝብ ሁሉ በሥርዓቱ ላይ እንዲገኝ ይጋበዛል፡፡ በዚህም ሕዝብ ይሰበሰባል፡፡ ለሥርዓቱ ሲባል በገዳይ ወገኖች የቀረበችው ላም፣ በሕዝብ ፊት፣ በሁለቱ ወገኖች አማካይነት አከርካሪዋ ይሰበራል፡፡ መሀላ መሆኑ ነው፡፡ የላሚቷን አከርካሪ ሁለቱ ባላናጣ ወገኖች በጋራ በሚሰብሩበት ወቅት ‹‹ከአሁን በኋላ ሁለታችንም *ኣምቦ* ወይም አንድ ቤተሰብ ነን፡፡ ከዛሬ ጀምሮ በክፉ ላንፈላለግ ይህ መሀላ በሁለታችን መካከል ይቀመጥ፡፡ በሁለታችን መካከል *ቦርቶማ* (ፍቅር፣ ሰላም) ይኑር›› ብለው ይምላሉ፡፡ የላሚቷ አከርካሪ እንዲሰብሩ መደረጉም እንዲህ ስለመስማማታቸው፣ ስለመማማላቸው በህዝብ ፊት ማስረጃ ማስቀመጣቸው ነው፡፡ ቀደም ሲል በመካከላቸው የነበረው ባላንጣነት፣ ቂም በቀል፣ ክፉ ሀሳብ ከዛሬ ጀምሮ ተቆረጠ፣ ተሰበረ፣ ቀረ ማለት ነው፡፡ ሁለቱም ጎሳዎች *አምቦ* ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ *አምቦ* ሆኑ ማለት አንድ ጎሳ፣ አንድ ቤተሰብ ሆኑ ማለት ነው፡፡ እንደ አንድ ቤተሰብ ስለሚቆጠሩም እርስ በርስ አይጋቡም፡፡ በክፉ አይፈላለጉም፡፡ ክፉ በመጣ ጊዜ ይተጋገዛሉ፡፡ ቦርቶማ ማለት እንግዲህ ይህ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም በፀብ፣ በክፉ ይፈላለጉ የነበሩ ሁለት ወገኖችን በማስታረቅ፣ በማንፃትና በማማማል ማስማማት፣ ማፋቀር፣ ማዋደድ፣ አንድ ቤተሰብ ማድረግ ማለት ነው *ቦርቶማ* ማለት፡፡ በዚህ መልክ ይህ እምነታዊ ስርዓት ከተፈፀመ በኋላ መሃላውን አፍርሶ ለበቀል የሚነሳሳ ወገን ዘሩ፣ መሰረቱ አንድ እንኳን ሳይተርፍ እልቅ፣ ሙትት ይላል ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ እምነት የተነሳ በሁለቱ ወገኖች መካከል ቀደም ሲል ተነስቶ የነበረው ክፉ ሀሳብ፣ ግጭት፣ በቀል እስከ ወዲያኛው ይከስማል፡፡

## 5.5. የባህላዊ መሪዎች ገደቦችና የቁጥጥር ሥርዓቶች

የቡርጂ ህዝብ የሚመራበት ባህላዊ የፖለቲካና የእምነት ተቋማት እንዳለው፣ ተቋማቱም በሌላዎችና በባለጋኖች እንደሚመሩ በቀደሙት ክፍሎች ገልፀናል፡፡ *ባለጋኖች* ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል ያላቸው ባህላዊ የእምነት መሪዎች ናቸው፡፡ *ሌላዎች* ግን የእምነት መሪዎች አይደሉም፡፡ ባለመሆናቸውም ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል *(Super Natural Power)* የላቸውም፡፡ እነርሱ ያላቸው የህዝብ ምርቃት፣ የአገር በረከት... ወዘተ ብቻ ነው፡፡ በዚህም በህዝቡ ዘንድ ክብርና ሞገስ አላቸው፡፡ ጥሩ ገድ፣ መልካም ዕድል ያለው ከእነርሱ ዘንድ ነው፡፡ የህዝቡ ዕድልና እጣፈንታ ከእነርሱ ዕድልና እጣፈንታ ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ በመሆኑም የመሪዎቹ እያንዳንዱ እንቅስቃሴ፣ እያንዳንዱ ድርጊት፣ ወዘተ የህዝቡን ዕድልና እጣፈንታ ይወስናል ተብሎ ይታመናል፡፡ ለዚህ ሲባልም የህዝብ መሪዎች እንዳሻቸው እንዳይሆኑ ገደብ ይጣልባቸዋል፡፡ የቁጥጥር ስርዓት ይበጅላቸዋል፡፡ ይህ ምዕራፍም የመሪዎቹ ገደቦች ምን ምን ናቸው? ለገደቦቹ መጣስስ ምክንያቱ ምንድነው? ገደቦቹን ቢጥሱስ ምን ይደረጋሉ? ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ ይሞክራል፡፡

በቡርጂ ህገ ደንብ መሰረት ባህላዊ መሪዎች በሥልጣን ላይ እስካሉ ድረስ ከሚኖሩበት ቀዬ ወይም አካባቢ፣ በተለይም ከቡርጂ ወጥተው ወይም ርቀው እንዲሄዱ፣ ቢሄዱም በሄዱበት እንዲያድሩ፣ ባገኙበት እንዲሸኑ (እንዲፀዳዱ) አይፈቀድላቸውም፡፡ ሌላዎች ከቡርጂ ውጪ ከሄዱ፣ በሄዱበት ካደሩ ወይም ከሸኑ (ከተፀዳዱ) በላያቸው ላይ ያለው የሕዝቡ ምርቃት፣ የሀገሩ በረከትና ፀጋ ከላያቸው ላይ ይገፈፋል፡፡ ለዚያ ለሄዱበት፣ ሄደው ላደሩበት፣ ለተፀዳዱበት ሀገርና ሕዝብ ይሆናል፡፡ ባለጋኖች ሲሆኑ ደግሞ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይላቸው (ጋን) ይረክሳል፡፡ ከላያቸው ላይ ይገፈፋል ተብሎ ይታመናል፡፡ እንዲሁም የሕዝብ መሪዎች ከማንም ሰው ጋር (ከሚስታቸውም ቢሆን) መጣላት የለባቸውም፡፡ ከአንደበታቸው መልካም እንጂ፣ ክፉ ንግግር ፈፅሞ ሊወጣ አይገባም፡፡ አልኮል መጠጦችን መጠጣት ለሌላዎች የሚፈቀድ ቢሆንም፣ ጠጥቶ መስከር ግን የተከለከለ ነው፡፡ ባለጋኖች ግን (ቦርዴ የሚባለውን ባህላዊ መጠጥ ካልሆነ በስተቀር) አልኮል መጠጥ[71] እንዲጠጡ ፈፅሞ አይፈቀድላቸውም፡፡ ምግብም ቢሆን እንዳገኙ

---

[71] አሁን አሁን አንዳንዶቹ መጠጣት የጀመሩ ይመስላል፡፡ ለዚህ ደግሞ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ከፍ ሲል፣ ‹‹የባህላዊ መሪዎች ተግባር›› በሚል ርዕስ (ክፍል 4.4.1) ስር ቀደም ሲል ዳይና ሆኖ ያገለገለ አንድ መረጃ ሰጪ በሥልጣኑ ዘመን ለሕዝቡ ሰራሁ ካለው ተወስዶ የተጠቀሰውን ሀሳብ በአስረጅነት ማንሳት ይቻላል፡፡ በጽሑፉ ውስጥ እንደተጠቀሰው፣ በአካባቢው በወቅቱ መዝነብ የነበረበት ዝናብ ባለመዝነቡ ምክንያት ያንገርበበውን የድርቅ አደጋ በመፍራት ዳይናውና ረዳቱ ጃልዐባው ‹‹ዝናብ ለሕዝቡ አዘንብለት›› ብለው ለመለመን፣ ይህንን የማድረግ ሥልጣን አለው ተብሎ ወደሚታመነው ባለጋን ሄደዋል፡፡ ሲሄዱ ታዲያ ለባለጋኑ ይዘውለት የሄዱት ሁለት ነገሮችን ነው፡፡ አንደኛው ገንዘብ ሲሆን ሁለተኛው አንድ ጀሪካን ሙሉ የአበሻ አረቄ ነው፡፡ አረቄውንም ባለጋኑና ጃልዐባው ሆነው መጠጣታቸውም በጽሑፉ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በመነሳት ለባለጋኖች አልኮል መጠጣት ዛሬ ዛሬ ሣይፈቀድ አልቀረም ማለት እንችላለን፡፡ አልኮል በመጠጣታቸውም እንደተባለው ያላቸውን ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል ሲያጡ፣ ሲገፈፍባቸው የማይችሉባቸው አጋጣሚዎችም አሉ ብለን (በድፍረትም ባይሆን) መናገር እንችላለን፡፡ ለምን ቢሉ ባለጋኑ አረቄውን ከጠጣ በኋላ የለመኑትን መስጠቱ፣ ባካባቢው ላይ ዝናብ ማዘነቡ በጽሑፉ ተጠቅሷልና ነው፡፡ አረቄ በቡርጂ የባሻ ሥርዐት ላይም ቢሆን ጥንት እንደማይቀርብ፣ ዛሬ ዛሬ ግን መቅረብ መጀመሩ ይነገራል፡፡

አይበሉም፡፡ ከቤታቸው አይወጡም፡፡ ከሌላ ሰው ቤት አይሄዱም፡፡ ቢሄዱም ባገኙበት አይቀመጡም፡፡ ከረዳቶቻቸውና ከሚስታቸው ካልሆነ በስተቀር ከሌላ ከማንም እጅ ተቀብለው አይበሉም፡፡ አይጠጡም፡፡ ሌላ ሰው በበላበትና በጠጣበት ዕቃ እንዲበሉ፣ እንዲጠጡ አይፈቀድላቸውም፡፡ ማመንዘርም ለባለጋኖች የተከለከለ ነው፡፡ ከእነዚህ አንዱን ወይም ሁሉን ቢፈፅሙ ወይም ቢያጎድሉ በላያቸው ላይ ያለው ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል ይረክሳል፡፡ ከላያቸው ላይ ይገፈፋል ተብሎ ይታመናል፡፡ እንዲሁም ባለጋኖቹም ሆኑ ሚስቶቻቸው (ወናዋ) የጉልበት ሥራ እንዲሰሩ አይፈቀድላቸውም፡፡ እርሻ አያርሱም፡፡ እህል አይፈጩም፡፡ አብዛኛውን የጉልበትም ሆነ እነርሱ እንዳይሰሩ የሚከለከሉ ሥራዎችን ሕዝቡ ይሰራላቸዋል፡፡

ባህላዊ የህዝብ መሪዎች በማንኛውም ጦርነት ውስጥ  እንዲሣተፉ ቀርቶ የጦር መሣሪያዎችን እንዲይዙ የቡርጂ ባህላዊ ደንብ አይፈቅድላቸውም፡፡ በባህላዊ ደንቡ መሰረት በአካባቢው ጦርነት የተቀሰቀሰ እንደሆነ የህዝብ መሪዎቹ ከቀዬአቸው ሆነው ወደ ጦርነቱ የሚሄዱትን አንዳች እንዳያገኛቸው፣ በድል እንዲመለሱ ከመመረቅ፣ ጦርነቱን ከማውገዝ ውጭ ወደ ጦርነቱ መሄድ፣ በጦርነቱ ውስጥ መሳተፍ አይችሉም፡፡ ይህ የሚሆነው፣ አንድ የህዝብ መሪ የሆነ ሰው በጦርነቱ የተሣተፈ፣ ሄዶ የተዋጋ እንደሆነ ጦርነቱ ከመርገብ ይልቅ ይፋፋማል፤ ይብስበታል እንጂ ፈጽሞ አይበርድም ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ይህንንም በቅርብ ጊዜ ውስጥ ከተፈጸመው፣ በእውነት ከሆነውና ባለጋን[72] የሆነው ሰው ከሚተርክልን ከሚከተለው እውነተኛ ታሪክ መረዳት ይቻላል፡፡

> በአንድ ወቅት እኛ ቃፌር ወጥተን በጥበቃ ላይ በነበርንበት ሌሊት፣ በድንገት ጦርነት ተከፈተብን፡፡ እኔ ጠብመንጃም ነበረኝ፡፡ ጠላት ጦርነቱን አፋፋመብን፡፡ ሌሊቱን ሙሉ ስንቷከስ፣ ስንዋጋ አደርን፡፡ በማግስቱም እንዲሁ ቀኑን ሙሉ ስንዋጋ፣ ስንቷከስ ዋልን፡፡ ጠላት ግን ንቅንቅ አልል አለ፡፡ በሚቀጥሉት ቀናትም ተጋጥመን እንዳደርን ተጋጥመን ዋልን፡፡ ጦርነቱ አልበርድ አለ፡፡ ጠላት በዚህ ስንዘጋበት በዚያ አልፎ ይተኩሳል፡፡ እንደ ወትሮው ሁሉ፣ ጦርነቱ ከአንድ፣ ከሁለት፣ ከሶስት ሰዓታት ውጊያ በኋላ ከመብረድ ይልቅ እየተፋፋመ፣ እየተጋጋለ ይሄድ ጀመር፡፡ ህዝቡ ምን እንዳሰበ አላውቅም፡፡ ከማሻው ጋር ከተነጋገሩ በኋላ ተኝቼ ከምዋጋበት ሥፍራ፣ ከተፋፋመው ጦርነት መሀል ተጠርቼ ወጣሁ፡፡ ከሹሞቹ ዘንድ እንደደረስኩ ‹‹እስቲ አንተ ከሠፈር፣ ከቤት ዋል፡፡ የአንተ ወደ ጦርነቱ መሄድ፣ በጦርነቱ ውስጥ መሳተፍም ሆነ መዋጋት ለእኛ አልተመቸንም›› አሉኝ፡፡ ‹‹ኧረ ወዲያ በሉ! እኔ ከሰፈር እምውለው አርጅቼ ነው?›› በማለት መለስኩላቸው፡፡ በሌላ ቀን ደግሞ ሌላ መልዕክት ተላከብኝ፡፡ ‹‹የህዝቡ ከፍተኛ ሹማምንት ‹እሳይ እኛ ዘንድ ይምጣ፡፡ ወደ እኛ ይምጣ› ብለውሃል›› ተባልኩኝ፡፡ ቀጠሉና ‹‹ጠብመንጃህን ለልጅህ ስጠው›› አሉኝ፡፡ ጠብመንጃዬን ለልጄ ሰጥቼ ወደ ተጠራሁበት፣ ወደ ከፍተኛ የህዝብ ሹማምንት ዘንድ ወጣሁ፡፡ ሹማምንቱም ‹‹ከዛሬ ጀምረህ ወደ ጦርነት አትሂድ፡፡ እሳይ ከደጋው ወዳለው ወደ አባትህ፣ ወደ ቤተሰቦችህ ዋና ግቢ ሂድ፡፡ ከዚያ ያለውን የአባትህን ቃራ (ጦር) አንሳ፡፡ እሱን

---

[72] ባለ ታሪኩ (ታሪኩን የሚተርክልን) በእርግጥ አሁን ባለጋን ነው፡፡ ጦርነቱ ውስጥ ከመሳተፉ በፊት ግን ባለጋን አልነበረም፡፡ ቡርጂ ውስጥ ጋን አላቸው ተብለው ከሚታመነው ከባንባላ ጎሳ ቢወለድም፣ አባቱ ከመሞታቸው በፊት ባለጋን የነበሩ ቢሆንም፣ እሱ ግን ባለጋን አልነበረም፡፡ በአባቱ እግር ተተክቶ ባለጋን አልሆነም፡፡ ሥርዐቱን አልፈጸመም፡፡ ይህን እንዲያደርግም ህዝቡ በወቅቱ አላስገደደውም ነበር፡፡ ሕዝቡ ያስገደደው፣ እሱም በአባቱ እግር ተተክቶ ባለጋን የሆነው ግን ከዚህ፣ ከሚተረከው ጦርነት በኋላ ነው፡፡

> ይዘህ ከእኛ ጋር፣ እዚያ ከተራራው ላይ ቁም። እንዲህ ሆነን እንለቅ? እውነተኛው የቤተሰቦችህ እምነት፣ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል (ጋን) በአንተ ውስጥ ያለ እንደሆነ እዚህ ቆመን እንናገርና እንይ›› አሉኝ። ሹማምንቱ ባሉኝ መሰረት የዚያኑ ዕለት ደጋ ካለው ከቤተሰባችን ዋና ግቢ ወጣሁ። የአባቴንም ቃራ (ጦር) ከተቀመጠበት አንስቼ ወሰድኩ። ጦሩን በቅቤ ካሻሸሁት፣ ከቀባባሁት (ኣጋዲ) በኋላ ይዤው ወደ አሮጊቷ፣ ወደ እናቴ ሄድኩኝ። የሆነውን ሁሉን ነገርኳት። እሷም ‹‹እንዲህ ማለታቸው ትክክል ነው። ያሉት ሁሉ ትክክል ነው። ትላንትና የእኔ አባት እኔን እዚህ ቤት፣ ለአባትህ ሲድረኝ ‹የጋን ቤት ነው› ብሎ፣ ለዚህ ዓይነቱ ነገር ነበር። ልጄ ወደ ጦርነቱ እንዳትሄድ ማገዳቸው ጥሩ አደረጉ። የህዝብ መሪዎች እንዳሉህ፣ አንተ ወጥተህ ህዝቡን ከመረቅህና ጦርነቱን ከአወገዝክ በኋላ ጠላት አልፎ መጥቶ ህዝብ የሚኖርበትን ቀዬ የተቆጣጠረ እንደሆነ፣ ልጄ በእርግጥም አልተመረቅህም፣ በረከቱ የለህም ማለት ነው። በል ቶሎ ብለህ ጦርህን ቅቤ ቀባባና ሄደህ መርቅ። አውግዝ›› ነበር ያለችኝ። እንዲህ ሲትለኝ ‹‹እሺ። ከጦሩ ላይ እንትፍ በይበት›› አልኳት። ‹‹እንትፍ›› አለችበት። ቅቤ አውጥታም ‹‹ይኸውልህ!›› ብላ ሰጠችኝ። ከዚያ በኋላ ቃራውን (ጦሩን) ይዤ፣ የህዝብ መሪዎችን አስከትዬ፣ ባህላዊ ሥርዓቱ ወደሚፈፀምበት ሥፍራ፣ ወደ ተራራው ሄድኩኝ። ከዚያ ሄጄ ጦርነቱን አወገዝኩኝ። ህዝቡን መረቅሁኝ። ከዚያን ቀን ጀምሮ ጦርነት የሚባል ነገር አላየሁም። የለም። ጠላትም መጥቶም ሆነ ቶክሶብን አያውቅም። ይህን የተመለከቱት የህዝብ መሪዎችም ‹‹ይህ እያለ ነበር ልንጠፋ የነበረው። በፊቱኑ ጀምረን ወደ ጦርነቱ እንዳትሄድ በከለከልንህ ኖሮ›› አሉ። ከዚያን ጊዜ ጀምረው ወደ ጦርነት እንዳልሄድ፣ ለጥበቃ እንዳልወጣ፣ አንዳች ሥራ እንዳልሰራ ተከለከልኩ። እኔም ሄጄ አላውቅም (ጫሜ፣ 2002፣ 61-63)።

ባህላዊ መሪዎች እስከ ስልጣን ዘመናቸው መጨረሻ ድረስ ጸጉራቸውንና ጽማቸውን አይቆረጡም። አይላጩም። የመሪዎች ፀጉር ለህዝቡ ጥላ ከለላ ነው። መሬት የሚቀዘቅዘው፣ ዝናብ የሚዘንበው በእነርሱ የጸጉር ጥላ አማካይነት ነው። ፀጉራቸው ከተመለጠ ግን የሕዝቡ ጥላ ይገፈፋል፣ ሀገሪቷ ምድረ በዳ ትሆናለች ተብሎ ይታመናል። ንጣት ወይም ነጭ ቀለም ለቡርጂ የድርቀት፣ የረሃብ፣…ባጭሩ የክፉ ነገር ተምሳሌት ነው። በአንጻሩ ደግሞ ጥቁረት ወይም ጥቁር ቀለም የዝናብ፣ የደመና፣ የልምላሜ ትዕምርት ነው ተብሎ ይታመናል (የግርጌ ማስታወሻ ቁ. 40፣ተመልከት)። ስለሆነም የህዝብ መሪዎች ጠቆርና ደብዘዝ ያሉትን እንጂ፣ ነጣ እና ደመቅ ያሉ ልብሶችን እንዲለብሱ አይፈቀድላቸውም።

ሁሉም መሪዎች እነዚህን ባህላዊ ደንቦች አክብረው እንዲሰሩ ይጠበቃል። ይህን እግድ፣ ባህላዊ ደንብ የተላለፈ መሪ በሥልጣኑ ላይ እንዲቆይ አይፈቀድለትም። ከሥልጣኑ እንዲወርድ ይደረጋል። በምትኩ ሌላ ሰው ይሰየማል። ይህ የሚፈፀመው በጎርሶማው አማካይነት ሲሆን የቡርጂ ህዝቦች ለዚህም የአፈጻፀም ደንብ ሥርዓት አላቸው። ሥርዓቱም የሚከተለውን ይመስላል።

ከሁሉም በፊት ከፍ ሲሉ የተመለከቱ ባህላዊ ደንቦችንና ገደቦችን የሚጥስ መሪ ከድርጊቱ እንዲቆጠብ በአማካሪዎቹ ይመከራል። ወደ ትክክለኛው መንገድ እንዲመለስ በተደጋጋሚ ይነገረዋል። የአማካሪዎችን ምክር ተቀብሎ ተግባራዊ ካደረገ መልካም። ምክራቸውን ካልተቀበለ፣ ወይም ተቀብሎ ተግባራዊ ካላደረገ ወይም ባህላዊ ደንቦችን ባይተላለፍም በሥልጣን

ዘመኑ አካባቢው በድርቅ የተመታ፣ ህዝብ የተራበ እንደሆነ፣ በአጭሩ ‹‹ገዱ ለህዝቡ መልካም አልሆነም›› ተብሎ የታመነ እንደሆነም መሪው ከሥልጣኑ እንዲወርድ ይደረጋል፡፡ ለዚህ ሲሉም ጎርሶማውን ጉባኤ እንዲጠራ ለራሱ፣ ለመሪው ይነግሩታል፡፡ ጎርሶማው ሲሰበሰብም አንዱ (ብዙውን ጊዜ ኣንሽ) ተነስቶ ‹‹እገሌ ሆይ! እስከዛሬ ድረስ ለህዝቡና ለሀገሩ ስትል ብዙ ለፋህ፡፡ ብዙ ደከምክ፡፡ ቤተሰብህን፣ ሥራህን ጣልክ፡፡ ለዚህ መልካም ተግባርህ እግዚአብሔር ይስጥህ፡፡ እስካሁን ያገለገልከን፣ የደከምክልን ይበቃናል፡፡ ከዛሬ ጀምረህ አንተ ከቤትህ ቁጭ እንድትል፣ ቤተሰብህን እንድትንከባከብና በምትክህ ሌላ መሪ ልንሰይም አስበናልና አንተ ምን ትላለህ?›› በማለት መሪውን ይጠይቁታል፡፡ ይህን እንዲሉ ያበቃቸውንም ምክንያት ዘርዝረው ያስረዱታል፡፡ እሱም ቢሆን አያንገራግርም፡፡ ሀሳባቸውን አይቃወምም፡፡ ይልቅ ‹‹ካላችሁ እሽ ደግ ነው፡፡ በምትኬ ያሻችሁትን ሰው ሰይሙ፡፡ እኔም እንደ ሌላው ሰው ሁሉ በእሱ ሥር እተዳደራለሁ›› ይላል፡፡ ይህን ጊዜ ቢታናች የሆነው ሰው ከጉባኤተኛው መካከል ይነሣና ሣር ነጭቶ በአንዱ ራስ ላይ ይነሰንስበታል፡፡ በዚህም በቀድሞው መሪ ምትክ የተሰየመውን፣ አዲሱን የህዝብ መሪ ማንነት ያስተዋውቃል፡፡ በዚህ መልክ ሹም ሽሩ ይፈፀማል፡፡

ባህላዊ ደንቡን የጣሰው፣ ገደቡን የተላለፈው ባለጋን የሆነ እንደሆነ፣ ከሥልጣን ማውረዱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሌላም እርምጃ ይወሰድበታል፡፡ የባለጋኖች ተግባር ለሕዝብ የሚበጀውን፣ ደግ ደጉን መሥራት ነው፡፡ በዚህም፣ በማህበረሰቡ ችግሮች ላይ ፈጥነው ይደርሳሉ፡፡ ደርሰው ከሕዝብ ችግሮች ጋር ፊት ለፊት ይጋፈጣሉ፡፡ ህዝቡን ከችግር ይታደጋሉ፡፡ በአጠቃላይ ባለጋኖች በማናቸውም ነገሮች ላይ ያላቸው ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው፡፡

ይሁን እንጂ፣ እንደፈ ለጉ እንዲሆኑ ህዝቡ አይፈቅ ድላቸውም፡፡ ህዝቡ ይቆጣጠራቸዋል፡ ፡ ተግባሩን በአግባቡ መወጣት ያልቻለ ባለጋን ይታመጽበታል፡፡ ህዝብ በነቂስ ወጥቶ ተቃውሞውን ይገልፃል፡፡ በእሱ ምክንያት ህዝቡ የተራበ እንደሆነ፣ ‹‹አንተ እያለህ እኛ የምንራበው ለምንድነው?›› ብለው ግቢውን ይወሩታል፡፡ ቤቱን ያፈራርሱበታል፡፡ ንብረቱን ይበታትኑበታል፡፡ ግቢውን፣ መንደሩን ቀውጢ ያደርጉታል፡፡ ሽብር ያስነሳሉ፡፡ ይህን ጊዜ የባለጋኑ ቤተሰቦች ይሸበራሉ፡፡ ባለጋኑም ወደ ትክክለኛው ተግባሩ ይመለሳል፡፡ ወደ ትክክለኛው ተግባሩ ካልተመለሰ ከዚህም አልፎ ህዝቡ ከስልጣኑ ሊያወርደው፣ ከማህበረሰቡ ሊያገለው ሁሉ ይችላል፡፡ በአጭር አነጋገር፣ በማህበረሰቡ ዘንድ ከጥሩ ተግባሩ ይልቅ በክፉ ተግባሩ የሚታወቅ ወይም ለማህበረሰቡ የሚጠቅም ነገር ከመስራት ይልቅ የሚጎዳ ተግባር የሚፈጽም ባለጋን ሲኖር ህዝቡ ዝም አይለውም፡፡ እንዳሻው እንዲሆን ዕድል አይሰጠውም፡፡ ከሥልጣኑ ያወርደዋል፡፡ ጫን ሲልም ከማህበረሰቡ እንዲገለል ሊያደርገው ይችላል፡፡

## 6. ማጠቃለያና ይሁንታ

ቡርጂ በደቡብ ኢትዮጵያ ከሚገኙ ብሔረሰቦች መካከል አንዱ ነው፡፡ በዋናነት ከአዲስ አበባ በ545 ኪ.ሜ ርቆ በሚገኘው በቡርጂ ልዩ ወረዳ ውስጥ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ በልዩ ወረዳው የሚኖረው የቡርጂ ህዝብ ብዛት 56523 ነው፡፡ ከዚህ ውጭ በሌሎች የኢትዮጵያ ክልሎች ውስጥ ደግሞ 15348 ቡርጂዎች ይኖራሉ፡፡ በዚህ መሰረት በጠቅላላው 71871 ቡርጂዎች በኢትዮጵያ ውስጥ አሉ፡፡ ከኢትዮጵያ ውጪ፣ በኬንያም በርካታ ቡርጂዎች ይገኛሉ፡፡ ግብርና የህዝቡ ዋነኛ መተዳደሪያው ነው፡፡

የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደር የጎሣ፣ *የሆግ* እና ክልላዊ በሚባሉ በሦስት አስተዳደራዊ ተቋማት የተዋቀረ ነው፡፡ ክልላዊ ተቋሙ ደግሞ *ጉል ጉባ፣ ጋሪንታ ቢያ፣ ቢያ፣ ቦሄ፣ ገሪኤና ኦላ* በሚባሉ በሌሎች የአስተዳደር ክፍሎች የተዋቀረ ነው፡፡ እንዲሁም በደረጃ የተዋቀሩ አራት የሕግ አውጪ ተቋማት *(ጎርሶማዎች)* እና ስድስት ወይም ሰባት አስፈፃሚ ተቋማት አሉ፡፡ የቢያም ሆነ ሌሎች አብዛኞቹ አስተዳደራዊ ተቋማት እርስ በርሳቸው ቀ ጥተኛ የሆነ ግንኙነት የላቸውም፡፡ ከሁሉም ጋር ቀጥተኛ ብቻ ሳይሆን የጠበቀ ግንኙነት ያለው የጎሳ አስተዳደራዊ ተቋም ብቻ ነው፡፡ የጎሳ አስተዳደራዊ ተቋም የቡርጂን ባህላዊ የፖለቲካና የእምነት ተቋማትን የሚያገናኝ ድልድይ ነው፡፡

በቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር ታሪክ ቀዳሚው የጎሳ አስተዳደራዊ ተቋም ነው፡፡ ቀጣዩ ደግሞ *የሆግ* ተቋም ነው፡፡ ከዚያም ክልላዊ አስተዳደር ይቀጥላል፡፡፡ ከክልላዊ አስተዳደር ውስጥ ደግሞ ቀዳሚው *የወማ* አስተዳደር ነው፡፡ የቡርጂዎች *የወማ* አስተዳደር ታሪክ የሚጀምረው *በጎዳ ወማ* ነው፡፡ ይሁን እንጂ ባህላዊ የአስተዳደር *ሥርዓቱ* እጅግ በተደራጀና *ሥርዓታዊ* በሆነ መንገድ መካሄድ የጀመረው ግን *ባሻ* የሚባለው የስልጣን አሰጣጥ *ሥርዓት* ከተጀመረ በኋላ ነው፡፡

*ባሻ* ወደ ስልጣን የሚመጡ የቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር ባለስልጣናት ስልጣናቸውን የሚያጸድቁበት፣ በይፋ የሚረከቡበት፣ ምርቃትና በረከት ከሕዝብ የሚቀበሉበት ወይም ወደ ስልጣን የሚወጡበት ስርዓት ነው፡፡ *ወማ፣ ዳይና፣ ፊዜ፣ ማሻ፣ ጋና እና ጃልዓባ* የሚባሉ የሕዝብ መሪዎች በምርጫና በባሻ *ሥርዓት* ወደ ስልጣን የሚመጡ ባሕላዊ መሪዎች ናቸው፡፡ መመዘኛው ደግሞ በዋናነት ሀብት ሲሆን የንግግር ችሎታ፣ ባህላዊ ዕውቀት፣ የሕዝብ ድጋፍ፣ የጎሳ ተገቢነት፣ በሕዝብ ዘንድ ያላቸው ተሰሚነት... ወዘተ ደግሞ ከሀብት ቀጥለው የሚመጡ መስፈርቶች ናቸው፡፡

*ወማ* ቡርጂን በሙሉ ለሚያስተዳድር ሰው የሚሰጥ ስልጣን ነው። ዳይና ከወማ ቀጥሎ የሚመጣ ሥልጣን ሲሆን በዓይነት ሦስት ናቸው። አንደኛው፣ *ጋሪንታ ዳይና የሚባለውና ከወማ* ዝቅ ብሎ ከስምንቱ የቡርጂ የቢያ አስተዳደሮች መካከል አምስቱን የሚያስተዳድር ሹም ነው። ሁለተኛው *ሼይሸንታ ዳይና* የሚባለው *ዳይና* ሲሆን ከስምንቱ የቢያ አስተዳደሮች *ሀና* የሚባለውን፣ አንዱን *ቢያ* ብቻ የሚያስተዳድር ሹም ነው። ሦስተኛውም እንዲሁ *ላዋጋ* የተባለውን አንድ *ቢያ* ብቻ ለሚያስተዳድር ሹም የሚሰጥ ማዕረግ ነው። *ፊዜ በማሻ* ማዕረግ *ለቢያ* አስተዳዳሪ የሚሰጥ ስልጣን ነው። በአብዛኞቹ የቡርጂ አካባቢዎች፣ ማሻ አንድን ቦሄ ለሚያስተዳድር ሰው የሚሰጥ ሥልጣን ሲሆን፣ በተወሰኑ አካባቢዎች ግን፣ *ለወማ* ወይም *ለዳይና ረዳት* ሆኖ ለሚሰራ ሰው ይሰጣል። *ጋና፣ የወማ* እና የዳይና ረዳት ሲሆን፣ *ጃልዓባ* ደግሞ *የወማ፣ የዳይና* እና *የማሻ (የፊዜ)* አማካሪና ረዳት ሆኖ የሚሰራ ሹም ነው።

*በባሻ* ስርዓት ወደ ስልጣን የሚመጡ ሁሉም ባለስልጣናት በስልጣን ላይ የሚቆዩት ለአንድ ዓመት ብቻ ነው። ይሁን እንጂ ከወማው በስተቀር ሌሎቹ ባለሥልጣናት፣ በስልጣን ዘመናቸው መልካም የሰሩ እንደሆነ፣ ለሌላ ተጨማሪ አመት እንዲያገለግሉ ይደረጋል። ተቃራኒውን ካደረጉ ደግሞ የስልጣን ዘመናቸው ሳይጠናቀቅ ከስልጣን እንዲወርዱ የሚደረጉበት ሁኔታም አለ። ወደፊት በሕዝቡ ላይ ይደርሳል የተባሉ ክፉ አጋጣሚዎችን፣ ማለትም በሽታን፣ ጦርነትን፣ ረሃብን፣ ወዘተ. እንዳይደርሱ፣ የደረሱም እንደሆነ ጉዳት ሳያደርሱ እንዲወገዱ ማድረግ፣ ወዘተ. የሁሉም ባህላዊ የአስተዳደር መሪዎች ዋነኛ ተግባር ነው። ይሁን እንጂ አንዳቸውም ከአያት ከቅድመ አያታቸው የወረሱት ወይም ከፈጣሪ የተቸራቸው ልዕለ ፈጥሮአዊ ኃይል (Super Natural Power) የላቸውም። ይህን ኃላፊነታቸውን የሚወጡትም *በባለጋኖች*፣ በተንባዮችና በጠንቋዮች በመታገዝ ይሆናል። ግጭቶችን ማርገብ ሌላው ተግባራቸው ነው። *ካላቻ* እና *ሊሶ* የሁሉም ባህላዊ መሪዎች መለያ ምልክታቸው፣ *ዳዋና* የክብር ዘፈናቸው ሲሆን *ግላንግሌ* ደግሞ የክብር ልብሳቸው ነው።

*ሃዩ* በተገረዙ ወጣት ወንዶች የተገነባውንና ሀግ የሚባለውን ተቋም የሚመራ ከፍተኛ ሹም ነው። *ሃዩ የሀግ መሪ*፣ የመከላከያ ተጠሪ ነው። *ኣርጉማንቾ* ደግሞ የእሱ ረዳት ነው። ዋንኛ ተግባራቸውም የሕዝቡን ደህንነትና የሀገሪቷን ዳር ድንበር ማስጠ በቅና መጠበቅ ሲሆን ስልጣናቸውም የዕድሜ ልክ ነው።

*ኣንሽ* የጎሳ መሪ ነው ። ማናቸውም የጎሳው *ፖለቲካዊ* ተግባራት የሚከናወኑት በእሱ አማካይነት ነው። ሕዝቡ የሚተዳደርበትን ባህላዊ ደንብ (ሕግ) የሚያወጡት የጎሳ መሪዎች

*(ኣንሾች)* ናቸው። አስፈፃሚ አካላትን የሚቆጣጠሩትም ኣንሽ የሆኑ ሰዎች ናቸው። በአጭሩ በቡርጂ *የፖለቲካና የእምነት ስርዓት ውስጥ ኣንሽ የማይገባበት ቦታ የለም። ኣንሽን የማይመለከት፣ ኣንሽ* ሳያውቅ የሚፈጸም አንዳች ነገር የለም።

*ጋን* የቡርጂ እምነት ነው። ቡርጂዎች ከአያት ከቅድም አያት የተሰጠን፣ ከፈጣሪ የተቸረን ጸጋ ነው ብለው የሚያምኑትን ልዕለ ተፈጥሯዊ ኃይል የሚጠሩበት ስም ነው *ጋን*። ይህ ልዕለ ተፈጥሯዊ ኃይል ያደረባቸው ሰዎች (ባለጋኖች) ደግሞ *ወማ፣ ቃሉ* ወይም *ወነይ* ይባላሉ። የማህበረሰቡ *መንፈሳዊ መሪ* በመሆንም ያገለግላሉ። ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል ስላላቸውም በሕዝቡ ችግሮች ላይ ፈጥነው ይደርሳሉ። ደርሰው ከችግሮቹ ጋር ይጋፈጣሉ። ሕዝቡን ከችግር ይታደጋሉ። በዚህም በሕዝቡ ዘንድ ይፈራሉ፣ ይከበራሉ። እንደ ቅዱስ ይቆጠራሉ። ይህም ሆኖ ግን ሕዝቡ ይቆጣጠራቸዋል። ሕዝቡን በሚገባ ያላገለገለ፣ ለህዝቡ መልካም ከመስራት ይልቅ ሕዝቡን የሚጎዱ ተግባራትን በሚያከናውኑ ባለጋኖች ላይ ሕዝቡ ያምጹባቸዋል። አምጸው ወደ ትክክለኛው ተግባራቸው እንዲመለሱ ያደርጓቸዋል። ወይም ደግሞ ከስልጣን ያስወግዷቸዋል። ጫን ሲልም ከማህበረሰቡ ያገሉዋቸዋል።

ቡርጂ ውስጥ በጠቅላላው አስራ ሁለት *ባለጋኖች* አሉ። ሁሉም የሚጠሩት በጎሳ ስም ነው። እያንዳንዳቸው ከአያት ከቅድመአያቶቻቸው የወረሷቸው የየራሳቸው ሰማያዊ ፀጋና ኃይል አላቸው። ሁሉም ላለበት አካባቢ ንጉስ፣ ቄስ ወይም ጌታ ነው። ሙሉ ቡርጂን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ግን *ባንባልንካ ጋን* ከሁሉ ፊት ይሆናል። ይሁን እንጂ በቡርጂ የእምነት መዋቅር ውስጥ አለቃና ምንዝር የለም። ማዕከላዊነት ብሎ ነገር የለም። ሁሉም እራሱን ችሎ የሚሰራ እንጂ፣ ከላይ የተቀመጠለት አዛዥ፣ የሚፈስለት ትዕዛዝ የለም።

በጋን የእምነት ተቋም ውስጥ የሚሰሩ አራት አባላት አሉ። አንደኛው ራሱ *ባለጋኑ* ሲሆን ሌሎቹ *ቢታናች፣ ኣላልች* እና *ቦክ* ናቸው። ባለጋን ወደ ስልጣን የሚመጣው በዘር ሐረግ፣ ከአባት ወደ ልጅ ነው። በድሮ ጊዜ፣ በአንድ ጎሳ ውስጥ ወደፊት ባለጋን የሚሆን ሰው ገና ሲወለድ በእጆቹ የወይራ ቅጠል፣ *ዳና* የሚባል ሣርና እህል (ስንዴ) ይዞ ይወለዳል ይባላል። ዛሬ ግን ይህ እምነት የለም። የባለጋን ዋነኛ ተግባርም መመረቅ፣ መባረክና ‹‹ማውገዝ›› ብቻ ነው።

*ቢታናችና ኣላልች* የቡርጂን እምነታዊ ስርዓት የሚያራምዱ፣ የሚቆጣጠሩ፣ የተዛባውን የሚያቃኑ፣ *ለባለጋን* ረዳት ሆነው የሚያገለግሉ ባለስልጣናት ናቸው። *ቢታናች* ግን ስልጣን የሚይዘው በምርጫ ሲሆን የአገልግሎት ዘመኑም እንደየአካባቢው ይለያያል። ቢታናች በቡርጂ

የፖለቲካና የእምነት ተቋማት ውስጥ ቁልፍ የሆነ ሰው ነው። ሁለቱን ተቋማት የሚያገናኝ፣ በሁለቱ ተቋማት መካከል የተዘረጋ ድልድይ ማለት ነው - *ቢታናች* ማለት።

ሌሎች የቡርጂ ባህላዊ እምነቶችና እምነታዊ ስርዓቶች የሚመነጩት ከጋን እምነት ነው። በዚህ ዓይነት መሠረታቸው፣ ምንጫቸው ጋን ከሆናቸው የቡርጂ እምነታዊ ስርዓቶች መካከል *ሐጣኖ፣ ሞጩ፣ ጎዴና ቦርቶማ* ተጠቃሾች ናቸው።

*ሐጣኖ* ቡርጂዎች ቦርዴን ወይም ደምን በኤሣ ላይ በመርጨት ለሙታን ሰዎች የሚያቀርቡት የመስዋዕት ስርዓት ነው። ዋና አላማውም ሟች ወገኖቻቸውና አምላካቸው አዲሱን ዓመት የሰላም፣ የደስታ፣ የብልጽግና፣ የጤና እንዲያደርጉላቸው መለመን ነው።

*ሞጩ* ሰውን ወይም ዕቃን ከእርኩሰት የማንጻት ስርዓት ነው። *ሥርዓቱም* ውሃን በሰዎች ላይ በመርጨት ወይም የሰዎችን አፍ በበግ ፈርስ በመጥረግ ይፈፀማል። ሌላው *ጎዴ* የሚባለው እምነታዊ ስርዓት ነው። *ጎዴ* ቡርጂዎች ‹‹ወደ ፊት በሕዝቡና በአካባቢው ላይ ይደርሳል›› የተባለን ክፉ አጋጣሚ ከወዲሁ ከራሳቸው ላይ ለመከላከል፣ በሌላው ላይ እንዲደርስ ሲሉ የሚፈጽሙት የመተት ስርዓት ነው። ሌላው *ቦርቶማ* የሚባለው እምነታዊ ስርዓት ነው። *ቦርቶማ* ማለት ማስማ ማት፣ ማፋቀር፣ ማ ዋደድ ወይም አንድ ማድረግ ማለት ሲሆን የሚፈፀመው የተጋጩና የተገዳደሉ ሁለት ጎሳዎች (ወገኖች) በሽምግልና ተቀራርበው ከታረቁ በኋላ ነው። ዋና አላማውም ሁለቱ ወገኖች ለወደፊቱ በክፉ እንዳይፈላለጉ በመሃላና በዝምድና ማሰሪያ ማበጀት ነው። በዚህም ሁለቱ ጎሳዎች *አምቦ* (አንድ ጎሳ አንድ ቤተሰብ) ይሆናሉ። እርስ በርስ አይጋቡም። እነዚህ እምነታዊ ስርዓቶች በሙሉ ከቡርጂ ባህላዊ አስተዳደር ጋር ተያይዘው የሚፈፀሙ ሲሆኑ፣ የሚፈጽሟቸው ደግሞ የፖለቲካና የእምነት መሪዎች ናቸው።

በባሕላዊ የአስተዳደርና የእምነት *ሥርዓት* ውስጥ የሚመደቡ ወይም የሚሾሙ መሪዎች አስተዳደራቸው አምባገነን ወይም ጨቋኝ እንዳይሆን በሚል የተበጁ የቁጥጥር *ሥርዓቶች*፣ የተጣሉ ገደቦችና አሉ። በዚህም ወደ *ሥልጣን* የወጡ ባህላዊ መሪዎች የ*ሥልጣን* ዘመናቸው እስከሚጠናቀቅ ድረስ ከቤታቸው፣ ከቀዬአቸው አይወጡም፣ ቢወጡም ርቀው መሄድ፣ ቢሄዱም በሄዱበት (ከቡርጂ ውጭ ማለት ነው) ማደር፣ መሽናት ወይም መፀዳዳት፣ መታጠብ፣ ወዘተ. አይፈቀድላቸውም። ከቡርጂ ውጪ ሄደው ካደሩ፣ ከታጠቡ፣ ከተፀዳዱ ወይም ከሸኑ በላያቸው ላይ ያለው የሕዝቡ ፀጋ፣ ሲሳይ፣ በረከት፣ ምርቃት፣ አዱኛ፣ ወዘተ. ከላያቸው ላይ ይገፈፋል፣ ለዚያ ለአደሩበት፣ ለታጠቡበት፣ ለተፀዳዱበት ወዘተ ሀገርና ሕዝብ ይሆናል ተብሎ ይታመናል።

ሁሉም ባህላዊ መሪዎች ያገኙትን ሁሉ አይመገቡም፡፡ ባገኙበት አይቀመጡም፡፡ በጦርነት ውስጥ ከተሣተፉ ጦርነቱ አይበርድም ተብሎ ስለሚታመን በማንኛውም ጦርነት ውስጥ እንዲሳተፉ አይፈቀድላቸውም፡፡

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው፣ ይህ ጥናት የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደርንና እምነትን በተለይም ከአስተዳደር ስርዓት ጋር ተያይዘው የሚፈፀሙ እምነታዊ ስርዓቶችን ለማሳየት የሞከረ ነው፡፡ በጥናቱ ሂደቶች ውስጥም በርካታ ነገሮች፣ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ተወስተዋል፡፡ ከዚህ በመነሳትም የሚከተሉት ይሁንታዎች ቀርበዋል፡፡

- ለዚህ ጥናት ከ20 እስከ 90 የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ የተለያዩ እምነት ተከታይ የሆኑ የብሔረሰቡን አባላት አነጋግሬያለሁ፡፡ የቃል መጠይቅ፣ የቡድን ውይይት አድርጌአለሁ፡፡ በሥርዓቱ ውስጥ ተሣትፈው ያለፉትንና በመሣተፍ ላይ ያሉ ባህላዊ መሪዎችን ጭምር ስለ ቡርጂ ባህላዊ አስተዳደርና እምነት አነጋግራቸዋለሁ፡፡ በዚህም፣ አብዛኞቹ ቡርጂዎች ባህላዊ ስርዓቱን ጠንቅቀው እንደማያውቁ፣ የሚያውቁትንም እየረሱ መሆናቸውን ተገንዝቤያለሁ፡፡ ሥርዓቱን ጠንቅቀው የሚያውቁትም በጣት የሚቆጠሩ ጥቂት አዛውንቶች ብቻ ናቸው፡፡ እነሱም ቢሆኑ ጥቂት የቀሩቸው፣ ዕድሜያቸው ከ70 በላይ የሆናቸው ናቸው፡፡ እነርሱ ካለፉ ስለ ትናንቱ የቡርጂ አጠቃላይ ባህል የሚተረክና የሚፃፍ ብዙ ላይኖር ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ የማህበረሰቡ አዛውንቶች (በሌላ አገላለጽ ያልተፃፉ የቡርጂ የእውቀት መዛግብት) ዕውቀቱን ይዘው ከማለፋቸው በፊት የሚያውቁትን ጠይቆ፣ የሚነግሩትን ቀርሶ ማስቀመጡ ጊዜ ባይሰጠው፣ ከዛሬ ቢጀመር ጥቅም እንጂ ጉዳት አይኖረውም፡፡
- የቡርጂ ሕዝቦች የራሳቸውን የእምነትና የአስተዳደር ስርዓት ዘርግተው በእርሱ መተዳደር ከጀመሩ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ይሁን እንጂ ይህን ባህላዊ ስርዓት አብዛኞቹ ቡርጂዎች፣ በተለይም ፊደል የቆጠሩት ወይም የአሁኑ ትውልድ በሚገባ የሚያውቅ አይመስለኝም፡፡ እነዚህ ባለጋኖችም ሆኑ በየዓመቱ ወደ ስልጣን የሚወጡትና ከሥልጣን የሚወርዱት ባህላዊ የፖለቲካ መሪዎች በሥልጣን ዘመናቸው ምን እንደሚሰሩና እንዴት እንደሚሰሩ ልብ ያሉ አይመስለኝም፡፡ ተግባራቸው ምንም ይሁን ምን ሁሉም ቡርጂዎች ባህላቸውን ጠንቅቀው ሊያውቁት ይገባል፡፡ ስለሆነም በተለይ ወጣቱ ትውልድ ይህን የአባቶቹን፣ የአያቶቹንና የቅድማያቶቹን ባህላዊ የፖለቲካና የእምነት ሥርዓቶችን

የሚያውቅበት፣ በሌላ አገላለጽ ማንነቱን የሚረዳበት፣ ራሱን የሚያውቅበት መንገድ ቢመቻች መልካም ይመስለኛል።

- የቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካ ሥርዓቶች (በተለይም *ወሚሶና ዳይኖማ)* ለበርካታ ዓመታት ተቋርጠው ከቆዩ በኋላ ዳይኖማው ብቻ ከ1996 ዓ.ም. ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል። ይህ በአብዛኛው መልካም ጅምር፣ ጥሩ ተግባር ነው። ይህ የሆነው በመንግሥትና በሕዝብ ያላሰለሰ ጥረት እንደሆነ ባውቅም፣ በተለይ መንግሥት ይህን ያደረገው ለራሱ፣ ለፖለቲካ መጠቀሚያነት ሲል ነው የሚል እምነት የለኝም። ወደፊትም ቢሆን ባህላዊው የፖለቲካ ሥርዓት ለመንግሥት ዓላማ ማስፈፀሚያነት መሣሪያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል ብዬም አላስብም። ይህ የሚሆን ከሆነ ግን የባህላዊ ሥርዓቱ ቀለም መፍዘዙ፣ ጠረን መለወጡ፣ ባጭሩ በሌላ ባህል መተካቱ አይቀሬ ነውና ከወዲሁ ጥንቃቄ ቢወሰድ ተገቢ ነው እላለሁ።

- ከፍ ሲል እንደተመለከተው፣ ተቋርጠው ከነበሩት ባህላዊ የፖለቲካ ሥርዓቶች መካከል *‹‹በጉል ጉባው ጎርሶማ››* እንዲቀጥል የተደረገው *ዳይኖማ* (በዳይና የመተዳደር) ሥርዓት ብቻ ነው። *ወሚሶ* (በወማ የመተዳደር) ሥርዓት ግን እንዲቀጥል አልተደረገም። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ያለፈው የወሚሶ ታሪክ ጥሎት ያለፈው ክፉ ጠባሳ እንደሆነ ይገባኛል። ውሳኔው ‹‹የሕዝብ›› ስለሆነም ክፋት አለው ባልልም፣ ውሳኔው ያስኮረፋቸው ወገኖች መኖራቸውን ስረዳ ግን ያሳስበኛል። የቡርጂን አንድነት እንዳያናጋም እሰጋለሁ።[73] ስለሆነም የወሚሶ ሥርዓት ቀድሞ በነበረው መልኩ፣ ሥልጣኑ በአንድ ቦሄ ወይም በአምስት ጎሣዎች እጅ ብቻ እንዲሆን ሣይሆን፣ ተሻሽሎና ተከልሶ፣ ሥልጣኑ በስምንቱም የቢያ አስተዳደሮች ውስጥ (ቅድሚያው ቀድሞ የሥልጣን ባለቤት ለነበረው ቦሄ ተሰጥቶ) ተራ በተራ እየተፈራረቀ የሚሰጥበት ሥርዓት ተበጅቶለት፣ እንደገና ተግባራዊ የሚደረግበት ሁኔታ ቢመቻች፣ በተለይ በጎሣ ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ሥርዓት በገነነበት በዚህ ዘመን፣ የህዝቡን አንድነት ጠብቆ ለማቆየት ያለው ጠቀሜታ ከፍ ያለ ነው እላለሁ።

[73] የስጋሁት አልቀረም። ይህን የማስተርስ ቴሲሴን አጠናቂቄ፣ የቃል ተቋቁሞ አድርጌ (ተፈትኜ) በአበቃሁት ማግስት፣ ለግል ጉዳዬ ወደ ቡርጂ ልዩ ወረዳ፣ ሶየማ ከተማ ብቅ ብዬ ነበር። እዚያም፣ ከፍ ብዬ በዚህ ሥራ ውስጥ የጠቀስኳቸው ወገኖች፣ ከሌላው ቡርጂ በተለየ መልኩ፣ ለረዥም ዓመታት ተቋርጦ የቆየውን፣ ‹‹ጨቋኝ ነበር›› በሚል ምክንያት ከሌሎች ባህላዊ የፖለቲካ ተቋማት (ከዳይኖማ) ጋር በአዲስ መልክ ተግባራዊ እንዳይደረግ ወይም እንዳይጀምር በ‹‹ሕዝብ›› የታገደውን የወሚሶን ሥርዓት፣ ብቻቸውን መጀመራቸውን ሰማሁ። ከመካከላቸው አንዱን ‹‹ወማ›› አድርገው በመሰየም፣ የዚያ የአንድ ቦሄ ነዋሪዎች በእሱ እየተተዳደሩ፣ በወሚሶ ሥርዓት እየተመሩ መሆናቸውን ስሰማ ደነገጥኩ። እጅግ አድርጌ አዘንኩ። ይህ ከመሆኑ በፊት፣ ለዚህ ጥናት የሚሆን መረጃ በሚሰበስብበት ወቅት ካስተዋልኩት ነገር ተነስቼ የሰነዘርኩት ሀሳብ ‹‹ይሁንታ ነው›› ወይንስ ‹‹ሙዋርት ነው›› እስከማለት ደረስኩ። ይሁን እንጂ፣ ለቡርጂ ሕዝብ አንድነት ለሚቆረቆሩ ወገኖች፣ ሕዝቡን ከመበታተን ለመታደግ፣ አሁንም ቢሆን ጊዜው ያላለፈ፣ እድሉ ያላከተመ ስለሆነ ‹‹ፍጠኑ!!!›› እላለሁ።

## ዋቢ መጻሕፍት


Aadland,Øyvind. (2006). "Sera: Traditionalism or Living Democratic Values?

Addis Ababa University, Ethiopian Languages Research Center (ELRC). (2005). Booklet.

Amborn, H.and Kellner, A. (1999)."Burji Vocabulary of Cultural Items" in AAP, No. 58; Institut fur Affikenistik: Uniiverstat zu koln, Germany.

Bahru Zewde and Siegfried Pausewang (eds.). (2006). Ethiopia: The Challenge of Democracy from Below. 2nd edition; Addis Ababa Ethiopia: United Printers.

Bahru Zewde. (1999). "The Burden of History: The Constraints and Challenges of the Democratization Process in Ethiopia." in Hyslop, Jonathan (ed.), African Democracy: in the era of globalization. Johannesburg: Witwatersrand University Press.

Braukamper, Ulrich. (1973). "The Correlation of Oral Tradition and Historical Records in Southern Ethiopia: A Case Study of Hadiya - Sidama Past." Journal of Ethiopian Studies (JES), vol. 11, 2, Addis Ababa: University press.

Case Study among the Sidama in Southern Ethiopia" in Ethiopia: The Challenge of Democracy from Below. Bahru Z. and Siegfried P. (Eds); 2nd edition; Addis Ababa Ethiopia: United Printers.

Cerulli, Emesta, (1956). "Peoples of South-West Ethiopia and its Border land: Ethnographic Survey of Africa." Forde, Dmryll (ed.), in North- Eastern Africa. part III, London: International African Institute.

Cowan, L.Gray. (1959). Local Government in West Africa. Columbia University Press: New York.

Donaldson, A. Smith. (1897)."Through Unknown African Countries" (Word list).

Dorson, M. Richardson (ed.). (1972). Folklore and Folk life: An Introduction. The University of Chicago Press: Chicago and London.

Downes, R.M., (1971). Tiv Religion. Ibadan University Press

Encarta, Encyclopedia, (2005).

Encarta, Encyclopedia, (2007).

Evans, E.E and Fortes, M. (1940); African Political Systems. London.

Federal Democratic Republic of Ethiopian Census Commission, (ECC); Dec. (2008).

Hallpike, C.R., (1972). The Konso of Ethiopia: A study of the value of a Cushitic People. Oxford: At the Clarindon press.

Harris, Philip, J., M.A., (1957). Local Government in Southern Nigeria: A manual of law and Proceducer under the eastern Region Local government Law, 1955 and the western Region Local government Law, 1952. Cambridge: At the university Press.

Hebding, Daniel E.; Glick, Leonard. (1996). Introduction to Sociology. Community college of Philadelphia:, Fifth Edition.

Hizkias Assefa and Wachira, George (1996). Peacemaking and Democratization in Africa: Theoretical Perspectives and Church Initiatives. East African Educational Publishers: Nairobi, Kampala.

Hyslop, Jonathan (ed.), 1999. African Democracy in the Era of Globalization. Johannesburg: Witwatersrand University Press.

Jary, D. and Jary, J. (eds.) (2005) Collins dictionary of Sociology. Collins: Harper Collins Publishers.

Kimambo, I.N., and Ranger, T.O., (eds.). (1972). The Historical Study of African Religion: With Special Reference to East and Central Africa. Heinemann: London-Nairobi-Ibadan.

Lewis, I.M., (1975). The Cushitic Speaking Peoples: A jig-saw puzzle for social anthropologist.

Lienhardt, Godfrey. (1961). Divinity and Experience: The Religion of the Dinka. Oxford: At the Charendon Press.

Messenger, C. Joha. (1972). "Folk Religion" in Dorson, M. Richardson (ed.), Folklore and Folk life: An Introduction. The University of Chicago Press: Chicago and London, 1972.

Nsarkoh, J.K., (1964). Local Government in Ghana. Ghana University press: Accra.

Posnansky, Merrick. (1972). "Archaeolagy, Ritual and Religion."; in Kimambo, I.N. and Ranger, T.O. (eds.). The Historical Study of African Religion: With Special Reference to East and Central Africa. Heinemann: London-Nirobi-Ibadan.

Roba, Dame. (1981) "Noun Morphology in Burji" A sinor essay presented to Department of Lingustics, A.A.U.

Sklar, L. Richard. (1999). “The Significance of Mixed Government in Southern African Studies: A Preliminary Assessment” in Hyslop, Jonathan (ed.), African Democracy: in the Era of Globalization. Johannesburg: Witwatersrand University Press.

Summary and Statistical Reports of the 2007 Population and Housing Census. Addis Ababa.

Torrance, M. Robert. (1994). The Spiritual Quest: Transcendence in Myth, Religion and Science. University of California Press.

Wallace, Anthony F.C., (1966). Religion: An Anthropological View. New York: Random House.

Wraith, E. Ronald. (1953). Local Government. Penguin.

Yacob Arsano. (2006). “Seera: A Traditional Institution of Kambata.” in Ethiopia: The Challenge of Democracy from Below. Bahru Zewde and Siegfried, P. (eds.); 2nd edition; Addis Ababa Ethiopia: United Prenters.

Yilma Tiruneh. (1984). "Burji Verb Morphology" A senior essay, presented to Department of Lingustics; ILS, A.A.U.

------------------. (2002). “Systems of Local Governance among the Gurage: The Yajoka, Qicha and Gordana Seera.” in Ethiopia: The Challenge of Democracy from Below. Stockhome: Elanders Gatos.

ብሔረሰቦች ባህል ቋንቋና ታሪክ ጥናት ተቋም። (2001 ዓ.ም)። የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ፕሮፋይል። አዋሳ፡ ፍቅረሰላም ማተሚያ ቤት።

አበበ አርጋሞ። (1999 ዓ.ም)። ‹‹ባሻ፡- የቡርጂ ብሔረሰብ ባህላዊ አስተዳደር››። ዳውአታ፣ በቡርጂ ልዩ ወረዳ ማስታወቂያና ባህል ጽ/ቤት እየታተመ የሚወጣ ዓመታዊ መጽሔት፣ ቁ. 3፣ አዋሳ፣ ቶኒ ማተሚያ ቤት።

ኪዳኔ ወልደ ክፍሌ። (1948 ዓ.ም)። መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ። አዲስ አበባ፡ አርቲስት ማተሚያ ቤት።

ጌታሁን አዶ። (1999)። ‹‹የኤሳ መገንቢያ ቁሳቁሶች ምንነትና ትርጉማቸው›› ዳውአታ፣ በቡርጂ ልዩ ወረዳ ማስታወቂያና ባህል ጽ/ቤት እየታተመ የሚወጣ አመታዊ መጽሔት ቁ. 3፣ አዋሳ፡ ቶኒ ማተሚያ ቤት።

ግርማ ቡኬ። (1982)። ‹‹ግርዛት እና ዘፈኖቹ በቡርጂ ህብረተሰብ›› ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ (ድማፅ)፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ።

ፊቃደ አዘዘ። (1991)። የሥነ-ቃል መምሪያ። አዲስ አበባ፡ ቦሌ ማተሚያ ደርጅት።

አባሪ 1

## የአውራ መረጃ አቀባዮች አጫጭር መግለጫዎች

- ❖ ሙሉ ስም - ቡኬ ጨዶ
- ❖ ማዕረግ - አቶ



- ❖ ፆታ - ወንድ
- ❖ ዕድሜ - 85 (በግምት)
- ❖ ሥራ - ገበሬ
- ❖ የትምህርት ደረጃ - አልተማሩም
- ❖ የቋንቋ ችሎታ - ቡርጂኛ
- ❖ ሃይማኖት - ፕሮቴስታንት
- ❖ በቡርጂ ባህላዊ ሥርዓት ውስጥ የነበራቸው (ያላቸው) ተሳትፎ - የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ ከመሆናቸው በፊት (በግምት እስከ ጎልማሳነታቸው ድረስ) በቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካና የእምነት ሥርዓት ውስጥ ቁልፍ ሚና በነበረው ቤተሰብ (ጎሳ) ውስጥ ተወልደው ያደጉ ናቸው:: ቤተሰባቸው፣ ቡርጂ ውስጥ ቀዳሚ እንደሆነ የሚነገረውንና "ስለ ቡርጂ ህዝብና አካባቢ መፃዕ ሁኔታ ይተነብያል" ተብሎ የሚታመነውን፣ *ዋጭ* (ውቃቢ) የሚባል ነበራቸው:: በመሆኑም በወቅቱ በማህበረሰቡ ውስጥ "ታላቅ" ከሚባሉ ቤተሰቦች መካከል አንዱ ነበሩ:: በዚህም ባህላዊ የፖለቲካ መሪዎች በቤተሰባቸው ዋጭ እየታገዙ ተግባራቸውን ሲያከናውኑ፣ ኃላፊነታቸውን ሲወጡ እያዩ፣ እየተመለከቱ፣ እያስተዋሉ፣ በሥርዓቱም እየተሳተፉ፣ ወዘተ. እስከ ጎልማሳነታቸው ድረስ ዘልቀውበታል:: ከዚህም በተጨማሪ ቡርጂ ተወልደው ያደጉ፣ ብዙ ያዩና ያስተዋሉ፣ በዚህም ስለ ብሔረሰቡ ባህላዊ ሥርዓቶች ሰፊ ዕውቀት ያካበቱ አዛውንት ናቸው::

❖ ሙሉ ስም - ቱኬ ህርቦ

❖ ማዕረግ - ኣንሽ (የጎሳ መሪ)



❖ ፆታ - ወንድ

❖ ዕድሜ - ከ90 በላይ (በግምት)

❖ ሥራ - ገበሬ

❖ የትምህርት ደረጃ - እስከ 3ኛ ክፍል ድረስ ተምረዋል


❖ የቋንቋ ችሎታ - የአፍ መፍቻቸው ከሆነው ከቡርጂኛ በተጨማሪ ኦሮምኛን መናገርና መስማት፥አማርኛን መስማት ይችላሉ።

❖ ሃይማኖት - ሙስሊም

❖ በቡርጂ ባህላዊ የእምነትና የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ያላቸው (የነበራቸው) ተሳትፎ - በቡርጂ ውስጥ ጋን ካላቸውና "ታላቅ" ከሚባሉ ጎሣዎች መካከል አንዱ የሆነው፣ የኣናቡራ ጎሣ መሪ ወይም የጎሣው የፖለቲካ ጉዳዮች ዋና ተጠሪ (ኣንሽ) ናቸው። ኣንሽ ሆነው ጎሣቸውን፣ የሚኖሩበትን የቢያ አስተዳደርንና በጠቅላላው የቡርጂን ህዝብ ለበርካታ ዓመታት አገልግለዋል። ዛሬም ድረስ (ኣንሽ ስለሆኑ) በማገልገል ላይ ናቸው። በጎሣ መሪነታቸውም የጉል ጉቤይንካ ጎርሶማ አባል ናቸው። በዚህም ጎሣቸውንና አካባቢያቸውን ወክለው በተለያዩ ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ተሳትፈዋል። ዛሬም ድረስ በመሳተፍ ላይ ናቸው። በአጭሩ ኣንሽ በመሆናቸው እሳቸው ያልተሳተፉበት ወይም የማይሳፉት የቡርጂ ጉዳይ የለም። በመሆኑም በቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካ፣ የእምነት፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓቶች ላይ ከፍተኛ ልምድና እውቀት ያካበቱ አዛውንት ናቸው።

❖ ሙሉ ስም - ማኒኦ ጉሪኤ

❖ ማዕረግ - ዳይና



❖ ጾታ - ወንድ

❖ ዕድሜ - 70 (በግምት)

❖ ሥራ - ገበሬ

❖ የትምህርት ደረጃ - ያልተማሩ

❖ የቋንቋ ችሎታ - ቡርጂኛ ብቻ

❖ ሃይማኖት - ኦርቶዶክስ

❖ በቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካና የእምነት ሥርዓት ውስጥ ያላቸው (የነበራቸው) ተሣትፎ - በቡርጂ ባህላዊ ሥርዓት ውስጥ ተኮትኩተው ያደጉ ከመሆናቸውም በላይ፣ ከ1999 — 2001 ዓ.ም አጋማሽ ድረስ *ጋሪንታ ዳይና* በመሆን አገልግለዋል። በዚህም ስለ ቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካና የእምነት ሥርዓት ጠለቅ ያለ እውቀትና ልምድ ያካበቱ አዛውንት ናቸው።

❖ ሙሉ ስም - ጫሜ ቦቃ

❖ ማዕረግ - ቃሉ

❖ ጾታ - ወንድ

❖ ዕድሜ - ከ50 በላይ (በግምት)

❖ ሥራ - ገበሬ

❖ የትምህርት ደረጃ - ያልተማሩ

❖ የቋንቋ ችሎታ - ቡርጂኛ ብቻ

❖ ሃይማኖት - ኦርቶዶክስ

❖ በቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካና የእምነት ሥርዓት ውስጥ ያላቸው (የነበራቸው) ተሣትፎ - ቡርጂ ውስጥ "ታላቅ" ከሚባል ከባንባላ ጎሣ የሚወለዱ *ባለጋን (ባንባልንካ ጋን)* ናቸው። *ባለጋን* በመሆናቸውም የማህበረሰቡ ባህላዊ ቄስ ሆነው በማገልገል ላይ ናቸው። በዚህም በቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካና የእምነት ሥርዓት ላይ በቂ እውቀትና ልምድ ያካበቱ ናቸው።

❖ ሙሉ ስም - አበበ አርጋሞ
❖ ማዕረግ - አቶ
❖ ጾታ - ወንድ
❖ ዕድሜ - 43
❖ ሥራ - የቡርጂ ልዩ ወረዳ ባህል፣ ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት የህዝብ ግንኙነት እና የባህል ዘርፍ ባለሙያ
❖ የትምህርት ደረጃ - ቢ. ኤ. ዲግሪ በውጭ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ (እንግሊዝኛ)
❖ የቋንቋ ችሎታ - ቡርጂኛ፣ አማርኛ፣ እንግሊዝኛ፣ ኮንስኛ፣ ጋዋድኛ፣ ኦሮምኛ
❖ ሃይማኖት - ኦርቶዶክስ
❖ በቡርጂ ባህላዊ የፖለቲካና የእምነት ሥርዓት ውስጥ ያለው (የነበረው) ተሣትፎ - በባህሉ ውስጥ ተወልደው ያደጉ፣ የባህል ባለሙያ በመሆን በበርካታ ባህላዊ ሥርዓቶች ላይ ተሳትፈዋል። ይህ መረጃ እስከተሰበሰበበት ጊዜ ድረስም ይህንኑ በማከናወን ላይ ናቸው። የብሔረሰቡን ባህል ለማጥናት ወደ አካባቢው ከሚመጡ ባለሙያዎች ጋር በአገናኝነት፣ በአስተርጓሚነትና በረዳትነት ሠርተዋል። በግልም በተለያዩ ባህላዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከብሔረሰቡ በርካታ አዛውንት ጋር ቃለ መጠይቅ አድርገዋል። በዚህና በመሳሰሉት አጋጣሚዎች ስለ ቡርጂ ባህላዊ የእምነትና የፖለቲካ ሥርዓቶች በቂ እውቀት አካብተዋል።

አባሪ 2 ሙዳዬ ቃላት

ቢያ ፡- ከጉልጉባ ዝቅብሎ፣ ከቦሄ ከፍ ብሎ የሚዋቀር አስተዳደራዊ ተቋም ነው፡፡

- በቁሙ ሀገር ወይም "ህዝብ" ማለት ነው፡፡ በዚህ አገባቡ ግን የራሱ ወሰን፣ መሪ ያለው፤ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ቦሄዎች (ቀበሌዎች) ጥምረት የሚመሠረት የአስተዳደር አካባቢ ነው፡፡
- ራሱን ችሎ፣ በህዝብ በሚመረጥ መሪ (በማሻ ወይም በፊዜ)፣ በራሱ የመተዳደሪያ ደንብ የሚተዳደር አካባቢ ነው፡፡
- በአጭሩ ኪዳኔ ወልድ ክፍሌ በ (1998፣ 365) ሀገር ለሚለው የአማርኛ ቃል፣ በቁሙ አገረ፣ መንደር፣ ከተማ፣ ገጠር፣ ብዙ ቤቶች የተሠሩበት፣ ብዙ ሰዎች የሚኖሩበት፣ በያቅኚውና በየክፍሉ ገዥ፣ አዛዥ፣ ዳኛ፣ መልከኛ ያለው ታላቁም ታናሹም በማለት እንደተረጎመው ማለት ነው፡፡

ኦላ፡- በቁሙ "ጎረቤት" ማለት ሲሆን "የኦላ አስተዳደር" ሲል በሚጎራበቱ ሰዎች የሚመሠረት አስተዳደር ማለት ነው፡፡

- በቡርጂ ባህላዊ የፓለቲካ መዋቅር ውስጥ ዝቅተኛውና የመጨረሻው አካል ነው፡፡

ቦሄ፡- በቁሙ "መንደር" ወይም "ቀበሌ" ማለት ነው፡፡

- በውስጡ ሁለትና ከዚያ በላይ "ገሪኤ" (ኦላ) ያለው፣ በአብዛኞቹ (በጋሪንታ ቢያ) የቡርጂ አካባቢዎች በማሻ የሚመራ፣ የራሱ መሪና ወሰን ያለው አካባቢ የሚጠራበት ስም ነው፡፡
- በቡርጂ ባህላዊ የፓለቲካ መዋቅር ውስጥ ከገሪኤ ከፍ ብሎ ከቢያ ዝቅ ብሎ ያለ የአስተዳደር መዋቅር ነው፡፡
- ፈረንጂኛ "village` ይለዋል፡፡

ገሪኤ፡- በቡርጂ ባህላዊ የፓለቲካ መዋቅር ውስጥ ከኦላ ከፍ ብሎ ያለ ወይም በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ኦላዎች ጥምረት የሚዋቀር የአስተዳደር አካል ነው፡፡

- በጥቂት የቡርጂ አካባቢዎች ብቻ ተግባራዊ የሚደረግ፣ የባህላዊ አስተዳደር መዋቅር ነው፡፡

ጉልጉባ ፡- "ጉል" እ "ጉባ" በሚባሉ፣ በሁለት ቃላት ጥምረት የተመሠረተ ቃል ነው፡፡ "ጉል" ማለት "ሥር" ወይም "ታች" ማለት ሲሆን፣ "ጉባ" ማለት ደግሞ ‹‹እላይ›› ማለት ነው፡ ፡ በዚህም "ጉል ጉባ" "የታችኛው እና ‹‹የላይኛው›› የሚል ፍቺ ይኖረዋል፡፡

- ቡርጂ ውስጥ የቡርጂ ህዝብ የሚኖርበት አጠቃላይ አካባቢ ወይም ስምንቱም የቢያ አስተዳደሮች የሚጠሩበት ጥቅል ስም ነው፡፡
- የጉልጉባ አስተዳደር ሲባል፣ በቡርጂ ባህላዊ የአስተዳደር መዋቅር፣ አናት (ቁንጮ) ላይ የሚገኝ፣ በወማ የሚመራ አካል ማለት ነው፡፡

ጋሪንታ ቢያ፡- በቁሙ ‹‹ሰፊ ሀገር›› ወይም ‹‹አብዛኛው ህዝብ የሚኖርበት ሀገር ወይም አካባቢ›› ማለት ነው፡፡

- ከ8ቱ የቡርጂ የቢያ አስተዳደሮች መካከል 5ቱን ወይም ሲሦውን አካባቢ የያዘ (ማለትም ጋሻራ፣ ኦቶማል፣ ወርዴይ፣ ራሰይ እና የበን የሚባሉት) የቢያ አስተዳደሮች በጥቅል የሚጠሩበት ስም ነው፡፡
- አንዳድ ጊዜ 5ቱ ካላች ተብለው ይጠራሉ፡፡

ቡርጂ፡- ሌሞ፣ ጋሚዮ እና ክልቾ በሚባሉ በሦስት ቦሄዎች ጥምረት የሚመሠረትና ከ8ቱ የቢያ አስተዳደሮች አንዱ ለሆነ አካባቢ የተሰጠ መጠሪያ ነው፡፡

ኤሣ፡- ከተለያዩ እንጨቶች የሚዘጋጅ፣ በባህላዊ መሪዎች (በወማ፣ በዳይና በማሻ እና በባለጋን) መኖሪያ ግቢ ወይም (ደጅ)፣ በህዝብ አደባባዬችና የስልጣን ሽግግሩ በሚፈፀምበት ስፍራ (ሱቡሮ) ላይ የሚተከል ባህላዊ ቁስ ነው፡፡

- የቡርጂዎች የአንድነት ተምሳሌት ነው
- የባህላዊ መሪ መለያ ምልክት ነው፡፡

ሱቡሮ፡- "ባሻ" የሚባለው ባህላዊ የሥልጣን ሽግግር በሁሉም ቡርጂዎች በጋራ የሚፈፀምበት፣ በጋሻራ የቢያ አስተዳደር ውስጥ የሚገኝ ሜዳማ አካባቢ ነው፡፡

ሒጣኖ፡- ቡርጂዎች የእንስሳት ደም ወይም ቦርዴ ወይም ትኩስ የላም ወተት በኤሣ እና ኤሣው በሚገኝበት አካባቢ በመርጨት የሚፈፅሙት እምነታዊ ስርዓት ነው፡፡

- ቡርጂዎች በአመት አንድ ጊዜ የእንስሳት ደምን ወይም ቦርዴን ወይም ትኩስ የላም ወተትን በኤሣው እና በኤሣው አካባቢ በመርጨት ለሟች ወገኖቻቸው የሚያቀርቡት የመስዋዕት ስርዓት ነው፡፡

ወማ፡- በቁሙ ‹‹ንጉስ›› ማለት ነው፡፡

- ከፍተኛው ባህላዊ ማዕረግ ነው፡፡
- በባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት ቁንጮ ላይ የሚገኙ የፓለቲካና የእምነት መሪዎች የሚጠሩበት የማዕረግ ስም ነው፡፡
- መላ ቡርጂን በበላይነት የሚመራ፣ የፓለቲካ ተግባራትን የሚሠራ ታላቅ ሹም ነው፡፡
- በእምነት ተቋማት ውስጥ ‹‹ሣጋናንካ ጋን›› እና ‹‹ባንባልንካ ጋን›› ቁንጮ የሆኑ ባህላዊ የእምነት መሪዎች (ቄሶች) የሚጠሩበት ማዕረግ ነው፡፡

ወሚሶ፡- በቁሙ ‹‹የንግሥና ስርዓት›› ማለት ነው፡፡ ወማው (ንጉሡ) ወደ ስልጣን የሚመጣበት ባህላዊ ስርዓት ነው፡፡

ዳይና፡- ከወማ ቀጥሎ ከፍተኛው ስልጣን ነው፡፡

ጋሪንታ ዳይና፡- ከወማ ቀጥለው ካሉት ዳይናዎች ሁሉ ብልጫ ያለው፣ ከ8ቱ 5ቱን ቢያ የሚመራ ሹም ነው፡፡

ሸይሼንታ ዳይና፡- ሸይሼ ‹‹ወሰን፣ ድምበር፣ ግዛት›› ማለት ሲሆን ‹‹ሸይሼንታ ዳይና›› ማለት ‹‹የወሰን ጠባቂ፣ የድንበር ሹም ወይም ባለሥልጣን›› ማለት ነው፡፡

- በቡርጂና በአማሮ ልዩ ወረዳ ወሰን ወይም ድንበር አካባቢ የሚገኝ ቀበሌ ነው፡፡

ጎዴ፡- ቡርጂዎች ወደፊት የሚደርስባቸው ክፉ አጋጣሚዎች (ማለትም በሽታ፣ ጦርነት ወዘተ. እንዳይደርስባቸው ለማድረግ (ለማክሸፍ) ወይም ከራሳቸው ላይ ክፉ አጋጣሚዎችን ለመከላከልና በሌላ ወገን ላይ እንዲደርስ ለማድረግ ሲሉ የሚፈፅሙት የመተት እምነታዊ ስርዓት ነው፡፡

ሞጬ፡- ቡርጂዎች ውሃን በሰው (በዕቃ ላይ) በመርጨት ወይም በበግ ፈርስ የሰውን አፍ በመጥረግ ሰውን ወይም እቃን ወይም አንድን ስፍራ ከኃጥያቱ ወይም ከእርኩሰቱ ለማንፃት ሲሉ የሚፈፅሙት እምነታዊ ስርዓት ነው፡፡

ጋና፦ የወማ እና የዳይና ረዳት የሆነ ሰው የሚጠራበት ማዕረግ ነው።

ጃልዓባ፦ የወማ፣ የዳይና እና የማሻ ከፍተኛ አማካሪና ረዳት የሆነ ሹም ነው።

ፊዜ፦ በቁሙ ‹‹ማሻ›› ማለት ነው።

- የማሻዎች አለቃ (የበላይ) የሆነ ሰው፣ ከዳይና ዝቅ ብሎ ያለ ባለ ሥልጣን የሚጠራበት ማዕረግ ነው

ኣንሸ፦ የጎሣ መሪ

- የአንድን ጎሣ ፓለቲካዊ ጉዳዮችን በበላይነት የሚመራ ባለሥልጣን።

ኣና፦ በቁሙ መሪ ማለት ነው።

ጎሣንካ ኣና፦ በቁሙ የጎሳ መሪ ማለት ነው።

- ያንድን ጎሳ እምነታዊ ተግባራትን በበላይነት የሚመራ፣ ፓለቲካዊ ጉዳዮች የማይመለከቱት ሹም ነው።

በልባላ፦ የአንድ መንደር ወይም የአንድ አካባቢ ነዋሪዎች ከመኖሪያ አካባቢያቸው ሲወጡም ሆነ ወደ መኖሪያቸው ሲመለሱ የሚጋሩት የመውጫና የመግቢያ ዋና በር ነው።

- የአንድ አካባቢ ነዋሪዎች የጋር የሆኑ ፓለቲካዊና እምነታዊ ጉዳያቸውን ለመወያየት የሚገናኙበት፣ የሚሰበሰቡበት እና እምነታዊ ሥርዓት የሚፈፅሙበት ስፍራ ነው።
- የባህላዊ ተቋማት ወይም መሪዎች ጽሕፈት ቤት ነው።

ጎርሶማ፦ ምክር ቤት ወይም ባህላዊ ሸንጎ

ጎርስ፦ አማካሪ

ባሻ፦ በቁሙ "ሣር" ማለት ሲሆን በዚህ ጥናት አገባቡ ግን፣ ቡርጂዎች በየዓመቱ ባህላዊ የፓለቲካ መሪዎቻቸውን የሚሠይሙበት ባህላዊ ክብረ በዓል ነው።

ሃዩ፦ የመከላከያ ሀይል (የሀግ) መሪ ነው።

ሀግ፦ በአንድ የግርዛት ወቅት የተገረዙ ወጣት ወንዶች የሚጠሩበት ጥቅል ስም ነው።

- የመከላከያ ኃይል ተቋም መጠሪያ ነው።
- ቡርጂዎች ትውልድን ለመመደብ የሚገለገሉበት ባህላዊ ስርዓት ነው።

ሉብ፡- በትውልድ ምድብ ውስጥ የተካተቱ፣ ማህበራዊና ፓለቲካዊ ስልጣንንና ኃላፊነትን ለመሸከም ብቁ የሆኑ ወጣት ወንዶች የሚጠሩበት ማዕረግ ነው፡፡

- ለባህላዊ መሪዎች ‹‹ፓሊስ›› ወይም ‹‹ወታደር›› ሆነው ለሚያገለግሉ ወጣቶች የተሰጠ መጠሪያ ነው፡፡

ቢታናች፡- በቡርጂ ባህላዊ የእምነት ተቋም ውስጥ መሪ ለሆነው (ለባለጋን) ረዳት የሆነ ሹም ነው፡፡

- ባህላዊ የምርጫ አስፈፃሚ ነው፡፡

ጋን፡- ቡርጂዎች ‹‹ሁሉን ማድረግ የሚችል፣ ለችግሮቻችን ፈጥኖ የሚደርስ፣ ከአያት ከቅድመ አያቶቻችን የተቸረ፣ ከሠማያዊ አምላካችን የተሰጠን ሰማያዊ ፀጋ ነው›› ብለው የሚያምኑትን ልዕለ ተፈጥሮአዊ ሀይል የሚጠሩበት ስም ነው፡፡

ባለጋን፡- ቡርጂዎች ‹‹ከአምላካችን የተሰጠን ሰማያዊ ፀጋ ነው›› ብለው የሚያምኑት ልዕለ ተፈጥሮአዊ ሀይል ያደረበት ወይም የሚያድርበት ሰው ነው፡፡

- ባህላዊ ቄስ ነው፡፡

ጉሱማ፡- ከአናቱ ተወስዶ በቅል ውስጥ የተሞላ ባህላዊ ድፍድፍ ጠላ ወይም ቦርዴ ነው፡፡

- ከጥቁር ላም ታልቦ ከአናቱ ተወስዶ በቅል ውስጥ የተሞላ ትኩስ የላም ወተት ነው፡፡

አላልች፡- በቡርጂ ባህላዊ የእምነት ተቋም ውስጥ ለባለጋኑ ረዳት ሆኖ የሚሠራ ባህላዊ ሹም ነው፡፡

ዳና፡- ቡርጂዎች ከሣሮች ሁሉ ቁንጮ፣ ቆንጆ ነው ብለው ለሚያምኑት ሣር የሚጠሩበት ስም ነው፡፡

- ሰንደዶ ነው፡፡

ጋኖማ፡- ባህላዊ ቄሶች (ባለጋኖች) ወደ ስልጣን የሚመጡበት ባህላዊ ስርዓት ነው፡፡

ካላች፡- ባህላዊ የፓለቲካና የእምነት መሪዎች ከግንባራቸው ላይ የሚያስሩት፣ ከነሀስ የሚሠራ ባህላዊ ቁስ ነው፡፡

ሊሶ፡- ሙሉ በሙሉ ከጉማሬ ቆዳ የሚዘጋጅ፣ እጀታው በነሐስ የተለበጠ፣ ለባህላዊ የፓለቲካና የእምነት መሪዎች ልዩ መለያቸው የሆነ፣ በቀኝ እጅ የሚያዝ ባህላዊ ቁስ ነው፡፡

- የሠላም ባንድራ ወይም ተምሳሌት ነው፡፡

ቃራ፡- ባህላዊ ቄሶች (ባለጋኖች) ክፉ አጋጣሚዎችን ሲያወግዙ ብቻ የሚይዙት ባህላዊ ጦር ነው፡፡

ኣርጉማንቾ፡- የሃዩ ረዳት ሆኖ የሚሰራ ሹም ነው፡፡

ቦርቶማ፡- በቁሙ ማፋቀር፣ ማስማማት፣ አንድ ማድረግ ማለት ነው፡፡

- ቡርጂዎች ሁለት የተጋጩና ደም የተቀባቡ ጎሣዎች በባህላዊ የሽምግልና ሥርዓት ተቀራርበው እርቅ ካወረዱ በኂላ፣ ለወደፊቱ በሁለቱ ጎሣዎች መካከል ቂም በቀል እንዳይኖር፣ በክፉ እንዳይፈላለጉ በሚል ሁለቱን ባላንጣ ጎሳዎችን አንድ ጎሳ በማድረግ ለችግሩ ዘለቄታዊ ማሰሪያ የሚያበጁበት ሥርዓት ነው፡፡

ዳዋኖ፡- ኣንሽ፣ ወማ፣ ዳይና፣ ማሻ፣ ጋና እና ጃልዓባ ለሆኑ የህዝብ መሪዎች ክብር ሲባል ወደ ስልጣን በሚመጡበት በባሻ ሥርዓትና በሞታቸው ጊዜ ብቻ የሚዘፈንላቸው ባህላዊ ሙዚቃ ነው፡፡

ሃዬም፡- ‹‹ልዕለ ተፈጥሮኣዊ ሀይል አላቸው›› ተብለው ለሚታመኑ ባህላዊ ቄሶች (ባለጋኖች) ክብር ሲባል በንግስናቸው እና በሞታቸው ጊዜ ብቻ የሚዘፈንላቸው ባህላዊ ሙዚቃ ነው፡፡

ኣራሾ፡- ሴት በግ (የወለደች ሴት በግ)

ሓሣዳ፡- ባህላዊ የምርቃትና የልመና ሥርዓት

ወነይ፡- በቁሙ "ቀዳማዊ" እንደ ማለት ነው፡፡

- አንድ ሰው ባህላዊ ቄስ (ባለገን) ሆኖ ሲሾም የሚሰጠው የማዕረግ ስም ነው፡፡

ወናዋ፡- በቁሙ "ቀዳማዊት እመቤት" ማለት ሲሆን፣ አንድ ሰው ባለጋን ሆኖ ሲሾም የሚያገባት እና አብሯት ለምትነግሰዋ (የንግስና) ሚስት የሚሰጥ ማዕረግ ነው፡፡

ቃሉ፡- ቡርጂ ውስጥ ያሉ የባንባላ ጎሣ የሆኑትና ከአንጋፋው ባለጋን ውጭ ያሉ ሌሎች ባለጋኖች በሙሉ የሚጠሩበት የማዕረግ ስም ነው፡፡

ኣጋዳ፡- የባህላዊ መሪዎች መለያ የሆኑት ባህላዊ ቁሶችን (ሲሶን እና ካላችን) በጥሬ ቅቤ የማሸት ወይም ቅቤ የመቀባት ባህላዊ ሥርዓት ነው፡፡

ዱርጋ፡- ጣዕረ ሙታን (ሙታን ወገኖች)

ጎማስ፡- ሙታን መናፍስት

ራጅ፡- ተንባይ

ማሻ፡- ከዳይና ቀጥሎ በሦስተኛ ደረጃ ላይ ላለ ሹም የሚሠጥ ማዕረግ ነው፡፡

- ጋሻራ፣ ኦቶማል፣ ወርዴይ፣ ራስይ እና የበን በሚባሉ አካባቢዎች፣ ራሱን ችሎ አንድን ቢያ ወይም ቦሄ (ቀበሌ) የሚያስተዳድር ሰው የሚጠራበት ማዕረግ ነው፡፡
- በሌሎች አካባቢዎች ደግሞ ከከፍተኛው ንጉስ እስከ ዝቅተኛው የጎረቤት መሪ ድረስ ላሉ ባለስልጣናት ረዳት ሆነ ለሚሠራ ሰው የሚሠጥ ማዕረግ ነው፡፡

ወሚንካ ማሻ፡- በማሻ ማዕረግ የወማ ረዳት

ዳይናንካ ማሻ፡- በማሻ ማዕረግ የዳይና ረዳት

ጎሣንካ ማሻ፡- በማሻ ማዕረግ ለጎሳው መሪ ረዳት ሆኖ የሚሠራ ሰው ነው፡፡

ጎሪኤንካ ኣነይ ማሻ፡- በማሻ ማዕረግ ለገሪኤ መሪው ረዳት ሆኖ የሚሰራ ሹም ነው፡፡

ኦለይንካ ኣነይ ማሻ፡- በማሻ ማዕረግ ለኦለይንካ ኣናው (ለጎረቤት መሪው) ረዳት ሆኖ የተመደበ ሹም፡፡

ጎሣንካ ባልባላ፡- የጎሣ አስተዳደር ጽ/ቤት

ሀግንካ ባልባላ፡- የመከላከያ ኃይል ጽ/ቤት

ቦሄንካ ባልባላ፡- የቦሄ (የቀበሌ) አስተዳደር ጽ/ቤት

ወሚንካ ባልባላ፡- የወማ ጽ/ቤት

ኡስ፡- ቡርጂዎች የእንስሳትን አንጀት እያዩ (እያነበቡ) ስለመጪው ሁኔታ የሚተነብዩ ሰዎችንና የእምነት ሥርዓቱን የሚጠሩበት ስያሜ ነው፡፡

ማቴ፡- በድሮ ጊዜ ከቡርጂ በስተምዕራብ አቅጣጫ የመጡ፣ በፈረስና በቀስት እየተጠቀሙ ቡርጂን ይወጉ ለነበሩት ወገኖች የተሠጠ መጠሪያ ነው፡፡

ጎዳ፡- ከቡርጂ ጎሣዎች አንዱ የሆነ ጎሣ መጠሪያ ስም ነው፡፡

ቡራ፡- “ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል አላቸው” ተብሎ የሚታመኑ ባለጋኖች ብቻ ባንገታቸው ላይ የሚያስሩት፣ የተለያየ ቅርፅ ያላቸው ዶቃዎች (ጨሌዎች) ስብስብ ነው፡፡

ጉልጉበይንካ ጎርሶማ፡- የአጠቃላይ ቡርጂ ምክር ቤት

- ቡርጅ አቀፍ ህዝባዊ ሸንጎ

ቢያንካ ጎርሶማ፡- የአንድ አካባቢ (የቢያ) ምክር ቤት

- በቢያ ደረጃ የተዋቀረ ህዝባዊ ሸንጎ

ቦሄንካ ጎርሶማ፡- የቀበሌምክር ቤት

ባንኬ፡- ወራጅ ወንዝ

ኦለይንካ ኣና፡- የሚጎራበቱ የአንድ ቀበሌ ነዋሪዎችን የሚመራ ሰው (የጎረቤት መሪ) ነው፡፡

ገሪኤንካ ኣና፡- የቀጠና (የገሪኤ) መሪ

ኤላ፡- በባሻ ስርዓት ወደ ስልጣን የወጡ፣ የወቅቱ ባህላዊ መሪዎች ማለትም ወማው (ንጉሱ) ዳይናውና ማሻው በጥቅል የሚጠሩበት ስም ነው፡፡

- በቁሙ የወቅቱ ባህላዊ ሹም ማለት ነው፡፡

ኣምቢቻ፡- ከተለያዩ፣ ከሁለት የቡርጂ ጎሳዎች ጋር የጋብቻ ዝምድና ያለው ወንድ ሰው የሚጠራበት ስም ነው፡፡

ኮትሌ፡- በዛሬዎቹ በቡርጂ እና በአማሮ ልዩ ወረዳዎች ወሰን ላይ የሚገኝና በጥንቱ ዘመን ቡርጂዎች የመጀመሪያ ንጉሳቸውን እና ጎዳ የሚባለውን ጎሳ አባረው ድምበር የተከሉበት ስፍራ ነው፡፡

ብርብር፡- የአበሻ ጥድ

የጌር፡- የወይራ ዛፍ

ቱንቶ፡- ብረት ቀጥቃጭ

ቢጅር፡- ሽክላ ሰሪ

ሙዳሙዴ፡- ኩላሊት እያሳበጠ የሚገድል በሽታ ነው፡፡

ዶጎሌ፡- የካቲት ወር

- በቡርጂዎች የዘመን አቆጣጠር የመጀመሪያው ወር መጠሪያ ነው፡፡

ጎደሴ፡- መጋቢት ወር

- በቡርጂዎች የዘመን አቆጣጠር ሁለተኛው ወር

ወሚንታ ኡራ፡- የንጉሥ ተራራ

ጪርዳ፡- አንድን ሰው ከህብረተሰቡ የማግለል ባህላዊ ሥርዓት ነው፡፡

ባንባላ፡- ከቡርጂ ጎሣዎች አንዱ የሆነው ጎሣ መጠሪያ ነው፡፡

ባንባልንካ ጋን፡- የባንባላ ጎሣ ባለጋን

ሣጋና፡- ከቡርጂ ጎሣዎች የአንዱ ጎሣ መጠሪያ ነው፡፡

ሣጋናንካ ጋን፡- የሣጋና ጎሣ ባለጋን

- "የዝናብ ንጉሥ"

- ዝናብ የማዝነብ ልዩ ኃይል አለው የሚባለው ሰው የሚጠራበት ስም ነው፡፡

## አባሪ 3 ‹‹የቡርጂ›› ስርጭት በዓለም ውስጥ፤





Fig.1. Burji Nigeria





Fig.2. Burji keney






Fig.3. Burji, Punjab, Pakistan



Microsoft® Encarta® 2007. © 1993-2006 Microsoft Corporation. All rights reserved.


Fig.4. Burji, Ethiopia

## መግለጫ

ይህ ቴሲስ (የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ) የእኔ ወጥ ስራ ሲሆን፣ ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩኒቨርስቲ የዲግሪ ማሟያ ሆኖ አልቀረበም። ለጥናቱ ምንጭነት የተጠቀምኩባቸው መረጃዎችም በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴን አረጋግጣለሁ።

[illegible]

ስም



ፊርማ


አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ህዳር 2003 ዓ.ም

# የቡርጂ ባህላዊ አስተዳደር
# እና
# እምነት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ ፕሮግራም
ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት
ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ



በግርማ ቡኬ ጨዶ

ህዳር 2003 ዓ ም
አዲስ አበባ